# ፍሬ

# ግእዝ

አዘጋጆች፡ የግእዝ ክፍል አባላት

አሳታሚ፡-መናገሻ ገነተ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ
ቤተክርስቲያን ሰንበት ት/ቤት፡፡
፳፻፮ ዓ.ም.
ሁለተኛው እትም

## መታሰቢያነቱ

ይህ  እትም መታሰቢያነቱ ግእዝን አስተምረውና በመጽሐፍ ለተከታዩ ትውልድ ላስተላለፉት ለመምህር ክፍለ ጊዮርጊስ ፣ለአለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ ና ለአለቃ ታዬ ገብረማርያም እንዲም ለሊቃውንተ ቤተክርስቲያን ይሁንልን።

## ምስጋና

በቅድሚያ እንድንሠራ ላነሳሳን አነሳስቶም ለዚህ ላደረሰን ለቅዱሳን አምላክ ክብር ምስጋና ይሁን። በመቀጠል ይህን መጽሐፍ በማዘጋጀት ሙሉ ጊዜያቸውን ለሰጡ የግእዝ ክፍል አባላት በሙሉ እና በተለያየ መልኩ ለተባበሩን ሁሉ እግዚአብሔር ዋጋቸውን ይክፈላቸው።



# መቅድም

የግእዝ ቋንቋ ዓለም ሲፈጠር አብሮ የተፈጠረና መጀመሪያ ቋንቋ ለመሆኑ “ፈጠረ” ባለው ግሥ እግዚአብሔር ፈጣሪ መባሉ ብቻ ሊአስረዳን ይችላል። እንጨምርም ብንል መጀመሪያ የተፈጠረው ሰው አዳም ተብሏል ይኸውም ምን ያምር ማለት ሲሆን “አደመ” አማረ ካለው ግሥ የተገኘ ነው።ሁለተኛይቱም ፍጥረት ሔዋን ተብላለች “ሐይወ” ሕያው ሆነ ካለው ግሥ የወጣ ሲሆን የሕያዋን ፍጥረቶች እናት ማለት ነው። አዳምና ሔዋን አቤል ልጃቸው ሞቶባቸው እጅግ አዝነው ሳሉ ምትኩን ወንድ ስላገኙ በልማድ ሴት ተባለ እንጂ እነሱ የሠየሙት እሤት ብለው ነው ይኸውም ዋጋዬ ምትኬ ማለት ሲሆን “አሰየ” ሰጠ ካለው ግሥ የተገኘ ነው።

የዓለም ቋንቋ ሁሉ በየነገዱ ስም ሲጠራ ግእዝ ብቻ በማንም ነገድ ስም አልተጠራም ግእዝ ማለት አንደኛ መጀመሪያ ማለት ስለሆነ።የብሉይ መምህራን “ወኮነ ኵሉ ምድር አሐተ ከንፈረ ወአሐደ ነገረ”ምድር ሁሉ በአንድ ቋንቋ ይጠቀም ነበር ያለውን ይዘው ግእዝ የአዳም ቋንቋ ነው ይላሉ።የሐዲስ መምህራንም የጰራቅሊጦስ ዕለት“ወአኀዙ ይንብቡ በልሳናት ካልዓት” በሌሎች ቋንቋዎች ይናገሩ ጀመር ያለውን ከዳዊት መዝሙር “ኢትዮጵያ ታበጽሕ እደዊሃ ኀበ እግዚአብሔር ” ኢትዮጵያ እጆችዋን ወደ እግዚአብሔር ትዘረጋለች ካለው ጋር አያይዘው ሌሎች ቋንቋዎች ከተባሉት አንደኛው ግእዝ መሆኑንና ኢትዮጵያውያንም በዕለቱ በግእዝ ቋንቋቸው ሰምተው አምነው ከሦስቱ ሺህ አማኞች ውስጥ እንደተቆጠሩ ገልጸዋል።

“ሙባአ ታሪክ ወዜና ውስተ ቤተ ግእዝ ቅድምና እምኦሪተ ሙሴ ወእምአብረክሲስ ጥንተ ብሉይ ወጥንተ ሐዲስ”።የነገርናታሪክ መግቢያየግእዝ ቀዳማዊነት ቤት  ከሙሴ ኦሪትና ከራዕይ ዮሐንስ የብሉይና የሐዲስ ጥንት ብለው መምህራኑ  እንደገለጹት የግእዝ ቋንቋ ከኦሪትም ከሐዲስም ቀድሞ የነበረ መሆኑ የታወቀ ነው።

ግእዝ በኢትዮጵያ መቼ ተጀመረ የሚለውን የተለያዩ ጸሐፊዎች በተለያየ ወቅት መጀመሩን ይገልጻሉ ዋናው ነጥብ ግን ቀደምቶቹ ኢትዮጵያውያን ነገደ ካም በካም ቋንቋ ይጠቀሙ እንደነበረ በሦስት ሺህ ስድስት መቶ ዓመተ ዓለም በያዕቀብ ዘመን ነገደ ሴም ቋንቋቸውን ይዘው ወደ ኢትዮጵያ እንደመጡና ቋንቋቸውን በኢትዮጵያ እንዳስፋፉ ይህም የኢትዮጵያ ቋንቋ እንደሆነ ሁሉም የሚስማሙበት ነው፡፡

ነገደ ሴም ከመምጣታቸውም በፊት በባቢሎን በሶሪያ ይኖሩ እንደነበረ በኃላ ግን ለሁለት ተከፍለው ግማሾቹ ሰሜንና ምስራቅ እስያን ግማሾቹ ደቡብ እስያን ይዘው ይኖሩ እንደነበረና የሰሜንናምስራቅ እስያ ሴማውያን ቋንቋ አራማይክን አራማይክ ዕብራይስጥን እንዳስገኘ የደቡብ እስያ ሴማውያን ቋንቋም ሳባን ግእዝን አስገኝቷል፡፡ከዚህም የምንረዳው ወደ ኢትዮጵያ የገቡት የደቡብ እስያ ሴማውያን መሆናቸውን ነው፡፡

ግእዝ ጥንታዊ ቋንቋ መሆኑን ሲአስረዱ በሊቅነታቸው የታወቁ ታላቆቹ የጀርመን ጸሐፊዎች ለቋንቋቸው ግሥን መሪ አድርገውት ይገኛል፡፡ምክንያቱም አንድ የጀርመን ፈላስፋ ወደ ሀገራችን መጥቶ የግእዝን ቋንቋ ከነቅኔው ከነአገባቡ አውቆ ወደ ሀገሩ ተመልሶ የግእዝ ቋንቋን በሰፊው አስተምሮ ለየመጻሕፍቱ መሪ ቋንቋ ማድረጉ ታውቋል፡፡
ግእዝ በኢትዮጵያ የቋንቋዎዎች ሁሉ አባት ሲሆንና የውጭ አገሮች በብዙ ሲመኙትና በቤተ መጻሕፍቶቻቸው እያስተረጎሙ ሲጠቀሙበት በገዛ አገሩ ለሚበልጠው ሕዝብ እንግዳ ሆኖ መኖሩ እንዲያበቃ ሁሉም ጥረት ማድረግ ይኖርበታል ለዚህም እግዚአብሔር ይርዳን፡፡





| መክስተ አርዕስት | ገጽ |
|---|---|
| መቅድም | |
| መግቢያ | |
| ምዕራፍ ፩፥ ግእዝ | ፩ |
| የግእዝ ቀዳማዊነት | ፪ |
| የግእዝ ቋንቋ መማር ጥቅም | ፪ |
| የግእዝ ፊደላት | ፬ |
| የአማርኛ ፊደላት | ፭ |
| የግእዝ አኃዝ | ፮ |
| ምዕራፍ፪፥ ሥርዓተንባብ ዘልሳነ ግእዝ | ፲ |
| ሕግጋተ ንባብ (በጥንታዊመልክ) | ፲፪ |
| ምዕራፍ ፫፥ መራሕያን | ፳፬ |
| የመራሕያን አገልግሎት | ፳፭ |
| የስም አበዛዝ ስልት | ፴፪ |
| ስሞች ተሳቢ ሲሆኑ | ፭ |
| ነባራዊ እና የግስ ዝርዝር | |
| የስም ዝርዝር | ፫ |
| የግስ ዝርዝር (የባለቤት ዝርዝር) | ፶ |
| ምዕራፍ ፬. ግስ | |
| አርእስተ ግስ / የሠራዊት አለቆች / | ፶፯ |
| የግስ አወራረድና የአናቅጽ ስያሜ | ፶፰ |
| አመላተ ሰዋሰው /ጸዋትው/ኅርመት | ፶፱ |
| . የሥምንቱ አርዕስትና የሠራዊቶቻቸው እርባ | ፷፮ |
| ዝርው | ፸ |

ምዕራፍ ፩፥ *የዘር አወጣጥ*

| | |
|---|---|
| መስም ውስጠ ዘ | ፹፪ |
| ሳቢ ዘር፡- | ፹፪ |
| ዘመድ ዘር | ፹፫ |
| ባዕድ ዘር | ፹፬ |
| ምዕላድ ዘር | ፹፬ |
| ባዕድ ከምዕላድ ዘር | ፹፭ |
| ጥሬ ዘር | ፹፭ |
| ሰያፍ ቅጽል | ፹፮ |
| መድበል | ፹፮ |
| **ምዕራፍ ፮፥ *ንዑስ / መለስተኛ / እርባታ*** | |
| አሥራወ ቀለማት እና ሥርጭታቸው | ፹፯ |
| የአርእስተ ግሥ መለስተኛ እርባታ | ፹፰ |
| **ምዕራፍ ፯፥፥ *ቱሱሐን*** | ፹፱ |
| **ምዕራፍ ፰፥ *ተመኵሳይያን*** | ፺፪ |
| አንደኛ ተመኵሳይያን | ፺፪ |
| ሁለተኛ ተመኵሳይያን | ፺፭ |
| ሦስተኛ ተመኵሳይያን | ፺፯ |
| አራተኛ ተመኵሳይያን | ፻፫ |
| **ምዕራፍ ፱. *አዕማድ*** | |
| ገቢር ግሥ | ፻፮ |
| ተገብሮ ግሥ | ፻፮ |
| የአዕማድ ምልአትና ሕፀፅ | ፻፱ |
| የአዕማድ ንዑስ /መለስተኛ / እርባ | ፻፲፭ |








ፍሬ ግእዝ


| | |
|---|---|
| **ምዕራፍ ፲. *ተቃርኖ ስዋሰው /አሉታ/*** | |
| የባዕዳን ቀለማት የሰዋሰው መቃረን | ፻፬ |
| የሰዋሰው እርስ በእርስ መቃረን | ፻፲፫ |
| **ምዕራፍ ፲፩፥ *ዝርዝር እርባታ*** | |
| ግሣውያን የተሳቢ አጸፋ ተውላጣተ ስም /የባለቤትና የተሳቢ ዝርዝር/ ሠንጠረዥ | ፻፳፮ |
| የዝርዝር እርባታ ንባብ ሠንጠረዥ | ፻፳፯ |
| የአእመረ ዝርዝር እርባታ | ፻፳፰ |
| የቀተለ ዝርዝር እርባታ | ፻፴፫ |
| የይቤ ዝርዝር እርባታ | ፻፴፮ |
| የኀደገ ዝርዝር እርባታ | ፻፴፱ |
| የአዕማድ ዝርዝር እርባታ- የአስደራጊ ዐምድን | ፻፵፪ |
| የ ቦዝ አንቀጽ ዝርዝር እርባታ | ፻፵፬ |
| **ምዕራፍ ፲፪፥ *ክፍላተ ንግግር*** | |
| ስም | ፻፵፯ |
| መስተአምር | ፻፶፬ |
| ቅጽል | ፻፶፬ |
| ተውላጠ ስም | ፻፷ |
| ግሥ | ፻፷፫ |
| አንቀጽ አጎላማሽ | ፻፷፫ |
| አገባብ | ፻፷፮ |
| ደቂቅ አገባብ | ፻፷፮ |
| አዳማቂ | ፻፸ |
| ዐቢይ አገባብ | ፻፸፭ |
| ንዑስ አገባብ | ፻፸፭ |
| ቃለ አጋኖ | ፻፸፮ |




ሠ

ምዕራፍ ፲፫. *ዐረፍተ ነገር*

የዐረፍተ ነገር ክፍሎች ፻፸፯

የዐረፍተ ነገር ዓይነት ፻፸፯

የዐረፍተ ነገር ውስጣዊ ክፍሎች ፻፸፱

የሐረግ ዓይነት ፻፹

የቃላት ጥናት ፻፹፩

መጠይቃን ቃላት ፻፹፬

፩. ሰውን ለመጠየቅ ፻፹፬

፪. ነገርን ለመጠየቅ ፻፹፭

፫. ጊዜን ለመጠየቅ ፻፹፮

፬. ቦታን ለመጠየቅ ፻፹፮

፭.ቁጥር ለመጠየቅ ፻፺፯

ምዕራፍ ፲፬. *የአበው ቅኔያት መተዋወቂያ*

ከጉባኤ ቃና እስከ መወድስ ፻፹፱

ነጠላ ግሥ ፻፺፭

ተሰጥዎ ዘ ምልማድ (የጥያቄ መልሶች) ፪፻፱





## ሙባእ

ይህ መጽሐፍ ቀድሞ በመናገሻ ገነተ ጽጌ ቅዱስ ጊዮርጊስ ቤተ ክርስቲያን ሰንበት ትምህርት ቤት እና በአዲስ አበባ በሚገኙ በሰንበት ትምህርት ቤት ደረጃ ግእዝን ለሚያስተምሩ ለሦስተኛ እና ከሦስተኛ ዓመት በላይ ላሉ ተማሪዎች መማሪያ ሆኖ ያገለገለ ሲሆን ዘመን አልፎ ዘመን ሲተካ በየጊዜው የተነሱ መምህራነ ግእዝ የራሳቸውን አስተዋጽኦ ያደረጉበት ሲሆን ከተለያዩ የግእዝ መጻሕፍት የተውጣጣ የግእዝን ቋንቋ በቀላሉ ለመማር ለሚፈልጉ ሁሉ በቀላል መንገድ በአማርኛ የተዘጋጀ ነው::

ይህ መጽሐፍ መሠረታዊውን የግእዝ ሰዋሰው የያዘ ሲሆን የግእዝ እውቀት ላላቸው ለክለሳ በዘመናዊ መልኩም ለማሻሻል ለጀማሪዎች ከመነሻው የግእዝ ቋንቋ ቀዳማዊነት የግእዝ ፊደላት አኀዝ ማስተዋወቅ ጀምሮ ሥርዐተ ንባብን መራሕያንን ከነአገልግሎታቸው አሳይቶ ስም መዘርዘር ግስ መግሰስ ከንዑስ እስከ ዝርዝር እርባታ የዘር አወጣጥንም ጨምሮ የሚያስጨብጥ ሲሆን ከዚህም በተጨማሪ የግእዝን ነጠላና ብዙ ቁጥር አሉታና አዎንታ ክፍላተ ንግግር ያካተተ ለአንባቢው ግልጽ እንዲሆን በማስረጃ የተደገፈ አንባቢው እራሱን በመልመጃዎች/ምልማድ/ እየመዘነ ግልጽ ሆኖለት ደረጃ በደረጃ ወደሰፊው የግእዝ ቋንቋ የምሥጢር አዳራሽ እንዲገባ ሆኖ በዓመታት የመማር ማስተማር ልምድ የተዘጋጀ ነው:: የተጠቀሱት ቅኔዎችም በተለያዩ አበው የተነገሩ ሲሆን ስለቅኔ አጠቃላይ ግንዛቤን ለማስጨበጥ የቀረቡ ናቸው:: ከዚህም በላይ የግእዝ ቋንቋ ከባለቤቱ ከእግዚአብሔር ለሰው ልጆች የተሰጠ አንድነትን የሚሰብክ የሁሉ ቋንቋ ስለሆነ ምእመናን እንዲጠቀሙበት በሚል ሲዘጋጅ ወደፊትም የአንባቢውን ምላሽ ተመልክተን ከዚህ በበለጠ የምናቀርብ መሆኑን ለመግለጽ ስንወድ አነሳስቶ ያስጀመረን እግዚአብሔር የተመሰገነ ይሁን::

አሜን!::

# ምዕራፍ ፩

## ግእዝ

ግእዝ ማለት መጀመሪያ /ቀዳማይ/ ርዕስ ጥንት አንድ በቃል ማለት ነው::

☞ ግእዝ መጀመሪያ ነው ስንል በምንድን ነው ቢሉ:-

፩. **በፊደል ስምነቱ**:- አንድ ቅንጣት ወይም ቅጥል ሁለተኛ ፈርጅ የሌለው ማለት ነው:: እስከ ፲፱፻፹፫ ዓ.ም የግእዝ ፊደልና ድምፅ ከካዕብ እስከ ሳብዕ ያሉት ቅርጾችና ድምፆች አልነበሩትም:: በኂላ ግን አባ ሰላማ በዘመኑ ከነበሩት መምህራን ጋር በመምከር ከ ፲፱፻፹፫ - ፲፱፻፶ ዓ.ም የቅርጽና የድምፅ ምልክቶች / - ዐ / በመጠቀም ፊደሉን ዘንበል ጋደም በማድረግ ስድስቱን ስልተ ፊደላት ጨምረዋል:: ከቀኝ ወደ ግራ እንዲፃፍ እንዲነበብ አድርገዋል:: ቀድሞ ግን አንድ ግእዝ ፊደል ብቻ ነበር::

ምሳሌ:- ኢትዮጵያ ለማለት - የጰየተአ  አግዓዚ ለማለት - አገዐዘ በማለት ይጠቀሙ ነበር ::

፪. **በንባብ ስምነቱ:**- የመጀመሪያ ንባብ ማለት ነው በቤተክርስቲያናችን ሦስት ዋና ዋና የንባብ ስልቶች አሉ እነሱም:- ግእዝ፣ውርድ፣ቁም ንባብ ናቸው:: ግእዝ የመጀመሪያ ንባብ ነው ተማሪ ከዚህ ተነስቶ ቁም ንባብ ይደርሳል::

፫. **በዜማ ስምነቱ:**- በቤተክርስቲያናችን ሦስት ዓይነት የቅዱስ ያሬድ የዜማ ስልቶች አሉ እነሱም:- ግእዝ፣ዕዝል፣አራራይ ናቸው::

ግእዝ የመጀመሪያ ነጠላ ብዙ ርክርክ የሌለው ሲሆን ዕዝል ድርብ ብዙ ርክርክ ያለው አራራይ ደግሞ የማስተዛዘን ስልት ያለው ዜማ ነው::





፬. **በቋንቋ ስምነቱ:**- አዳማዊ ቀዳማይ ጥንታዊ ቋንቋ ማለት ነው::

## ፩.፩. የግእዝ ቋንቋ ቀዳማዊነት

ግእዝ ከእግዚአብሔር ተገኝቶ ቀዳማዊ ቋንቋ ለመሆኑ የቤተ ክርስቲያን ሊቃውንት

፩. የአዳም ትውልድ ሁሉ እስከ የሰናዖር ግንብ መጀመሪያ ድረስ አዳማዊ በሆነ ቋንቋ በግእዝ ይግባቡ እንደነበረ ይገልፃሉ:: ሌላው ቀርቶ በመጽሐፈ ኩፋሌ ፫፥፪ «ወበይእቲ ዕለት ተፈጸመ አፈኵሉ አራዊት ወእንስሳ ወዘአዕዋፍ ወዘያንሶሱ ወይትሐወስ እምነቢብ እስመ ኵሎሙ ይትናገሩ ዘንተ ምስለ ከንፈረ አሐደ ወልሳነ አሐደ::» ተብሎ እንደተ ገለፀው አዳም ከመበደሉ በፊት የእንስሳቱ የአራዊቱ በጠቅላላው የፍጥ ረት ሁሉ ቋንቋ አንድ እንደነበር የታወቀ ነው::

፪. በባቢሎን የተመሠረቱ ቋንቋዎች የፍጡራንን ስም ወገን ያደርጋሉ::

**ለምሳሌ**:- በጽርዕ - ጽርዕ  በኤቦር - ዕብራይስጥ

በሮም - ሮማይስጥ  በዐረብ - ዐረብ

ግእዝ ግን ወገን የሚያደርገው አግዐዚ እግዚአብሔርን ነው::

## ፩.፪. የግእዝ ቋንቋ መማር ጥቅም

፩፥በግእዝ ቋንቋ የተጻፉ መጻሕፍትን አንብቦ ለመረዳት ለመተርጎም::

፪፥ የግእዝን ቋንቋ ምንነት ፣ አባቶቻችን ወግ፣ባህል፣ታሪክ ፣ ሥነ ጽሑፍና ከተለያዩ ቋንቋዎች ወደ ግእዝ የተተረጎሙ መጻሕፍትን ያስተላለፉልን መሆኑን በመረዳት ያልሞተ ቋንቋ መሆኑን ለመግለጽ::

፫፥ አጫጭር ንግግሮችን የመግባቢያ ሃሳቦችን፣ሥነ ጽሑፎችን በግእዝ ቋንቋ ለማቅረብ::

፬÷ ቅዱሳት መጻሕፍትን በተለይ የጸሎት፣የትምህርት መጻሕፍትን ለመተርጎም ከትርጉም ከምሥጢር ሕፀፅ ለመዳን

- ☞ ምሳሌ:- መዝ ፩፻፶ በግእዙ ሙሉ ሲሆን በአማርኛው በእንተ ርእሱ / ስለራሱ/ የጻፈው የለም ይህም የክርስቶስን የማዳን ሥራ ከሰው ልጆች ሁሉ ስድብን በመስቀል ላይ ተሰቅሎ ማራቁን የሚገልጽ ታላቅ ምሥጢርን የያዘ ነው::
- ☞ መዝ ፹፮ በግእዙ «መሠረታቲሃ ውስተ አድባር ቅዱሳን» ሲል በአማርኛው መሠረቶቹ ብሎ በወንድ አንቀጽ ይናገራል:: መሠ ረታቲሃ ማለት ግን መሠረቶቿ ማለት ነው:: ይህም ስለ እመቤ ታችን ስለ ቤተክርስቲያን የተነገረ ነው::
- ☞ ፩ኛ ዮሐ ፪:፩ በግእዙ «ደቂቅየ ዘንተ እጽሕፍ ለክሙ ከመ ኢተአብሱ ወእመኒ ቦ ዘአበሰ ጰራቅሊጦስ ብነ ኀበ አብ ኢየሱስ ክርስቶስ» ሲል በአማርኛው ግን ከአብ ዘንድ ጠበቃ አለን የሚል ጽሑፍ አለ በግእዙ የተጻፈው ግን ስለ ጠበቃ የተናገረው የሚጠጋም ትርጉም የለም:: ትክክለኛ የግእዙ ቃል ትርጉም ግን «ልጆቼ ይህን እጽፍላችኋለሁ እንዳትበድሉ:: የበደለ ቢኖር ከኢየሱስ ክርስቶስ ዘንድ የሚያጽናና፣የሚያረጋጋ ፣የሚያጸና ፣የሚያነጻ /ጰራቅሊጦስ/ አለን » የሚል ነው:: ይህም ጌታ ራሱ እኔ ብሄድ ይሻላችኋል እኔ ከሄድኩ መንፈስ ቅዱስን እልክላችኋለሁ ያለው ነው:: ሐዋርያውም የተናገረው ስለ መንፈስ ቅዱስ ማረጋጋት ማጽናናት ነው::
- ☞ አቡነ ዘበሰማያትን በግእዝ ቃል «አላ አድኅነነ ወባልሐነ » እንላለን በአማርኛ ግን አድነን እንጂ ብቻ እንላለን የግእዙ ትርጉም ግን ከክፉ ሁሉ አድነን ጠብቀን እንጂ ነው::





፭÷ በየጊዜው ከውጭ ቋንቋ ሲተረጎም ሌላው የሀገራችን ቋንቋ ያልተረጎመውን በግእዙ ተተርጉሞ እናገኘዋለን::

*ለምሳሌ:-* ግራቪቲ - ስህበተ ምድር
ማግኔት - ምስሐበ ብርት
ቴሌቪዥን - መክስተ ትርዒት

## ፩.፫. የግእዝ ፊደላት

ፊደል ፈደለ ጻፈ ከሚለው የግእዝ ግሥ የወጣ ሲሆን ፊደል ማለት የቋንቋና የቃል የአነጋገር የጽሑፍ ሁሉ ምልክት አምሳል ወይም መግለጫ ማስታወቂያ ማለት ነው:: እግዚአብሔር ፊደልን ለሄኖስ በሰማይ ገበታነት ጽፎ ለመጀመሪያ ጊዜ አሳይቶታል:: እሊህም በመዝሙረ ዳዊት ፩፻፲፰ የተገለፁት ሃያ ሁለቱ አሌፋት ናቸው::

የግእዝ ፊደላት በጠቅላላው ፳፮ ናቸው:: እነዚህም ፳፪ አሌ ፋትና ፬ቱ ድርብ ፊደላት ናቸው:: ድርቦቹን ሳንጨምር በ፳፪ መድበን በሰባት ስልተ ፊደል መናገራችን እግዚአብሔር ፳፪ቱን ስነፍጥረት በሰባት ዕለታት መፈፀሙን ያስረዳል::

### ፳፮ቱም ፊደላት የሚከተሉት ናቸው

አ, በ, ገ, ደ ,ሀ ,ወ ,ዘ ,ሐ, ጠ, የ ,ከ, ለ, መ ,ነ ,ሰ, ዐ ,ፈ, ጸ, ቀ, ረ, ሠ ,ተ ,ኀ ,ጸ, ፀ, ፐ ናቸው:: እነዚህም ፊደላት በተለያዩ የሰውነታችን ክፍሎች እናነባቸዋለን::

በጉሮሮ የሚነገሩ:- አ, ዐ, ኀ, ሀ, ሐ
በከንፈር የሚነገሩ:- በ, መ, ፈ,ፐ, ጰ, ወ
በጥርስ የሚነገሩ:- ዘ, ሠ, ጸ, ፀ, ሰ
በትናጋ የሚነገሩ:- ገ, የ ,ከ, ቀ
በምላስ የሚነገሩ:- ደ, ጠ, ለ, ረ,ተ,ነ

የግእዝ ዝርዋን /ዲቃላ/ ፊደሎች የሚባሉት አራት ሲሆኑ አምስት ስልተ ፊደላት ያሏቸው ናቸው::

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ኰ | ኵ | ኲ | ኳ | ኴ |
| ጐ | ጕ | ጒ | ጓ | ጔ |
| ቈ | ቍ | ቊ | ቋ | ቌ |
| ኈ | ኍ | ኊ | ኋ | ኌ |

ግእዝ እና ሳብዕ ፣ ካዕብ እና ሳድስ ቀለማት ይወራረሳሉ::

## ፩.፬. የአማርኛ ፊደላት

ከነገደ ዮቅጣን ልጆች በኋላ ነገደ ፋሌቅ እነሱም ነገደ አብርሃም ናቸው:: ከየነበሩበት ቦታ በየጊዜው እየተጓዙ ከነኦሪታቸው ወደ ኢትዮጵያ ገብተዋል:: ከዳዊት እና ከሰሎሞን በፊት ከኩሽ ጀምሮ የነበረውን ጥንታዊና ሕጋዊ የሳባ መንግስት ከድል ነዓድ ቤት ወጥቶ ከአክሱም ወደ ላስታ አገው እስከተዛወረ ድረስ የግእዝ ቋንቋ በመላዋ ኢትዮጵያ ሁሉም ይጠቀሙበት ነበር:: በኋላ ግን አክሱማዊው መንግሥት ወደ ላስታ ከተዛወረ በኋላ በአክሱሞችና በአገዎች መሐል በነበረው ንትርክ ምክንያት ሰው ሁሉ በየብሔሩ ቋንቋ መጠቀም ጀመረ:: በዚያን ጊዜ በሰቆጣ በዋግና በዓይናቡግና በአንድ ላይ በአንድ ጊዜ ትግርኛና አገውኛ ቋንቋዎች ሰልጥነው በየአደባባዩ በቤተመንግሥት እና በቤተክህነት መነጋገሪያ ሲሆኑ በላስታና በሳይንት አማራ ደግሞ አማርኛ ቋንቋ እየሰፋና እየተሻሻለ እየገነነ መሄድ ጀመረ::የአማርኛ ፊደላት ከግእዝ የተለዩ አይደሉም:: ነገር ግን በግእዝ መጻሕፍት የማይገኙና በጥንታዊ አነጋገርም የሌሉ በኋላ ዘመን የገቡ የአማርኛ ፊደላት አሉ እነሱም ሸ, ቸ, ኘ, ኸ, ዠ, ጀ, ጨ, ናቸው::



## ፩.፭. የግእዝ አኅዝ

አኀዝ ማለት ቁጥር ማለት ሲሆን የአኀዝ ዓይነቶች አምስት ናቸው:: እነርሱም

፩. መደባዊ አኀዝ:- የግእዝ መደበኛ (ዐቢይ) አኀዝ የሚባሉት የሚከተሉት ናቸው:: መደባዊ አኀዝ የተበተኑትን አሥሮ ሰብስቦ የሚያሳይ የጅምላ ቁጥር ማለት ነው::

| አኀዝ | ዐረብ | ፊደል | አኀዝ | ዐረብ | ፊደል |
|---|---|---|---|---|---|
| ፩. | 1 | አሐዱ | ፳. | 20 | ዕሥራ |
| ፪. | 2 | ክልዔቱ | ፴. | 30 | ሠላሳ |
| ፫. | 3 | ሠለስቱ | ፵ | 40 | አርብዓ |
| ፬. | 4 | አርባዕቱ | ፶. | 50 | ሃምሳ |
| ፭. | 5 | ኀምስቱ | ፷. | 60 | ስሳ |
| ፮. | 6 | ስድስቱ | ፸ | 70 | ሰብዓ |
| ፯. | 7 | ሰብዓቱ | ፹ | 80 | ሠማንያ |
| ፰. | 8 | ሠመንቱ | ፺ | 90 | ተስዓ |
| ፱. | 9 | ተሰዓቱ | ፻ | 100 | ምዕት |
| ፲. | 10 | ዐሠርቱ | | | |

ከላይ ያየናቸው አኀዛት መሠረታዊ የግእዝ አኀዝ ሲሆኑ እነዚህም በማጣመድ ሌሎች ቁጥሮችን መሥራት እንችላለን::

ምሳሌ ፩ :-‹11›ን በግእዝ ለመጻፍ በመጀመሪያ 10 (፲) በመቀጠል 1 (፩)ን በማጣመድ 11 (፲፩)ን መሥራት እንችላለን::

ምሳሌ ፪:- 252 ለመጻፍ መጀመሪያ ፪ን ቀጥሎ ፻ ቀጥሎ ፶፪ በመጻፍ 252 በግእዝ ፪፻፶፪ ይጻፋል አነባበቡም ክልዔቱ ምእት ሃምሳ ወክልዔቱ ተብሎ ይነበባል::

ምሳሌ ፫:- 1ሺን ለመጻፍ ፲፻ ዐሠርቱ ምእት (አስር መቶዎች 10 X100)፣ 2ሺን ለማለት ደግሞ ፳፻ እሥራ ምእት (ሃያ መቶዎች (20X100) እንላለን:: በዚሁም መሠረት ሌሎቹንም ቁጥሮች በማጣመድ መሥራት ይቻላል ::

ከዚህ በታች ያሉት ቁጥሮች መሠረታዊውን ቁጥር በማጣመድ የተገኙ ዐቢያን ቁጥሮች ናቸው። እነዚህም፦

፻፻ 10,000 እልፍ

፲፻፻ 100,000 አእላፍ /ዐሠርቱ እልፍ/

፻፻፻ 1,000,000 አእላፋት

፲፻፻፻ 10,000,000 ትእልፊት

፻፻፻፻ 100,000,000 ትእልፊታት

፲፻፻፻፻ 1,000,000,000 ምእልፊት

ምልማድ ፦ ፩ ዘይተሉ አኀዛተ ግእዝ ወልጥ ኀበ አኀዘ ዐረብ

፩÷ ፰፭

፪÷ ፳፯

፫÷ ፹፰

፬÷ ፻፶፯

፭÷ ፪፻፴፭

፮÷ ፳፻፺፮

፯÷ ፲፻፯፻፶፩

ምልማድ ፦ ፪ ዘይተሉ አኀዛተ ዐረብ ወልጥ ኀበ አኀዘ ግእዝ

፩÷ 559

፪÷ 677

፫÷ 912

፬÷ 1122

፭÷ 3455

፮÷ 23981

፯÷ 101897





፪. **ሕጋዊ አኀዝ፦** ሕገኛ ደረጃን የሚያሳይ ነው።

| | | | |
|---|---|---|---|
| ቀዳማይ /ዊ/ | አንደኛ | ቀዳማይት /ዊት/ | መጀመሪያዪቱ |
| ካልዓይ/ዊ/ | ሁለተኛ | ካልዓይት /ዊት/ | ሁለተኛይቱ |
| ሣልሳይ | ሶስተኛ | ሣልሳይት | ሶስተኛይቱ |
| ራብዓይ | አራተኛ | ራብዓይት | አራተኛይቱ |
| ኃምሳይ | አምስተኛ | ኃምሳይት | አምስተኛይቱ |
| ሳድሳይ | ስድስተኛ | ሳድሳይት | ስድስተኛይቱ |
| ሳብዓይ | ሰባተኛ | ሳብዓይት | ሰባተኛይቱ |
| ሣምናይ | ሥምንተኛ | ሣምናይት | ሥምንተኛይቱ |
| ታስዓይ | ዘጠነኛ | ታስዓይት | ዘጠነኛይቱ |
| ዓሥራይ | አሥረኛ | ዓሥራይት | አሥረኛይቱ |
| ዓሥራይወቀዳማይ | አሥራ አንደኛ | ዓሥራይትወቀዳማይት | አሥራ አንደኛይቱ |
| ... | ... | ... | |
| ዕሥራይ | ሃያኛ | ዕሥራይት | ሃያኛይቱ |
| ሠላሳይ | ሠላሳኛ | ሠላሳይት | ሠላሳኛይቱ |
| .. | .. | .. | ... |
| ተስዓይወታስዓይ | ዘጠና ዘጠነኛ | ተስዓይትወታስዓይት | ዘጠና ዘጠነኛይቱ |
| ለምዕት የለውም | | | |

፫. **ክፍላዊ አኀዝ፦** የክፍሎችን መጠን በየመልኩና በየደረጃው ለይቶ የሚያመለክት ነው።

፫.፩. **ሁኔታን የሚያመለክቱ አኀዞች**

| | |
|---|---|
| እሕድ /ትእሕዲት | አንድነት |
| ክላዔ /ትክልዕት | ሁለትነት |
| ሠላሴ /ትሠልስት | ሦስትነት |
| ርባዔ /ትርብዕት | አራትነት |
| ኅማሴ /ትኅምስት | አምስትነት |
| ስዳሴ /ትስድስት | ስድስትነት |
| ስባዔ /ትስብዕት | ሰባትነት |
| ሠማኔ /ትሠምንት | ስምንትነት |
| ትሳዔ /ትስዕት | ዘጠኝነት |
| ዕሣሬ /ትዕሥርት | ዐሥርነት |

፫.፪ <u>**ጊዜ በሚል የሚፈቱ**</u>

| | | | |
|---|---|---|---|
| እሐር/እሐድ | አንድ ጊዜ | ስድስ | ስድስት ጊዜ |
| ክልዕ | ሁለት ጊዜ | ስብዕ | ሰባት ጊዜ |
| ሥልስ | ሦስት ጊዜ | ሥምን | ስምንት ጊዜ |
| ርብዕ | አራት ጊዜ | ትስዕ | ዘጠኝ ጊዜ |
| ኀምስ | አምስት ጊዜ | ዕሥር | ዐሥር ጊዜ |

፫.፫. <u>**የዕለታት አኀዝ**</u> የዕለታት አኀዝ ከመደበኛው የግእዝ አኀዝ ተለይቶ የሚነገር ሲሆን ይህም በሳምንት እና በወር ተከፍሎ የሚነገር በሳምንት እና በወር ውስጥ ያሉትን ዕለታትን ለመቁጠር የሚያገለግል ነው።

| | |
|---|---|
| እሑድ /አሚር/ አሚሩ | አንደኛ ቀን |
| ሰኑይ/ሰኑዩ | ሁለተኛ ቀን |
| ሠሉስ/ሠሉሱ | ሦስተኛው ቀን |
| ረቡዕ/ረቡዑ | አራተኛ ቀን |
| ኀሙስ/ኀሙሱ | አምስተኛ ቀን |
| ሰዱስ/ስዱሱ | ስድስተኛ ቀን |
| ሰቡዕ/ሰቡዑ | ሰባተኛ ቀን |
| ሠሙን/ሠሙኑ | ስምንተኛ ቀን |
| ተሱዕ/ተሱዑ | ዘጠነኛ ቀን |
| ዐሡር/ዐሡሩ | አስረኛ ቀን |
| ዐሥሩ ወአሚሩ | አስራአንደኛ ቀን |
| ዐሥሩ ወሰኑዩ | አስራሁለተኛ ቀን |
| ዐሥሩ ወሠሉሱ | አስራ ሦስተኛ ቀን |
| : : | : : : |
| ዐሥሩ ወሰሙኑ | አስራ ስምንተኛ ቀን |
| ዐሥሩ ወተሱዑ | አስራ ዘጠነኛ ቀን |
| ዕሥራ/ዕሥራሁ | ሃያኛ ቀን |
| ዕሥራ ወአሚሩ | ሃያአንደኛ ቀን |
| ዕሥራ ወሰኑዩ | ሃያ ሁለተኛ ቀን |
| ዕሥራ ወሠሉሱ | ሃያ ሦስተኛ ቀን |
| : : | : : : |
| ዕሣራ ወተሱዑ | ሃያ ዘጠነኛ ቀን |
| ሠላሳ/ሠላሳሁ | ሰላሳኛ ቀን |





**ማስታወሻ**፡- ስድስተኛውን ቀን ሰዱስ ሲሆን ዐርብ ተብሎ ለምን ይጠራል ቢሉ ዐርብ ዐረበ ገባ ካለው ግሥ የወጣ ሲሆን ዐርብ ማለት መግቢያ መካተቻ ማለት ነው። ይህም የመና መካተቻ የሥራ መካተቻ ነው። ስድስቱን ቀን እሥራኤል መና ይወርድላቸው ነበር። ዐርብ ድርብ ሆኖ የቅዳሜን ፈንታ ተካቶ ይወርድላቸዋል። ይሥራ መካተቻ ነው ዐርብ ሥራቸውን ፈጽመው ቅዳሜ አይሠሩም ይህ ምሳሌ ነው። ምሥጢሩን ጌታችን እና አምላካችን ኢየሱስ ክርስቶስ ለእኛ ሲል ራሱን አሳልፎ ሰጥቶ የአድኅኖት ሥራውን የፈጸመበት ስለሆነ አንድም የፍጥረት መካተቻ ነው ይህም ከእሑድ ጀምሮ ሲፈጥር ቆይቶ ዐርብ የመጨረሻው ፍጥረት ሰው የተፈጠረበት ስለሆነ ከምሥጢር የተነሳ ዐርብ ተብሏል።
ቅዳሜስ ለምን ተባለ ቢሉ ቅዳሜ የሚለው ቀደመ ከሚለው ግሥ የወጣ ሲሆን ቀደመ ማለት ቀደመ ፊተኛ ሆነ ማለት ነው። ይህም ከሰንበተ ክርስቲያን ከእሑድ በመከበር ትቀድማለች እና በዚህ ምሥጢር ምክንያት ቀዳሚት ተብላለች።

ምሳሌ፡- ፩. አመ አሚሩ ለወርኀ ግንቦት ተወልደት እግዝእትነ ቅድስት ድንግል ማርያም ::

፪÷ አመ ሠላሳሁ ለሚያዝያ ኮነ ስምዐ ቅዱስ ማርቆስ ::

፫÷ አመ ዐሥሩ ወሠሉሱ ለመጋቢት አዕረፈ አብ ቅዱስ ዲዮናስዮስ

፬ `አመ ዐሥሩ ወሰዱሱ ለወርኀ ሚያዝያ ተወለድኩ።

፬. <u>**ዕጽፋዊ አኀዝ**</u>፡- መደበኛውን ቁጥር እያጠፈና እየደረበ የሚቆጥር ነው።

| | |
|---|---|
| ምእኀዲት /ካዕበተ አሐዱ/ | አንድ እጅ /እጥፍ/ |
| ምክዕቢት /ካዕበተ ክልዔቱ/ | ሁለት እጅ /እጥፍ/ |
| ምሥልሲት /ካዕበት ሠለስቱ/ | ሦስት እጅ /እጥፍ/ |
| ምርብዒት /ካዕበተ አርባዕቱ/ | አራት እጅ /እጥፍ/ |
| ምኀምሲት /ካዕበት ኀምስቱ/ | አምስት እጅ /እጥፍ/ |
| ምስድሲት /ካዕበተ ስድስቱ/ | ስድስት እጅ /እጥፍ/ |
| ምስብዒት /ካዕበት ሰብዓቱ/ | ሰባት እጅ /እጥፍ/ |
| ምሥምኒት /ካዕበተ ሠመንቱ/ | ሥምንት እጅ /እጥፍ/ |
| ምትስዒት /ካዕበተ ተስዓቱ/ | ዘጠኝ እጅ /እጥፍ/ |
| ምዕሥሪት /ካዕበተ ዐሠርቱ/ | አሥር እጅ /እጥፍ/ |

## የፊደል አኀዝ

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| አ ፩ | ሀ ፭ | ጠ ፱ | መ ፵ | ፈ ፹ | ሰ ፫፻ | ጸ ፺፻ |
| በ ፪ | ወ ፮ | የ ፲ | ነ ፶ | ደ ፺ | ተ ፬፻ | ፐ ፰፻ |
| ገ ፫ | ዘ ፯ | ከ ፳ | ሠ ፷ | ቀ ፻ | ኀ ፭፻ | |
| ደ ፬ | ሐ ፰ | ለ ፴ | ዐ ፸ | ረ ፪፻ | ፀ ፮፻ | |

ምሳሌ:- መርምያዎያስ =፮፻፷፮ መ=፵ ዎ=፮ ሰ=፫፻ ር=፪፻ ያ= ፸ ያ=፲ ም=፵

## ምርጫን /ውሱንነትን/ የሚያሳይ አኀዝ

| | | | |
|---|---|---|---|
| አሐዱሙ | አንዳቸው | ስድስቲሆሙ | ስድስታቸው |
| ክልዔሆሙ | ሁለታቸው | ሰብዓቲሆሙ | ሰባታቸው |
| ሠለስቲሆሙ | ሶስታቸው | ሠመንቲሆሙ | ስምንታቸው |
| አርባዕቲሆሙ | አራታቸው | ተሰዓቲሆሙ | ዘጠኛቸው |
| ኃምስቲሆሙ | አምስታቸው | ዐሠርቲሆሙ | አሥራቸው |

| **በቅርቦች** | | **በአንደኛ መደብ/ባለቤት** | |
|---|---|---|---|
| አሐዱክሙ | አንዳችሁ | አሐዱነ | አንዳችን |
| ክልዔክሙ | ሁለታችሁ | ክልዔነ | ሁለታችን |
| ሠለስቲክሙ | ሦስታችሁ | ሠለስቲነ | ሶስታችን |
| አርባዕቲክሙ | አራታችሁ | አርባዕቲነ | አራታችን |
| ኃምስቲክሙ | አምስታችሁ | ኃምስቲነ | አምስታችን |
| ስደስቲክሙ | ስድስታችሁ | ስደስቲነ | ስድስታችን |

| **በቅርቦች** | | **በአንደኛ መደብ/ባለቤት** | |
|---|---|---|---|
| ሰብዓቲክሙ | ሰባታችሁ | ሰብዓቲነ | ሰባታችን |
| ሠመንቲክሙ | ስምንታችሁ | ሠመንቲነ | ስምንታችን |
| ተሰዓቲክሙ | ዘጠኛችሁ | ተሰዓቲነ | ዘጠኛችን |
| ዐሠርቲክሙ | አሥራችሁ | ዐሠርቲነ | አሥራችን |

፫. **<u>መድበላዊ አኀዝ:-</u>** ያለቁጥር የሚነገር ሰብሳቢና ከታች ቁጥር ሲሆን ስፍሩና ቁጥሩ ባልታወቀ ሁሉ በቅጽልነት እየገባ የሚያገለግል ነው::

**<u>ምሳሌ:-</u>** ብዙኀ ንዑስ ኀዳጥ

ምሉዕ ንስቲት





# ምዕራፍ ፪.

## ሥርዓተ ንባብ ዘልሳነ ግእዝ

በማንኛውም ቋንቋ ንባብ ከተፋለሰ ቋንቋው ለዛ አይኖረውም አንባቢውም የሚነበብለትም ምሥጢሩን አይረዱትም ቃላቱም ትርጉማቸውን ያጣሉ:: ስለሆነም ንባብ በሥርዓት መነበብ አለበት:: ከሌሎች ቋንቋዎች በተለየ ግእዝ የራሱ የሆነ የንባብ ሥርዓት አለው:: ዋናዎቹ የግእዝ የንባብ ዓይነቶች የሚከተሉት ናቸው::

### ፪.፩. ሕግጋተ ንባብ (በጥንታዊ መልክ)

☞ *ከዚህ ቀጥለን የግእዝ ሥርዓተ ንባብን በዝርዝር እናሳያለን::*

1. <u>ተነሽ ንባብ</u>:- አንስቶ ማንበብ ማለት እንደ ቁጣ ቃል መናገር /ማንበብ/ ማለት ነው:: ተነባቢ ቀለሙም ቅድመ መድረሻው ነው:: የተነሽ ንባብ ስልተ ፊደላት አምስት ሲሆኑ እነሱም:- ግእዝ፣ ካዕብ፣ሣልስ፣ራብዕ እና ሳብዕ ቀለም ናቸው:: አብዛኞቹ ተነሽ ንባቦች ከግሥ እና ከግሥ ክፍል የተመሠረቱ ቃላትን የሚያጠቃልል ነው:: ምሳሌ:-

| <u>ግእዝ</u> | <u>ካዕብ</u> | <u>ሣልስ</u> | <u>ራብዕ</u> | <u>ሳብዕ</u> |
|---|---|---|---|---|
| ቀተለ | ሐሙ | ሑሪ | ቀደሳ | ሀቦ |
| ቀደሰ | ቀተሉ | ጸውዒ | ሑራ | ቀተለቶ |
| መጽአ | ንዑ | ሰአሊ | ሀለዋ | ሰዐሮ |
| ከብረ | ዐርጉ | ቀድሲ | ንግራ | አድሕኖ |
| አእመርከ | ገበርክሙ | ቀተልኪ | ርእያ | ኵንኖ |
| ቤትየ | ኀደጉ | ቤትኪ | ኀደጋ | ንወድሶ |
| ሕይወተ | ረኀቡ | ወድሲ | ተፈሥሓ | አእመረቶ |

፬፥ **<u>ወዳቂ ንባብ</u>**፡- ማለት መድረሻ ፊደልን ያዝ ቆየት አድርጎ ማንበብ ማለት ነው። ተነባቢ ቀለሙም ራሱ ነው። የወዳቂ ንባብ ስልተ ፊደላት ሰባቱም ስልተ ፊደላት ናቸው።

**<u>ምሳሌ</u>** ፦

| ግእዝ | ካዕብ | ሣልስ | ራብዕ | ኃምስ | ሳድስ | ሳብዕ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| አሐደ | ኰሉ | ዛቲ | ቅድስና | ጽጌ | ዝ | መሰንቆ |
| አሐተ | ዝንቱ | ቀዳሲ | ዜና | ጊዜ | እምዝ | እፎ |
| ክልዔተ | እሉ | ብእሲ | ደመና | ሥላሴ | ከመዝ | አእምሮ |
| እስፍንተ | መኑ | አረጋዊ | ቀተላ | ሙሴ | | ባረኮ |
| ህየ | ቤቱ | ኰናኒ | ሠምራ | ውዳሴ | | ቀተሎ |

፭፥ **<u>ተጣይ ንባብ</u>**፡- ማለት ተነባቢውን ቀለም ያዝ ቆየት አድርጎ ማንበብ ማለት ነው። ተነባቢ ቀለሙም ቅድመ መድረሻው ነው። የተጣይ ንባብ መድረሻ ሳድስ ቀለም ነው።

**<u>ምሳሌ</u>** ፦

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ዮም | ፆፍ | ዓለም | ወልድ | ወርቅ | ክብር | ትእምርት | ኀብስት |
| እም | ቃል | ወለት | ርግብ | ግብር | ስምዕ | ሊቃውንት | ርኅብት |
| አብ | ማይ | ቅዱስ | ምክር | ዘርእ | ረድእ | ቀሳውስት | አርድእት |
| ሞት | ኄር | ኮከብ | ፍቅር | ባሕር | ፍትሕ | ትስብዕት | እግዚአብሔር |
| ስም | ሦክ | ሢመት | ሀብት | ምድር | ጣዕም | ትሥልስት | ሑር |





፮፥ **<u>ሰያፍ ንባብ</u>**፡- እንደ ተነሽ ንባብ ያለ ሲሆን የሰያፍ ንባብ መድረሻ ሳድስ ቀለም ነው። ሰያፍ ንባብ በሳድስ የሚደርሱ እና ተነስተው የሚነበቡ የግሥ እና የተጸውዖ ስሞችን ያጠቃልላል።

**<u>ምሳሌ</u>** ፦

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ዮሐንስ | አማኑኤል | ጳውሎስ | ይቀትል | የሐውር |
| ጴጥሮስ | ገብርኤል | ኢሳይያስ | ይግበር | ትትሐነጽ |
| ቴዎፍሎስ | ሰንድሮስ | ጤግሮስ | አቤል | አእመረት |

***<u>ማስታወሻ፡-</u>***

ግሦች ሁሉ ተነስተው ይነበባሉ ግሦችን በአሥሩ መራሕያን በምንዘረዝርበት ጊዜ «አንትን» ብቻ ተጣይ ሲሆን ሌሎቹ ዘጠኙ ተነስተው ይነበባሉ። በንዑስ እርባታም ጊዜ ከ «አንትን» በስተቀር ፴፱ኙ ተነስተው ይነበባሉ። በሁለተኛ መደቦች ትእዛዝ አንቀጽ ሁለት ፊደል እና መድረሻው ሳድስ ቀለም ከሆነ ተጣይ ሆኖ ይነበባል።

ምሳሌ ፡- ቀተለ፣ ተንበለ፣ ቀደሰ፣ ቆመ

ከዚሁ ጋር በተጨማሪ በዝርዝርም ሆነ በእርባታ ጊዜ ‹‹ክን›› የሚለው ቀለም መድረሻ ከሆነ ንባቡ ተጣይ ሆኖ ይነበባል።

ምሳሌ በዝርዝር ጊዜ ፡- ተንበልክን፣ ቀደስክን ፣ አእመርክን

ምሳሌ በእርባታ ጊዜ ፡- አእመሩክን ፣ አእመረክን ፣ አእመረተክን

ትእዛዝ አንቀጽ ሁለት ፊደል ከሆነ እና ሳድስ ከሆነ ተጣይ ንባብ ሆኖ ይነበባል። ምሳሌ፡- ሑር፣ ቁም፣ዑድ

በዝርዝር እርባታ ጊዜም ውእቱ፣ አንተ፣ ንሕነ፣ ውእቱን፤ ይእቲን፤ ውእቶንን በሚዘረዝሩበት ጊዜ ኃላፊና ትንቢት አንቀጽ ወዳቂ ወይም ተጣይ ሆነው ይነበባሉ። /ተጣይ በሳድስ ከደረሱ/ ውእቱ፣ ውእቱን ሲዘረዝር

| ምሳሌ፡- ውእቱ | <u>ውእቱን</u> | <u>ይእቲን</u> | <u>ውእቶንን</u> |
|---|---|---|---|
| | አእመሮ | አእመራ | አእመሮን |
| | የአምሮ | የአምራ | የአምሮን |

| | | | |
|---|---|---|---|
| አንተ ሲዘረዘር | ውእቱን | ይእቱን | ውእቶንን |
| | አእመርኮ | አእመርካ | አእመርኮን |
| | ተአምሮ | ተአምራ | ተአምሮን |
| ንሕነ ስንዘረዝር | ውእቱን | ይእቲን | ውእቶንን |
| | አእመርኖ | አእመርና | አእመርኖን |
| | ነአምሮ | ነአምራ | ነአምሮን |

**ይእቲ፣አነ፣ *ውእቱን፤ ይእቲን፤ ውእቶንን*** በሚዘረዝሩበት ጊዜ ካልዓይ አንቀጽ ወዳቂ ወይም ተጣይ ሆነው ይነበባሉ።

| | | | |
|---|---|---|---|
| ይእቲ ስትዘረዝር | ውእቱን | ይእቲን | ውእቶንን |
| | ተአምሮ | ተአምራ | ተአምሮን |
| አነ ስዘረዝር | ውእቱን | ይእቲን | ውእቶንን |
| | አአምሮ | አአምራ | አአምሮን |

**አንትን** ውእቶንን ሲዘረዝሩ ኃምስና ትንቢት አንቀጽ ተጣይ ሆነው ይነበባሉ።

| | |
|---|---|
| አንትን ሲዘረዝሩ | ውእቶንን |
| | አእመርክናሆን |
| | ተአምራሆን |

**ውእቶን** ውእቶንን ሲዘረዝሩ ኃምስና ትንቢት አንቀጽ ተጣይ ሆነው ይነበባሉ።

| | |
|---|---|
| ውእቶን ሲዘረዝሩ | ውእቶንን |
| | አእመራሆን |
| | የአምራሆን |

**ውእቶሙ** ሲዘረዝሩ ከአንትን በስተቀር ሁሉም ተነሽ ሆኖ ይነበባል። **አንትሙ** እና አንቲ ሲዘረዝሩ ሁሉም ተነሽ ሆኖ ይነበባል።

በዝርዝርም ሆነ በእርባ ጊዜ መድረሻ ቀለሙ ‹‹ክን›› የሆነ ቃል ተጣይ ሆኖ ይነበባል እንዳልነው ሁሉ መድረሻ ቀለሙ ‹‹ሁ››፣ ‹‹ሃ›› የሆነ የ‹‹ሀ›› ቤት ግሥ ካልሆነ በስተቀር ወዳቂ ቀለም ሆኖ ይነበባል።

ምሳሌ ፩፦ የተነሽ ንባብ ምሳሌ፦ በርሃ፣ ተግሃ፣ ሎሃ

፪. የወዳቂ ንባብ ምሳሌ፦ *ሥጋሁ፣ ሥጋሃ*፣ አእመራሁ፣ አእመራሃ

አንዳንድ ቀለማት በትርጉማቸው መሠረት ተነስተው ወይም ወዳቂ ሆነው ይነበባሉ።

| ምሳሌ | ተነሽ | ወዳቂ |
|---|---|---|
| | አእመራ (አወቁ) | አእመራ (አወቃት) |
| | የአምራ (ያውቃሉ) | የአምራ (ያውቃታል) |
| | እመኒ (እመኝ) | እመኒ (ቢ) አገባብ |
| | እምነ (እናታችን) | እምነ (ከ) አገባብ |





## ንዑሳን ንባባት

እነዚህ ከአራቱ ዐበይት ንባባት ውስጥ ሲሆኑ ነገር ግን የአነባበብ ስልታቸውን በማየት ይህ ስያሜ ተሰጥቷቸዋል።

ሀ/ **ዐራፊ ንባብ**፦ ማለት በዐረፍተ ነገር ውስጥ እያንዳንዱን ቃል በተለየ ማንበብ ወይም አንድን ቃል ካነበቡ በኋላ በማረፍ ሌላውን ቃል ማንበብ ማለት ነው።

| | |
|---|---|
| አክብር አባከ ወእመከ ። | እፎ ይከውን ። |
| ተንሥእ ወንሣእ ዐራተከ ። | ዓዲ ኢበጽሐ። |
| ኢትዝግቡ ለክሙ መዝገበ ። | |

ሁ/ **ቆጣሪ ወይም ጠቅላይ ንባብ**፦ «እ» ወይም «ሀ» በመካከሉ የሚገኙበት ቃል ተጠቅልሎ ወይም ፊደሉን በመቁጠር የሚነበብ ስለሆነ ቆጣሪ ወይም ጠቅላይ ንባብ ይባላል።

አዕረገ አዕሩግ አዕጹቅ ማኅቶት

ሂ/ **ተናባቢ ንባብ**፦ አንድ ቃል ከሌላ ቃል ጋር ያለ እረፍት በአንድ ትንፋሽ ከተነበበ ተናባቢ ነው። ተናባቢ የሚሆኑ ቀለማት ግእዝ፣ ራብዕ፣ ኃምስ፣ ሳብዕ ቀለማት ናቸው።

ሀ. **ሳድስ ቀለም ወደ ግእዝ ተለውጦ ተናባቢ ይሆናል**።

ተአምር ማርያም ፡ ተአምረ ማርያም

ሙዳይ ምጽዋት ፡ ሙዳየ ምጽዋት

መሠረት ሕይወት ፡ መሠረተ ሕይወት

ወልድ ዳዊት ፡ ወልደ ዳዊት

መጽሐፍ ልደቱ ፡ መጽሐፈ ልደቱ

ለ. <u>ራብዕ፣ ኃምስ፣ ሳብዕ ቀለማት ሣይለወጡ ተናባቢ ይሆናሉ።</u>

| | | |
|---|---|---|
| ደብተራ ኦሪት | ትንሣኤ ሙታን | ከበሮ ማኅሌት |
| መሐላ ብእሲ | ፍካሬ ኢየሱስ | ተዋሕዶ ሥጋ |
| ጥቃ ቤት | ውዳሴ አምላክ | መሰንቆ ዳዊት |

ሐ. <u>ሣልስ ቀለም ወደ ኃምስ ተለውጦ ተናባቢ ንባብ ይሆናል</u>

| | |
|---|---|
| ሰባኪ ወንጌል | ሰባኬ ወንጌል |
| ገባሪ ተአምር | ገባሬ ተአምር |

መ. <u>የሥያሜ ተናባቢዎች</u>

መልአከ ገብርኤል

ሰማዕተ ጊዮርጊስ

ነቢየ ሙሴ

ሃ/ <u>ጠብቆ የሚነበብ</u>፡- ጠባቂ ንባብ ረገጥ ጫን ተደርጎ የሚነበብ የንባብ ዓይነት ነው። ምሳሌ፡-

| | | | |
|---|---|---|---|
| ቀደሰ | ሰብሐ | ይቄድስ | ወጠነ |
| ጸውዐ | የበበ | ይቀትል | ጠባብ |
| መካሕ | ይቀትል | ኀደገ | ሐመ |
| ኀዳግ | ነካር | አጥመቅሙ | ነበ |

- ቀደሰን የመሰለ ግሥ ሁሉ ጠብቆ ይነበባል። «አ» ወይም «ሀ» ከሌሉበት ካልዓይ አንቀጽ የሁሉም ጠብቆ ይነበባል። «ቀ» «ከ» «ገ» የግሥ መድረሻ ሲሆኑ በሁለተኛ መደብና በአነ ባለቤት አመልካቹን አስወጥተው እራሳቸው ጠብቀው ይነበባሉ። «ነ» የግሥ መድረሻ ሲሆን በንሕነ ባለቤት አመልካቹን አስወጥቶ እራሱ ጠብቆ ይነበባል።
- ፍጹም ግእዝ ሁለት ቀለማት የሆነ ግሥ መድረሻው ይጠብቃል።





ሄ/ <u>ላልቶ የሚነበብ</u>፡- ሳይጠብቅ ከፊደል ገበታ ላይ እንደምናነበው ያለ የንባብ ሥልት የሚላላ ንባብ ነው።

ቀተለን የመሰለ ግሥ ሁሉ ላልቶ ይነበባል። ካልዓይ አንቀጽ ጠብቆ የሚነበብ ቢሆንም «ሀ» ወይም «አ» በመሀል ካሉ ላልቶ ይነበባል።

| | | |
|---|---|---|
| ቀተለ | ሐመመ | ነበበ |
| ይሜህር | ነደደ | ይቅትል |
| ገብረ | ይስእል | |
| ድኅነ | ይስዐር | |

ህ/ <u>አላህላህያን /አ፡ሀ፡በ/</u>

እናህ ቀለማት መነሻ መሀል መድረሻ ሲሆኑ በሁሉ አይጠብቁም ላልተው ይነበባሉ እንጂ «በ» ደግሞ በሁለት ቀለማት መድረሻ ሲሆን ይጠብቃል እንጂ በተቀረው ላልቶ ይነበባል።

ምሳሌ፡-

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ድሕነ | መሀረ | ሰአለ | ሰዐለ | ሆከ | በርሀ |
| ይድሕን | ይሜህር | ይስእል | ይስዕር | የሀውክ | ይበርህ |
| ይድሐን | ይምሀር | ይስአል | ይስዓር | ይሁክ | ይብራህ |

ነበረ ነበበ

<u>ይነብር</u> <u>ይነብብ</u> <u>ጠበ</u> <u>ነበ</u> ጠብቆ ይነበባል

ይንበር ይንብብ

**የትራስ ፊደላት ንባብ** ፡- ትራስ ፊደላት የሚባሉት ሰ፣ ሶ፣ መ፣ ሀ፣ ሂ፣ ሃ፣ ኒ፣ አ፣ ኬ የመሰሉት ናቸው እነዚህ ፊደላት ተነሽ ተጣይና ሰያፍ ንባባትን ወዳቂ ሲያደርጉ ወዳቂውን ተነሽ ንባብ ያደርጉታል ።

ምሳሌ ወዳቂውን ተነሽ ሲያደርጉ ፡- ዝንቱስ፣ እፎኑመ፣ ይእዜሰ ኢያሪኮመ

ምሳሌ ወዳቂ፣ ተጣይ፣ ሰያፍ፣ ተነሽ ቀለማትን ወዳቂ ሲያደርጉ፡-

| | | | |
|---|---|---|---|
| ሰብእሰ | አብርሃምሰ | ሰማየኒ | እፎኑ |
| ምድርሰ | ይስሐቅሀ | ዘንተአ | ሙሴኒ |
| ማርያምሃ | አድሕንሶ | እዴየአ | |
| ዳዊትኒ | ማትያስሀ | ለከአ | ኅቤዛአ |
| ምንትኬ | አእምርኬ | ዓለመሰ | እገሌአ |

«ሰ» አገባብ ላይ በመድረሻ ከተገኘ ለተገብሮ አጸፋነት «ዝ» ለገቢር አጸፋነት «ዘ» የሚለው ብቻ ተነሽ ንባብ ሲያደርግ በተቀረው ግን ወዳቂ ንባብ ያደርጋል።

ዝሰ - ተነሽ ንባብ    እመሰ - ወዳቂ ንባብ

ዘሰ - ተነሽ ንባብ    ሶበሰ - ወዳቂ ንባብ

- «ኑ»«ሁ» መጠይቃን ቃላት ሲሆኑ ንባባቸው ወዳቂ ንባብ ነው።

ምሳሌ ፡- ምንትኑ  አኮሁ  ምንትሁ  ሶበሁ

## <u>የተጸውዖ ስም የንባብ ሕግጋት</u>

፩፥ ሀ. ሦስት ቀለም ሆኖ በግእዝ ተነስቶ ድርድሩ ራብዕ፣ ኃምስ፣ ሳብዕ የሆነ ስም ተነሽ ንባብ ነው።

*ምሳሌ ፦ አቤል ፣ አጋር ፣ አሞጽ፣ ረዓብ፣ አዜብ*

ለ. በግእዝ ተነስቶ ቅድመ መድረሻው ሳብዕ የሆነ ስም ተነስቶ ይነበባል።

ሰሎሞን፣ አርዮስ፣ ፈርዖን፣ መርቆርዮስ፣ ገላውዴዎስ፣ አውሳብዮስ፣

ሐ. በግእዝ ወይም በራብዕ ተነስቶ ቅድመ መድረሻው ሣልስ የሆነ ስም ተነስቶ አይነበብም

ምሳሌ ፦ አቡቀለምሲስ፣ አብጥሊስ፣ፋሲል፣ዳዊት

፪፥ ሀ. በካዕብ ተነስቶ ድርድሩም ካዕብ፣ ኃምስ፣ ሳብዕ የሆነ ስም ተነስቶ ይነበባል። ምሳሌ፡- ሱቱኤል፣ ቡኤዝ

ለ. በካዕብ ተነስቶ ደካማ ቀለም /ራብዕ/ ካለው ተነስቶ አይነበብም

ምሳሌ፡- ሩፋኤል፣ ኡራኤል





፫፥ ሀ. በሣልስ ተነስቶ በድርድሩ ሁለት ደካማ ቀለም የያዘ ስም ተነሽ ንባብ ነው።

ምሳሌ ፡- ቂርቆስ፣ ሲላስ፣ ሚናስ፣ ጢሞቴዎስ፣ ሲድራቅ

ተነስቶ የማይነበብ ሕገወጥ የሆነ ቀለም፡- ሚሳኤል ፣ሚካኤል

ለ. በሣልስ ተነስቶ ሦስት ደካማ ቀለም ሲደረድር እና ቅድመ መድረሻው ሣልስ፣ ኃምስ፣ ሳብዕ፣ የሆነ ስም ተነስቶ አይነበብም።

ምሳሌ ፡- ጊዮርጊስ፣ ሚካኤል፣ ጲላጦስ፣ ሊባኖስ

፬፥ በራብዕ ተነስቶ ድርድሩ ካዕብ፣ራብዕ፣ ኃምስ፣ ሳድስ፣ ሳብዕ የሆነ ስም ተነስቶ ይነበባል።

ምሳሌ ፡- ማቴዎስ፣ ሳሙኤል፣ ፋኑኤል፣ ባቱኤል፣ ራጉኤል፣ ባሮክ፣ ራሔል፣ ያሬድ፣ ሳሌም

ተነስቶ የማይነበብ፡- ናብሊስ፣ ራፋስቂስ

፭፥ ሀ. በኃምስ ተነስቶ ድርድሩ ካዕብ፣ ራብዕ፣ኃምስ፣ ሳድስ፣ ሳብዕ የሆነ ስም ተነስቶ ይነበባል።

ምሳሌ፡- ሄኖክ፣ ሴሎሜ፣ኤፍራጥስ፣ ኤልቄዶን፣ ኤፍሬም፣ ቴዎፍሎስ፣ ኤርምያስ፣ ቄርሎስ።

ለ. በኃምስ ተነስቶ ድርድሩ ሦስት ደካማ ቀለማት የሆነ ቅድመ መድረሻው ኃምስ፣ሁለት ሳድስ ቀለም የሆነ ስም ተነስቶ አይነበብም

ምሳሌ ፡- ሄሮድስ፣ ኤልሳቤጥ፣ ኤልሳቤል

፮÷ ሀ. በሳድስ ተነስቶ ድርድሩ ራብዕ፣ ኃምስ፣ ሳድስ፣ ሳብዕ የሆነ ስም ተነስቶ ይነበባል::

ምሳሌ :-ጥብርያዶስ፣ እንድርያስ፣ ሕዝቅያስ፣ ንስጥሮስ፣ ስምዖን

ተነስቶ የማይነበብም አለ:: እስራኤል

ለ. በሳድስ ተነስቶ ሦስት ደካማ ቀለም ሲኖር ተነስቶ አይነበብም

ምሳሌ :- እስጢፋኖስ፣ እግዚአብሔር

ፍጹም ሳድስ ከሆነም ተነስቶ አይነበብም ከአንድ በስተቀርም ቢሆን

ምሳሌ :- ግብፅ፣ ክርስቶስ፣ እስክንድሮስ፣ እስክንድር፣ጽርእ

፯÷ ሀ. በሳብዕ ተነስቶ ድርድሩ ራብዕ፣ ኃምስ ሳብዕ፣ የሆነ ስም ተነስቶ ይነበባል::

ምሳሌ :- ቶማስ፣ ሮቤል፣ ቆሮንቶስ፣ ዮሴፍ ሶፎንያስ፣ ዮናታን፣ ዮናስ፣ ዮሐንስ

ለ. በሳብዕ ተነስቶ ቅድመ መድረሻው ሣልስ ከሆነ ተነስቶ አይነበብም::       ምሳሌ :- ዮዲት ፣ሆሊሆርኒስ

፰÷ ሀ. ሁለት ቀለም የሆነ ስም ወዳቂ ወይም ተጣይ ንባብ ነው::

ምሳሌ :- ሙሴ፣ ካም፣ ሎጥ፣ ሩት

ለ. ማንኛውም ስም መድረሻው ከሳድስ ውጪ ከሆነ ተነስቶ አይነበብም::

ምሳሌ:- አበበ ፣ በቀለ





# ቅዱስ ያሬድ

በዛቲ ዕለት አመ-ዐሡሩ ወ-አሚሩ ለ-ግንቦት አዕረፈ ያሬድ ማሕሌታይ አምሳሊሆሙ ለሱራፌል  ወዝንቱ እምአዝማዲሁ ውእቱ አባ ጌዴዎን እምካህናተ አክሱም እንተ ይእቲ ቀዳሚት እም እለ ተሐንጻ አብያተ ክርስቲያናት በሀገረ ኢትዮጵያ። ወተሰብከ ባቲ ሃይማኖተ ክርስቶስ ወተቀደሰት በስመ እግዝእትነ ማርያም ወዝንቱ አባ ጌዴዎን ወሰበ ወጠነ ይምሀሮ መዝሙረ ዳዊት ለብጹዕ ያሬድ ስእነ አጽንዖቶ አስከ ብዙኅ መዋዕል ወእም ዝ ሶበ ዘበጦ ወአሕመሞ ኀየ ውስተ ገዳም ወ አጽለለ ታሕተ ዖም ወርእየ ዕፄ እንዘ የዐርግ መልዕልተ ዖም ወበጺሖ ኀበ መንፈቃ ይወርድ ውስተ ምድር ብዙኀ ጊዜ ይገብር ከማሁ ወእም ዕፁብ ዐርደ መልዕልተ ዖም ወሶበ ርእየ ያሬድ ትጋሆ ለ ዕፄ ነስሐ በነፍሱ ወተመይጠ ኀበ መምህሩ መንፈሳዊ ወሶበ ሰአለ ኀበ እግዚአብሔር በብካይ ተርኅወ ልቡናሁ ወተምህረ በአሐቲ ዕለት መጻሕፍተ ብሉይ ወሐዲስ።

ወእምዝ ተመይጠ ዲያቆነ። ወበውእቱ መዋዕል አልቦ ማሕሌተ ቅኔ በልዑል ዜማ ዘእንበለ ለሆሳስ። ወሶ በፈቃደ እግዚአብሔር ከመ ያቅም ሎቱ ተዝካረ። ወፈነወ ሠለስተ አዕዋፈ ኤዶም ወተናገርዎ በልሳነ ሰብእ ወመሰጥዎ ምስሌሆሙ ውስተ ኢየሩሳሌም ሰማያዊት ወበህየ ተምህረ ማሕሌቶሙ ለእስራ ወአርባዕቱ ካህናተ ሰማይ። ወሶበ ተመይጠ ኀበ ህላዌሁ ቦአ ውስተቤተክርስቲያን ቅድስት ዘገበዘ አክሱም በጊዜ ሠለስቱ ሰዓት ወከልሀ በልዑል ቃል እንዘ ይብል ሃሌ ሉያ ለአብ ሃሌ ሉያ ለወልድ ሃሌ ሉያ ለ-መንፈስ ቅዱስ። ቀዳሚሃ ለጽዮን ሰማየ ሣረረ ወበዳግም አርአዮ ለሙሴ ዘከመይገብር ግብራ በደብተራ። ወሰመያ ለዛቲ ማሕሌተ አርያም። ወሶበ ሰምዑ ድምፀቃሉ ሮጹ ንጉስኒ ምስለ ጳጳስ ወከህናት ወዐበይተ ንጉሥ ወወዐሉ እንዘ ይሰምዕዎ ማህሌተ ለለ ዘመኑ እም ዓመት እስከ ዓመት። ዘሐጋይ ወዘክረምት ዘጸደይ ወዘመፀው ወዘበዓላት ወዘሰናብት ዘመላእክት ወዘነቢያት ወዘሰማዕታት ወዘጻድቃን። ወሠለስቱ ዜማ ዘውእቱ ግእዝ ወዕዝል ወአራራይ ወኢየዐዱ እም ሠለስቱ ዜማሁ እመሂ ንባበ ሰብእ አው ንቃወ ዖፍ ወእንስሳ። ወበአሐቲ ዕለት አንዘ ይዜምር ቀዊሞ ታሕተ መከየደ እገሪሁ ለንጉሥ ገብረ መስቀል ወንጉሥኒ ያደምፅ ቃሎ በትረሐጺን ውስተ መከየደ እገሪሁ እስከ ይውኅዝ እምኔሁ ደም ብዙኅ ወኢተዐውቆ ለያሬድ እስከ ፈጸመ ማሕሌቶ። :

ወሶበ ርእየ ንጉሥ ደንገጸ ወመልሐ በትሮ እምእግሩ ወይቤሎ ሰአለኒ ዘትፈቅድ ዐስበ ዝንቱ ደምከ ዘተከህወ። ወይቤሎ ያሬድ ፈንወኒ ከመ እመንኰስ፡ ወሰሚያ ንጉሥ ተከዘ ጥቀ ምስለ ኵሉ ሠራዊቱ። ወከመ ይከልኦ ሂ ፈርሀ መሐላሁ ወበዊኦ ያሬድ ውስተ ቤተ ክርስቲያን ቆመ ቅድመ ታቦተ-ጽዮን። ወሶበ ይቤ ቅድስት ወብፅዕት ስብሕት ወቡርክት ክብርት ወልዕልት እስከ ተፍጻሜቱ ተሰዐለ እምምድር መጠነእመት።
ወእምዝ ሖረ ኀበ ገዳመ ሰሜን ወነበረ በህየ ወወሀቦ እግዚአብሔር ኪዳነ ለዘይጼውዕ ስሞ ወይገብር ተዝካሮ። ወእምዝ አዕረፈ በሰላም። መቃብሪሁሰ ኢተዐውቀ እስከዮም።

## በእንተ ትስብእቱ በዕለተ እሑድ

ተአምሪሃ ለእግዝትነ ቅድስት ማርያም ድንግል በክክዔ ማርያም ወላዲተ አምላክ ጸሎታ ወበረከታ የሃሉ ምስሌነ ለዓለመ ዓለም አሜን። ወበአሐቲ ዕለት አመ ወ ለወርኀ መጋቢት ዘውእቱ ሰንበት እንዘ ትጼሊ ጸሎተ እግዝእትነ ቅድስት ድንግል በክልዔ ማርያም ወላዲተ አምላክ አስተራአያ ገብርኤል በዐቢይ ግርማ ወዜነዋ ትፍስሕተ ወሶበ ርእየቶ ደንገጸት ወይቤላ ሰላም ለኪ ኦ ምልእተ ጸጋ እግዚአብሔር ምስሌኪ ወሰሚዓ ደንገጸት እም ቃሉ ወፈርሐት ወጕየት ወቦአት ውስተ ቤታ ወነበረት በከመ ልማዳ እንዘ ትፈትል ወርቀ ወሜላተ ወትሔሊ በልባ ወትቤ ምንትኑ ዝ ነገር ዘርኢኩ ወዝ ሰላም ዘሰማዕኩ ወእንዘ ትሔሊ ከመዝ አስተራአያ ገብርኤል መልአክ ወዜነዋ ትፍስሕተ ወይቤላ ኢትፍርሂ ማርያም እስመ ረከብኪ ሞገሰ በኀበ እግዚአብሔር ወናሁ ትጸንሲ ወትወልዲ ወልደ ወትሰምዪዮ ስሞ ኢየሱስ ወውእቱ ዐቢይ ወያድኅኖሙ ለሕዝቡ እምኃጢአቶሙ ወትቤሎ ማርያም እፎ-ኑ ይከውነኒ ዝንቱ እንዘ ኢ የአምር ብእሴ ወይቤላ መልአክ መንፈስ ቅዱስ ይመጽእ ላዕሌኪ ወኃይለ ልዑል ይጼልለኪ እስመ ዘይትወለድ እምኔኪ እምመንፈስ ቅዱስ ውእቱ ወይሰመይ ወልደ እግዚአበሔር ሕያው ወናሁ ኤልሳቤጥኒ እንተ እም አዝማድኪ ፀንሠት በልሕቃቲሃ ወበርስዓቲሃ እስመ አልቦ ነገር ዘይሰአኖ ለእግዚአብሔር ወትቤሎ ማርያም ይኩነኒ በከመ ትቤለኒ ወሰሚያ መልአክ ነገራ ለእግዝእትነ ቅድስት ድንግል በክልዔ ማርያም ወላዲተ አምላክ አስተፍስሓ ወመልአተ ኃይለ እም አይቴ ሰዓት ወኀደረ ቃለ እግዚአብሔር ውስተማሕፀና ወነበረት እግዝእትነ ማርያም እንዘ ትትፌሣሕ ወትትኀሠይ ወመላእክት ይናዝዝዋ ጸሎታ ወበረከታ የሃሉ ምስሌነ ለዓለመ ዓለን አሜን።





## ምዕራፍ ፫

## መራሕያን

መራሕያን የሚለው ሣልስ ቅጽል መርሐ(መራ) ከሚለው የግእዝ ግሥ የወጣ ሲሆን መራሕያን ማለት መሪዎች ማለት ነው። መራሕያን እነማንናቸው መሪዎችስ ለምን ተባሉ ቢሉ መራሕያን ፲ ናቸው እነሱም በመደብ በቁጥር እና በጾታ ተለይተው እንደሚከተለው ቀርበዋል።

| መደብ | ነጠላ | ብዙ | ጾታ |
|---|---|---|---|
| ፩ኛ ባለቤት (ነባቢ) | አነ (እኔ) | ንሕነ (እኛ) | የወል |
| ፪ኛ ቅርብ | አንተ (አንተ) | አንትሙ (እናንተ) | ተባዕት |
| | አንቲ (አንቺ) | አንትን (እናንተ) | አንስት |
| ፫ኛ ሩቅ | ውእቱ (እሱ) | ውእቶሙ/እሙንቱ (እነሱ) | ተባዕት |
| | ይእቲ (እሷ) | ውእቶን/እማንቱ (እነሱ) | አንስት |

መራሕያን መሪዎች መባላቸው በወንድና በሴት በሩቅና በቅርብ በነጠላና በብዙ የሚነገረውን እርባታ ስለሚያመለክቱ /ስለሚመሩ/ ግሥ መሪ እርባ ዘርዛሪ ስለሆኑ መሪዎች ተብለዋል። ያለመራሕያንም የግእዝ ሰዋሰው አንድና ብዙ ቅርብና ሩቅ ወንድና ሴት አይነገርም።

# የመራሕያን አገልግሎት

መራሕያን ፈርጀ ብዙ አገልግሎት አላቸው፡፡ ከነዚህም መካከል የተወሰኑትን ከዚህ እንደሚከተለው እናቀርባለን፡፡

## ፫.፩. የስም ምትክ (ተውላጠ ስም ) ይሆናሉ

መራሕያን ስምን አህለው የስምን ቦታ ተክተው ሲነገሩ የስም ምትክ ይባላሉ፡፡ መራሕያን ስምን ተክተው ሲነገሩ ያላቸው ትርጉም ከላይ አሥሩን መራሕያን በመደብ በቁጥር እና በጾታ ለይተን እንዳየነው ሲሆን ነገሩን ግልጽ ለማድረግ የሚከተሉትን ምሳሌዎች እናሳያለን፡፡

ምሳሌ ፩. አበበ መጽአ እምቤቱ (አበበ ከቤቱ መጣ)

የስም ምትክ ስንጠቀም፡-ውእቱ መጽአ እምቤቱ (እሱ ከቤቱ መጣ)

ምሳሌ ፪. (አልማዝ ወደ ቤተክርስቲያን ሄደች) አልማዝ ሖረት ኀበ ቤተክርስቲያን የስም ምትክ ስንጠቀም፡- ይእቲ ሖረት ኀበ ቤተ ክርስቲያን፡፡ (እሷ ወደቤተ ክርስቲያን ሄደች)

ምሳሌ ፫. ሙሴ ወኤልያስ ቆሙ ለጸሎት፡፡

(ሙሴ እና ኤልያስ ለጸሎት ቆሙ)

**የስም ምትክ ስንጠቀም፡-** ውእቶሙ ቆሙ ለጸሎት (ሙሴ እና ኤልያስ ለጸሎት ቆሙ)

ከላይ በሦስቱም ምሳሌዎች እንዳየነው መራሕያን ስምን ተክተው ያገለግላሉ፡፡ መጽአ (መጣ) ሖረት (ሄደች) ቆሙ (ቆሙ) ብለን መናገራችን መራሕያን ግስ መሪ እርባ ዘርዛሪ መሆናቸውን ያሳያል፡፡ የግስ ዝርዝር ትምህርትን ወደፊት የምናቀርብ ሲሆን ተጨማሪ መልመጃዎችን ለመሥራት ይረዳን ዘንድ ቀደሰ (አመሰገነ) የሚለውን ግሥ በመራሕያን እንደሚከተለው እንዘረዝራለን፡፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| ውእቱ | ቀደሰ (አመሰገነ) | ውእቶሙ | ቀደሱ (አመሰገኑ) |
| ይእቲ | ቀደሰት (አመሰገነች) | ውእቶን | ቀደሳ (አመሰገኑ) |
| አንተ | ቀደስከ(አመሰገንክ) | አንትሙ | ቀደስክሙ(አመሰገናችሁ) |
| አንቲ | ቀደስኪ(አመሰገንሽ) | አንትን | ቀደስክን(አመሰገናችሁ) |
| አነ | ቀደስኩ(አመሰገንኩ) | ንሕነ | ቀደስነ(አመሰገንን) |





ምሳሌ ፬. የሚከተሉትን ቃላት ካጠናችሁ በኋላ በምሳሌው መሠረት መራሕያን የስም ምትክ ሆነው ሲያገለግሉ አሳዩ፡፡

| | |
|---|---|
| ፈጠረ (ፈጠረ) | ሰገደ (ሰገደ) |
| መኳንንተ ዓለም (የዓለም ገዢዎች) | እምሥያጥ (ከገበያ) |
| ቅድመ መስቀል (ከመስቀል ፊት) | መጽአ (መጣ) |

- አንተ እግዚአብሐር ፈጠርከ ፀሐየ ወወርኀ፡፡
  አንተ ፈጠርከ ፀሐየ ወወርኀ
- አበበ መጽፈ እምብሔረ ዐረብ
  ውእቱ መጽአ እምብሔረ ዐረብ፡፡
- *ማርያወማርታ* ሰገዳ ለክርስቶስ:: *ውእቶን* ሰገዳ ለክርስቶስ፡፡
- *ጳውሎስ ወጴጥሮስ* መኳንንተ ዓለም አንትሙ::
  *አንትሙ* መኳንንተ ዓለም አንትሙ ::
- *አልማዝ ወአስቴር* መጻእክን እምሥያጥ::
  *አንትን* መጻእክን እምሥያጥ::
- *ማርያም ወዮሐንስ* ቆማ ቅድመ መስቀል::
  *ውእቶን* ቆማ ቅድመ መስቀል::
- ♦ *ዮሐንስ ወማርያም* ቆሙ ቅድመ መስቀል::
  *ውእቶሙ* ቆሙ ቅድመ መስቀል::

## ፫.፪. ነባር አንቀጽ ይሆናሉ

ነባር ዘርነት የሌለው ከዘር አንቀጽ የማይገኝ በውጥንቅጥነት የሚገኝ ጥሬ ቃል ሲሆን የማይፈልስ የማይለወጥ ማለት ነው፡፡ ነባር አንቀጽ ማለት ሳይለወጥ የኖረ ኗሪ አንቀጽ ማለት ሲሆን ይህም የአንድ ሁኔታ መሆን ወይም የአንድ ነገር መኖር አንቀጽ ነው፡፡ ነባር መባሉ ኃላፊ፣ ትንቢት፣ ዘንድ፣ ትእዛዝን ቦዝ አንቀጽን በእርባታ ፍች ካልሆነ በቀር ለንባብ ስለማያስረዳ ንዑስ አንቀጽ ሳቢዘርና ጥሬዘር ስለሌለው ነው፡፡

መራሕያን ነባር ማሠሪያ አንቀጽ ሆነው ያገለግላሉ ስንል የዐረፍተ ነገር ማሠሪያ አንቀጽ ይሆናሉ ማለታችን ነው። ስምን ተክተው ሲነገሩ ከነበራቸው ትርጉም በተለየ እንደሚከተለው ይተረጎማሉ።

| | |
|---|---|
| አነ ነኝ፣ ነበርኩኝ | ንሕነ ነን፣ ነበርን |
| አንተ ነህ፣ ነበርክ | አንትሙ ናችሁ፣ ነበራችሁ (ተባዕት) |
| አንቲ ነሽ፣ ነበርሽ | አንትን ናችሁ፣ ነበራችሁ (አንስት) |
| ውእቱ ነው፣ ነበረ | ውእቶሙ ናቸው፣ ነበሩ (ተባዕት) |
| ይእቲ ናት፣ ነበረች | ውእቶን ናቸው፣ ነበሩ (አንስት) |

ምሳሌ ፩ ፡- መኑ አነ (ማን ነኝ)

፪ መኑ ይእቲ (ማን ናት)

፫ እለመኑ አንትሙ (እነማን ናችሁ)

፬ ፡- ማርያም ይእቲ ወላዲተ አምላክ።

ማርያም አምላክን የወለደች ናት

፭ ፡- መሐሪ ውእቱ እግዚአብሔር (እግዚአብሔር ይቅር ባይ ነው)

ማስታወሻ፡- ውእቱ በማሠሪያ አንቀጽነት ከራሱ በተጨማሪ የሌሎቹን ሙያ ደርቦ ይሠራል ይህም በአንድ ዐረፍተ ነገር ውስጥ ሌሎቹ ዘጠኙ መራሕያን የስም ምትክ (ባለቤት) ሆነው ውእቱ ደግሞ ነባር ማሠሪያ አንቀጽ ሆኖ ያገለግላል ማለቱ ነው። ውእቱ ነው ነበረ ከመባሉ በተጨማሪ ናት ነበረች፤ ነኝ ነበርኩኝ፤ ነን ነበርን፤ ናቸው ነበሩ፣ እያለ የሁሉንም ሙያ ደርቦ ይሠራል።

ምሳሌ ፩ መኑ ውእቱ አነ። (እኔ ማን ነኝ)

አነ እኔ (የስም ምትክ) ባለቤት

ውእቱ ነኝ ተብሎ ተተርጉሟል ይህም ውእቱ የአነን ማሠሪያ አንቀጽነት ተክቶ አገልግሏል ማለት ነው።

፪. አንትሙ ውእቱ ብርሃኑ ለዓለም (እናንተ የዓለም ብርሃን ናችሁ)

አንትሙ እናንተ ውእቱ ናችሁ ተብሎ ተተርጉሟል። ስለዚህ ውእቱ የአንትሙን የማሠሪያ አንቀጽነት ሙያ ተክቶ አገልግሏል ማለት ነው።

፫ አንተ ውእቱ ንጉሠ እስራኤል (አንተ የእስራኤል ንጉሥ ነህ)

አንተ አንተ ውእቱ ነህ ተብሎ ተተርጉሟል ስለሆነም ውእቱ የአንተን የማሠሪያ አንቀጽነት ሙያ ተክቶ አገልግሏል ማለት ነው።





ውእቱ በነባር ማሠሪያ አንቀጽነቱ በዐረፍተ ነገር ውስጥ ሳይጠራም ማሠሪያ አንቀጽ ይሆናል።

ምሳሌ ፩ ፡-መስቀል ኃይልነ። መስቀል ኃይላችን ነው።

፪. መንክር እግዝአብሔር። እግዝአብሔር ድንቅ ነው።

በእነዚህ ዐረፍተ ነገሮች ነው ተብሎ የተነገረው ውእቱ በነባር ማሠሪያ አንቀጽነቱ ነው። ምክንያቱም በነባር አንቀጽነት ነው ነበረ ተብሎ ሊፈታ የሚችለው ውእቱ ብቻ ስለሆነ።

## ፫.፫. አመልካች ቅጽል ይሆናሉ

ከስሙ እንደምንረዳው መራሕያን ባለቤትን ያመለክታሉ ወይም የባለቤት ቅጽል ይሆናሉ።

ውእቱ - አመልካች ቅጽል ሲሆን ትርጉሙ ያ ነው።

| | |
|---|---|
| | ውእቶሙ - እነዚያ |
| ይእቲ - ያች | ውእቶን - እነዚያ |
| አንተ - አንተ | አንትሙ - እናንተ |
| አንቲ - አንቺ | አንትን - እናንተ |
| አነ - እኔ | ንሕነ - እኛ |

**ተጨማሪ**

| | |
|---|---|
| ዝ ፣ዝንቱ - ይህ | እሉ፣ እሎንቱ - እኒህ |
| ዛ ፣ዛቲ - ያች | እላ ፣እላንቱ - እኒህ |

ውእቱ፣ዝኩ፣ዝስኩ፣ዝክቱ ትርጉሙ ያ

ይእቲ፣ እንታክቲ ፣እንትኩ ትርጉሙ ያች

ውእቶሙ፣ እልክቱ፣ እሙንቱ ትርጉሙ እኒያ

ውእቶን፣ እልኩ፣ እማንቱ ትርጉሙ እኒያ

☞ መራሕያን የባለቤት ቅጽል ሲሆኑ ከስም በፊት ይመጣሉ::

ምሳሌ:- *ንሕነ* ክርስቶሳውያን ::

*አንተ* ዳንኤል ዕጽዎ ለዝ ነገር::

*ይእቲ* መምህርት ረከበት ሞገሰ::

*ውእቱ* ብእሲ ሖረ::

*አንቲ* ማርታ ገበርኪ ሠናየ::

*አንትሙ* ሐዋርያት ሰበክሙ ወንጌለ::

*አንትን* ሰሎሜ ወዮሴፍ ፈለስክን ምስለ ማርያም::

*አነ* ጳውሎስ ፈፀምኩ ግብርየ::

*ውእቶሙ* ዕደው አብደሩ ሠናየ እምእኪት

*ውእቶን* አንስት ዐደዋ ባሕረ::

ወፈርሃት *ይእቲ* ብእሲት::

## ፫.፬. ተሳቢ ይሆናሉ

ተሳቢ ማለት የአድራጊ ድርጊት የጊኝ ሁኔታ የሚነገርበት ሰዋሰው ማለት ነው:: መራሕያንም አንድና ብዙ ሩቅና ቅርብ ወንድና ሴት ጾታቸውን ሳይለቁ በፊደል ቅርጻቸውን በመለወጥ የማሠሪያ አንቀጽ ተሳቢ ሆነው ይነገራሉ::

| | |
|---|---|
| አነ - ተሳቢ ሲሆን ኪያየ (እኔን) | ንሕነ - ኪያነ (እኛን) |
| አንተ - ኪያከ (አንተን) | አንትሙ - ኪያክሙ (እናንተን) |
| አንቲ - ኪያኪ (አንቺን) | አንትን - ኪያክን (እናንተን) |
| ውእቱ - ኪያሁ (እሱን) | ውእቶሙ - ኪያሆሙ (እነርሱን) |
| ይእቲ - ኪያሃ (እርሷን) | ውእቶን - ኪያሆን (እነርሱን) |





ምሳሌ ፩:- ኪያከ ተወከልኩ እግዚኦ (አቤቱ አንተን ታመንሁ)

አንተ → ኪያከ (አንተን)

ኪያከ የተባለው ቅርብ መደብ ባለቤት ሲሆን በስም ፋንታ ገብቶ እና ተሳቢ (ማሰሪያ ተቀባይ) ሆኖ ተነግሯል። ማሰሪያ ተቀባይ ማለታችን *ታመንሁ* ያለው አንተን በሚለው ተሳቢ ስለተገለጸ ነው።

ኪያክሙ ይሰድዱ። (እናንተን ያሳድዳሉ) ።

፪. ወሬዛ ኀደገ *ኪያሃ*::
፫. አብርሃም ሦዐ *ኪያሁ*::
፬. ሐዋርያት ሰበኩ *ኪያክሙ*::
፭. ዘተወክፈ *ኪያነ* ተወክፈ ኪያሆሙ::
፮. ኖላዊ ዐቀበ *ኪያሆን* ከመ ኢይማስና::
፯. ኦ አኃውየ *ኪያየ* ተመሰሉ::

## ፫.፭. የተሳቢ ቅጽል ይሆናሉ፡-

ከላይ የባለቤት ቅጽል ወይም ባለቤትን እንደሚያመለክቱ አይተናል አሁን ደግሞ መራሕያን የተሳቢ ቅጽል /ተሳቢን ሲያመለክቱ እናያለን።

ምሳሌ ፩:- ወረሰ አብርሃም ኪያሃ ሀገረ።

(አብርሃም ያችን ሀገር ወረሰ)

አብርሃም ሀገርን ወረሰ። ሀገሪቷ ደግሞ የተለየች (የታወቀች) መሆኗን ለመግለጽ ኪያሃ (ያችን) የሚለው ለሀገር ተቀጽላለች።

- ☞ ሐረየ ክርስቶስ *ኪያክሙ* ሐዋርያተ::
- ☞ እሬኢኑ እንጋ *ኪያሃ* ዕለተ::
- ☞ ነሥኡ ሐዋርያት *ኪያሁ* መንፈሰ::
- ☞ ቀተሉ አሕዛብ *ኪያሆሙ* ሰማዕተ::
- ☞ ኄራን ዐቀቡ *ኪያሆን* ሕግጋተ::
- ☞ ፈነወ አብ ወልዶ እስመ ረከበ *ኪያኪ* ንጽሕተ::
- ☞ ፈጠረ *ኪያነ* ሕዝበ::
- ☞ ሐጸነት እምየ *ኪያየ* ወለታ/ወልዳ::
- ☞ ሰበከ መልአክ *ኪያክን* አንስተ::

ሀ. **ወገን ቅጽል፡-** መድረሻቸውን ወደ ራብዕ በመቀየር ‹‹ው*ያ*›› ን አጋዥ በማድረግ ለ ተባዕታይ ‹‹ን›› ለአንስታይ ‹‹ት›› በመጨመር ይበዛሉ፡፡

| | |
|---|---|
| - ኢትዮጵያ | ኢትዮጵያውያን /ት/ |
| - እስራኤል | እስራኤላውያን /ት/ |
| - ሰማያዊ | ሰማያውያን /ት/ |

ለ. **ሣልስ ቅጽል** ‹‹ያ›› ን አጋዥ በማድረግ ለተባዕታይ ‹‹ን›› ን ለአንስታይ ‹‹ት›› ን በመጨመር ይበዛሉ

| | | | |
|---|---|---|---|
| ቀታሊ | ቀታልያን | መሃሪ | መሃርያን |
| ቀታሊት | ቀታልያት | መሃሪት | መሃርያት |
| ሰባኪ | ሰባክያን | | |
| ሰባኪት | ሰባክያት | | |

*‹‹አ›› ን መነሻ በማድረግ የሚበዙ ስሞች*

| | | | |
|---|---|---|---|
| - ደብር | አድባር | - ፈረስ | አፍራስ |
| - ወግር | አውግር | - ነገድ | አንጋድ |
| - ጠሊ | አጣሊ | - ዘመድ | አዝማድ |
| - በግዕ | አባግዕ | | |

*‹‹ሙ›› ን በመጨመር የሚበዙ*

| | | | |
|---|---|---|---|
| አንተ | አንትሙ | ኩሉ | ኩሎሙ |
| ውእቱ | ውእቶሙ | ለሊሁ | ለሊሆሙ |

*‹‹እ›› በመጨመር የሚበዙ*

| | |
|---|---|
| ኃጢአት | ኀጣውእ |
| መንጦላዕት | መንጠዋልዕ |

*‹‹ል›› በመጨመር የሚበዙ ስሞች*

| | |
|---|---|
| ኪሩብ | ኪሩቤል |
| ሱራፊ | ሱራፌል |





ሰ. ውሳጣዊ ውላጤን በማድረግ የሚበዙ ስሞች

እነዚህ ከውጭ ባዕድ ቀለም ሳይጨምሩ ከቃሉ ውስጥ ያሉትን ቀለማት በመለዋወጥ የሚበዙ ስሞች ሲሆኑ ተመሳሳይ የአበዛዝ ስልት የላቸውም፡፡ ብዙዎቹ ድኅረ መድረሻቸውን በመለወጥ ብቻ ሲበዙ የቀሩት ደግሞ ቀለማቱን በመለወጥ ‹‹ት›› ን በመጨመር ይበዛሉ፡፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| ድንግል | ደናግል | ደብተራ | ደባትር |
| ወልድ | ውሉድ | ሠርዌ | ሠራዊት |
| አንቀጽ | አናቅጽ | መንፈስ | መናፍስት |
| መቅደስ | መቃድስ | | |

ማስታወሻ ፩÷ የስሞች ፊደል ሣልስ ኃምስና ሳብዕ በመሆን ተኀርደው የነበሩት ‹‹ወ›› እና ‹‹የ›› ስሙ በሚበዛበት ጊዜ ይከሰታሉ፡፡

| | | | |
|---|---|---|---|
| ኀር | አግዋር | ሌሊት | ለያልይ |
| ፆም | አፅዋም | ቢጽ | አብያጽ |
| ኮከብ | ከዋክብት | ፆፍ | አዕዋፍ |

፪. የሚከተሉትን የመሠሉ ሁለት ፊደል ስሞች የሚበዙት መድረሻቸውን ግእዝ በማድረግና ‹‹ው››ን በመጨመር ነው

| | | | |
|---|---|---|---|
| ዕድ | ዕደው | ዕፅ | ዕፀው |
| አፍ | አፈው | አብ | አበው |

፫÷ በጥንታዊው ግእዝ ስሞች በተለየ የአበዛዝ ስልት ነጠላ ብዙ የብዙ ብዙ ተብለውም ይነገራሉ።

| <u>ነጠላ</u> | <u>ብዙ</u> | <u>የብዙ ብዙ</u> |
|---|---|---|
| ደብር | አድባር | አድባራት |
| ልብስ | አልባስ | አልባሳት |
| ጾም | አጽዋም | አጽዋማት |
| ግብ | ግበብ | ግበባት |
| ዕብን | ዕበን | አዕባን |
| ሊቅ | ሊቃን | ሊቃውንት |
| ከልብ | ከለባት | አክላብ |
| እግር | እገር | አእጋር |

## ፫.፮. ስሞች ተሳቢ ሲሆኑ / ተሳቢ /

ተሳቢ የአድራጊ ድርጊት የኂኝ ሁኔታ የሚነገርበት ወይም ድርጊት የሚፈጸምበት ወይም ድርጊት የተፈጸመበት የዐረፍተ ነገር ክፍል ነው::

☞ ተሳቢ በሁለት ይከፈላል

ሀ. ቀጥተኛ ተሳቢ ለ. ቀጥተኛ ያልሆነ ተሳቢ

ሀ. ቀጥተኛ ተሳቢ፡- በቀጥታ ገቢር ተናግሮ ለግሥ የሚሳብ ሲሆን ተሳቢ በሚሆንበት ጊዜ የስልተ ፊደል ለውጥ ሊኖር ይችላል::

**ምሳሌ ፡-** አምላክ ፈጠረ ዓለመ ። አምላክ ዓለምን ፈጠረ::

ዓለምን የሚለው ስም ፈጠረ ለሚለው ግስ በቀጥታ ተሳቢ ሆኗል:: ፈጠረ የሚለው ምንን ቢባል ዓለምን እንላለን ስለዚህ ግሱም ገቢር ወይም አድራጊ ግስ ነው::

☞ መድረሻቸው ሳድስ ቀለም የሆኑ ስሞች ወደ ግእዝ ይለወጣሉ::

***ምሳሌ፡-***

ዓለም → ዓለመ መነኑ ጻድቃን ዓለመ :: ጻድቃን ዓለምን ናቁ::

ብርሃን - ብርሃነ ርእዩ ብርሃነ :: ብርሃንን አዩ::

ሰብእ→ሰብአ ዐደሙ አግብርት ሰብአ:: አገልጋዮች ስዎችን ጠሩ::

ምክር →ምክረ ምክረ ይሰምዑ ለባውያን::አስተዋዮች ምክርን ይሰማሉ::

እግር→እግረ እግረ የሐጽቡ መነኮሳት:: መነኮሳት እግርን ያጥባሉ::

ቤት→ቤተ ቤተ ሐነፀ ሰሎሞን:: ስሎሞን ቤትን ሠራ::

ግብር→ግብረ ፈፀምኩ ግብረ ዘወሀብከኒ:: የሰጠኸኝ ሥራን ጨረስኩ::

ቃልከ→ ቃለከ ቃል → ቃለ ቃልክሙ → ቃለክሙ

☞ መድረሻቸው ካዕብ ቀለም ቀጥተኛ ተሳቢ ሲሆኑ ወደ ሳብዕ ይለወጣሉ:: ይህም የውእቱን የስም ዝርዝር ተሳቢ የሚያሳይ ነው::

ምሳሌ፡- ፀሩ → ፀሮ ቀተለ ፀሮ:: ጠላቱን ገደለ::

ወልድ→ወልዶ ፈነወ ወልዶ:: ልጁን ላከ::

ግብሩ→ግብሮ ገብረ ግብሮ:: ሥራውን ሠራ::

ቤቱ →ቤቶ ቤቶ ሐነጸ:: ቤቱን ሠራ::

ስሙ→ስሞ ልብሱ→ልብሶ መጽሐፉ→መጽሐፎ ብእሲቱ→በእሲቶ





☞ መድረሻቸው ሣልስ ቀለም ቀጥተኛ ተሳቢ ሲሆኑ ወደ ኃምስ ይለወጣሉ::

ምሳሌ፡- ብእሲ→ብእሴ አክበረ ብእሴ:: ሰውን አከበረ::

ነዓዊ→ነዓዌ አሠረ ነዓዌ:: አዳኝን አሠረ::

ከይሲ→ከይሴ ቀጥቀጠ ከይሴ:: እባብን ቀጠቀጠ::

ጸሐፊ→ፈሐፌ ጸሐፌ አክበረ:: ጸሐፊን አከበረ::

በላዒ→በላዔ ጸውአ በላዔ :: በላተኛን ጠራ::

☞ መድረሻው ራብዕ ኃምስ ሳብዕ ቀለም እና የአነና የውእቱ ዝርዝር መድረሻ ፊደሉን ሳይለውጥ ቀጥተኛ ተሳቢ ይሆናል::

ምሳሌ፡- እንዚራ→እንዚራ ዜና→ዜና ቃልየ→ቃልየ

ቅዳሴ →ቅዳሴ ቅኔ→ቅኔ እዴሁ→እዴሁ

ከበሮ→ከበሮ መርኆ→ መርኆ እግዚኡ→ እግዚኡ

በዐረፍተ ነገር ልዩነቱ ሲታይ

ተአንዘረ እንዚራ:: በገና ተመታ:: አንዘረ እንዚራ:: በገናን መታ::

ተስምዐ ቅዳሴ:: ቅዳሴ ተሰማ:: ሰምዐ ቅዳሴ:: ቅዳሴን ሰማ::

ተነግረ ቃልየ:: ቃሌ ተነገረ:: ነገረ ቃልየ:: ቃሌን ነገረ::

ተፈነወ እዴሁ:: እጁ ተላከ:: ፈነወ እዴሁ:: እጁን ላከ::

## ቅጽል ከስም ጋር አብሮ ይሳባል::

ቅጽል ማለት የባለቤት ጠባይ፣ ግብር፣ መልክ፣ ዓይነትንና መጠንን የሚገልጽ ማለት ሲሆን ከስም በፊትም በኋላም ሊገባ ይችላል::

ምሳሌ፡- ቀይሕ ብእሲ:: ብእሲ ቀይሕ::

የግእዝ ቅጽል በመልክ ባለቤቱን/ የሚገልጸውን ስም/ ይመስላል:: ባለቤቱ ተገብሮ ሲሆን ቅጽሉም ተገብሮ ይሆናል:: ባለቤቱ የገቢርን /የተሳቢን/ መልክ ሲይዝ ቅጽሉም ያንኑ ይመስላል::

ምሳሌ:-

| ባለቤት/ተገብሮ/ | ተሳቢ/ገቢር/ |
|---|---|
| መንፈስ ቅዱስ | መንፈሰ ቅዱሰ |
| ዝ ውእቱ ጥዑም ኅብስት | በልዐ ብእሲ ጥዑመ ኅብስተ |
| አሐዱ ሕፃን | አሐደ ሕፃነ |
| ስብሐት ሐዲስ | ስብሐተ ሐዲሰ |
| ከይሲ እኩይ | ከይሴ እኩየ |
| ጊዮርጊስ ሰማዕት | ጊዮርጊስሃ ሰማዕተ |

**የመራሕያን ተሳቢዎች:-**

ውእቱ→ ኪያሁ ውእቶሙ→ ኪያሆሙ
ይእቲ → ኪያሃ ውእቶን→ ኪያሆን
አነ → ኪያየ ንሕነ→ ኪያነ
አንተ→ኪያከ አንትሙ→ ኪያክሙ
አንቲ→ኪያኪ አንትን → ኪያክን
→ ኪያከ ንሴብሕ:: አንተን እናመሰግናለን::
→ ዘተወክፈ ኪያክሙ:: እናንተን የተቀበለ::
→ ኪያየ ተወክፈ:: እኔን ተቀበለ::

**የተጸውዖ ስም ተሳቢ** :-የተጸውዖ ስም ተሳቢ ሲሆን መድረሻው ላይ "ሀ" "ሃ"ይጨምራል::

ምሳሌ:- ሰሎሞን→ሰሎሞንሀ ዳዊት ወለደ ሰሎሞንሀ::
ማርያም→ማርያምሃ ኵሉ ስብእ አፍቀረ ማርያምሃ::
ጴጥሮስ→ጴጥሮስሀ ጴጥሮስሀ ሰቀሉ ቍልቍሊት::
ርብቃ→ርብቃሃ ያዕቆብ ሐረየ ርብቃሃ::





**አኃዝ ቀለማት ቀጥተኛ ተሳቢ** ሲሆኑ እንደቀደመው ካዕብ ቀለም ወደ ሳብዕ ሳይሆን ካዕብ ቀለም ወደ ግእዝ ቀለም ተለውጦ ነው አንዳንድ ቃላትም እንዲሁ ይለወጣሉ::

ምሳሌ:- አሐዱ→አሐደ አሐደ ወለደት::አንድ/ን ወለደች::
ክልዔቱ→ክልዔተ
ሠለስቱ→ሠለስተ

**ሌሎች:-** እስፍንቱ →እስፍንተ
ውእቱ→ውእተ ቀተለ ውእተ:: ያንን ገደለ::
ዝንቱ→ዘንተ ንሣእ ዘንተ:: ይህን ውሰድ::
ዛቲ→ዛተ
እሎንቱ →እሎንተ

**ተጠቃሽ ተሳቢ**:-ተጠቃሽ ተሳቢ "ለ" ን በመነሻ እየጨመረ ተሳቢ የሚያደርግ ሲሆን በትርጉም ጊዜ እንደቀጥተኛ ተሳቢ "ን" ን ያመጣል:: "ለ" ተጠቃሽ መባሉ በተጠቃሽ ስም ላይ ስለሚወድቅ ነው::

**ምሳሌ:-** ቀተሎ ለይስሐቅ :: ይስሐቅን ገደለው::
ርእዮ ለጴጥሮስ:: ጴጥሮስን አየችው ::
አምሐታ ለኤልሳቤጥ:: ኤልሳቤጥን ተሳለመቻት::
ፈጠሮ እግዚአብሔር ለአዳም::እግዚአብሔር አዳምን ፈጠረው::
ወይቤሎ እግዚአብሔር ለሙሴ:: እግዚአብሔር ሙሴን አለው::

## ለ. ቀጥተኛ ያልሆነ ተሳቢ

ቀጥተኛ ያልሆነ ተሳቢ በቀጥታ ለግስ የማይሳብ ሲሆን መስተዋድዳን ቃላት ቀጥተኛ ያልሆነ ተሳቢ ያደርጉታል፡፡ እንደቀጥተኛ ተሳቢ የመድረሻ ቀለም ለውጥ የለም፡፡

ምሳሌ፡- ተሐንፀ ቤት፡፡ ቤት ተሠራ

ቤት የሚለው ስም ተሠራ ለሚለው ግስ በቀጥታ አልተሳበም ግሱም ተገብሮ ነው ፡፡

ምሳሌ፡- መጽአ ውስተ ጉባዔ፡፡ ወደ ጉባዔ መጣ፡፡

ሖረ ምስለ እሙ፡፡ ከእናቱ ጋር ሄደ፡፡

ተሰቅለ ላዕለ መስቀል፡፡ በመስቀል ላይ ተሰቀለ፡፡

**ምልማድ ፫.፭.፡-**

**ሀ. የሚከተሉትን ተርጉሙ፡፡**

፩. ነገረ ወልድ ከመይመጽእ፡፡

፪.ገብሩ እስራኤል በከመ አዘዞሙ፡፡

፫.ቀባዕከኒ አንተ በዘይት ፡፡

፬. ረከብኩ ዘይሰምዐኒ፡፡

፭.ርእየት ዓይንየ በጸላዕትየ፡፡

**ለ. የሚከተሉትን ወደ ተሳቢ ለውጡ፡፡**

| | |
|---|---|
| ፩. ዜናዊ→ | ፪. ትካዜ→ |
| ፫. ሀገሩ→ | ፬. ማርቆስ ወንጌላዊ→ |
| ፭. ተዋሕዶ→ | ፮. ተሰዓቱ ቅዱሳን → |
| ፯. ናትናኤል→ | ፰. ዝማሬ ሐዲስ→ |
| ፱. ድንግልና→ | ፲. ቀይሕ ላሕም→ |





፲፩.በቀዳሚ ገብረ እግዚአብሔር............../ሰማይ/ወ............../ምድር/ ፡፡

፲፪.ንሣእ............../ሕፃን/ ወ ............./እሙ/ ወሑር ኀበ ብሔረ ግብፅ ፡፡

፲፫.ሕዝብ ዘይነብር ውስተ ጽልመት ርእየ..................../ዐብይ ብርሃን/፡፡

፲፬. ዐላውያን ቀተሉ_............................../ዮሐንስ መጥምቅ/፡፡

፲፭. ዕቀብ ................................./ዐሠርቱ ትዕዛዛት/፡፡

| | |
|---|---|
| ፲፮.ወልድ → | ፲፯.ሐና → |
| ፲፰.ሥላሴ → | ፲፱.አብ → |

**ሐ. የሚከተሉትን ዐረፍተ ነገሮች ተሳቢ በመለየት ተርጉሙ፡፡**

፩. ፈነወ ዳዊት እደው፡፡

፪. ውእቱ ነሥአ ደዌነ፡፡

፫.ምጽዋተ አበድር እምነመሥዋዕት፡፡

፬.ወሕዝብኒ ነበቡ ከንቶ ፡፡

፭.ይገብር እግዚአብሔር መድምመ፡፡

## ፫.፰.ነባራዊ እና የግስ ዝርዝር

ዝርዝር በስዋሰወ ግእዝ መድረሻ ላይ እየገባ አንድና ብዙ ቁጥርን ቅርብና ሩቅ መደብን ተባዕታይና አንስታይ ጾታን ለይቶ በማሳየት በፊደል በቅርጽ ተገልጾም በድምፅ ሳይገለጽም ባለቤትንና ተሳቢን የሚያመለክት ቅርጸ ግእዝ ድምፀ ግእዝ ሲሆን ዝርዝር ማለት አመልካች ጠቃሽ ፊደል ቅርጽና ድምፅ ማለት ነው፡፡

ነባራዊ ዝርዝር የሚባሉ በነባር አንቀጽና ስም በደቂቅና በንዑስ አገባብ ገብተው የሚነገሩ ድምፃተ ፊደል ሲሆኑ በነባር ሰዋሰው መድረሻ ላይ ገብተው የተሳቢና የባለገንዘብን አንድና ብዙ ቁጥር ቅርብና ሩቅነት ወንድና ሴት ጾታን የሚያስረዱ ናቸው፡፡

**ምልማድ**

የሚከተሉትን ዐ.ነገሮች በመተርጎም የመራሕያኑን ሙያ ለዩ::

፩. እስመ ኵልነ ውሉደ እግዚአብሔር ንሕነ::

፪. አንቲ ውእቱ ንጽሕት እምንጹሓን::

፫. ወዝውእቱ አስተማቲሆሙ ለ፲ወ፪ ሐዋርያት::

፬. አንተ ትሁብ ምሕረተ::

፭. አንትሙ ለምንት ቆምክሙ ዝየ::

፮. ንሕነ ተለውነ ፍኖተ ጽድቅ::

፯. ወወጺኦሙ እሙንቱ አጋንንት ቦኡ ላዕለ አኅርው::

፰. ተፈሥሐት ይእቲ ብእሲት እስመ ረከበት ሕይወተ::

፱. ወሀለው ኖሎት ውስተ ውእቱ ብሔር ደንገፁ::

፲. አንትሙ ቤተመቅደሱ ለእግዚአብሔር አንትሙ::

፲፩. ረሐቀት ይእቲ ብእሲት ኪያሃ ዘማ::

፲፪. አንተ ፈወስከ ኪያሆሙ ጽሙማነ::

፲፫. ኪያከ እግዚኦ ነአኵት ወንሴብሐከ::

፲፬. ዳዊት ዘነግሠ መልዕልተ እስራኤል ሐራ ኪያኪ ሰብሐ በአውታር ወበእንዚራ::

፲፭. ዘተወክፈ ኪያየ ተወክፎ ለአቡየ::

፲፮. ወውእቱሰ ኀለፈ እንተ ማዕከሎሙ ወሖረ::

፲፯. አልቦ ዘአሥገሩ በይእቲ ሌሊት::

፲፰. መኑ ውእቱ ስሙ ለአቡከ::

፲፱. ዮሐንስ ውእቱ ስሙ ለአቡየ::

፳.ዝንቱ ውእቱ ስምዑ ለዮሐንስ::

፳፩. ወበይእቲ ዕለት ሶበ መስየ መጽአ::





## ፫.፯.የስም አበዛዝ ስልት

ስም ማንኛውም ህላዌ ሰውም ሆነ አምላክ አካል ያለውም የሌለውም የሚጠራበት ቃል ነው። የስም አበዛዝ ስልት ማለት ደግሞ ነጠላ ቁጥሩን ስም ወደ ብዙ ቁጥር ስም የምንለውጥበት የሰዋሰው ክፍል ነው።

የስም አበዛዝ ስልት የሚመሰረተው በሁለት ዓይነት መንገድ ነው።

ሀ. አፍአዊ ውሳጤን በማድረግና

ለ. ውስጣዊ ውሳጤን በማድረግ

ሀ. <u>አፍአዊ ውሳጤን በማድረግ፦</u>የሚበዙ ስሞች ከቃሉ ሌላ ባዕድ ቀለም በመጨመር ስሞች የሚበዙበት ስልት ነው። ስለዚህ አብዛኛው የሚዘወተሩት ‹‹ት,ን,አ,ያት,ዋት›› ናቸው።

በራብዕ የሚደርስ ስም ያለ አንዳች ለውጥ ‹‹ት›› ን ይጨምራል።

በኃምስ የሚደርስ ስም ‹‹ያት›› ን ይጨምራል። በሳብዕ የሚደርስ ስም ‹‹ዋት›› ን በመጨመር ይበዛል።

| <u>ነጠላ</u> | <u>ብዙ</u> | <u>ነጠላ</u> | <u>ብዙ</u> |
|---|---|---|---|
| ሐዋርያ | ሐዋርያት | ደዌ | ደዌያት |
| ህቦ | ህቦዋት | ኖትያ | ኖትያት |
| ፀልቦ | ፀልቦዋት | ዝማሬ | ዝማሬያት |
| ቅዳሴ | ቅዳሴያት | | |

በሳድስ የሚደርሱ ስሞች መድረሻቸውን ራብዕ በማድረግ

***‹‹ት›› ን በመጨመር ይበዛሉ።***

| | | | |
|---|---|---|---|
| ልሳን | ልሳናት | ሰማዕት | ሰማዕታት |
| ነፍስ | ነፍሳት | ማይ | ማያት |
| ቀላይ | ቀላያት | ኈር | ኈራት |
| ዝናም | ዝናማት | | |

- ☞ በነባራዊ ዝርዝር ጊዜ አገናዛቢ ቅጽል የምንጠቀመው :-
- ☞ ለአነ «የ» ለ ንሕነ «ነ » ለውእቱ - ካዕብ ለውእቶሙ - (ሳብዕ+ሙ) ለይእቲ - ራብዕ ለውእቶን - (ሳብዕ+ን)
- ☞ ለሁለተኛ መደቦች እንደ ባለቤት ዝርዝር ለአንተ ‹‹ከ›› ለአንትሙ ‹‹ክሙ›› ለአንቲ ‹‹ኪ›› ለአንትን ‹‹ክን›› ነው::

ሎ፣ ቦ የነባር አንቀጽ አዎንታዎች ሲሆኑ አልቦ የ «ቦ» አሉታ ነው፡፡

፩. ” ለ” ደቂቅ አገባብ ሲሆን በነባር አንቀጽነቱ በመኖር ግሥ ይፈታል::

ውእቱ - ሎ/ሎቱ ትርጉሙ አለው፣ አለለት፣ ኖረለት፣ ኖረው፣ ነበረው

ውእቶሙ - ሎሙ/ሎቶሙ ውእቶን - ሎን/ሎቶን ይእቲ- ላቲ

አንቲ- ለኪ አንትን - ለክን አንተ- ለከ

አንትሙ - ለክሙ አነ - ልየ/ሊተ ንሕነ - ለነ

፪. «ብ» ደቂቅ አገባብ ሲሆን በነባር አንቀጽነቱ በመኖር ግሥ ይፈታል::

ቦ - አለ፣ ኖረ፣ ኖሯል፣ ነበረ ቦ - አሉ፣ ኖሩ፣ ኖረዋል፣ ነበሩ

ቦ - አለች፣ ኖረች፣ ኖራለች፣ነበረች ቦ - አሉ፣ ኖሩ፣ ኖረዋል፣ ነበሩ

ቦ -አለህ፣ ኖርህ፣ ኖረሃል፣ ነበርህ ቦ-አላችሁ፣ ኖራችሁ፣ ኖራችኋል፣ ነበራችሁ ቦ-አለሽ፣ ኖርሽ፣ ኖረሻል፣ ነበርሽ ቦ-አላችሁ፣ ኖራችሁ፣ ኖራችኋል፣ ነበራችሁ

ቦ -አለሁ፣ኖርሁ፣እኖራለሁ፣ነበርሁ ቦ - አለን፣ኖርን፣እንኖራለን፣ነበርን

**3. «ብ» በዝርዝር አፈታት ሲፈታ**

ውእቱ- ቦ/ቦቱ - ኖረው፣ ነበረው፣ ይኖረዋል፣አለ፣ በርሱ አለበት፣ አለለት፣ ነበረለት

ውእቶሙ- ቦሙ/ቦቶሙ ውእቶን - ቦን/ቦቶን ይእቲ - ባ/ባቲ

አንተ - ብከ አንትሙ - ብክሙ አንቲ - ብኪ አንትን - ብክን

አነ- ብየ ንሕነ - ብነ





| | | |
|---|---|---|
| ፬. አልቦ የ«ቦ» አሉታ ነው:: | አልብየ | አልብነ |
| | አልብከ | አልብክሙ |
| | አልብኪ | አልብክን |
| | አልቦ/አልቦቱ | አልቦሙ |
| | አልባቲ | አልቦን |

ምሳሌዎች :- ሎሙ ሕግወሎሙ ሥርዓት::

ሰላም ለኪ ማርያም ወላዲተ እግዚአብሔር::

ሰአሊ ለነ ቅድስት ::

ፍታሕ ሊተ እግዚኦ ::

ቦ አበበ ውስተ ጉባዔ ::

ዘቦ እዝነ ሰሚዐ ለይስማዕ::

ቦ ውእቶን አንስት ውስተ ምስያጥ::

ቦ አዳምውስተ ገነት::

እመኑ ብየ ወእመኑ በአቡየ::

በጽሐ ቦቱ መከራ::

አልብየ ዘመድ በዝንቱ ሀገር::

ወአምኑ ቦቱ አርዳኢሁ::

ዕዳ ቦሙ::

፭. «ነ» መስተአምራዊ አንቀጽ አጎላማሽ ሲሆን አገናዛቢ ቅጽል ሆኖ በ፲ሩ መራሕያን ይዘረዘራል፡፡

አነ - ነየ - ትርጉሙ አነሆኝ ነየነ - እነሆን

ነየከ - እነሆህ ነየክሙ - እነኋችሁ

ነየኪ - እነሆሽ ነየክን - እነኋችሁ

ነዋ - እነሆ ነዮ/ነየሙ - እነኋቸው

ነያ - እነኋት ነዮን - እነኋቸው

☞ ነዋ - ግኡዝ ነው ፆታ አይለይም

<u>ምሳሌ -</u> ነያ አምከ -እነኋት እናትህ::

ነዋ ወልድኪ - አነኋት ልጅሽ::

ነዋ በግዑ ለእግዚአብሔር ዘየአትት ኃጢአተ ዓለም::

ነዮሙ ዕደው እለ መጽኡ ትማልም::

ነየ መጻእኩ ምንተ ተኃሥሡ እምኔየ::

<u>የሎ አጸፋ ዝርዝር</u>

| | | |
|---|---|---|
| ልየ - እኔ - | ለልየ - እኔ ራሴ | ለነ - ለሊነ |
| ለከ - ለሊከ | ለክሙ - ለሊክሙ | |
| ለኪ - ለሊኪ | ለክን - ለሊክን | |
| ሎቱ -ለሊሁ | ሎቶሙ -ለሊሆሙ | |
| ላቲ - ለሊሃ | ሎቶን- ለሊሆን | |

<u>ምሳሌ:-</u> አንሰ ለልየ ርኢኩከ::

## <u>*የስም ዝርዝር*</u>

አገናዛቢ ቅጽሎች ከተጸውዖ ስም በቀር በሌሎቹ ስሞች መድረሻ ገብተው ባለገንዘብነትን በማመልከት ይዘረዝራሉ፡፡

### <u>፩.በሳድስ የሚደርሱ ስሞች ዝርዝር</u>

<u>ምሳሌ</u>፡- ጸሎት

| | |
|---|---|
| አነ - ጸሎትየ | ንሕነ - ጸሎትነ |
| አንተ - ጸሎትከ | አንትሙ— ጸሎትክሙ |
| አንቲ - ጸሎትኪ | አንትን - ጸሎትክን |
| ውእቱ- ጸሎቱ | ውእቶሙ- ጸሎቶሙ |
| ይእቲ - ጸሎታ | ውእቶን - ጸሎቶን |





| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| *<u>ስም</u>* | ስምየ | ስምነ | *<u>ቤት</u>* | ቤትየ | ቤትነ |
| | ስምከ | ስምክሙ | | ቤትከ | ቤትክሙ |
| | ስምኪ | ስምክን | | ቤትኪ | ቤትክን |
| | ስሙ | ስሞሙ | | ቤቱ | ቤቶሙ |
| | ስማ | ስሞን | | ቤታ | ቤቶን |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| *<u>ፍኖት:</u>* | ፍኖትየ | ፍኖትነ | *<u>ምስካይ</u>*: | ምስካይየ | ምስካይነ |
| | ፍኖትከ | ፍኖትክሙ | | ምስካይከ | ምስካይክሙ |
| | ፍኖትኪ | ፍኖትክን | | ምስካይኪ | ምስካይክን |
| | ፍኖቱ | ፍኖቶሙ | | ምስካዩ | ምስካዮሙ |
| | ፍኖታ | ፍኖቶን | | ምስካያ | ምስካዮን |

<u>ምልማድ ፫.፪</u> - ሀ. ርስት ለ. ብሔር ሐ.ግብር

### ፪. <u>ከሳድስ ውጭ ያሉ ስሞች ዝርዝር</u>

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| *<u>ዜና</u>* | ዜናየ | ዜናነ | *<u>ዝማሬ</u>* | ዝማሬየ | ዝማሬነ |
| | ዜናከ | ዜናክሙ | | ዝማሬከ | ዝማሬክሙ |
| | ዜናኪ | ዜናክን | | ዝማሬኪ | ዝማሬክን |
| | ዜናሁ | ዜናሆሙ | | ዝማሬሁ | ዝማሬሆሙ |
| | ዜናሃ | ዜናሆን | | ዝማሬሃ | ዝማሬሆን |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| *<u>መሰንቆ</u>* | መሰንቆየ | መሰንቆነ | *<u>ገብላ</u>* | ገብላየ | ገብላነ |
| | መሰንቆከ | መሰንቆክሙ | | ገብላከ | ገብላክሙ |
| | መሰንቆኪ | መሰንቆክን | | ገብላኪ | ገብላክን |
| | መሰንቆሁ | መሰንቆሆሙ | | ገብላሁ | ገብላሆሙ |
| | መሰንቆሃ | መሰንቆሆን | | ገብላሃ | ገብላሆን |

*ከሳድስ ውጭ የሚደርሱ ስሞች ልዩነታቸው ሣስተኛ መደብ ላይ ብቻ ነው።

**<u>ምልማድ ፫.፫.</u>**:-ሀ.ቅዳሴ፣ ለ.ጌራ፣ ሐ.ኅሊና፣ መ.ውቅሮ፣ ሠ.ፀልቦ ፣ ረ.ፍካሬ፣ ሰ.ጽጌ፣ ቀ.ሥጋ፣ በ.ቤዛ ፣ ተ.ኵለንታ፣ ነ.ጊዜ

፫.በሳድስ የሚደርሱ ብዙ ቁጥር ስሞች ከሳድስ ውጪ እንደሚደርሱ ስሞች ይዘረዘራሉ።

| | | |
|---|---|---|
| ምሳሌ:-***<u>ሐዋርያት</u>*** | ሐዋርያትየ | ሐዋርያቲነ |
| | ሐዋርያቲከ | ሐዋርያቲክሙ |
| | ሐዋርያትኪ | ሐዋርያቲክን |
| | ሐዋርያቲሁ | ሐዋርያቲሆሙ |
| | ሐዋርያቲሃ | ሐዋርያቲሆን |

| ***<u>አብያት</u>*** | | ***<u>አዕይንት</u>*** | |
|---|---|---|---|
| አብያትየ | አብያቲነ | አዕይንትየ | አዕይንቲነ |
| አብያቲከ | አብያቲክሙ | አዕይንቲከ | አዕይንቲክሙ |
| አብያትኪ | አብያቲክን | አዕይንትኪ | አዕይንቲክን |
| አብያቲሁ | አብያቲሆሙ | አዕይንቲሁ | አዕይንቲሆሙ |
| አብያቲሃ | አብያቲሆን | አዕይንቲሃ | አዕይንቲሆን |

ዝርዝር በዘመድ እና በባዕድ ተብሎ በሁለት ይከፈላል። በሣልስ በራብዕ በኃምስ በሳብዕ የሚደርሱ በባዕድ ይዘረዝራል።

ምሳሌ ብእሲ

| | |
|---|---|
| ብእሲሁ | ብእሲሆሙ |
| ብእሲሃ | ብእሲሆን |
| ብእሲከ | ብእሲክሙ |
| ብእሲኪ | ብእሲክን |
| ብእሲየ | ብእሲነ |





በሳድስ የሚደርሱ ስሞች በዘመድ እና በባዕድ ይዘረዝራሉ ።

| | | | |
|---|---|---|---|
| ምሳሌዎች :- | ፩. አብ | አቡ/አቡሁ | አቡሆሙ |
| | ፪. አዕይንት | አዕይንቱ/አዕይንቲሁ | አዕይንቲሆሙ |
| | ፫. እድ | እዱ/እዴሁ | እዴሆሙ |
| | ፬. ምግባር | ምግባሩ/ምግባሪሁ | ምግባሪሆሙ |

## <u>የደቂቅ አገባብ ዝርዝር</u>

ደቂቅ አገባብ ቃልን ከቃል የሚያያይዙ ሲሆኑ እነዚህም:- ዲበ፣ ላዕለ፣ መልዕልተ፣ ታሕተ፣ መትሕተ፣ ውስተ፣ ውሳጤ ፣ ቅድመ፣ ድኅረ፣ ማዕከለ፣ ኀበ ፣መንገለ እኒህንም የመሰሉ ናቸው።

| | | |
|---|---|---|
| ***<u>ዲበ</u>*** | አነ - ዲቤየ | ንሕነ - ዲቤነ |
| | አንተ - ዲቤከ | አንትሙ - ዲቤክሙ |
| | አንቲ - ዲቤኪ | አንትን - ዲቤክን |
| | ውእቱ - ዲቤሁ | ውእቶሙ - ዲቤሆሙ |
| | ይእቲ - ዲቤሃ | ውእቶን - ዲቤሆን |

| ***<u>ላዕለ</u>*** | | ***<u>መልዕልተ</u>*** | |
|---|---|---|---|
| ላዕሌየ | ላዕሌነ | መልዕልቴየ | መልዕልቴነ |
| ላዕሌከ | ላዕሌክሙ | መልዕልቴከ | መልዕልቴክሙ |
| ላዕሌኪ | ላዕሌክን | መልዕልቴኪ | መልዕልቴክን |
| ላዕሌሁ | ላዕሌሆሙ | መልዕልቴሁ | መልልቴሆሙ |
| ላዕሌሃ | ላዕሌሆን | መልዕልቴሃ | መልዕልቴሆን |

| *ታሕተ* | | *መትሕተ* | |
|---|---|---|---|
| ታሕቴየ | ታሕቴነ | መትሕቴየ | መትሕቴነ |
| ታሕቴከ | ታሕቴክሙ | መትሕቴከ | መትሕቴክሙ |
| ታሕቴኪ | ታሕቴክን | መትሕቴኪ | መትሕቴክን |
| ታሕቴሁ | ታሕቴሆሙ | መትሕቴሁ | መትሕቴሆሙ |
| ታሕቴሃ | ታሕቴሆን | መትሕቴሃ | መትሕቴሆን |

| *ውስተ* | | *ውሳጤ* | |
|---|---|---|---|
| ውስቴየ | ውስቴነ | ውሳጤየ | ውሳጤነ |
| ውስቴከ | ውስቴክሙ | ውሳጤከ | ውሳጤክሙ |
| ውስቴኪ | ውስቴክን | ውሳጤኪ | ውሳጤክን |
| ውስቴቱ | ውስቴቶሙ | ውሳጤሁ | ውሳጤሆሙ |
| ውስቴታ | ውስቴቶን | ውሳጤሃ | ውሳጤሆን |

| *ቅድመ* | | *ድኅረ* | |
|---|---|---|---|
| ቅድሜየ | ቅድሜነ | ድኅሬየ | ድኅሬነ |
| ቅድሜከ | ቅድሜክሙ | ድኅሬከ | ድኅሬክሙ |
| ቅድሜኪ | ቅድሜክን | ድኅሬኪ | ድኅሬክን |
| ቅድሜሁ | ቅድሜሆሙ | ድኅሬሁ | ድኅሬሆሙ |
| ቅድሜሃ | ቅድሜሆን | ድኅሬሃ | ድኅሬሆን |

| *ማዕከለ* | | *ኀበ* | |
|---|---|---|---|
| ማዕከሌየ | ማዕከሌነ | ኀቤየ | ኀቤነ |
| ማዕከሌከ | ማዕከሌክሙ | ኀቤከ | ኀቤክሙ |
| ማዕከሌኪ | ማዕከሌክን | ኀቤኪ | ኀቤክን |
| ማዕከሌሁ | ማዕከሌሆሙ | ኀቤሁ | ኀቤሆሙ |
| ማዕከሌሃ | ማዕከሌሆን | ኀቤሃ | ኀቤሆን |





| *መንገለ* | | *ምስለ* | |
|---|---|---|---|
| መንገሌየ | መንገሌነ | ምስሌየ | ምስሌነ |
| መንገሌከ | መንገሌክሙ | ምስሌከ | ምስሌክሙ |
| መንገሌኪ | መንገሌክን | ምስሌኪ | ምስሌክን |
| መንገሌሁ | መንገሌሆሙ | ምስሌሁ | ምስሌሆሙ |
| መንገሌሃ | መንገሌሆን | ምስሌሃ | ምስሌሆን |

**ምልማድ ፫.፬፡- ሀ.**እምነ ፣ ለ.እስከ

## የንዑስ አገባብ ዝርዝር

| *ምንት* | | *ዓዲ* | |
|---|---|---|---|
| ምንትየ | ምንትነ | ዓዲየ | ዓዲነ |
| ምንትከ | ምንትክሙ | ዓዲከ | ዓዲክሙ |
| ምንትኪ | ምንትክን | ዓዲኪ | ዓዲክን |
| ምንቱ | ምንቶሙ | ዓዲሁ | ዓዲሆሙ |
| ምንታ | ምንቶን | ዓዲሃ | ዓዲሆን |

ኵሉ ትርጉሙ ሁሉ ሲሆን በሰባት መራሕያን ይዘረዘራል እነሱም፡-

| | | | |
|---|---|---|---|
| ንሕነ | ኵልነ | | |
| ውእቱ | ኵሉ | ውእቶሙ | ኵሎሙ |
| ይእቲ | ኵላ | ውእቶን | ኵሎን |
| አንትሙ | ኵልክሙ | አንትን | ኵልክን |

*ባሕቲቱ፡-* ትርጉሙ ብቻው

| | |
|---|---|
| ባሕቲትየ | ባሕቲትነ |
| ባሕቲትከ | ባሕቲትክሙ |
| ባሕቲትኪ | ባሕቲትክን |
| ባሕቲቱ | ባሕቲቶሙ |
| ባሕቲታ | ባሕቲቶን |

*__በበይናቲሁ__* ትርጉም እርስ በርሱ ሲሆን በሰባት መራሕያን ይዘረዘራል እነሱም:-

| | | | |
|---|---|---|---|
| በበይናቲሁ | በበይናቲሆሙ | በበይናቲነ | |
| በበይናቲሃ | በበይናቲሆን | በበይናቲክሙ | በበይናቲክን |

## የዐቢይ አገባብ ዝርዝር

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| *__በእንተ__* | በእንቲአየ | በእንቲአነ | *__ህየንተ__* | ህየንቴየ | ህየንቴነ |
| | በእንቲአከ | በእንቲአክሙ | | ህየንቴከ | ህየንቴክሙ |
| | በእንቲአኪ | በእንቲአክን | | ህየንቴኪ | ህየንቴክን |
| | በእንቲአሁ | በእንቲአሆሙ | | ህየንቴሁ | ህየንቴሆሙ |
| | በእንቲአሃ | በእንቲአሆን | | ህየንቴሃ | ህየንቴሆን |
| *__ከመ__* | ከማየ | ከማነ | *__ዘ__* | ዚአየ | ዚአነ |
| | ከማከ | ከማክሙ | | ዚአከ | ዚአክሙ |
| | ከማኪ | ከማክን | | ዚአኪ | ዚአክን |
| | ከማሁ | ከማሆሙ | | ዚአሁ | ዚአሆሙ |
| | ከማሃ | ከማሆን | | ዚአሃ | ዚአሆን |

| | | | |
|---|---|---|---|
| *__እንበለ__* እንበሌየ | እንበሌነ | *__ብሂል፣ባህል፣ብሂሎት__* | |
| እንበሌከ | እንበሌክሙ | ብሂልየ ፣ባህልየ፣ብሂሎትየ | ብሂልነ፣ ባሕልነ፣ብሂሎትነ |
| እንበሌኪ | እንበሌክን | ብሂልከ፣ባህልከ፣ብሂሎትከ | ብሂልክሙ፣ባሕልክሙ፣ብሂሎትክሙ |
| እንበሌሁ | እንበሌሆሙ | ብሂልኪ፣ባህልኪ፣ብሂሎትኪ | ብሂልክን፣ባሕልክን፣ብሂሎትክን |
| እንበሌሃ | እንበሌሆን | ብሂሉ፣ባህሉ፣ብሂሎቱ | ብሂሎሙ፣ባህሎሙ፣ብሂሎቶሙ |
| | | ብሂላ፣ባህላ፣ብሂሎታ | ብሂሎን፣ባህሎን፣ብሂሎቶን |

☞ አገባቦች ዐብይም ንዑስም ዐብይም ደቂቅም ሊሆኑ ይችላሉ ክፍላተ ንግግርን ተመልከት::

በአሥሩ መራሕያን በዘመድ በባዕድ የሚዘረዘር ቃል ሁሉ ደቂቅ እርባታ ይባላል::





## የግስ ዝርዝር /የባለቤት ዝርዝር/

ግስ ድርጊት መደረጉን ሁኔታ መሆኑን የሚገልጽ የግእዝ ቃል ሲሆን ግስ ማለት የቋንቋ ኀዝ የዘርና የነባር እክት የቃላት መራቢያ ተመላላሽና ተወራራሽ ቃል ማለት ነው::

መራሕያን ግሥን በሁለት መንገድ ይዘረዝራሉ እነሱም

፩. የባለቤት ዝርዝር በዘመድ ዝርዝር

በፊደል ሳይገለጽ ወይም ምዕላድ ፊደልን ሳይጨምር በድምፅ ብቻ/ የግሡን መድረሻ ቀለም በመለወጥ / የግሥ ባለቤትን የሚያመለክት ነው:: ይህም **ለውእቱ እራሱ ግሡ ለውእቶሙ ካዕብ ቀለም ለውእቶን ራብዕ ቀለም** ማድረግ ነው::

ምሳሌ :- **ቀደሰ** ውእቱ→**ቀደሰ** ውእቶሙ→**ቀደሱ** ውእቶን →**ቀደሳ**

__፪. የባለቤት ዝርዝር በባዕድ ዝርዝር :-__ በግሡ ሥርወ ቃል ያልነበረ ምዕላድ ፊደልን በመጨመር ባለቤትን የሚያመላክት ነው::

ይህም ለአነ→ ኩ ለንሕነ→ነ ለአንተ→ ከ ለአንትሙ→ ክሙ ለአንቲ→ ኪ ለአንትን→ ክን ለይእቲ→ ት በመጨመር ነው::

ምሳሌ:- **ቀደሰ** አነ→ቀደስኩ ንሕነ→ቀደስነ አንተ→ቀደስከ

አንትሙ→ ቀደስክሙ አንቲ→ቀደስኪ

አንትን → ቀደስክን ይእቲ→ቀደሰት

__መደበኛ አካሄድ ያላቸው ግሦች የባለቤት ዝርዝር__

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| __ቀተለ__ | ውእቱ | ቀተለ | ውእቶሙ | ቀተሉ |
| | ይእቲ | ቀተለት | ውእቶን | ቀተላ |
| | አንተ | ቀተልከ | አንትሙ | ቀተልክሙ |
| | አንቲ | ቀተልኪ | አንትን | ቀተልክን |
| | አነ | ቀተልኩ | ንሕነ | ቀተልነ |

| ፈነወ | | አቤተ | |
|---|---|---|---|
| ፈነወ | ፈነው | አቤተ | አቤቱ |
| ፈነወት | ፈነዋ | አቤተት | አቤታ |
| ፈነውከ | ፈነውክሙ | አቤትከ | አቤትክሙ |
| ፈነውኪ | ፈነውክን | አቤትኪ | አቤትክን |
| ፈነውኩ | ፈነውነ | አቤትኩ | አቤትነ |

| ሀለወ | | አእመረ | |
|---|---|---|---|
| ሀለወ | ሀለዉ | አእመረ | አእመሩ |
| ሀለወት | ሀለዋ | አእመረት | አእመራ |
| ሀለውከ | ሀለውክሙ | አእመርከ | አእመርክሙ |
| ሀለውኪ | ሀለውክን | አእመርኪ | አእመርክን |
| ሀለውኩ | ሀለውነ | አእመርኩ | አእመርነ |

**ምልማድ ፫.፮**:-፩ሖረ ፣ ፪ሐለመ ፣፫ኀሠሠ ፣ ፬ሐወጸ ፣ ፭ነበረ፣፮ቆመ ፣ ፯በከየ ፣ ፰ርኅበ ፣፱ጸለየ ፣ ፲ተለወ ፣ ፲፩አኀዘ ፣፲፪ ተሣየጠ

**መሀላቸው ሳድስ ቀለም የሆኑ ግሦች የባለቤት ዝርዝር**

| በልዐ | | | ሰትየ | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | በልዐ | በልዑ | | ሰትየ | ሰትዩ |
| | በልዐት | በልዓ | | ሰትየት | ሰትያ |
| | በላዕከ | በላዕክሙ | | ሰተይከ | ሰተይክሙ |
| | በላዕኪ | በላዕክን | | ሰተይኪ | ሰተይክን |
| | በላዕኩ | በላዕነ | | ሰተይኩ | ሰተይነ |

| መጽአ | | | ሠምረ | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | መጽአ | መጽኡ | | ሠምረ | ሠምሩ |
| | መጽአት | መጽኣ | | ሠምረት | ሠምራ |
| | መጻእከ | መጻእክሙ | | ሠመርከ | ሠመርክሙ |
| | መጻእኪ | መጻእክን | | ሠመርኪ | ሠመርክን |
| | መጻእኩ | መጻእነ | | ሠመርኩ | ሠመርነ |





**ምልማድ ፫.፯**:- ፩ወጽአ ፣፪በጽሐ፣ ፫መርሐ ፣፬ተፈሥሐ፣ ፭ገብረ፣ ፮ነሥአ ፣ ፯ጸውዐ ፣ ፰ሰብሐ፣ ፱ርእየ ፣ ፲ብህለ

**የገዳፍያነ ዘመድ ወወኃጢ ግሶች የባለቤት ዝርዝር**

**ገዳፍያነ ዘመድ** :- የሚባሉ ቀ፣ከ፣ገ ሲሆኑ እነዚህ ቀለማት የግሥ መድረሻ ሲሆኑ በሁለተኛ መደብና በአነ ባለቤት አመልካቹን "ከ" አስወጥተው ስልተ ፊደሉን በመውረስ እራሳቸው ጠብቀው ይነበባሉ ::

| ምሳሌ:- ወድቀ | | | | |
|---|---|---|---|---|
| | ውእቱ | ወድቀ | ውእቶሙ | ወድቁ |
| | ይእቲ | ወድቀት | ውእቶን | ወድቃ |
| | አንተ | ወደቀ | አንትሙ | ወደቅሙ |
| | አንቲ | ወደቂ | አንትን | ወደቅን |
| | አነ | ወደቁ | ንሕነ | ወደቅነ |

| ለአከ | | | ደግደገ | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ለአከ | ለአኩ | | ደግደገ | ደግደጉ |
| | ለአከት | ለአካ | | ደግደገት | ደግደጋ |
| | ለአከ | ለአክሙ | | ደግደገ | ደግደግሙ |
| | ለአኪ | ለአክን | | ደግደጊ | ደግደግን |
| | ለአኩ | ለአክነ | | ደግደጉ | ደግደግነ |

**ምልማድ ፫.፰** :- ፩. ኀደገ ፪. አጥመቀ ፫. ባረከ ፬. ልህቀ ፭. ሠሐቀ ፮. መለከ

**ወኃጢ የሚባል "ነ"ሲሆን** መድረሻ የሆነው ግሥ በንሕነ ባለቤት አመልካቹን አስወጥቶ እራሱ ጠብቆ ይነበባል።

ምሳሌ:- ኮነ

| | | | |
|---|---|---|---|
| ውእቱ | ኮነ | ውእቶሙ | ኮኑ |
| ይእቲ | ኮነት | ውእቶን | ኮና |
| አንተ | ኮንከ | አንትሙ | ኮንክሙ |
| አንቲ | ኮንኪ | አንትን | ኮንክን |
| አነ | ኮንኩ | ንሕነ | ኮነ |

አምነ

| | |
|---|---|
| አምነ | አምኑ |
| አምነት | አምና |
| አመንከ | አመንክሙ |
| አመንኪ | አመንክን |
| አመንኩ | አመነ |

**ምልማድ ፫.፱** :-ሀ. የሚከተሉትን ግሶች በ አሥሩ መራሕያን ዘርዝር።

፩. ማሰነ፣ ፪. ኰነነ፣ ፫. አጽነነ፣ ፬. ከፈነ ፣ ፭. አፍጠነ ፣፮. ከደነ

ለ. በምሳሌው መሠረት የሚከተለውን ክፍት ቦታ ሙላ።

ምሳሌ:- ውእቱ ------------- /መጽአ/ ውስተ ጉባዔ።

→ ውእቱ መጽአ ውስተ ጉባዔ።

፩. አንትሙ ለምንት ...................../መጽአ/ ዝየ።

፪. ለምንት ...................../ሖረ/ ባሕቲትኪ።

፫. ይእቲ ................./በልዐ/ ኅብስተ።

፬. ንግርኒ ለምንት_................../ሰሐቀ / አነ።

፭. ንሕነሰ ................../ኮነ/ ከመ አባግዕ ዘይጠብሑ።

፮. ................../ረፈቀ/ እስመ ደከምኩ ።

፯. ሙሴ ወአሮን ................../ዐርገ/ ውስተ ደብር።

፰. ኦ እጐየ ማእዜ ................../በጽሐ/ ዝየ።

፱. ..................../ ባልሐ/ እምኵሉ እኩይ።

፲. ................../ደንገፀ/አመ ................../ርእየ/አንበሳ።





## የቦዝ አንቀጽ የባለቤት ዝርዝር

ቀተለ → ቀቲሎ

| | | | |
|---|---|---|---|
| ውእቱ | ቀቲሎ | ውእቶሙ | ቀቲሎሙ |
| ይእቲ | ቀቲላ | ውእቶን | ቀቲሎን |
| አንተ | ቀቲለከ | አንትሙ | ቀቲለክሙ |
| አንቲ | ቀቲለኪ | አንትን | ቀቲለክን |
| አነ | ቀቲልየ | ንሕነ | ቀቲለነ |

## የአርዕስት የባለቤት ዝርዝር

ቀተለ → ቀቲሎት

| | | | |
|---|---|---|---|
| ውእቱ | ቀቲሎቱ | ውእቶሙ | ቀቲሎቶሙ |
| ይእቲ | ቀቲሎታ | ውእቶን | ቀቲሎቶን |
| አንተ | ቀቲሎትከ | አንትሙ | ቀቲሎትክሙ |
| አንቲ | ቀቲሎትኪ | አንትን | ቀቲሎትክን |
| አነ | ቀቲሎትየ | ንሕነ | ቀቲሎትነ |

ቀተለ → ቀቲል

| | | | |
|---|---|---|---|
| ውእቱ | ቀቲልሁ | ውእቶሙ | ቀቲልሆሙ |
| ይእቲ | ቀቲልሃ | ውእቶን | ቀቲልሆን |
| አንተ | ቀቲልከ | አንትሙ | ቀቲልክሙ |
| አንቲ | ቀቲልኪ | አንትን | ቀቲልክን |
| አነ | ቀቲልየ | ንሕነ | ቀቲልነ |

## የሣልስ ውስጠ ዘ የባለቤት ዝርዝር

ቀተለ → ቀታሊ

| | | | |
|---|---|---|---|
| ውእቱ | ቀታሊሁ | ውእቶሙ | ቀታሊሆሙ |
| ይእቲ | ቀታሊሃ | ውእቶን | ቀታሊሆን |
| አንተ | ቀታሊከ | አንትሙ | ቀታሊክሙ |
| አንቲ | ቀታሊኪ | አንትን | ቀታሊክን |
| አነ | ቀታሊየ | ንሕነ | ቀታሊነ |

***ቃታልያን***

*ቃታልያኒሁ ቃታልያኒሆሙ/ቃታልያኒሃ/ ቃታልያኒሆን/ቃታልያኒክ/ ቃታልያኒክሙ/ቃታልያንኪ/ቃታልያኒክን/ቃታልያንየ/ቀታልያኒነ*

***ቀታሊት***

*ቀታሊቱ፣ቀታሊቶሙ/ቀቃሊታ/ቀታሊቶን/ቀታሊትከ/ቀታሊትክሙ/ ቀታሊትኪ/ቀታሊትክን/ቀታሊየት/ቀታሊትነ*

***ቀታልያት***

*ቀታልያቲሁ/ቀታልያቲሆሙ/ቀታልያቲሃ/ቀታልያቲሆን/ቀታልያቲከ/ ቀታልያቲክሙ/ቀታልያትኪ/ቀታልያቲክን/ቀታልያትየ/ቀታልያቲነ*

**<u>የሳድስ ውስጠ ዘ የባለቤት ዝርዝር</u>**

ቀተለ → ቅቱል

| | | | |
|---|---|---|---|
| ውእቱ | ቅቱሉ | ውእቶሙ | ቅቱሎሙ |
| ይእቲ | ቅቱላ | ውእቶን | ቅቱሎን |
| አንተ | ቅቱልከ | አንትሙ | ቅቱልክሙ |
| አንቲ | ቅቱልኪ | አንትን | ቅቱልክን |
| አነ | ቅቱልየ | ንሕነ | ቅቱልነ |

**<u>ቅቱላን</u>**

ቅቱላኒሁ/ቅቱላኒሆሙ/ቅቱላኒሃ/ቅቱላኒሆን/ቅቱላኒከ/ቅቱላኒክሙ/ ቅቱላንኪ/ቅቱላኒክን/ቅቱላንየ/ቅቱላኒነ

**<u>ቅትልት</u>**

ቅትልቱ/ቅትልቶሙ/ቅትልታ/ቅትልቶን/ቅትልትከ/ቅትልትክሙ/ ቅትልትኪ/ቅትልትክን/ቅትልትየ/ቅትልትነ

**<u>ቅቱላት</u>**

ቅቱላቲሁ/ቅቱላቲሆሙ/ቅቱላቲሃ/ቅቱላቲሆን/ቅቱላቲከ/ቅቱላቲክሙ/ ቅቱላትኪ/ቅቱላቲክን/ቅቱላትየ/ቅቱላቲነ

**<u>የሳቢ ዘር የባለቤት ዝርዝር</u>**

ቀተለ → ቅትለት

| | | | |
|---|---|---|---|
| ውእቱ | ቅትለቱ | ውእቶሙ | ቅትለቶሙ |
| ይእቲ | ቅትለታ | ውእቶን | ቅትለቶን |
| አንተ | ቅትለትከ | አንትሙ | ቅትለትክሙ |
| አንቲ | ቅትለትኪ | አንትን | ቀትለትክን |
| አነ | ቅትለትየ | ንሕነ | ቅትለትነ |





# ምዕራፍ ፬

## <u>ግስ</u>

ስለ ግስ ከመናገራችን በፊት ስለአስገኚው ዘር እና ነባር መናገር ያስፈልጋል ። ዘር ነጠላ ግሥን ከነእርባው የሚያስገኝ ጥሬ ዘርን ኹሉ የሚወልድ ስለሆነም አባት ዘር ይባላል ። ሌላው ቃል ቢያስገኝ እንጂ ለርሱ አስገኝ የለውምና ። ማሰር የማይችል እና ዐጉል አንቀጽ ስለሆነ ንዑስ ይባላል። በሌላም በኩል በተጨማሪም መሠረተ ቃል ነውና አርእስት ይባላል ። የግሥ እና የዘር መነሻዎች አምስት ናቸው። እኒህም መራሑት ተብለው ይታወቃሉ ። የዘር መድረሻ ሳድስ እና ሳብዕ ናቸው ። **ምሳሌ፡-** ቀቲል ቀቲሎት

ቀድሶ ቀድሶት

በድርብ *መነገሩ* እና ‹ት› *መጨመሩ ለማብዛትና ለማብለጥ* ንባብ *ለማስጌጥ* ነው። ነባር ዘርነት የሌለው *ቃል* ሲሆን ስም እና አገባብ አንቀጽንም ያስገኛል። ነባር መባሉ *ሥሩና* ምንጩ ስላል*ታ*ወቀ ነው ነባር በሰባቱ ስልተ *ፊ*ደላት ይነሣል። በሰባቱ ስልተ *ፊ*ደላት ይጨርሳል። ነገር ግን ከግእዝ በስተቀር በስድስቱ ስልተ *ፊ*ደላት ይጨርሳል *ያ*ገባብ *ቃል* እና ሌላውም በግእዝ የተገለጹ ነገሮች መድረሻቸው ሳድስ ነው። ግእዝ መሆናቸውና ሲናበብበት ነው የሚሉም አሉ።

ግስ የሚለው *ቃል* ገሰ/ገሰሰ ዳበሰ *ያ*ዘ ጨበጠ ከሚለው ግስ የወጣ ሲሆን ግስ ማለት እክት ግስንግስ የሚያዝ የሚዳሰስ ማለት ሲሆን በቋንቋ የዘርና የነባር መሰብሰቢያ ፣ መዝገበ *ቃል* ምሥጢሩ ተወራራሽ *ቃል* ማለት ነው። ግስ መግሰስ አንዱን *ቃል* ማርባት ማብዛት ማለት ነው። ግስ ድርጊት መደረጉን ሁኔታ መሆኑን የሚገልጽ የዐረፍተ ነገር ማሠሪያ አንቀጽ ነው። በአንድ ዐረፍተ ነገር ውስጥ ያለ ግስ አንቀጽ ይባላል።አንቀጽ በሦስት ይከፈላል ፡- ፩.ዐቢይ አንቀጽ ፪.ንዑስ አንቀጽ ፫.ደቂቅ አንቀጽ ናቸው እነዚህም በግስ እርባታ ጊዜ ተገልፀው ይገኛሉ።

**<u>፩.፫. መራኁት</u>**:-መራኁት ማለት ከፋኞች ማለትነው::የግስ እና የዘር መነሻዎች አምስት ቀለማት ናቸው:: እነርሱም:-ግእዝ ፣ ራብዕ ፣ ኀምስ፣ ሳድስ፣ ሳብዕ ናቸው:: የግሥ ሁሉ መድረሻ ግእዝ ቀለም ነው::

ምሳሌ:- ቀተለ ፣ቀደሰ ፣ በልዐ፣ ገብረ፣ አስተሰነአለ፣ ባረከ ፣ጻመወ፣ ባልሐ፣ ሣቀየ፣ ሤመ፣ ቤተ፣ ዔለ፣ ጌገየ፣ ውኅዘ፣ ብህለ ፣ ጥዕየ፣ ቆመ፣ ፆደ፣ ሞተ::

☞ የግሥ ሁሉ ሆሄያት /ቀለማት/ብዛት ከሁለት ቀለም አይወርድም ከሰባት ቀለም አይወጣም /አይበልጥም/::

ምሳሌ:- ቤተ- ሁለት ቀለም:: አስተሰነአለ - ሰባት ቀለም::

## <u>፩.፬. የሠራዊት አለቆች /አርዕስት/</u>

የሠራዊት አለቆች ሥምንት ሲሆኑ ሃምሳ ሠራዊት /ጭፍራ/ አሏቸው:: ሥምንቱ የሠራዊት አለቆች የሚባሉት:- ቀተለ፣ ቀደሰ ፣ገብረ፣ አእመረ፣ ባረከ፣ ሤመ፣ ብህለ፣ ቆመ ናቸው:: ሃምሳው ሠራዊት ለሥምንቱ አለቆች ሲከፋፈሉ ለቀተለ ፳ ይደርሱታል እነርሱም:-ሐፀ ና ሐተተ ፣መሐለ ና ሰአለ፣ ወሀበ ና ወዐለ፣ ነቀወ፣ ከወወ፣ ወደየ፣ ወረደ፣ ጸገየ ናቸው:: ለቀደሰ ፲ ይደርሱታል እነርሱም:-ሰብሐ ና ጸውዐ፣ ለበወ ፣ ተወከለ፣ ተነበየ፣ ሀለወ ፣ሐለየ፣ተመክሐ፣ አንገለገ ፣ተሰፈወ ናቸው::

ለገብረ ፮ ይደርሱታል እነርሱም:- ሰክረ ፣ በልዐ ና መልሐ ፣ወድቀ፣ መስወ ፣መስየ ናቸው:: ለአእመረ ፲፩ ይደርሱታል እነርሱም:- አድለወ፣ አጥረየ፣ አመንተወ ፣ አመክነየ፣ አመድበለ፣ አንቀልቀለ ፣አንስሐስሐ፣ አቅየሐይሐ፣ አስተሰነአለ፣ ቀበያውበጠ፣ ተወህውሀ ናቸው::ለባረከ ፯ ይደርሱታል እነርሱም:- ሣረረ፣ፃመወ፣ ሣቀየ ፣ፃዕደወ ፣ፃህየየ ፣ማህረከ ናቸው:: ለሤመ ፬ ይደርሱታል እነርሱም:- ቄቅሐ ፣ዜነወ፣ ጌገየ፣ ዔወወ ናቸው::ለብህለ ፫ ይደርሱታል እነርሱም:-ውኅዘ ፣ስሕወ፣ ጥዕየ ናቸው::ለቆመ ፬ ይደርሱታል እነርሱም:-ኖሠሠ፣ ቶስሐ፣ ሞርቅሐ ፣ሎለወ ናቸው::





**<u>ምልማድ ፩.፬ :</u>**-የሚከተሉትን ግሦች በሥምንቱ አለቆች ሥር መድብ::

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ኖለወ | በዝኀ | ሐረየ | ሜጠ | ወደሰ | ፎሐ |
| ወርዘወ | ነሥአ | ሰትየ | አርመመ | ሐወጸ | ማሰነ |
| ውዕየ | ወሀበ | ምዕዘ | ሞዐ | ቤዘወ | መሐለ |

## <u>፩.፭.የግስ አወራረድ /አገሣሰስ/ እና የአናቅጽ ሥያሜ</u>

ግሥ መግሰስ ማለት አንድን ቃል ማርባት ማብዛት ማለት ሲሆን በዚህ ክፍል አንድ ግስ እንዴት እንደሚረባ እና ስያሜውም ምን እንደሆነ እናያለን። ግስ ለመግሰስ የሚረዱ ቀለማት አሥራው ቀለማት ሲባሉ እነርሱም («ተ»፣ ‹‹አ››፣ ‹‹የ››፣ ‹‹ነ››) ናቸው:: ለሦስተኛ መደቦች ከይእቲ በስተቀር ‹‹ነ››፣ለንሕነ በግእዛቸው በራብአቸው በሳድሳቸው ያገለግላሉ:: ከዚህ ቀጥለን የወደሰን እርባ ና የአናቅጽ ሥያሜ እናያለን።

<u>ምሳሌ</u>:- ወሰደ

ወደሰ - አመስግኗል፣አመሰገነ **ኀላፊ አንቀጽ / ቀዳማይ አንቀጽ**
ይዌድስ - ያመሰግናል **ትንቢት አንቀጽ / ካልዓይ አንቀጽ**
ይወድስ - ያመሰግን ዘንድ/እንዲያመሰግን/ሊያመሰግን **ዘንድ አንቀጽ**
ይወድስ - ያመስግን **ትእዛዝ አንቀጽ**
ወድሶ/ወድሶት - ማመስገን **አርዕስት**
ወዳሲ - የሚያመሰግን/አመስጋኝ **ሣልስ ውስጠ ዘ**
ወዳስያን - (ተ) የሚያመሰግኑ/አመስጋኞች **ሣልስ ውስጠ ዘ**
ወዳሲት - የምታመሰግን/አመስጋኝ **ሣልስ ውስጠ ዘ**
ወዳስያት - (አ) የሚያመሰግኑ/አመስጋኞች **ሣልስ ውስጠ ዘ**
ውዱስ - የተመሰገነ/ምስጉን **ሳድስ ውስጠ ዘ**
ውዱሳን - (ተ) የተመሰገኑ/ምስጉኖች **ሳድስ ውስጠ ዘ**
ውድስት - የተመሰገነች/ምስጉን **ሳድስ ውስጠ ዘ**
ውዱሳት-(አ)የተመሰገኑ/ምስጉኖች **ሳድስ ውስጠ ዘ**

♦ ኀላፊ ካልዓይ እና ትእዛዝ አናቅጽ ዐቢይ አንቀጽ ይባላሉ ማሠር ስለሚችሉ ተሳቢ ስለሚያደርጉ ነው::

ምሳሌ:-አለሙ ቀተለ ጸረ:: አለሙ ይቀትል ጸረ::አለሙ ይቅትል ጸረ:: ዘንድ አንቀጽ አርዕስት ውስጠዘ ሳቢዘር ቦዝ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ይባላሉ:: ዐረፍተ ነገር ማሠር አይችሉም::

## ፬.፬. አመላተ ሰዋስው /ጸዋትው/ጎርመት

አመላተ ሰዋስው የምንላቸው የስዋሰው አመሎች መደበኛውን የሰዋሰው ጠባይ አካሄድ ወይም የግሥ አገሳሰስ የሚቀይሩ ሲሆን ጎርመት ተብለውም ይታወቃሉ፡፡ ጎረመ ማለት ተወ ጎርመት ማለት መተው ማለት ነው፡፡ በዚህ የትምህርት ርዕስ በተለየ የምናጠናቸው የሚከተሉትን ቃላት ነው፡-

‹‹ ወ ፣የ ፣ሀ ፣ኃ ፣ ሐ ፣ አ ፣ ዐ ፣ተ.... ወ ፣ ተሰ ፣ ተዘ ፣ተጠ ፣ ተደ፣ ተተ ፣ ተጸ ››

፩. "ወ" የግሥ መድረሻ በሚሆንበት ጊዜ በካልዓይ በዘንድና በትእዛዝ አናቅጽ ፊቱ ያለውን ሆሄ ወደ ካዕብ ለውጦ ይጎርዳል/ይጠፋል/፡፡

ምሳሌ፡-

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ነቀወ | ቤዘወ | ዜነወ | ፈነወ | ሀለወ | ዘረወ |
| ይነቁ | ይቤዙ | ይዜኑ | ይፌኑ | ይሄሉ | ይዜሩ |
| ይንቁ | ይቤዙ | ይዜኑ | ይፈኑ | የሀሉ | ይዘሩ |
| ይንቁ | ይቤዙ | ይዜኑ | ይፈኑ | የሀሉ | ይዘሩ |

- የሳድስ ውስጠ «ዘ»ን መሀል ሳድስ ያደርጋል፡፡
  ምሳሌ፡- ወደሰ - ውዱስ ቀተለ - ቅቱል እንዳለው ሳይሆን
  ለበወ - ልብው ፈነወ - ፍንው ሀለወ - ህልው

፪. "ወ" ደጊመ ቀለም ሆኖ ከተገኘ አይጎርድም በሳድስ ያልቃል እንደሌላው፡፡

ምሳሌ፡-

| | | |
|---|---|---|
| ቀተለ | ከወወ | ዔወወ |
| ይቀትል | ይከውው | ይዔውው |
| ይቅትል | ይከውው | ይዔውው |
| ይቅትል | ይከውው | ይዔውው |





፫. በመድረሻቸው "ወ"ን የያዙ ግሦች ወደ ተገብሮ በተለወጡ ጊዜ ካልዓይ ዘንድና ትእዛዝ አናቅጽ በሳብዕ ይደርሳሉ፡፡"ወ" ይጠፋል፡፡

ምሳሌ፡-

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| <u>ገቢር</u> | <u>ተገብሮ</u> | ተሠገወ | ተፈነወ | ተደለወ | ተሰፈወ | ተቀነወ |
| | | ይሤጎ | ይትፌኖ | ይዴሎ | ይሴፎ | ይትቄኖ |
| ቀተለ | ተቀትለ | ይሠጎ | ይትፈኖ | ይዴሎ | ይሰፎ | ይትቀኖ |
| ፈነወ | ተፈነወ | ይሠጎ | ይትፈኖ | ይዴሎ | ይሰፎ | ይትቀኖ |

"ወ" የሌለባቸው እንዲህ አይደሉም ፡፡

ምሳሌ፡-

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ተትሀተ | ተጠብለለ | ተደመረ | ተዘከረ | ተጸወነ |
| ይቴሀት | ይጤብለል | ይዴመር | ይዜከር | ይጼወን |
| ይተሀት | ይጠብለል | ይደመር | ይዘከር | ይጸወን |
| ይተሀት | ይጠብለል | ይደመር | ይዘከር | ይጸወን |

፬. "ወ" በቀተለ ገብረ ብህለ ቤት መነሻ ሲሆን በዘንድና በትእዛዝ አናቀጽ "ወ" ይጠፋል "ሀ" እና "አ" በመሐል ከገቡ አሥራው ቀለማት በዘንድና በትእዛዝ አናቅጽ ግእዝ ይሆናሉ፡፡

***ምሳሌ፡-***

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ወደየ | ወረደ | ወለደ | ወድቀ | ውኅዘ |
| ይወዲ | ይወርድ | ይወልድ | ይወድቅ | ይውኅዝ |
| ይደይ | ይረድ | ይለድ | ይደቅ | የኀዝ |
| ይደይ | ይረድ | ይለድ | ይደቅ | የኀዝ |

፭. "ወ" በቀደሰ ቤትና በአእመረ ቤት መነሻ ሲሆን "ወ" አይጠፋም፡፡

ምሳሌ፡-

| | |
|---|---|
| ወደሰ | ወርዘወ |
| ይዌድስ | ይወረዙ |
| ይወድስ | ይወርዙ |
| ይወድስ | ይወርዙ |

፮.“ሀ”ወይም“አ” “ወ”ን ከተከተሉ አሥራው በዘንድና በትእዛዝ አናቅጽ ግእዝ ይሆናሉ::

ምሳሌ:-

| | | |
|---|---|---|
| ውእየ | ወዐለ | ወሀበ |
| ይውኢ | ይውዕል | ይሁብ/ይውህብ |
| የአይ | የዐል | የሀብ |
| የአይ | የዐል | የሀብ |

በባረከ ፣ሤመ ፣ቆመ ቤት ወ በመነሻ አይገኝም::

፯. “የ” የግሥ መድረሻ በሚሆንበት ጊዜ በካልዓይ ፣በዘንድና በትእዛዝ አናቅጽ ፊቱ ያለውን ሆሄ ወደ ሣልስ ለውጦ ይጠፋል::

ምሳሌ:-

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ሐለየ | ኀለየ | ጸገየ | ጌገየ | ሣቀየ | ሰትየ |
| ይሔሊ | የኀሊ | ይጸጊ | ይጌጊ | ይሣቂ | ይሰቲ |
| የሐሊ | ይኅሊ | ይጽጊ | ይጌጊ | ይሣቂ | ይስቲ/ ይስተይ |
| የሐሊ | ይኅሊ | ይጽጊ | ይጌጊ | ይሣቂ | ይስቲ/ ይስተይ |

| | | | |
|---|---|---|---|
| ገነየ | ይገኒ | ይግኒ | ይግኒ |
| አመክነየ | ያመከኒ | ያመክኒ | ያመክኒ |

፰. በአርዕስት ጊዜ ቀቲል ፣ብሂል ፣ውኂዝ እንደሚለው ቅድመ መድ ረሻውን ሣልስ በማድረግ ፈንታ ሳድስ ያደርጋል::

*ምሳሌ:-*

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ጸገየ | ጸለየ | ጌገየ | ሰትየ | ጥዕየ |
| ይጸጊ | ይጼሊ | ይጌጊ | ይሰቲ | ይጥዒ |
| ይጽጊ | ይጸሊ | ይጌጊ | ይስቲ/ይስተይ | ይጥዐይ |
| ይጽጊ | ይጸሊ | ይጌጊ | ይስቲ/ይስተይ | ይጥዐይ |
| ጸግይ/ጸግዮት | ጸልይ/ጸልዮት | ጌግይ/ጌግዮት | ሰትይ/ሰትዮት | ጥዕይ/ጥዕዮት |





፱. “የ”መድረሻ የሆነው ግሥ ቦዝ አንቀጽ ቀቲሎ፣ ቀዲሶ፣ ወዲሶ፣ ባሪኮ እንደሚለው ቅድመ መድረሻውን ሣልስ በማድረግ ፈንታ ሳድስ ያደርጋል::

ምሳሌ:- ቀተለ→ቀቲሎ ባረከ→ባሪኮ ሠነየ→ሠንዮ

ፈደየ→ፈድዮ ሣቀየ→ሣቅዮ ጸለየ→ጸልዮ

ጸገየ→ጸግዮ ገነየ→ገንዮ

፲. “የ”በሁለት ቀለም መድረሻና ደጊመ ቀለም ሁኖ ከተገኘ አይጠፋም::

ምሳሌ:-

| | | | |
|---|---|---|---|
| ጐየ | ፃሀየየ | አየየ | ተኀየየ |
| ይጐዪይ | ይፀሀይይ | የአይይ | ይትኀየይ |
| ይጕየይ | ይፃህይይ | ይእይይ | ይትኀየይ |
| ይጕየይ | ይፃህይይ | ይእይይ | ይትኀየይ |
| ጕይይ/ጕይዮት | ፃህይዮ/ፃህይዮት | አይይ/አይዮት | ተኀይዮ/ተኀይዮት |

፲፩. “የ”በተገብሮ ጊዜም አይጠፋም::

ምሳሌ:-

| | | |
|---|---|---|
| ከረየ | ተከርየ | ተሐሰየ |
| ይከሪ | ይትከረይ | ይትሐሰይ |
| ይክሪ | ይትከረይ | ይትሐሰይ |
| ይክሪ | ይትከረይ | ይትሐሰይ |
| ከርይ/ከርዮት | ተከርዮ/ተከርዮት | ተሐስዮ/ተሐስዮት |

፲፪.፩. “ሀ”ና“አ” ቀለማት በቀተለ ቤት መነሻ ሲሆኑ አሥራው ቀለማት በካልዓይ ግእዝ በዘንድና ትእዛዝ ሳድስ ቀለም ይሆናሉ::

*ምሳሌ:-*

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ሐመ | ሐለመ | አነመ | ዐለለ | ኄሰ | ዖረ |
| የሐምም | የሐልም | የአንም | የዐልል | የኀይስ | የዐውር |
| ይሕምም | ይሕልም | ይእንም | ይዕልል | ይኂስ | ይዑር |
| ይሕምም | ይሕልም | ይእንም | ይዕልል | ይኂስ | ይዑር |

፲፪.፪. "ሀ"ና"አ" ቀለማት በቀተለ ቤት በመሐል ሲገኙ ካልዓይ አንቀጽ ፍጹም ሳድስ የዘንድና ትእዛዝ አናቅጽ ቅድመ መድረሻ ግእዝ ይሆናል::

| | | | |
|---|---|---|---|
| ምሳሌ:- መሐለ | ይምሕል | ይምሐል | ይምሐል |
| ሰአለ | ይስእል | ይስአል | ይስአል |

፲፪.፫. በአርዕስት ጊዜ መነሻውን ቀቲል እንዳለው ግእዝ በማድረግ ፈንታ ሳድስ ያደርጋል::

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ምሳሌ:- መሐለ | ይምሕል | ይምሐል | ይምሐልም | ሐሊል/ምሐሎት |
| ሰአለ | ይስእል | ይስአል | ይስአል | ስኢል/ስኢሎት |

"ሀ" "አ" ቀለማት በቀተለ ቤት በመድረሻ አይገኙም::

፲፫.፩. "ሀ"ና"አ" በቀደሰ ቤት ሦስት ቀለም መነሻ ሲሆኑ አሥራው ቀለማት በካልዓይ ሳድስ በዘንድና ትእዛዝ አንቀጽ ግእዝ ይሆናሉ::

| | | | |
|---|---|---|---|
| ምሳሌ:-ሐወጸ | ዐበሰ | ሐደሰ | ዐመደ |
| ይሔውጽ | ይዔብስ | ይሔድስ | ይዔምድ |
| የሐውጽ | የዐብስ | የሐድስ | የዐምድ |
| የሐውጽ | የዐብስ | የሐጻስ | የዐምድ |

፲፫.፪. "ሀ"ና"አ" በቀደሰ ቤት በመሐል ሳድስ ቀለም ያለባቸው ግሦች መድረሻ ሲሆኑ አሥራው ቀለማት በካልዓይ በዘንድና በትእዛዝ አናቅጽ ሳድስ ይሆናሉ::

| | | | |
|---|---|---|---|
| ምሳሌ:- ሰብሐ | ጸውዐ | ተመክሐ | ተፈግዐ |
| ይሴብሕ | ይጼውዕ | ይትሜካ ሕ | ይትፌጋዕ |
| ይሰብሕ | ይጸውዕ | ይትመካ ሕ | ይትፈጋዕ |
| ይሰብሕ | ይጸውዕ | ይትመካ ሕ | ይትፈጋዕ |

"ሀ"ና"አ" በቀደሰ ቤት በመሀል አይገኙም::





፲፬.፩. "ሀ"ና"አ" በገብረ ቤት መነሻ ሲሆኑ አሥራው ቀለማት በካልዓይ ግእዝ በዘንድና በትእዛዝ ሳድስ ይሆናሉ::

*ምሳሌ:-*

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ኀልቀ | ዐብደ | አብየ | ኀጥአ | ኀብአ |
| የኀልቅ | የዐብድ | የአቢ | የኀጥእ | የኀብአ |
| ይኅልቅ | ይዕበድ | ይእበይ | ይኅጣእ | ይኅባእ |
| ይኅልቅ | ይዕበድ | ይእበይ | ይኅጣእ | ይኅባእ |

፲፬.፪. "ሀ"ና"አ" በገብረ ቤት መድረሻ ሲሆኑ የዘንድና የትእዛዝ አናቅጽ ቅድመ መድረሻ ራብዕ ይሆናል::

| | | | |
|---|---|---|---|
| ምሳሌ:- በልዐ | መርሐ | በጽሐ | መልአ |
| ይበልዕ | ይመርሕ | ይበጽሕ | ይመልእ |
| ይብላዕ | ይምራሕ | ይብጻሕ | ይምላእ |
| ይብላዕ | ይምራሕ | ይብጻሕ | ይምላእ |

"ሀ"ና"አ" በገብረ ቤት በመሀል አይገኙም::

፲፭. "ሀ"ና"አ" በአእመረ ቤት መነሻ ሲሆኑ አሥራው ቀለማት በካልዓይ በዘንድና በትእዛዝ አናቅጽ ግእዝ ይሆናሉ::

| | | | |
|---|---|---|---|
| ምሳሌ:- ኀንገረ | የኀነግር | የኀንግር | የኀንግር |
| ዐንዘረ | የዐነዝር | የዐንዝር | የዐንዝር |

- አመድበለን አኅመልመለን የመሰሉ ግሦች ይህን አይከተሉም::

| | | | |
|---|---|---|---|
| አመድበለ | ያመደብል | ያመድብል | ያመድብል |
| አኅመልመለ | ያኅመለምል | ያኅመልምል | ያኅመልምል |

- "ሀ"ና"አ" በአእመረ ቤት በመነሻ በመድረሻ በመሀል ይገኛሉ::

## ፲፪."ተ " የሚዋጥበት ሁኔታ

«ተ» በስድስት ፊደላት ስ ተ ዘ ደ ጠ ጸ መነሻ ሲሆን በእርባታ ጊዜ በ ትንቢት በዘንድና በትእዛዝ ይዋጣል::

ምሳሌ:-

| | | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ተሰብሐ | ተሰቅለ | ተትሕተ | ተዘከረ | ተደመረ | ተጠውቀ | ተጸወነ | ተሣለቀ |
| ይሴባሕ | ይሰቀል | ይቴሐት | ይዜከር | ይዴመር | ይጤወቅ | ይጼወን | ይሣለቅ |
| ይሰባሕ | ይሰቀል | ይተሐት | ይዘከር | ይደመር | ይጠወቅ | ይጸወን | ይሣለቅ |
| ይሰባሕ | ይሰቀል | ይተሐት | ይዘከር | ይደመር | ይጠወቅ | ይጸወን | ይሣለቅ |

# የሥምንቱ አርዕስትና የሠራዊቶቻቸው እርባ

## ፪. የቀደሰና ዘጠኙ ሠራዊቱ እርባ፡-

### ፩.የቀተለናሥምንቱ ሠራዊቱ እርባ፡-

| ቀተለ | ፩.ሐፀ | ሐተተ | ፪.ስአለ | መሐለ | ፫.ወዐለ | ወሀበ | ፬.ነቀወ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ይቀትል | ሐፅፅ | የሐትት | ይስእል | ይምሕል | ይውዕል | ይሁብ | ይነቁ |
| ይቅትል | ይሕፅፅ | ይሕትት | ይስኣል | ይምሓል | የዐል | የሀብ | ይንቁ |
| ይቅትል | ይሕፅፅ | ይሕትት | ይስኣል | ይምሓል | የዐል | የሀብ | ይንቁ |
| ቀቲል/ሎት | ሐፂፅ/ፆት | ሐቲት/ቶት | ስኢል/ሎት | ምሒል/ሎት | ውዒል/ሎት | ውሂብ/ቦት | ነቂው/ዎት |
| ቀታሊ | ሐፃፂ | ሐታቲ | ሰኣሊ | መሓሊ | ወዓሊ | ወሃቢ | ነቃዊ |
| ቀታልያን | ሐፃፅያን | ሐታትያን | ሰኣልያን | መሓልያን | ወዓልያን | ወሃብያን | ነቃውያን |
| ቀታሊት | ሐፃፂት | ሐታቲት | ሰኣሊት | መሓሊት | ወዓሊት | ወሃቢት | ነቃዊት |
| ቀታልያት | ሐፃፅያት | ሐታትያት | ሰኣልያት | መሓልያት | ወዓልያት | ወሃብያት | ነቃውያት |
| ቅቱል | ሕፁፅ | ሕቱት | ስኡል | ምሑል | ውዑል | ውሁብ | - |
| ቅቱላን | ሕፁፃን | ሕቱታን | ስኡላን | ምሑላን | ውዑላን | ውሁባን | - |
| ቅትልት | ሕፅፅት | ሕትት | ስእልት | ምሕልት | ውዕልት | ውህብት | - |
| ቅቱላት | ሕፁፃት | ሕቱታት | ስኡላት | ምሑላት | ውዑላት | ውሁባት | |

| ፭.ከወወ | ፮.ወደየ | ፯.ወረደ | ፰.ጸገየ | ቀደሰ | ፩.ጸውዐ | ሰብሐ | ፪.ለበወ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ይከውው | ይወዲ | ይወርድ | ይጸጊ | ይቄድስ | ይጼውዕ | ይሴብሕ | ይሌቡ |
| ይከውው | ይደይ | ይረድ | ይጽጊ | ይቀድስ | ይጸውዕ | ይሰብሕ | ይለቡ |
| ይከውው | ይደይ | ይረድ | ይጽጊ | ይቀድስ | ይጸውዕ | ይሰብሕ | ይለቡ |
| ከዊው/ዎት | ወድይ/ዮት | ወሪድ/ዶት | ጸግይ/ዮት | ቀድሶ/ሶት | ጸውዖ/ዖት | ሰብሖ/ሖት | ለብዎ/ዎት |
| ከዋዊ | ወዳዩ | ወራዲ | ጸጋዩ | ቀዳሲ | ጸዋዒ | ሰባሒ | ለባዊ |
| ከዋውያን | ወዳይያን | ወራድያን | ጸጋይያን | ቀዳስያን | ጸዋዕያን | ሰባሕያን | ለባውያን |
| ከዋዊት | ወዳዩት | ወራዲት | ጸጋዩት | ቀዳሲት | ጸዋዒት | ሰባሒት | ለባዊት |
| ከዋውያት | ወዳይያት | ወራድያት | ጸጋይያት | ቀዳስያት | ጸዋዕያት | ሰባሕያት | ለባውያት |
| ክዉው | ውዱይ | ውሩድ | ጽጉይ | ቅዱስ | ጽውዕ | ስቡሕ | ልብው |
| ክዉዋን | ውዱያን | ውሩዳን | ጽጉያን | ቅዱሳን | ጽውዓን | ስቡሓን | ልብዋን |
| ክውውት | ውድይት | ውርድ | ጽግይት | ቅድስት | ጽውዕት | ስብሕት | ልብውት |
| ክዉዋት | ውዱያት | ውሩዳት | ጽጉያት | ቅዱሳት | ጽውዓት | ስቡሓት | ልብዋት |



ሠ/ገ/ጽ/ቅ/ጊዮርጊስ ሰንበት ት/ቤ

# የሥምንቱ አርዕስትና የሠራዊቶቻቸው እርባ

## ፪. የቀደሰና ዘጠኙ ሠራዊቱ እርባ፡-

### ፩.የቀተለናሥምንቱ ሠራዊቱ እርባ፡-

| ቀተለ | ፩.ሐፀ | ሐተተ | ፪.ስአለ | መሐለ | ፫.ወዐለ | ወሀበ | ፬.ነቀወ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ይቀትል | ሐፅፅ | የሐትት | ይስእል | ይምሕል | ይውዕል | ይሁብ | ይነቁ |
| ይቅትል | ይሕፅፅ | ይሕትት | ይስኣል | ይምሓል | የዐል | የሀብ | ይንቁ |
| ይቅትል | ይሕፅፅ | ይሕትት | ይስኣል | ይምሓል | የዐል | የሀብ | ይንቁ |
| ቀቲል/ሎት | ሐፂፅ/ፆት | ሐቲት/ቶት | ስኢል/ሎት | ምሒል/ሎት | ውዒል/ሎት | ውሂብ/ቦት | ነቂው/ዎት |
| ቀታሊ | ሐፃፂ | ሐታቲ | ሰኣሊ | መሓሊ | ወዓሊ | ወሃቢ | ነቃዊ |
| ቀታልያን | ሐፃፅያን | ሐታትያን | ሰኣልያን | መሓልያን | ወዓልያን | ወሃብያን | ነቃውያን |
| ቀታሊት | ሐፃፂት | ሐታቲት | ሰኣሊት | መሓሊት | ወዓሊት | ወሃቢት | ነቃዊት |
| ቀታልያት | ሐፃፅያት | ሐታትያት | ሰኣልያት | መሓልያት | ወዓልያት | ወሃብያት | ነቃውያት |
| ቅቱል | ሕፁፅ | ሕቱት | ስኡል | ምሑል | ውዑል | ውሁብ | - |
| ቅቱላን | ሕፁፃን | ሕቱታን | ስኡላን | ምሑላን | ውዑላን | ውሁባን | - |
| ቅትልት | ሕፅፅት | ሕትት | ስእልት | ምሕልት | ውዕልት | ውህብት | - |
| ቅቱላት | ሕፁፃት | ሕቱታት | ስኡላት | ምሑላት | ውዑላት | ውሁባት | |

| ፭.ከወወ | ፮.ወደየ | ፯.ወረደ | ፰.ጸገየ | ቀደሰ | ፩.ጸውዐ | ሰብሐ | ፪.ለበወ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ይከውው | ይወዲ | ይወርድ | ይጸጊ | ይቄድስ | ይጼውዕ | ይሴብሕ | ይሌቡ |
| ይከውው | ይደይ | ይረድ | ይጽጊ | ይቀድስ | ይጸውዕ | ይሰብሕ | ይለቡ |
| ይከውው | ይደይ | ይረድ | ይጽጊ | ይቀድስ | ይጸውዕ | ይሰብሕ | ይለቡ |
| ከዊው/ዎት | ወድይ/ዮት | ወሪድ/ዶት | ጸግይ/ዮት | ቀድሶ/ሶት | ጸውዖ/ዖት | ሰብሖ/ሖት | ለብዎ/ዎት |
| ከዋዊ | ወዳዩ | ወራዲ | ጸጋዩ | ቀዳሲ | ጸዋዒ | ሰባሒ | ለባዊ |
| ከዋውያን | ወዳይያን | ወራድያን | ጸጋይያን | ቀዳስያን | ጸዋዕያን | ሰባሕያን | ለባውያን |
| ከዋዊት | ወዳዩት | ወራዲት | ጸጋዩት | ቀዳሲት | ጸዋዒት | ሰባሒት | ለባዊት |
| ከዋውያት | ወዳይያት | ወራድያት | ጸጋይያት | ቀዳስያት | ጸዋዕያት | ሰባሕያት | ለባውያት |
| ክውው | ውዱይ | ውሩድ | ጽጉይ | ቅዱስ | ጽውዕ | ስቡሕ | ልብው |
| ክውዋን | ውዱያን | ውሩዳን | ጽጉያን | ቅዱሳን | ጽውዓን | ስቡሓን | ልብዋን |
| ክውውት | ውድይት | ውርድ | ጽግይት | ቅድስት | ጽውዕት | ስብሕት | ልብውት |
| ክውዋት | ውዱያት | ውሩዳት | ጽጉያት | ቅዱሳት | ጽውዓት | ስቡሓት | ልብዋት |

| ፫.ተወከለ | ፬.ተነበየ | ፭.ሀለወ | ፮.ሐለየ | ፯.ተመክሐ | ፰.አንገለገ | ፱.ተሰፈወ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ይትዌከል | ይትኔበይ | ይሄሉ | ይሔሊ | ይትሜካሕ | ያንጌልግ | ይሴፎ |
| ይትወከል | ይትነበይ | የሃሉ | የሐሊ | ይትመካሕ | ያንገልግ | ይሰፎ |
| ይትወከል | ይትነበይ | የሃሉ | የሐሊ | ይትመካሕ | ያንገልግ | ይሰፎ |
| ተወክሎ/ሎት | ተነብዮ/ዮት | ሀልዎ/ዎት | ሐልዮ/ዮት | ተመክሖ/ሖት | አንገልጎ/ጎት | ተሰፍዎ/ዎት |
| ተወካሊ | ተነባዪ | ሀላዊ | ሐላዪ | ተመካሒ | አንገላጊ | ተሰፋዊ |
| ተወካልያን | ተነባይያን | ሀላውያን | ሐላይያን | ተመካሕያን | አንገላግያን | ተሰፋውያን |
| ተወካሊት | ተነባዪት | ሀላዊት | ሐላዪት | ተመካሒት | አንገላጊት | ተሰፋዊት |
| ተወካልያት | ተነባይያት | ሀላውያት | ሐላይያት | ተመካሕያት | አንገላግያት | ተሰፋውያት |
| ውኩል | - | ህልው | ሕሉይ | ምኩሕ | እንግሉግ | - |
| ውኩላን | - | ህልዋን | ሕሉያን | ምኩሓን | እንግሉጋን | - |
| ውክልት | - | ህልውት | ሕልይት | ምክሕት | እንግልግት | - |
| ውኩላት | - | ህልዋት | ሕሉያት | ምኩሓት | እንግሉጋት | -- |

፫.የገብረና አምስቱ ሠራዊቱ እርባ፡-

| <u>ገብረ</u> | ፩.ሰክረ | ፪.በልዐ | መልሐ | ፫.ወድቀ | ፬.መሰወ | ፭.መሰየ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ይገብር | ይሰክር | ይበልዕ | ይመልሕ | ይወድቅ | ይመሱ | ይመሲ |
| ይግበር | ይስክር | ይብላዕ | ይምላሕ | ይደቅ | ይምሱ | ይምሲ |
| ይግበር | ይስክር | ይብላዕ | ይምላሕ | ይደቅ | ይምሱ | ይምሲ |
| ገቢር/ሮት | ሰኪር/ሮት | በሊዕ/ዖት | መሊሕ/ሖት | ወዲቅ/ቆት | መሲው/ዎት | መስይ/ዮት |
| ገባሪ | ሰካሪ | በላዒ | መላሒ | ወዳቂ | መሳዊ | መሳዪ |
| ገባርያን | ሰካርያን | በላዕያን | መላሕያን | ወዳቅያን | መሳውያን | መሳይያን |
| ገባሪት | ሰካሪት | በላዒት | መላሒት | ወዳቂት | መሳዊት | መሳዪት |
| ገባርያት | ሰካርያት | በላዕያት | መላሕያት | ወዳቅያት | መሳውያት | መሳይያት |
| ግቡር | ስኩር | ብሉዕ | ምሉሕ | ውዱቅ | ምስው | -- |
| ግቡራን | ስኩራን | ብሉዓን | ምሉሓን | ውዱቃን | ምስዋን | -- |
| ግብርት | ስክርት | ብልዕት | ምልሕት | ውድቅ | ምስውት | -- |
| ግቡራት | ስኩራት | ብሉዓት | ምሉሓት | ውዱቃት | ምስዋት | -- |





፬.የአእመረና ዐሥራአንዱ ሠራዊቱ እርባ፡-

| <u>አእመረ</u> | ፩.አድለወ | ፪.አጥረየ | ፫.አመንተወ | ፬.አመክነየ | ፭.አመድበለ | ፮.አንቀልቀለ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| የአምር | ያደሉ | ያጠሪ | ያመነቱ | ያመክኒ | ያመደብል | ያንቀለቅል |
| ያእምር | ያድሉ | ያጥሪ | ያመንቱ | ያመክኒ | ያመድብል | ያንቀልቅል |
| ያእምር | ያድሉ | ያጥሪ | ያመንቱ | ያመክኒ | ያመድብል | ያንቀልቅል |
| አእምሮ/ት | አድልዎ/ት | አጥርዮ/ዮት | አመንትዎ/ዎት | አመክንዮ/ዮት | አመድብሎ/ሎት | አንቀልቅሎ/ት |
| አእማሪ | አድላዊ | አጥራዪ | አመንታዊ | አመክናዪ | አመድባሊ | አንቀልቃሊ |
| አእማርያን | አድላውያን | አጥራይያን | አመንታውያን | አመክናይያን | አመድባልያን | አንቀልቃልያን |
| አእማሪት | አድላዊት | አጥራዪት | አመንታዊት | አመክናዪት | አመድባሊት | አንቀልቃሊት |
| አእማርያት | አድላውያት | አጥራይያት | አመንታውያት | አመክናይያት | አመድባልያት | አንቀልቃልያት |
| እሙር | -- | -- | ምንትው | -- | ምድቡል | እንቅልቁል |
| እሙራን | -- | -- | ምንትዋን | -- | ምድቡላን | እንቅልቁላን |
| እምርት | -- | -- | ምንትውት | -- | ምድብልት | እንቅልቅልት |
| እሙራት | -- | -- | ምንትዋት | -- | ምድቡላት | እንቅልቁላት |

| ፯.አንስሐስሐ | ፰.አቅየሐይሐ | ፱.አስተሰነአለ | ፲.ቀበያውበጠ | ፲፩.ተወሀውሀ |
|---|---|---|---|---|
| ያንሰሐስሕ | ያቅየሐይሕ | ያስተሰናእል | ይቀበያወብጥ | ይትወሀዋህ |
| ያንሳሕስሕ | ያቅያሕይሕ | ያስተሰንእል | ይቀበያውብጥ | ይትዋህዋህ |
| ያንሳሕስሕ | ያቅያሕይሕ | ያስተሰንእል | ይቀበያውብጥ | ይትዋህዋህ |
| አንሳሕስሖ/ሖት | አቅያሕይሖ/ሖት | አስተሰንእሎ/ሎት | ቀበያውብጦ/ጦት | ተዋህውሆ/ሆት |
| አንሳሕሳሒ | አቅያሕያሒ | አስተሰንአሊ | ቀበያውባጢ | ተዋህዋሂ |
| አንሳሕሳሕያን | አቅያሕያሕያን | አስተሰንአልያን | ቀበያውባጥያን | ተዋህዋህያን |
| አንሳሕሳሒት | አቅያሕያሒት | አስተሰንአሊት | ቀበያውባጢት | ተዋህዋሂት |
| አንሳሕሳሕያት | አቅያሕያሕያት | አስተሰንአልያት | ቀበያውባጥያት | ተዋህዋህያት |
| -- | -- | --- | -- | -- |
| -- | -- | --- | -- | -- |
| -- | -- | --- | -- | -- |
| -- | -- | --- | -- | -- |

፮.የባረከና ስድስቱ ሠራዊቱ እርባ:-

| ባረከ | ፩.ሣረረ | ፪.ዓመወ | ፫.ሣቀየ | ፬.ዓዕደወ | ፭.ዓህየየ | ፮.ማህረከ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| ይባርክ | ይሣርር | ይዓሙ | ይሣቂ | ይፀንዱ | ይፀህይይ | ይማህርክ |
| ይባርክ | ይሣርር | ይዓሙ | ይሣቂ | ይዓዕዱ | ይዓህይይ | ይማህርክ |
| ይባርክ | ይሣርር | ይዓሙ | ይሣቂ | ይዓዕዱ | ይዓህይይ | ይማህርክ |
| ባርኮ/ኮት | ሣርሮ/ሮት | ዓምዎ/ዎት | ሣቅዮ/ዮት | ዓዕድዎ/ዎት | ዓህይዮ/ዮት | ማህርኮ/ኮት |
| ባራኪ | ሣራሪ | ዓማዊ | ሣቃዪ | ዓዕዳዊ | ዓህያዪ | ማህራኪ |
| ባራክያን | ሣራርያን | ዓማውያን | ሣቃይያን | ዓዕዳውያን | ዓህያይያን | ማህራክያን |
| ባራኪት | ሣራሪት | ዓማዊት | ሣቃዪት | ዓዕዳዊት | ዓህያዪት | ማህራኪት |
| ባራክያት | ሣራርያት | ዓማውያት | ሣቃይያት | ዓዕዳውያት | ዓህያይያት | ማህራክያት |
| ቡሩክ | ሥሩር | -- | -- | ፅዕድው | ፅህዩይ | ምህሩክ |
| ቡሩካን | ሥሩራን | -- | -- | ፅዕድዋን | ፅህዩያን | ምህሩካን |
| ቡርክት | ሥርርት | -- | -- | ፅዕዱት | ፅህይይት | ምህርክት |
| ቡሩካት | ሥሩራት | -- | -- | ፅዕድዋት | ፅህዩያት | ምህሩካት |

፯.የብህለናሦስቱ ሠራዊቱ እርባ:

| ብህለ | ፩.ውኀዘ | ፪.ስሕወ | ፫.ጥዕየ |
|---|---|---|---|
| ይብህል | ይውኅዝ | ይስሑ | ይጥዒ |
| ይብሃል | የኀዝ | ይስሐው | ይጥዓይ |
| ይብሃል | የኀዝ | ይስሐው | ይጥዓይ |
| ብሂል/ሎት | ውኂዝ/ት | ስሒው/ዎት | ጥዕይ/ዮት |
| በሃሊ | ወኃዚ | ሰሓዊ | ጠዓዪ |
| በሃልያን | ወኃዝያን | ሰሓውያን | ጠዓይያን |
| በሃሊት | ወኃዚት | ሰሓዊት | ጠዓዪት |
| በሃልያት | ወኃዝያት | ሰሓውያት | ጠዓይያት |
| ብሁል | ውኑዝ | ስሕው | ጥዑይ |
| ብሁላን | ውኑዛን | ስሕዋን | ጥዑያን |
| ብህልት | ውኅዝት | ስሕውት | ጥዕይት |
| ብሁላት | ውኑዛት | ስሕዋት | ጥዑያት |

፰.የሤመና አራቱ ሠራዊቱ እርባ:

| ሤመ | ፩.ቀቅሐ | ፪.ዜነወ | ፫.ጌገየ | ፬.ዔወወ |
|---|---|---|---|---|
| ይሠይም | ይቄቅሕ | ይዜኑ | ይጌጊ | ይዔውው |
| ይሢም | ይቀቅሕ | ይዜኑ | ይጌጊ | ይዔውው |
| ይሢም | ይቀቅሕ | ይዜኑ | ይጌጊ | ይዔውው |
| ሠይም/ት | ቀቅሖ/ት | ዜንዎ/ት | ጌግዮ/ዮት | ዔውዎ/ት |
| ሠያሚ | ቀቃሒ | ዜናዊ | ጌጋዪ | ዔዋዊ |
| ሠያምያን | ቀቃሕያን | ዜናውያን | ጌጋይያን | ዔዋውያን |
| ሠያሚት | ቀቃሒት | ዜናዊት | ጌጋዪት | ዔዋዊት |
| ሠያምያት | ቀቃሕያት | ዜናውያት | ጌጋይያት | ዔዋውያት |
| ሥዩም | ቂቁሕ | -- | ጊጉይ | ዒውው |
| ሥዩማን | ቂቁሓን | -- | ጊጉያን | ዒውዋን |
| ሥዩምት | ቂቅሕት | -- | ጊግይት | ዒውውት |
| ሥዩማት | ቂቁሓት | -- | ጊጉያት | ዒውዋት |





፱.የቆመና አራቱ ሠራዊቱ እርባ:-

| ቆመ | ፩.ኖሠሠ | ፪.ቶስሐ | ፫.ሞርቅሐ | ፬.ሎለወ |
|---|---|---|---|---|
| ይቀውም | ይኖሥሥ | ይቶስሕ | ይሞረቅሕ | ይሎሉ |
| ይቁም | ይኖሥሥ | ይቶስሕ | ይሞርቅሕ | ይሎሉ |
| ይቁም | ይኖሥሥ | ይቶስሕ | ይሞርቅሕ | ይሎሉ |
| ቀዊም/ሞት | ኖሢሥ/ሦት | ቶስሖ/ሖት | ሞርቅሖ/ሖት | ሎልዎ/ዎት |
| ቀዋሚ | ኖሣሢ | ቶሳሒ | ሞርቃሒ | ሎላዊ |
| ቀዋምያን | ኖሣሥያን | ቶሳሕያን | ሞርቃሕያን | ሎላውያን |
| ቀዋሚት | ኖሣሢት | ቶሳሒት | ሞርቃሒት | ሎላዊት |
| ቀዋምያት | ኖሣሥያት | ቶሳሕያት | ሞርቃሕያት | ሎላውያት |
| ቅውም | ኑሡሥ | ቱሱሕ | ሙርቁሕ | ሉልው |
| ቅውማን | ኑሡሣን | ቱሱሓን | ሙርቁሓን | ሉልዋን |
| ቅውምት | ኑሥሥት | ቱስሕት | ሙርቅሕት | ሉሉት |
| ቅውማት | ኑሡሣት | ቱሱሓት | ሙርቁሓት | ሉልዋት |

## ፲.፫. ዝርው

ዝርው የሚባሉት ከአርእስት እና ከሠራዊት ስምም የሌላቸው "ኈ፣ኰ፣ጐ፣ቈ "ን መነሻ፣መኻል፣መድረሻ ያደረጉ ግሦች ናቸው:: እነዚህም ስልተ ፊደላቸው አምስት ስለሆነ የተለየ እርባ ያላቸው ይመስላል እንጂ ከመደበኛው የግሥ አካሔድ የተለዩ አይደሉም:: ካዕብ ቀለምና ሳድስ ግእዝ ቀለምና ሳብዕ ይወራረሳሉ በዚህም የተለዩ እንዳይደሉ ይታወቃል:: ምሳሌ:-

| ኈለቈ | ለሐኰ | ላኰየ | ቈቈዐ | ጐየ | ጐሕቈ |
|---|---|---|---|---|---|
| ይኌልቍ | ይልሕኵ | ይላኵ | ይቈቍዕ | ይጐዪይ | ይጐሕቍ |
| ይኈልቍ | ይልሐኵ | ይላኵ | ይቈቍዕ | ይጐየይ | ይጐሐቍ |
| ይኈልቍ | ይልሐኵ | ይላኵ | ይቈቍዕ | ይጐየይ | ይጐሐቍ |
| ኈልቈ/ | ልሒኵ/ | ላኵዮ/ | ቈቍዖ/ | ጐይዮ/ | ጐሒቍ/ |
| ኈልቈት | ልሒኰት | ላኵዮት | ቈቍዖት | ጐዩዮት | ጐሒቈት |

# ምዕራፍ ፭
# የዘር አወጣጥ

የግእዝ ቋንቋ ሰዋሰው በጠቅላላው በአራት ይከፈላል :: እነርሱም:-

፩.እርባ ቅምር ፪.እርባ ግሥ ፫.ነጠላ ግሥ ፬.አገባብ ናቸው

**፩.** **እርባ ቅምር**:- ከዘር የሚወጡን የግሥ አርእስት የሚሆኑን ቀለማት ከሠራዊታቸው ጋር አመላቸውን የሚያስለይ የሚጠብቅና የሚላላውን ባንድ ቃል ብዙ የሚፈታውን በራሱ ቋሚ ሲሆን ገቢርና ተገብሮ የመሰለውን በሥርዓት የማይሄደውን ግሥ ሁሉ በየሥርዓቱ ከፍሎ አካሄዱንና ጠባዩን ሁሉ የሚያስታውቅ ነው::

**፪** **እርባ ግሥ:-** በ፬ ሠራዊት ተዘርዝሮ በ፰አርዕስት ተከፍሎ በ፭ አዕማድ ተጠቅልሎ በዐቢይ በንዑስ በደቂቅ አንቀጽ በባዕድ ቅጽል በመራሕያን በዝርዝር ቅጽል እየገባ በምላት የሚገሠሥ እርባታነው

**፫. ነጠላ ግሥ ዘርና ነባር:-**

ነጠላ ግሥ ከ ሀ - ፐ ድረስ ያለ መድረሻውን ግእዝ እያደረገ በኃላፊ ብቻ ያለ እርባታ የሚሄድ ግሥ ነው::

**ዘር-** አንቀጽ የሌለው ሁሉ ዘር ይባላል:: አንቀጽ ማለት ደጅ ወይም መግቢያና መውጫ ነው:: እንዲሁም ዘር በነገር ሁሉ መውጫና መግቢያ ያለው ባንድ ቃል ብቻ ያልተወሰነ ነገር ነው ዘር መባሉም በምሳሌ ነው:: አንዲት ፍሬ ቢዘሩዋት ብዙ ፍሬ እንድታፈራ እንዲሁም ዘር በነገር አናቅጽ ሁሉ እየገባ ሥሩ አንድ ሲሆን በልዩልዩ እርባታ የሚረባ ግሥ ሁሉ ሥር ወይም እናት ነው ስለዚህ ስሙ ዘር ተባለ::

**ነባር-** አንቀጽ የሌለው ሁሉ ነባር ይባላል- ነባር ማለት እርባ የሌለው በቁም ቀሪ ነገር ነው መድረሻውም በሁሉም ስልተ ፊደል ነው::

**፬.** **አገባብ:-** የነገርን ቅጽል በሁሉም ስልተ ፊደል የሚያናግረውን በአንድና በብዙ በሩቅና በቅርብ በወንድና በሴት በነዳሪና በማኀደር





በስምና በግብር በተገብሮና በገቢር የነገር ፊደላት እንዴት እንዲገቡ እንዴት እንዲተረጎሙ የሚያስለይ የመጽሐፍን አካሄድ የቅኔን መንገድ የቁጥርን እርባታ የቋንቋውን ጠባይና ልማድ የነገርን ምርምርና ሐተታ ሁሉ የሚያስታውቅ ነው::

በዚህ ምዕራፍ የምናየው በተራ ቁጥር ሦስት የተገለጸውን የዘር አወጣጥ ነው::

***ለምሳሌ:-*** ስብከት፣ መቅደስ፣ ማኅቶት፣ ቅዳሴ፣ ሙዳይ የሚሉት የተለያዩ ዘሮች ሲሆኑ

ስብከት - ሳቢ ዘር ፤ መቅደስ- ባዕድ ዘር ፤ ማኅቶት- ባዕድ ከምዕላድ ዘር ፤ ቅዳሴ ጥሬ ዘር ፤ ሙዳይ - ባዕድ ዘር እንላለን እንጂ አንቀላቅልም ሳቢ ዘሩን ጥሬ ዘር ዘመድ ዘሩን ጥሬ ዘር አንልም ይህስ እንደምን ይታወቃል ቢሉ ከዚህ እንደሚከተለው እናሳያለን::

**፭.፩.** **መ ስም ውስጠ ዘ** :- ማለት ባዕድ ቀለም «መ» ያለበት ውስጠ ዘ ማለት ሲሆን በአማርኛ በሣልስ ውስጠ ዘ ይተረጎማል:: መስም ውስጠ ዘ በሁሉም ግሦች አይገኝም::

ምሳሌ :- ዘመረ ⟶ መዘምር  ድኅነ ⟶ መድኅን
ኰነነ ⟶ መኰንን  መሀረ ⟶ መምህር
ቀተለ ⟶ መቅትል  ፈከረ ⟶ መፈክር

*ምልማድ ፭.፩.:- መ ስም ውስጠ ዘ ዘር አውጣላቸው::*

| | | |
|---|---|---|
| ፩. ቀደሰ | ፪. አድኀነ | ፫.ፈወሰ |
| ፬. ተርጐመ | ፭. ተንበለ | ፮. ገብረ |
| ፯. ሰአለ | ፰. ሰቀለ | ፱. አመድበለ |

**፭.፪.ሳቢ ዘር:-** አሠራርን አደራረግን የሚያሳይ ሲሆን በአማርኛ በአርዕስት ሊተረጎም ይችላል::ሳቢ ዘር የሚኘው ከሕገወጥ በቀር በሦስት ቀለማትና ከዚያ በታች ባሉ ግሦች ነው:: የሳቢ ዘር መለያ ምልክት መነሻውና ድኅረ መነሻው ሳድስ ቀለም ከዚያም ግእዝ ቀለም በመጨረሻም «ት» መጨመር ነው::

ምሳሌ :-

ሰበከ ⇨ ስብከት    መጽአ ⇨ ምጽአት    ሰቀለ ⇨ ስቅለት

ስብሐ ⇨ ስብሐት    ገብረ ⇨ ግብረት    ቀተለ ⇨ ቅትለት

ነበረ ⇨ ንብረት    ፈጠረ ⇨ ፍጥረት

- በ«ወ» የሚነሣ ግሥ በሳቢ ዘር ጊዜ «ወ» ን ሲጎርድ

ምሳሌ:- ወረደ⇨ ርደት    ወለደ⇨ልደት    ወጽአ⇨ ጻአት

በቆመ ቤት በካዕብ ተነስቶ መደበኛውን አካሄድ ይሄዳል

*ምሳሌ:-* ቆመ ⇨ ቁመት    ፆደ ⇨ ዑደት    ሖረ⇨ ሑረት

- በ«ወ» የሚነሣ ግሥ በሳቢ ዘር ጊዜ «ወ» ን ሳይጎርድ

*ምሳሌ:-* ወገረ⇨ውግረት    ውኀደ⇨ውኀደት    ውኀጠ⇨ውኀጠት

ወጠነ⇨ውጥነት    ወፀፈ⇨ውፅፈት

በሤመ ቤት በሣልስ ይነሳል::

*ምሳሌ:-* ሤመ ⇨ ሢመት    ዔለ⇨ ዒለት    ሜጠ ⇨ ሚጠት

<u>ምልማድ ፭.፪.:-ለሚከተሉት ግሦች ሳቢ ዘር አውጣላቸው ::</u>

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| <u>፩</u>. ቀብዐ ⇨ | <u>፪.</u> መተረ⇨ | ፫. ሰአለ⇨ | ፬. ኀብረ⇨ | ፭. ሐይወ⇨ |
| ሠርዐ⇨ | መሐረ⇨ | ውእየ⇨ | ፆረ⇨ | ሤጠ ⇨ |
| ወድቀ⇨ | ፆረ⇨ | ቈሐ⇨ | ቦአ⇨ | ወጽአ⇨ |
| ኄረወ⇨ | ኤነ⇨ | ዐረየ⇨ | ቴሐ⇨ | ገብአ⇨ |
| ኀደረ⇨ | በልዐ⇨ | ሠዐረ⇨ | በጽሐ⇨ | |

<u>፭.፫</u> <u>ዘመድ ዘር</u>:- ዘመድ ዘር ማለት ምንም ባዕድ ቀለም ያልተደባለቀበት ዘር ማለት ሲሆን ባዕድ ቀለም ስለማይጨምር ዘመድ ዘር ተብሏል::መድረሻ ቀለሙም ሳድስ ነው::

ምሳሌ:- ከብረ⇨ክብር    ቀተለ⇨ቀትል    ጠበበ⇨ጥበብ    ነበበ⇨ንባብ

ለበወ ⇨ልብ    ቈጽለ⇨ቈጽል    ፆደ⇨ዐውድ    ዘርዐ⇨ዘርዕ    ገብረ⇨ግብር

ሤጠ⇨ሤጥ





<u>ምልማድ ፭.፫:-ለሚከተሉት ግሦች ዘመድ ዘር አውጣላቸው::</u>

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| <u>፩</u>. ዐጠነ⇨ | <u>፪.</u> ለምደ⇨ | ፫. ሐመ⇨ | ፬. ሰክረ⇨ | ፭. ሰንበተ |
| ኄረወ⇨ | ሰምዐ⇨ | ውዕየ⇨ | ኖመ⇨ | ነደ |
| ሣቀየ⇨ | ቤተ⇨ | ነፍሰ⇨ | ጦመረ⇨ | ሐፀ |
| ነቀወ⇨ | አንቀልቀለ⇨ | መከረ⇨ | መርሐ⇨ | አመድበለ |

<u>፭.፬.ባዕድ ዘር:-</u> ቀድሞ ከግሡ ያልነበረ ባዕድ ቀለም በመነሻ የሚጨምር ባዕድ ዘር ይባላል:: በመነሻ የምንጨምራቸው ባዕዳን ቀለማትም «አ፣ተ፣መ፣ታ፣ት፣ሙ፣ማ፣ሞ፣ ም» ናቸው::

ምሳሌ:-ቀደሰ⇨መቅደስ    ኀደረ⇨ማኅደር    ወደየ⇨ሙዳይ    ወጸፈ⇨ሞጸፍ

ነበበ ⇨ምንባብ    መለከ⇨አምላክ    ከለለ⇨አክሊል/ተክሊል    ርእየ⇨አርአያ

መሰለ⇨አምሳል    ገብረ⇨ምግባር/ተግባር    ሖረ⇨ምሕዋር

ቀተለ⇨ምቅታል    ወለጠ⇨ተውላጥ    ውኀዘ⇨ሙኀዝ    ሰበከ⇨ምስባክ

ነደ⇨ምንዳድ    ወፈረ⇨ሙፋር    ቤተ⇨ታቦት    ቆመ⇨ምቅዋም/ተቅዋም

ሐደሰ⇨ተሐድሶ

<u>ምልማድ ፭.፬.:-ለሚከተሉት ግሦች ባዕድ ዘር አውጣላቸው::</u>

| | | | |
|---|---|---|---|
| <u>፩</u>. አሠረ⇨ | <u>፪.</u> ሠረቀ⇨ | ፫. ነበረ⇨ | ፬. ወረደ⇨ |
| ሰከለ⇨ | ወረቀ⇨ | ከረየ⇨ | ኄበ⇨ |
| ለአከ⇨ | ሰፈነ⇨ | ከወወ⇨ | ሰአለ⇨ |

<u>፭.፭. ምዕላድ ዘር</u> :- ቀድሞ ከግሡ ያልነበረ ባዕድ ቀለም በመድረሻ የሚጨምር ምዕላድ ዘር ይባላል ከመድረሻ የምንጨምራቸው ባዕዳን ቀለማትም «ም፣ል፣ት፣ን፣ና፣ው፣ዊ፣ያ፣ይ» ናቸው::

ምሳሌ:- ተነበየ ⇨ ትንቢት    ሖረ ⇨ ሐዋርያ    በርሀ ⇨ ብርሃን

ተኬነወ ⇨ ኬንያ    ኀጥአ ⇨ ኃጢአት    ጸለየ ⇨ ጸሎት

ቀደሰ ⇨ ቅድስና    ሐመየ ⇨ ሐሜት    ቀነወ ⇨ ቀኖት

ቀደመ ⇨ ቅድምና    ፈለጠ ⇨ ፍልጣን/ፍልጠት

የ "ል፣ ው፣ ይ" ምዕላድነት እንዴት ነው ቢሉ በብዙ ቁጥርና በቅጽል የሚታይ ነው::ይህም:-

ባሕር ⇨ ባሕራይ ላዕል⇨ላዕላይ ሌሊት⇨ለያልይ ቅድም⇨ቀዳማይ ፈየተ⇨ፈያታይ ግብጽ⇨ግብጻይ ቀርን⇨ቀርናይ አይሁድ⇨አይሁዳይ የማን⇨የማናይ አብ⇨አበው ኪሩብ ⇨ ኪሩቤል ያለውን ነው::

<u>ምልማድ ፩.፭. :-ለሚከተሉት ግሦች ምዕላድ ዘር አውጣላቸው::</u>

<u>፩</u>. ኆብሠረ⇨ <u>፪</u>. ቈረበ⇨ <u>፫</u>. ነጽሐ⇨ <u>፬</u>. ሰምዐ ⇨ <u>፭</u>. ተመክሐ⇨
ወሀበ ⇨ ዐረየ ⇨ ተዐገሠ ⇨ ተካየደ⇨ መዐደ⇨
ለበወ ⇨ ጸመወ ⇨ ጥዕየ⇨ ተደንገለ⇨ አመክነየ⇨
ተወከለ⇨ ሐለየ⇨

<u>፩.፮.ባዕድ ከምዕላድ ዘር:-</u> ቀድመው ከግሡ ያልነበሩ ባዕዳን ቀለማት በመነሻና በመድረሻ የሚጨምር ባዕድ ከምዕላድ ዘር ይባላል::

ባዕድናምዕላድ የሚሆኑ ቀለማት ከላይ በተራ ቁጥር ፩፬እና፩፭ ያሉት ናቸው::

*ምሳሌ:-* መሀረ⇨ትምህርት ቀሠፈ⇨መቅሠፍት ኀለየ⇨ማኀሌት
ኀተወ⇨ማኀቶት ጠብሐ⇨መጥባሕት ዐደወ⇨ማዕዶት
ወዐለ⇨መዐልት

<u>ምልማድ ፩.፮.:-ለሚከተሉት ግሦች ባዕድ ከምዕላድ ዘር አውጣላቸው::</u>

<u>፩</u>. ነግሠ⇨ <u>፪</u>. ሦዐ⇨ <u>፫</u>. ዐጠነ⇨ <u>፬</u>. ሣረረ⇨ <u>፭</u>. ለአከ⇨
ከፈለ⇨ አመረ⇨ ሠለሰ⇨ አሥገረ⇨ አንጦልዐ⇨
ደመረ⇨ ሠፈረ⇨

<u>፩.፯.ጥሬ ዘር</u> :- እንደ ዘመድ ዘር ባዕድ ቀለማት የማይጨምር በራብዕ ፣በኃምስ ፣በሳብዕ የሚደርስ ጥሬ ዘር ይባላል ጥሬ መባሉም ተናባቢም ሆነ ተሳቢ ሲሆን ያለምንም ለውጥ ስለምንጠቀምበት ነው::





*ምሳሌ:-* ፃመወ⇨ፃማ ቀደሰ⇨ቅዳሴ ዘመረ⇨ዝማሬ
ወደሰ⇨ውዳሴ ሰንቀወ⇨መሰንቆ ተንበለ⇨ትንባሌ
ቤዘወ⇨ቤዛ ሀለወ⇨ህላዌ ጸገወ⇨ጽጌ
ዜነወ⇨ዜና ባረከ⇨ቡራኬ

<u>ምልማድ ፩.፯.:-ለሚከተሉት ግሦች ጥሬ ዘር</u> <u>አውጣላቸው::</u>

<u>፩</u>. ሐደሰ⇨ <u>፪</u>. ወለጠ⇨ <u>፫</u>. መሐለ⇨ <u>፬</u>. ደንገፀ⇨ <u>፭</u>. ወርዘወ⇨
ተሠገወ⇨ ተወከለ⇨ ተሰፈወ ⇨ አንገለገ⇨ አስተጋብአ⇨
ዐፀወ⇨ አርኀወ⇨

<u>፩.፰.ሰያፍ ቅጽል:-</u> ሙያው ከመስም ውስጠዘ ጋር የሚመሳሰል ባዕድ ቀለም የማይጨምር ሰያፍ ቅጽል ይባላል ::

ምሳሌ:- ኀየለ⇨ኀያል ጠበበ⇨ጠቢብ ሐደሰ⇨ሐዲስ
ዐብየ⇨ዐቢይ በሴት አንቀጽና ብዙ ቁጥሩን ማየት እንችላለን:-
ሐዲስ⇨ሐዲሳት ሐዳስ⇨ሐዳሳት ጠቢብ⇨ጠቢባን
ኀያል⇨ኀያላን ኀያልት⇨ኀያላት ጠባብ⇨ጠባባት
ዐቢይ⇨ዐቢያን ዐባይ⇨ዐባያት

<u>፩.፱. መድበል:-</u> ማለት መሰብሰቢያ መከማቻ ማለት ሲሆን በብዙ ቁጥር ወንዶችም ሴቶችም የሚጠሩበት ነው:: ሁለቱንም ጾታ አጠቃሎ ስለያዘ መድበል ተብሏል:: መድበል ብሎ ነጠላ ቁጥር የለም የሣልስ ቅጽል /የሣልስ ውስጠ ዘ/ ብዙ ቁጥር ነው:: ፍቺውም አድራጊነትን የሚያሳይ ነው:: መለያ ምልክቱም መነሻውና ድኅረ መነሻው ግእዝ ቀለም መድረሻውና ቅድመ መድረሻው ሳድስ ቀለም መድረሻውን «ት» የሚደርግ ነው::

*ምሳሌ:-* ቀተለ⇨ቀተልት ነግሠ⇨ነገሥት ጠበ⇨ጠበብት
ዐብየ⇨ዐበይት ጾረ⇨ጸወርት ጸሐፈ⇨ጸሐፍት
መገበ⇨መገብት ዐቀበ⇨ዐቀብት

<u>ምልማድ፩.፰.:-</u> <u>፩</u>.ሐተተ⇨ <u>፪</u>.ሰአለ⇨ <u>፫</u>.ሰቀለ⇨ <u>፬</u>.ሰረቀ⇨
ወሀበ⇨ ወረደ⇨ ዐጸደ⇨ መሠጠ⇨

# ምዕራፍ ፮.

## ንዑስ/መለስተኛ/እርባታ

የአንቀጽ ዝርዝር በ ፲ ሩ መራሕያን ከዚያም አሥራው ቀለማትን በመጠቀም አንድን ግስ እስከ ትእዛዝ አንቀጽ ማርባት ንዑስ እርባታ ይባላል፡፡

### ፮.፩. አሥራው ቀለማት

አሥራው ቀለማት የሚባሉት “ተ” “አ” “የ” “ነ” ሲሆኑ አሥራው /ሥሮች/ መነሻዎች/ መጀመሪያዎች/ መባላቸው ከካልዓይ እስከ ትእዛዝ (በሁለተኛ መደቦች ትእዛዝ አንቀጽ ይጎርዳሉ) መነሻ በመሆናቸውና ያለ እነርሱ ግሥ ባለመርባቱ ነው፡፡ አሥራው ቀለማት እንደግሡ ዐመል ስለተፈደላቸው ግእዝ፣ ካዕብ፣ራብዕ ወይም ሳድስ ሊሆኑ ይችላሉ፡፡

**የአሥራው ቀለማት ሥርጭት /አጠቃቀም/**

ሦስተኛ መደቦች ከ “ይእቲ” በስተቀር “የ” ን በመጠቀም ግሡን እንዘረዝራለን፡፡ ሁለተኛ መደቦችና ይእቲ “ተ”ን በመጠቀም ግሡን እንዘረዝራለን ለአነ “አ” ለንሕነ “ነ” ን በመጠቀም ግሱን እንዘረዝራለን፡፡

ከዚህ ቀጥለን ንዑስ እርባታን እንጀምራለን ንዑስ እርባታ ከላይ እንደገለጽነው ግሥን እስከ ትእዛዝ አንቀጽ በ፲ሩም መራሕያን መዘርዘር ነው፡፡ ለዚሁም ባለፉት ምዕራፎች ያየናቸው የግሥ ዝርዝር በ፲ሩ መራሕያን ግሥን እስከ ትእዛዝ አንቀጽ እና ከዚያም በታች ማርባት ለንዑስ እርባታ መሠረቶች ናቸው፡፡ በዚህ ምዕራፍ አሥራው ቀለማትን ለይቶ ዘጠኙን መራሕያን እስከ ትእዛዝ አንቀጽ ማርባት ነው፡፡





### ፮.፪. የአርእስተ ግሥ መለስተኛ እርባታ

**የቀተለ ንዑስ እርባታ፡-**

| | ውእቱ | ውእቶሙ | ይእቲ | ውእቶን | አነ |
|---|---|---|---|---|---|
| ኃላፊ | ቀተለ | ቀተሉ | ቀተለት | ቀተላ | ቀተልኩ |
| ካልዓይ | ይቀትል | ይቀትሉ | ትቀትል | ይቀትላ | እቀትል |
| ዘንድ | ይቅትል | ይቅትሉ | ትቅትል | ይቅትላ | እቅትል |
| ትእዛዝ | ይቅትል | ይቅትሉ | ትቅትል | ይቅትላ | እቅትል |

| | አንተ | አንትሙ | አንቲ | አንትን | ንሕነ |
|---|---|---|---|---|---|
| ኃላፊ | ቀተልከ | ቀተልክሙ | ቀተልኪ | ቀተልክን | ቀተልነ |
| ካልዓይ | ትቅትል | ትቀትሉ | ትቀትሊ | ትቀትላ | ንቀትል |
| ዘንድ | ትቅትል | ትቅትሉ | ትቅትሊ | ትቅትላ | ንቅትል |
| ትእዛዝ | ቅትል | ቅትሉ | ቅትሊ | ቅትላ | ንቅትል |

☞ ከላይ እንዳየነው ግሡ ሲገሠሥ ቀተለ ብሎ ይቀትል ይቅትል ስላለ አሥራው ቀለማት በሁሉም መራሕያን ሳድስ ቀለም ሆነዋል፡፡

☞ ከላይ በመግቢያው እንዳየነውም በሁለተኛ መደቦች ትእዛዝ አንቀጽ አሥራው ቀለማት ተጎርደዋል፡፡

☞ የንዑስ እርባታ ንባብንም ስንመለከት የአንትን ኃላፊ አንቀጽ ብቻ ተጥሎ ሲነበብ ሌሎቹ ግን ተነስተው ይነበባሉ፡፡ አንዳንድ ጊዜ ሁለተኛ መደቦች ትእዛዝ አንቀጽ ሁለት ፊደል እና መድረሻውም ሳድስ ፊደል ከሆነ ተጥሎ ይነበባል፡፡

ምሳሌ፡- ሑር፣ ቁም፣ ጹም

## የቀደሰ ንዑስ እርባታ

| ውእቱ | ውእቶሙ | ይእቲ | ውእቶን | አነ |
|---|---|---|---|---|
| ቀደሰ | ቀደሱ | ቀደሰት | ቀደሳ | ቀደስኩ |
| ይቄድስ | ይቄድሱ | ትቄድስ | ይቄድሳ | እቄድስ |
| ይቀድስ | ይቀድሱ | ትቀድስ | ይቀድሳ | እቀድስ |
| ይቀድስ | ይቀድሱ | ትቀድስ | ይቀድሳ | እቀድስ |
| **አንተ** | **አንትሙ** | **አንቲ** | **አንትን** | **ንሕነ** |
| ቀደስከ | ቀደስክሙ | ቀደስኪ | ቀደስክን | ቀደስነ |
| ትቄድስ | ትቄድሱ | ትቄድሲ | ትቄድሳ | ንቄድስ |
| ትቀድስ | ትቀድሱ | ትቀድሲ | ትቀድሳ | ንቀድስ |
| ቀድስ | ቀድሱ | ቀድሲ | ቀድሳ | ንቀድስ |

## የገብረ ንዑስ እርባታ

| ውእቱ | ውእቶሙ | ይእቲ | ውእቶን | አነ |
|---|---|---|---|---|
| ገብረ | ገብሩ | ገብረት | ገብራ | ገበርኩ |
| ይገብር | ይገብሩ | ትገብር | ይገብራ | እገብር |
| ይግበር | ይግበሩ | ትግበር | ይግበራ | እግበር |
| ይግበር | ይግበሩ | ትግበር | ይግበራ | እግበር |
| **አንተ** | **አንትሙ** | **አንቲ** | **አንትን** | **ንሕነ** |
| ገበርከ | ገበርክሙ | ገበርኪ | ገበርክን | ገበርነ |
| ትገብር | ትገብሩ | ትገብሪ | ትገብራ | ንገብር |
| ትግበር | ትግበሩ | ትግበሪ | ትግበራ | ንግበር |
| ግበር | ግበሩ | ግበሪ | ግበራ | ንግበር |





## የአእመረ ንዑስ እርባታ

| ውእቱ | ውእቶሙ | ይእቲ | ውእቶን | አነ |
|---|---|---|---|---|
| አእመረ | አእመሩ | አእመረት | አእመራ | አእመርኩ |
| የአምር | የአምሩ | ተአምር | የአምራ | አአምር |
| ያእምር | ያእምሩ | ታእምር | ያእምራ | ኣእምር |
| እምር | ያእምሩ | ታእምር | ያእምራ | ኣእምር |
| **አንተ** | **አንትሙ** | **አንቲ** | **አንትን** | **ንሕነ** |
| አእመርከ | አእመርክሙ | አእመርኪ | አእመርክን | አእመርነ |
| ተአምር | ተአምሩ | ተአምሪ | ተአምራ | ነአምር |
| ታእምር | ታእምሩ | ታእምሪ | ታእምራ | ናእምር |
| አእምር | አእምሩ | አእምሪ | አእምራ | ናእምር |

## የብህለ ንዑስ አርባ

| ውእቱ | ውእቶሙ | ይእቲ | ውእቶን | አነ |
|---|---|---|---|---|
| ብህለ | ብህሉ | ብህለት | ብህላ | ብህልኩ |
| ይብህል | ይብህሉ | ትብህል | ይብህላ | እብህል |
| ይብሀል | ይብሀሉ | ትብሀል | ይብሀላ | እብሀል |
| ይብሀል | ይብሀሉ | ትብሀል | ይብሀላ | እብሀል |
| **አንተ** | **አንትሙ** | **አንቲ** | **አንትን** | **ንሕነ** |
| ብህልከ | ብህልክሙ | ብህልኪ | ብህልክን | ብህልነ |
| ትብህል | ትብህሉ | ትብህሊ | ትብህላ | ንብህል |
| ትብሀል | ትብሀሉ | ትብሀሊ | ትብሀላ | ንብሀል |
| በሀል | በሀሉ | በሀሊ | በሀላ | ንብሀል |

## የሤመ ንዑስ እርባታ

| ውእቱ | ውእቶሙ | ይእቲ | ውእቶን | አነ |
|---|---|---|---|---|
| ሤመ | ሤሙ | ሤመት | ሤማ | ሤምኩ |
| ይሠይም | ይሠይሙ | ትሠይም | ይሠይማ | እሠይም |
| ይሢም | ይሢሙ | ትሢም | ይሢማ | እሢም |
| ይሢም | ይሢሙ | ትሢም | ይሢማ | እሢም |

| አንተ | አንትሙ | አንቲ | አንትን | ንሕነ |
|---|---|---|---|---|
| ሤምከ | ሤምክሙ | ሤምኪ | ሤምክን | ሤምነ |
| ትሠይም | ትሠይሙ | ትሠይሚ | ትሠይማ | ንሠይም |
| ትሢም | ትሢሙ | ትሢሚ | ትሢማ | ንሢም |
| ሢም | ሢሙ | ሢሚ | ሢማ | ንሢም |

## የቆመ ንዑስ እርባታ

| ውእቱ | ውእቶሙ | ይእቲ | ውእቶን | አነ |
|---|---|---|---|---|
| ቆመ | ቆሙ | ቆመት | ቆማ | ቆምኩ |
| ይቀውም | ይቀውሙ | ትቀውም | ይቀውማ | እቀውም |
| ይቁም | ይቁሙ | ትቁም | ይቁማ | እቁም |
| ይቁም | ይቁሙ | ትቁም | ይቁማ | እቁም |

| አንተ | አንትሙ | አንቲ | አንትን | ንሕነ |
|---|---|---|---|---|
| ቆምከ | ቆምክሙ | ቆምኪ | ቆምክን | ቆምነ |
| ትቀውም | ትቀውሙ | ትቀውሚ | ትቀውማ | ንቀውም |
| ትቁም | ትቁሙ | ትቁሚ | ትቁማ | ንቁም |
| ቁም | ቁሙ | ቁሚ | ቁማ | ንቁም |





## የባረከ ንዑስ አርባታ

| ውእቱ | ውእቶሙ | ይእቲ | ውእቶን | አነ |
|---|---|---|---|---|
| ባረከ | ባረኩ | ባረከት | ባረካ | ባረኩ |
| ይባርክ | ይባርኩ | ትባርክ | ይባርክ | እባርክ |
| ይባርክ | ይባርኩ | ትባርክ | ይባርክ | እባርክ |
| ይባርክ | ይባርኩ | ትባርክ | ይባርክ | እባርክ |

| አንተ | አንትሙ | አንቲ | አንትን | ንሕነ |
|---|---|---|---|---|
| ባረከ | ባረክሙ | ባረኪ | ባረክን | ባረክነ |
| ትባርክ | ትባርኩ | ትባርኪ | ትባርካ | ንባርክ |
| ትባርክ | ትባርኩ | ትባርኪ | ትባርካ | ንባርክ |
| ባርክ | ባርኩ | ባርኪ | ባርካ | ንባርክ |

- ንዑስ እርባታውን በቀላሉ ለመረዳት መራሕያኑን እርስ በርስ ማነጻጸር:-
  - ☞ ውእቱ መሠረት ነው። ከይእቲ፣ ከአነ፣ ከአንተ እና ከንሕነ ጋር ማነጻጸር::
  - ☞ ውእቶሙን ከአንትሙ ውእቶሙን ከውእቶንጋር ማነጻጸር::
  - ☞ ውእቶንን ከአንትንጋር ማነጻጸር::
- በሠራዊት አለቆቹ እርባ መሠረት የሌሎች/ሠራዊቶቻቸውን/ ንዑስ እርባታ መስራት ይቻላል።

<u>ምልማድ ፯.፩.</u>:- ሀ.<u>ንዑስ እርባታቸውን አጥኑ።</u>

**፩.መጽአ ፪.ሀለወ ፫.ወሀበ ፬.አክበረ ፭.ዖደ .ሖረ**
**፯.ጸገወ ፰.ወደየ ፱. ጸለየ ፲ .በልዐ ፲፩ .አጥመቀ ፲፪ .ነጸረ**

## ፩.መጽአ

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ውእቱ | መጽአ | ይመጽእ | ይምጻእ | ይምጻእ |
| ውእቶሙ | መጽኡ | ይመጽኡ | ይምጽኡ | ይምጽኡ |
| ይእቲ | መጽአት | ትመጽእ | ትምጻእ | ትምጻእ |
| ውእቶን | መጽኣ | ይመጽኣ | ይምጽኣ | ይምጽኣ |
| አንተ | መጻእከ | ትመጽእ | ትምጻእ | ንዓ |
| አንትሙ | መጻእክሙ | ትመጽኡ | ትምጽኡ | ንዑ |
| አንቲ | መጻእኪ | ትመጽኢ | ትምጽኢ | ንዒ |
| አንትን | መጻእክን | ትመጽኣ | ትምጽኣ | ንዓ |
| አነ | መጻእኩ | እመጽእ | እምጻእ | እምጻእ |
| ንሕነ | መጻእነ | መጽእ | ንምጻእ | ንምጻእ |

## ፪.ሀለወ

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ውእቱ | ሀለወ | ይሄሉ | የሃሉ | የሃሉ |
| ውእቶሙ | ሀለዉ | ይሄልዉ | የሀልዉ | የሀልዉ |
| ይእቲ | ሀለወት | ትሄሉ | ተሀሉ | ተሀሉ |
| ውእቶን | ሀለዋ | ይሄልዋ | የሀልዋ | የሀልዋ |
| አንተ | ሀለውከ | ትሄሉ | ተሀሉ | ሀሉ |
| አንትሙ | ሀለውክሙ | ትሄልዉ | ተሀልዉ | ሀልዉ |
| አንቲ | ሀለውኪ | ትሄልዊ | ተሀልዋ | ሀልዊ |
| አንትን | ሀለውክን | ትሄልዋ | ተሀልዋ | ሀልዋ |
| አነ | ሀለውኩ | እሄሉ | አሀሉ | አሀሉ |
| ንሕነ | ሀለውነ | ንሄሉ | ነሀሉ | ነሀሉ |

## ፫.ወሀበ

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ውእቱ | ወሀበ | ይሁብ | የሀብ | የሀብ |
| ውእቶሙ | ወሀቡ | ይሁቡ | የሀቡ | የሀቡ |
| ይእቲ | ወሀበት | ትሁብ | ተሀብ | ተሀብ |
| ውእቶን | ወሀባ | ይሁባ | የሀባ | የሀባ |
| አንተ | ወሀብከ | ትሁብ | ተሀብ | ሀብ |
| አንትሙ | ወሀብክሙ | ትሁቡ | ተሀቡ | ሀቡ |
| አንቲ | ወሀብኪ | ትሁቢ | ተሀቢ | ሀቢ |
| አንትን | ወሀብክን | ትሁባ | ተሀባ | ሀባ |
| አነ | ወሀብኩ | እሁብ | አሀብ | አሀብ |
| ንሕነ | ወሀብነ | ንሁብ | ነሀብ | ነሀብ |





## ፬.አክበረ

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ውእቱ | አክበረ | ያከብር | ያክብር | ያክብር |
| ውእቶሙ | አክበሩ | ያከብሩ | ያክብሩ | ያክብሩ |
| ይእቲ | አክበረት | ታከብር | ታክብር | ታክብር |
| ውእቶን | አክበራ | ያከብራ | ያክብራ | ያክብራ |
| አንተ | አክበርከ | ታከብር | ታክብር | ኣክብር |
| አንትሙ | አክበርክሙ | ታከብሩ | ታክብሩ | አክብሩ |
| አንቲ | አክበርኪ | ታከብሪ | ታክብሪ | ኣክብሪ |
| አንትን | አክበርከን | ታከብራ | ታክብራ | ኣክብራ |
| አነ | አክበርኩ | ኣከብር | ኣክብር | ኣክብር |
| ንሕነ | አክበርነ | ናከብር | ናክብር | ናክብር |

## ፭.ዖደ

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ውእቱ | ዖደ | የዐውድ | ይዑድ | ይዑድ |
| ውእቶሙ | ዖዱ | የውውዱ | ይዑዱ | ይዑዱ |
| ይእቲ | ዖደት | ተዐውድ | ትዑድ | ትዑድ |
| ውእቶን | ዖዳ | የዐውዳ | ይዑዳ | ይዑዳ |
| አንተ | ዖድከ | ተዐውድ | ትዑድ | ዑድ |
| አንትሙ | ዖድክሙ | ተዐውዱ | ትዑዱ | ዑዱ |
| አንቲ | ዖድኪ | ተዐውዲ | ትዑዲ | ዑዲ |
| አንትን | ዖድክን | ተዐውዳ | ትዑዳ | ዑዳ |
| አነ | ዖድኩ | አዐውድ | እዑድ | እዑድ |
| ንሕነ | ዖድነ | ነዐውድ | ንዑድ | ንዑድ |

## .ሖረ

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ውእቱ | ሖረ | የሐውር | ይሑር | ይሑር |
| ውእቶሙ | ሖሩ | የሐውሩ | ይሑሩ | ይሑሩ |
| ይእቲ | ሖረት | ተሐውር | ትሑር | ትሑር |
| ውእቶን | ሖራ | የሐውራ | ይሑራ | ይሑራ |
| አንተ | ሖርከ | ተሐውር | ትሑር | ሑር |
| አንትሙ | ሖርክሙ | ተሐውሩ | ትሑሩ | ሑሩ |
| አንቲ | ሖርኪ | ተሐውሪ | ትሑሪ | ሑሪ |
| አንትን | ሖርክን | ተሐውራ | ትሑራ | ሑራ |
| አነ | ሖርኩ | አሐውር | እሑር | እሑር |
| ንሕነ | ሖርነ | ነሐውር | ንሑር | ንሑር |

## ፲፯.ጸገወ

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ውእቱ | ጸገወ | ይጼጉ | ይጸጉ | ይጸጉ |
| ውእቶሙ | ጸገዉ | ይጼግዉ | ይጸግዉ | ይጸግዉ |
| ይእቲ | ጸገወት | ትጼጉ | ትጸጉ | ትጸጉ |
| ውእቶን | ጸገዋ | ይጼግዋ | ይጸግዋ | ይጸግዋ |
| አንተ | ጸገውከ | ትጼጉ | ትጸጉ | ጸጉ/ጸግው |
| አንትሙ | ጸገውክሙ | ትጼግዉ | ትጸግዉ | ጸግዉ |
| አንቲ | ጸገውኪ | ትጼግዊ | ትጸግዊ | ጸግዊ |
| አንትን | ጸገውክን | ትጼግዋ | ትጸግዋ | ጸግዋ |
| አነ | ጸገውኩ | እጼጉ | እጸጉ | እጸጉ |
| ንሕነ | ጸገውነ | ንጼጉ | ንጸጉ | ንጸጉ |

## ፲፰.ወደየ

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ፲፰.ወደየ | ወደየ | ይወዲ | ይደይ | ይደይ |
| ውእቶሙ | ወደዩ | ይወድዩ | ይደዩ | ይደዩ |
| ይእቲ | ወደየት | ትወዲ | ትደይ | ትደይ |
| ውእቶን | ወዲያ | ይወድያ | ይደያ | ይደያ |
| አንተ | ወደይከ | ትወዲ | ትደይ | ደይ |
| አንትሙ | ወደይክሙ | ትወድዩ | ትደዩ | ደዩ |
| አንቲ | ወደይኪ | ትወድዪ | ትደዪ | ደዪ |
| አንትን | ወደይክን | ትወድያ | ትደያ | ደያ |
| አነ | ወደይኩ | እወዲ | እደይ | እደይ |
| ንሕነ | ወደይነ | ንወዲ | ንደይ | ንደይ |





## ፲፱. ጸለየ

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ውእቱ | ጸለየ | ይጼሊ | ይጸሊ | ይጸሊ |
| ውእቶሙ | ጸለዩ | ይጼልዩ | ይጸልዩ | ይጸልዩ |
| ይእቲ | ጸለየት | ትጼሊ | ትጸሊ | ትጸሊ |
| ውእቶን | ጸለያ | ይጼልያ | ይጸልያ | ይጸልያ |
| አንተ | ጸለይከ | ትጼሊ | ትጸሊ | ጸሊ/ጸልይ |
| አንትሙ | ጸለይክሙ | ትጼልዩ | ትጸልዩ | ጸልዩ |
| አንቲ | ጸለይኪ | ትጼልዪ | ትጸልዪ | ጸልዪ |
| አንትን | ጸለይክን | ትጼልያ | ትጸልያ | ጸልያ |
| አነ | ጸለይኩ | እጼሊ | እጸሊ | እጸሊ |
| ንሕነ | ጸለይነ | ንጼሊ | ንጸሊ | ንጸሊ |

## ፳ .በልዐ

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ውእቱ | በልዐ | ይበልዕ | ይብላዕ | ይብላዕ |
| ውእቶሙ | በልዑ | ይበልዑ | ይብልዑ | ይብልዑ |
| ይእቲ | በልዐት | ትበልዕ | ትብላዕ | ትብላዕ |
| ውእቶን | በልዓ | ይበልዓ | ይብልዓ | ይብልዓ |
| አንተ | በላዕከ | ትበልዕ | ትብላዕ | ብላዕ |
| አንትሙ | በላዕክሙ | ትበልዑ | ትብልዑ | ብልዑ |
| አንቲ | በላዕኪ | ትበልዒ | ትብልዒ | ብልዒ |
| አንትን | በላዕክን | ትበልዓ | ትብልዓ | ብልዓ |
| አነ | በላዕኩ | እበልዕ | እብላዕ | እብላዕ |
| ንሕነ | በላዕነ | ንበልዕ | ንብላዕ | ንብላዕ |

## ፲፩ .አጥመቀ

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ውእቱ | አጥመቀ | ያጠምቅ | ያጥምቅ | ያጥምቅ |
| ውእቶሙ | አጥመቁ | ያጠምቁ | ያጥምቁ | ያጥምቁ |
| ይእቲ | አጥመቀት | ታጠምቅ | ታጥምቅ | ታጥምቅ |
| ውእቶን | አጥመቃ | ያጠምቃ | ያጥምቃ | ያጥምቃ |
| አንተ | አጥመቀ | ታጠምቅ | ታጥምቅ | አጥምቅ |
| አንትሙ | አጥመቅሙ | ታጠምቁ | ታጥምቁ | አጥምቁ |
| አንቲ | አጥመቂ | ታጠምቂ | ታጥምቂ | አጥምቂ |
| አንትን | አጥመቅን | ታጠምቃ | ታጥምቃ | አጥምቃ |
| አነ | አጥመቁ | ኣጠምቅ | ኣጥምቅ | ኣጥምቅ |
| ንሕነ | አጥመቅነ | ናጠምቅ | ናጥምቅ | ናጥምቅ |

## ፲፪ .ነጸረ

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ውእቱ | ነጸረ | ይኔጽር | ይነጽር | ይነጽር |
| ውእቶሙ | ነጸሩ | ይኔጽሩ | ይነጽሩ | ይነጽሩ |
| ይእቲ | ነጸረት | ትኔጽር | ትነጽር | ትነጽር |
| ውእቶን | ነጸራ | ይኔጽራ | ይነጽራ | ይነጽራ |
| አንተ | ነጸርከ | ትኔጽር | ትነጽር | ነጽር |
| አንትሙ | ነጸርክሙ | ትኔጽሩ | ትነጽሩ | ነጽሩ |
| አንቲ | ነጸርኪ | ትኔጽሪ | ትነጽሪ | ነጽሪ |
| አንትን | ነጸርክን | ትኔጽራ | ትነጽራ | ነጽራ |
| አነ | ነጸርኩ | እኔጽር | እነጽር | እነጽር |
| ንሕነ | ነጸርነ | ንኔጽር | ንነጽር | ንነጽር |





**ለ. የሚከተሉትን ዐረፍተ ነገሮች ከተረጎምክ በኋላ አንቀጾችን ለይ።**

ምሳሌ፡- ንሕነ *ንገብር* ምዕራፈ። ትርጉም፡-እኛ ማረፊያን እንሰራለን።

- ገበርነ *ንገብር* ንግበር ንግበር ።*ንገብር* ካልዓይ አንቀጽ።

፩. አንትሙ ትከውኑ ሰማዕትየ።

፪. ማርታ ትሠርሒ ብዙኀ።

፫. ሰማያት ይነግራ ስብሐተ እግዚአብሔር።

፬.ውእቱ የሀብ ዘርአ።

፭. ውእቶሙ የዐሉ ምስሌሁ።

.አፍቅር ቢጸከ ከመነፍስከ።

፯.ይግባእ ሰላምክሙ።

፰. ምንተ ትሔልዩ።

፱. ሑር ወአፍትን ርእሰከ ለካህን።

. ጥበብ ትኄይስ እምኵሉ።

፲፩ ተንሥእ ወንሣእ ዐራተከ ወሑር።

## ሐ. አዛምድ

| ሀ | ለ |
|---|---|
| ፩.አንተ ............... | ሀ. ትምጻእ |
| ፪.አንትሙ............. | ለ. ልህቁ |
| ፫.ይእቲ................. | ሐ. እመኑ |
| ፬.ውእቶን ............. | መ. ፍጥር |
| ፭.ውእቱ................ | ሠ. እነብር |
| ፮.አንቲ................. | ረ. ጸልያ |
| ፯.አንትን............... | ቀ. ያክብራ |
| ፰.ውእቶሙ............. | በ. ንቁም |
| ፱.አነ ..................... | ተ. ማሰነ |
| .ንሕነ ................. | ወ. ንዒ |
| | ገ. የሐውጹ |

# ምዕራፍ ፯
# ቱሱሐን/ተጻይ እርባታ

ቱሱሐን የቀተለን ከቀደሰ የቀደሰን ከቀተለ የሚያደባልቁ/ የሚያለዋውጡ/ ግሦች ሲሆኑ አካሔዳቸውም በአምስት ወገን ነው::

፩. የቀተለን የባረከንና የብህለን ተገብሮ የመሰሉ በእርባታ ጊዜ ፍጹም የቀደሰን አካሔድ ይሔዳሉ::

*ምሳሌ:-*

| | | | |
|---|---|---|---|
| ተወዐረ /ወዐረ | ተዝኅረ | ተድኅረ | ተልዕለ |
| ይትዌዐር /ይዌዕር | ይዜኅር | ይዴኅር | ይትሌዐል |
| ይትወዓር / ይወዐር /የዐር | ይዘኃር | ይደኃር | ይትለዓል |
| ይትወዓር /ይወዓር /የዐር | ይዘኃር | ይደኃር | ይትለዓል |

| | | |
|---|---|---|
| ተኀየየ | ተፅዕረ | ተሥዕለ |
| ይትኄየይ | ይፄዐር | ይሤዐል |
| ይትኀየይ | ይፀዓር | ይሠዓል |
| ይትኀየይ | ይፀዓር | ይሠዓል |

፪. "ወረወ"ን "ወጠነ"ን "ፀዐለ"ን "ገረመ"ን የመሰሉ ግሦች በኀላፊ የቀተለን በትንቢት የቀደሰን ከዚያ በታች እንደገና የቀተለን አካሔድ ይሔዳሉ::

*ምሳሌ:-*

| | | | |
|---|---|---|---|
| ወረወ | ወጠነ | ፀዐለ | ገረመ |
| ይዌሩ | ይዌጥን | ይፄዕል | ይጌርም/ይገርም |
| ይውሩ | ይውጥን/ይጠን | ይፅዓል | ይግርም |
| ይውሩ | ይውጥን/ይጠን | ይፅዓል | ይግርም |





፫. "ጠፈረ"ን "ጸፈረ"ንየመሰሉ ግሦች በኃላፊ የቀደሰን በትንቢት በዘንድና በትእዛዝ የቀተለን ከዚያ በታች እንደገና የቀደሰን አካሔድ ይሔዳሉ::

| ምሳሌ:- | | |
|---|---|---|
| | ጠፈረ | ጸፈረ |
| | ይጠፍር | ይጸፍር |
| | ይጥፍር | ይጽፍር |
| | ይጥፍር | ይጽፍር |
| | ጠፍሮ/ሮት | ጸፍሮ/ሮት |

፬. "መሀረ"ን "ወገረ"ን የመሰሉ ግሦች በኃላፊ ፍጹም የቀተለ ሲሆኑ በአንድ ቃል ሁለት ነገር እየፈቱ በአንድ ፍቺ የቀደሰን በሁለተኛው ፍቺ ደግሞ የቀተለን እርባታ አካሔድ ይሔዳሉ::

*ምሳሌ:-*

| | | | |
|---|---|---|---|
| መሀረ (አስተማረ) | መሐረ(ራራ ይቅር አለ) | ወገረ(መታ) | ወገረ(ዕጣን አሳረገ) |
| ይሜህር | ይምሕር | ይዌግር | ይወግር |
| ይምሀር | ይምሐር | ይገር | ይውግር |
| ይምሀር | ይምሐር | ይገር | ይውግር |

## ተጨማሪ:-

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ሥኀተ(አሳረፈ) | ስሕተ(ሳተ) | ቀሠመ(አጣፈጠ) | ቀሰመ(ለቀመ) | ኀየሰ(ተሻለ) | ኄሰ(ነቀፈ) |
| ይሜኅት | ይስሕት | ይቄሥም | ይቀስም | ይኄይስ | የኀይስ |
| ይሥኀት | ይስሐት | ይቀሥም | ይቅስም | የኀይስ | ይኂስ |
| ይሥኀት | ይስሐት | ይቀሥም | ይቅስም | የኀይስ | ይኂስ |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ቀረበ(ቆረበ) | ቀርበ(ቀረበ) | ወሀከ(አነሳሳ/አስቆጣ) | ሆከ(አወከ) | ረዐየ(ጠበቀ) | ርእየ(አየ) |
| ይቄርብ | ይቀርብ | ይዌህክ | የሀውክ | ይሬዒ | ይሬኢ |
| ይቀርብ | ይቅርብ | የሀክ | ይሁክ | ይርዓይ | ይርአይ |
| ይቀርብ | ይቅርብ | የሀክ | ይሁክ | ይርዓይ | ይርአይ |

፭. በአንድ ቃል ሁለት እየፈቱ በመጥበቅ የቀደሰን በመላላት የቀተለን የሚሆኑ ግሦች ናቸው።

*ምሳሌ፡-*

| መልሐ(አጣፈጠ) | መልሐ(መዘዘ) | ሰብሐ(አመሰገነ) | ሠብሐ(ሰባ) | ሰበከ(ቀረጸ) | ሰበከ(አስተማረ) |
|---|---|---|---|---|---|
| ይሜልሕ | ይመልሕ | ይሴብሕ | ይሠብሕ | ይሴብክ | ይሰብክ |
| ይመልሕ | ይምላሕ | ይሰብሕ | ይሥባሕ | ይሰብክ | ይስብክ |
| ይመልሕ | ይምላሕ | ይሰብሕ | ይሥባሕ | ይሰብክ | ይስብክ |

| ጸብሐ(ገበረ) | ጸብሐ(ነጋ) | ፈፀመ(ጨረሰ) | ፈጸመ(ዘጋ) | መከረ(ፈተነ) | መከረ(መከረ) |
|---|---|---|---|---|---|
| ይጼብሕ | ይጸብሕ | ይፌፅም | ይፈጽም | ይሜክር | ይመክር |
| ይጸብሕ | ይጽባሕ | ይፈፅም | ይፍጽም | ይመክር | ይምክር |
| ይጸብሕ | ይጽባሕ | ይፈፅም | ይፍጽም | ይመክር | ይምክር |

| ሐለየ(አሰበ) | ኀለየ(ዘመረ) | ጸለለ(ጋረደ) | ጸለለ(ሰፈፈ) | ሠርሐ(አሠለጠነ) | ሠርሐ(ደከመ) |
|---|---|---|---|---|---|
| ይሔሊ | የኀሊ | ይጼልል | ይጸልል | ይሜርሕ | ይሠርሕ |
| የሐሊ | ይኀሊ | ይጸልል | ይጽልል | ይሠርሕ | ይሥራሕ |
| የሐሊ | ይኀሊ | ይጸልል | ይጽልል | ይሠርሕ | ይሥራሕ |

| ነስሐ(ተጸጸተ) | ነሥሐ(ከረፋ/ሸተተ) | መሰለ(በምሳሌ ተናገረ) | መሰለ(በመለክ መሰለ) |
|---|---|---|---|
| ይኔስሕ | ይነሥሕ | ይሜስል | ይመስል |
| ይነስሕ | ይንሣሕ | ይመስል | ይምስል |
| ይነስሕ | ይንሣሕ | ይመስል | ይምስል |





## ምዕራፍ ፰

## ተመኵሳይያን

ተመኩሳይያን የሚለው የግእዝ ቃል መኩስየ ሞክሸ ኾነ በስም ተባበረ ከሚለው የግእዝ ግስ የወጣ ሲሆን ተመኩሳይያን ማለት ሞክሸ የሆኑ ማለት ነው። በስዋሰው ግእዝ ትምህርታችንን ተመኩሳይያን ብለን የምናያቸው ሞክሸ የሆኑ ቃላትን ነው። እኒህም በአራት ይከፈላሉ እነርሱ፡-

### አንደኛ ተመኵሳይያን

አንደኛ ተመኵሳይያን በምሥጢር የማይገናኙ እየራሳቸው የቆሙ ሲሆኑ አድራጊ፣ አስደራጊ ፣ተደራጊ የመሰሉ ተመኵሳይያን ናቸው:: ጥቂቶቹን ለማሳየት:-

☞ በእንተ እለ ይሠርሑ ከመ ትባርክ ፍሬ ተግባሮሙ:: ሠርሐ - ደከመ ፣ ሠራ

- ስለሚደክሙ/ስለሚሠሩ የሥራቸውን ፍሬ እንድትባርክ::

☞ አርትዕ ተሠራሕ ወንገሥ:: ተሠርሐ - ተከናወነ

- በቅንነትና በመከናወን ንገሥ::

☞ ተባጽሖታ ለልብ ምስለ እግዚአብሔር ሠናይ ወሕይወት:: ተባጽሐ - ተመላለሰ

- የልብ ከእግዚአብሔር ጋር መመላለስ ያማረና ሕይወት ነው::

☞ በጽሐ ጊዜ ዘርእ ለዘሪእ:: በጽሐ - ደረሰ

- ለሚዘራ የዘር ጊዜ ደረሰ::

☞ ይስእሉ ኀበ እግዚአብሔር ሲሳዮሙ:: ሰአለ - ለመነ

- ከእግዚአብሔር እንጀራቸውን ይለምናሉ::
  - ☞ ወተስእልዎ ወይቤልዎ በእፎ እንከ ታጠምቅ ለእመ ኢኮንከ ክርስቶስሃ:: ተስእለ - ጠየቀ
- ክርስቶስን ካልሆንክ እንግዲህ ስለምን ታጠምቃለህ ብለው ጠየቁት::
  - ☞ ዘይስሕል ሰይፈ ለቢጹ ይትቀተል ቦቱ ለሊሁ:: ሰሐለ - ሳለ
- ለባልንጀራው ሰይፍን የሚስል በሳለው ሰይፍ እርሱ ራሱ ይገደልበታል::
  - ☞ ተሠሐለኒ እግዚኦ በከመ ዕበየ ሣህልከ:: ተሠሐለ - ይቅር አለ
- አቤቱ እንደቸርነትህ ብዛት ይቅር በለኝ::
  - ☞ ረዐይኬ አባግዐየ:: ረዐየ - ጠበቀ
- በጎቼን ጠብቅ::
  - ☞ አስተርአየ በሥጋ ሰብእ ወጸድቀ በመንፈስ ወአስተርአዮሙ ለመላእክት::አስተርአየ - ታየ ተገለጠ
- የሰውን ሥጋ ለብሶ ተገለጠ በመንፈስ ጸደቀ ለመላእክት ታያቸው/ ተገለጠላቸው::
  - ☞ ምሕረተ ወፍትሐ አኀሊ ለከ:: ኀለየ - ዘመረ
- ምሕረትንና ፍርድን እንድታደርግልኝ አውቄ እዘምርልሃለሁ::
  - ☞ አሕለይኪዮሙ ይምጽኡ ኀቤኪ:: አሕለየ - መማለጃ ተቀበለ
- ወደአንቺ ይመጡ ዘንድ መማለጃን ተቀበልሻቸው::

  ይነሥእ ደቂቅክሙ ወይሬስዮሙ ሐራሁ ወወዓሊሁ::

  ነሥአ - ወሰደ
- ልጆቻችሁን ይወስዳል ወታደሮቹና ባለሟሎቹ ያደርጋቸዋል::
  - ☞ ይትነሣእ እግዚአብሔር ወይዘረዉ ፀሩ:: ተንሥአ - ተነሣ
- እግዚአብሔር ይነሣ ጠላቶቹም ይበተኑ::





- ☞ ዘይሜህሮሙ ለሰብእ ጥበበ:: መሀረ - አስተማረ
- ለሰው ልጆች ጥበብን የሚያስተምራቸው::
  - ☞ ያምሕሩኒ እሉ ሰብእ ናሁ ሣልሶሙ ወአልቦሙ ዘይበልዑ:: አምሐረ - አሳዘነ
- እነሆ ሦስተኛቸው ነው የሚበሉት የላቸውምና እኒህ ሰዎች ያሳዝኑኛል::
  - ☞ አስተምሕር ለነ ሚከኤል:: አስተምሐረ - ለመነ ማለደ
- ሚካኤል ለምንልን/አማልደን::
  - ☞ ወእመሰ ዔው ለስሐ በምንትኑ ይቄሥምዎ::ቀሠመ -አጣፈጠ
- ጨው አልጫ ቢሆን እንግዲህ በምን ያጣፍጡታል::
  - ☞ በከመ ሐሰበ ወአስተቀስመ ለአማስኖቶሙ:: አስተቀስመ - ተተነኰለ
- እንደ ቈጠረ ለጥፋታቸው ተተነኰለ/አምዋረተ::
  - ☞ ወጸለለ ዝክቱ ኀፂን ማኀዔ ላዕለ ማይ:: ጸለለ - ሰፈፈ
- ይህ የብረት መጥረቢያ በወሃ ላይ ተንሳፈፈ::
  - ☞ ረከበ ዕፅ ፅፍቅተ ወአጽለለ ከመ ያዕርፍ ንስቲተ::

    አጽለለ - ተጸጋ አረፈ
- ለጥላ የሚሆን እንጨት አገኘና ትንሽ ያርፍ ዘንድ ተጸጋ::
  - ☞ ይመልእ ወይን ኵሉ ዝቅ:: መልአ - መላ
- እንስራ/ማድጋ ሁሉ ወይን ይመላል::
  - ☞ ራትዓን የሐውሩ ወያሜልዑ ቅድመ:: አመልዐ -መራ ወደፊት ሔደ
- ቅኖች በፊት እየመሩ ይሔዳሉ::

## ሁለተኛ ተመኵሳይያን

- ሁለተኛ ተመኵሳይያን በአንድ ቃል ሁለት ነገር እየፈቱ በመጥበቅ የቀደሰ በመላላት የቀተለ የሚሆኑ ግሦች ናቸው::
  - ☞ እስመ ለኵሉ በእሳት ይሜልሕዎ ወኵሉ ዘይጠባሕ ይትሜላሕ በዔው::
- ሁሉን በእሳት ያጣፍጡታል የሚታረደውም ሁሉ በጨው ይጣፍጣል( ይቀሰማል )
  - ☞ ወእመሰ ኢተመየጥክሙ ሰይፎ ይመልሕ::
- ካልተመለሳችሁ ሰይፉን ይመዛል::
  - ☞ ተሰአል ኀበ እግዚአብሔር እመ ይሜርሐነ ፍኖተነ እንተ ነሐውር ውስቴታ ንሕነ::
- በውስጧ ስለምንሔድባት መንገዳችን ያቀናልን ዘንድ/እንዲያቃናልን ወደ እግዚአብሔር ጠይቅ::
  - ☞ ይሜርሕ እግዚአብሔር ፍናዊሁ::
- እግዚአብሔር መንገዱን ያቀናል::
  - ☞ ይሜርሐከ በኵሉ ግብርከ ::
- በሥራህ ሁሉ ያቀናልሀል::
  - ☞ ይሰርሕ እስከ ያገርር ተያፍኒሁ::
- ወይፈኑን እስኪያሰለጥን/እስኪመራ/ይደክማል::
  - ☞ ወይሴብሑ ለስሙ በትፍሥሕት ::
- በደስታ ስሙን ያመሰግናሉ::
  - ☞ ዘሰብሐ ትጠብሑ ወትበልዑ ወባሕቱ ኢረዐይክሙ አባግዒሁ::
- የሰባውን ታርዳላችሁ ትበሉማላችሁ ነገር ግን በጎቹን አልጠበቃችሁም::





- ☞ መሐለ እግዚአብሔር በጽድቅ ወኢይኔስሕ::
- እግዚአብሔር በእውነት ማለ አይጸጸትም::
  - ☞ እሬኢ ንስንተ ሥጋየ ከመ ብሕባሔ አንበሳ::
- እንደ አንበሳ ክርፋት የሥጋዬን መሸተት አያለሁ::
  - ☞ እንተ ጸብሐት ኢትወልጥ ዐርከ::
- በነጋ በጠባ ባልንጀራ አትለውጥ::
  - ☞ እለ ፍሬ ይጼብሑ ለቅዱሳት አብያተክርስቲያናት::
- ለቅዱሳት አብያተክርስቲያናት ፍሬ ይገብራሉ::
  - ☞ ይሜስሉ ሳዕሌክሙ ምሳሌ::
- ምሳሌ ይመስሉባችኋል::
  - ☞ ይመስሎ ዝንቱ ወልድ ለጠቢት::
- ይህ ልጅ ጦቢትን ይመስላል/ይመስለዋል::
  - ☞ ወይዔቅም ቃሎ በውስተ ፍትሕ::
- በፍርድ ቃሉን ፈጸመ::
  - ☞ አቀውም ገጽየ ላዕለ ይእቲ ነፍስ::
- በዚያች ነፍስ ፊቴን እመልሳለሁ::
  - ☞ ኵሉ ዘነበብኩ ላዕለ ዔሊ ወላዕለ ቤቱ እእኀዝዚ ወእፌጽም::
- በዔሊ እና በቤቱ ላይ የተናገርኩትን ሁሉ እጀምራለሁ እጨርሳለሁ::
  - ☞ ፈጸመ አፈ አናብስት::
- የአንበሶችን አፍ ዘጋ::
  - ☞ ከመ ይፈጽም/ይፌጽም/ አናቅጺሃ::
- በሮቿን እንዲዘጋ::
  - ☞ ይፌጽሞሙ አፉሆሙ ለጠቢባን::

  የጥበበኞችን አንደበት ይዘጋል::
  - ☞ አብድ ይትናገር በዕበድ ወልቡ ከንቶ ይኄሊ::

- ሰነፍ በስንፍና ይናገራል ልቡም ከንቱን /ብላሽ/ነገርን ያስባል::
    - ☞ ልበ ወሀቦሙ በዘይኄልዩ::
- የሚያስቡበት/ያስቡበት ዘንድ/ ልብን ሰጣቸው::
    - ☞ ተፋቅሮ ኢያኄሊ እኩየ::
- መዋደድ/ፍቅር/ ክፉን አያሳስብም::
    - ☞ ንኅሊ ማኅሌተ መንፈሳዊተ::
- መንፈሳዊ የሆነች ጨዋታን እንጫወት::
    - ☞ ኀልዩ ለእግዚአብሔር በጸናጽል::
- ለእግዚአብሔር በጸናጽል ዘምሩ::

## ሦስተኛ ተመኩሳይያን

- ሦስተኛ ተመኩሳይያን በአንድ ቃል/ድምፅ/ ተነበው በብዙ ነገር የሚፈቱ ግሦች ናቸው::
    - ለስሐ:-በ፳ ይፈታል
    - ☞ ወእመሰ ዔው ለስሐ በምንት እንከ ይቄስምዎ::
- ጨው አልጫ ከሆነ እንግዲህ በምን ያጣፍጡታል::
    - ☞ ዘነበበ ዘከመ ረከበ ያለስሕ ርእሶ::
- እንዳገኘ የሚያወራ ራሱን ያስነውራል::
    - ☞ እግዚአብሔር ያልስሕክሙ ኦ አጋንንት::
- አጋንንት ሆይ እግዚአብሔር ያድክማችሁ::
    - መልሐ:-በ፮ ይፈታል ጥቂቶቹም
    - ☞ ወለእመ ትቤልዋ ለዛቲ ሰግላ ተመልኂ እምሥርውኪ ወተወረዊ ውስተ ባሕር ይከውን በከመ ነበብክሙ::
- ይህችን ሾላ ከሥርሽ ተነቀዪና ወደ ባሕር ተጨመሪ ብትሏት እንዳላችሁት ይሆናል::
    - ☞ ለእመ ዓይንከ ዘየማን ታስሕተከ ምልኀወግድፋ::
- ቀኝ ዓይንክ ብታስትህ አውጣትና ጣላት::





- ☞ አልቦሙ ምልሕ ወኢሃይማኖት::
- ምግባርም ሃይማኖትም የላቸውም::
    - ☞ እምቅድመ ይትመልጉ መባርቅት ህልው ውእቱ በህላዌሁ::
- መብረቆች ከመወርወራቸው በፊት በአኗኗሩ ኗሪ ነው::
    - ረስሐ:-በ፬ ይፈታል ጥቂቶቹም
    - ☞ ልብሱ ለእመ ረስሐ ኢየኀጽብ::
- ልብሱ ቢያድፍ አያጥብም::
    - ☞ አሌ ሎቱ ዘአርስሐ ሥጋሁ በፍትወተ ዝሙት::
- ሥጋውን በዝሙት ያረከሰ ወዮለት::
    - ☞ ብሩር ርሱሕ::
- የዛገ ብሮች::
    - ☞ ወዘሰ ቀተለ ረስሐ ውእቱ ለኰነኔ::
- የገደለ በደለ ለፍርድ::
    - ሰብሐ:- በ፳ ይፈታል ጥቂቶቹም
    - ☞ ወተሰብሐ ኀብረ ገጹ ለሙሴ::
- የሙሴ የፊቱ ገጽ አበራ::
    - ☞ ሰብሖ ለምሕረትከ እግዚኦ::
- አቤቱ ምሕረትህን ግለጸው::
    - ☞ ሰብሐኒ በቅድመ ሊቃውንቲሆሙ ለእስራኤል::
- በእስራኤል አለቆች ፊት አክብረኝ::
    - ☞ በአይ ሞት ሀለዎ ይሴብሖ ለእግዚአብሔር::
- በምን ዓይነት ሞት እግዚአብሔርን ያገለግለው እንዳለው::
    - ነፍሐ:- በ ፩ ይፈታል
    - ☞ ወነፍሐ ዲበ ገጹ መንፈሰ ሕይወት::
- የሕይወት እስትንፋስ በፊቱ እፍ አለ::
    - ☞ ወነፍሐ ነፋሰ አዜብ::

- የደቡብ ንፋስ ነፈሰ፡፡
    - ☞ ንፍሑ ቀርነ በዕለተ ሠርቅ፡፡
- በመባቻ ቀን መለከት ንፉ፡፡
    - ☞ ዘተነፍሐ ከርሡ፡፡
- ሆዱ የተነፋ፡፡
    - ጸብሐ፡-በ፬ ይፈታል ጥቂቶቹም
        - ☞ ወታወፅኡ ጸባሕቶ ለእግዚአብሔር፡፡
- ለእግዚአብሔር መባውን ታወጣላችሁ፡፡
    - ☞ ወአጽሐፈ ኵሎ ብሔሮ ከመ የሀቡ ጸባሕተ ለፈርዖን፡፡
- ለፈርዖን ግብርን ይሰጡ ዘንድ አገሩን ሁሉ አስጻፈ፡፡
    - ☞ ዘጸብሐ ምስሌየ እዴሁ ውስተ መጽብሕ ውእቱ ያገብአኒ፡፡
- እጁን ከእኔ ጋር ከወጨት የሚጠልቅ እሱ ያሲዘኛል፡፡
    - ፈትሐ፡-በ፱ ይፈታል ጥቂቶቹም
        - ☞ ፈነወ ንጉሥ ወፈትሖ፡፡
- ንጉሥ ላከና ፈታው፡፡
    - ☞ ወተፈትሐ አዕይንቲሆሙ፡፡
- ዓይኖቻቸው ተከፈተ፡፡
    - ☞ ፍትሖሙ ለአሕዛብ ከመ ይሑሩ፡፡
- አሕዛብ እንዲሔዱ አሰናብታቸው፡፡
    - ☞ ወፈትሑ ከብዶ ለዓሣ፡፡
- የዓሣውን ሆዱን ቀደዱ፡፡
    - ☞ ወተፈትሐ ማይ ዘረግዓ፡፡
- የረጋው ወሃ ሟሟ፡፡
    - መሰለ፡-በ ፫ ይፈታል ጥቂቶቹ
        - ☞ ገለፎ ወመሰሎ በአምሳለ ሰብእ፡፡





- በሰው አምሳል ጣዖት ሠራ፡፡
    - ☞ ይመስሎ ዝንቱ ወልድ ለጦቢት፡፡
    - ይህ ልጅ ጦቢትን ይመስለዋል፡፡
        - ከለለ፡- በ፬ ይፈታል ጥቂቶቹም
        - ☞ ወይኬልልዎ ለመድኃኔ ዓለም፡፡
- መድኃኔ ዓለምን ያመሰግኑታል፡፡
    - ☞ ወክሉል ዓውዱ በእሳት፡፡
- አደባባዩ በእሳት የታጠረ ነው፡፡
    - ☞ ዘይኬልለከ በሣህሉ ወበምሕረቱ፡፡
- በቸርነቱና በይቅርታው ይከብብሃል፡፡
    - ☞ ወከለልዎ ክሣዶ፡፡
- አንገቱን ቆረጡት፡፡
    - ጸለለ፡- በ ፬ ይፈታል ጥቂቶቹም
        - ☞ ናሁ ደመና ብሩህ ጸለሎሙ፡፡
- እነሆ ብሩህ ደመና ጋረዳቸው፡፡
    - ☞ ይጼልለከ በገበዋቲሁ፡፡
- በጎኖቹ ይሠውርሃል፡፡
    - ☞ ወተጸለለ ልቦሙ በኢያእምሮ፡፡
- ልባቸው ባለማወቅ ተሸፈነ፡፡
    - ☞ ወመንፈሰ እግዚአብሔር ይጼልል መልዕልተ ማይ፡፡
- የእግዚአብሔር መንፈስ በውሃ ላይ ይሠፋል፡፡
    - ኀተመ፡- በ ፲፩ ይፈታል ጥቂቶቹም
        - ☞ በምጽአትከ ተኀትመ አበሳ፡፡
- በመምጣትህ በደል ጠፋ፡፡
    - ☞ ወይትኀተም ታቦት በሜሮን፡፡

- ታቦት በሜሮን ይቀባል::
    - ☞ ወንተሞ በመንኮብያቲሁ::
- በአውራ ጣቱ ባረከው::
    - ሜመ:-በ፵ ይፈታል ጥቂቶቹም
        - ☞ ወውስተ ፀሐይ ሜመ ጽላሎቶ::
- ጸዳሉን በክበቡ አኖረ/ገለጸ/አሳየ::
    - ቆመ:-በ፻ ይፈታል ጥቂቶቹም
        - ☞ ሰሎሞን ቆመ በመንበረ አቡሁ::
- ሰሎሞን በአባቱ መንበር ተተከ/ነገሠ::
    - ☞ ያቀውም ደብተራሁ::
- ድንኳኑን ይተክላል::
    - ፈጸመ:-በ፹ ይፈታል ጥቂቶቹም
        - ☞ ወገጹ ዘፍጹም በጽልመት::
- ፊቱ በጨለማ የተሸፈነ::
    - ☞ ፈፀሙ እዘኒሆሙ::
- ጆሮአቸውን ደፈኑ::
    - መሀረ:-በ፴ ይፈታል ጥቂቶቹም
        - ☞ ወኵሎ አሚረ ይምሕር ወይሌቅሕ::
- ሁልጊዜ ያበድራል ይመጸውታል::
    - መከረ:-በ፷ ይፈታል
        - ☞ ኢታመክሮ ለእግዚአብሔር አምላክከ::
- እግዚአብሔር አምላክህን አትፈትነው::
    - ☞ ተማከሩ ሊቃነ ከህናት ከመ ይቅትልዎ::
- የካህናት አለቆች ይገድሉት ዘንድ ተማከሩ::
    - ጸፈረ:-በ፺ ይፈታል ጥቂቶቹም





- ☞ ትላጽያ ርእሳ ወትዔፍራ::
- ራሷን ትላጫታለሽ ጥፍሯንም ትቆርጫታለሽ::
    - ☞ ወጸፈሩ ሐራ አክሊል ዘሦክ::
- ወታደሮች የሾህ አክሊል ጎነጎኑ::
    - ☞ ወአኮ በተፀፍሮ ስእርቶን::
- ሹርባ በመሠራት አይደለም::
    - ኮነ በ ፳ ይፈታል ጥቂቶቹም
        - ☞ ወኮኑ አበዊሃ ለኢየሩሳሌም::
- የኢየሩሳሌም አባቶቿ አለቁ::
    - ☞ ወኮነ እምድንግል በሥጋ::
- ከድንግል በሥጋ ተወለደ::
    - ☞ ወኮነ አቤል በእደ ቃየል::
- አቤል በቃየል እጅ ሞተ::
    - ☞ ወኮነ ሳኦል ላዕለ እስራኤል::
- ሳኦል በእስራኤል ላይ ነገሠ::
    - ባረከ:-በ ፪ ይፈታል
        - ☞ ወባረከ ኢዮብ ለዕለተ ልደቱ::
- ኢዮብ የተወለደበትን ቀን ረገመ::
    - ወደየ:-በ፮ ይፈታል
        - ☞ ኢትደይ ዕቅፍተ ቅድመ ዕውር::
- በዓይነ ስውር ፊት እንቅፋት አታድርግ::

## አራተኛ ተመኵሳይያን

አራተኛ ተመኵሳይያን ከአገባብ ከነባር ከዘር የሚገኙ በንባብ አንድነት በነገር ልዩነት ያላቸው ቃላት ናቸው::አካሔዳቸውም በአራት ወገን ነው::

**፩. በእርባ ጊዜ በፊደል ፍጹም አንድ ይሆናሉ በአመጣጥና በምሥጢር ይለያሉ::**

*ምሳሌ፡-* ውእቱ ይእቲን ሲዘረዝር እና የውእቶን እርባ::

አእመራ - አወቃት        ውእቶን ሲያውቁ   አእመራ - አወቁ

የአምራ -- ያውቃታል                     የአምራ - ያውቃሉ

ያእምራ - ያውቃት ዘንድ                   ያእምራ - ያውቁ ዘንድ

ያእምራ - ይወቃት                        ያእምራ - ይወቁ

- ኢይመውት - እሱ አይሞትም::
- መሐለ ሳኦል ወይቤ ሕያው እግዚአብሐር ከመ ኢይመውት ዳዊት:: ሳኦል ማለ እንዲህ ብሎ ሕያው እግዚአብሔርን ዳዊት እንዳይሞት::
- ኢይመውት - እኔ አልሞትም::
- ኢይመውት ዘእንበለ ዘአሐዩ::    አልሞትም እድናለሁ እንጂ::
- ኢትመውት - እርሷ አትሞትም
- ኢትመውት - አንተ አትሞትም

**፪.ነባር ከአገባብ ተዋርሰው የሚገኙበት በፊደል ተመሳሳይ ቢሆኑም በመጥበቅና በመላላት ይለያያሉ::**

*ምሳሌ፡-* እም - ሲጠብቅ ትርጉሙ እናት

አልቦ አብ ወአልቦ እም::





እም ሲላላ ትርጉሙ ከ

ወጽአ ትእዛዝ እም ኀበ ቄሣር::

ከመዝ - እንዲህ     ከመዝ - የወሃ እናት

እምነ - እናታችን     እምነ - ከ

ሀሎ  - አለ::           ሐሎ - የሰው ስም

ዘር ከአገባብ ተዋርሰው የሚገኙበት በፊደል ተመሳሳይ ቢሆኑም በመጥበቅና በመላላት ይለያያሉ::

እመኒ - ቢ ::        ዘየአምን ብየ እመኒ ሞተ የሐዩ::

እመኒ - እመኝ ::      ለምንት ትቴክዚ ነፍስየ ወለምንት ተሀውክኒ እመኒ በእግዚአብሔር::

**፫. ዘር ከዘር ነባር ከዘር በፊደል አንድ በንባብ በመጥበቅና በመላላት የሚለዩ ቃላት**

*ምሳሌ፡-* ዘርከዘር ፡-ስቡሕ - ምስጉን::  ውስተ ቅዱሳኒከ ተንድር ስቡሐ እስራኤል::

ስቡሕ - የሰባ:: ወባቲ ይእቲ ብእሲት ዕጓለ ላህም ስቡሕ ውስተ ቤታ ወጠብሐቶ ፍጡነ::

ምሳሌ፡-ዘር ከነባር ነባር ከዘር

ማዕበል - ማዕበል::   ኵሉ ማዕበልከ ወሞገድከ እንተ ላዕሌየ ኀለፈ::

ማዕበል - ሰይፍ በምሥጢር ብልጭታ:: በብርሃነ መዐበልከ የሐውሩ::

ማዕበል - አክሊል::       ወትገብር ውስቴቱ ማዕበል ዘወርቅ::

ዐፀድ   - ዙሪያ::        ስግዱ ለእግዚአብሔር በዐፀደ መቅደሱ::

ዐፀድ - ቦታ::    ዐፀደ ወይን ኮነ ለሰሎሞን በብዔላሞን::

ዐፀድ - አጫጆች::  እብሎሙ ለዐፀድ ርእዩ ቅድመ ክርዳደ::

ቅሡም - የተለቀመ::   አሌ ሊተ እስመ ኮንኩ ከመ ወይን ቅሡም እምድኅረ ማዕረር::

ቅሡም - የጣፈጠ::   ተግሣጽ ጥዑም ወዜና ቅሡም ከመ ዔው::

ቅሣሜ - ሟርት:: ሕልም ወሰገል ወመቃሥም ከንቱ ኵሎሙ::

ቅሣሜ - ዓይነት/ፍጥረት::  እምፅቡር ብሕባሔከ ከማየ ወእምኔሁ ቅሣሜነ::

## ፬. ከዘርና ከነባር የሚወጡ በፊደልና በንባብ አንድ እየሆኑ በብዙ ነገር የሚፈቱ ቃሎች ናቸው::

መቅድሐ እዝን::ጆሮ መበሻ::

መቅድሕተ እሳት ይክዕው ላዕሌሆሙ:: የእሳት ፍምን በላያቸው ላይ ይደፋል/ያፈሳል::

ምቅዳሐ ፈውስ ወአዘቅተ በረከት:: የፈውስ መቅጃ የበረከት ጉድጓድ::

ትከውን ምቅዳሐ ለኵሉ ነገሥተ ዓለም:: ለዓለም ነገሥታት ሁሉ ጥቅም/እርባታ ትሆናለህ::

ቅዳሕ ወይኖ:: ወይኑን ቅዳ::

ትትነበብ ዛቲ ቅዳሕ እመዝሙር:: ከመእሙር ያች ክፍል ትነበባለች::

ዐቃቢሁ ለቀምሕ ይሬኢ ፍሬሁ:: አዝመራውን የሚጠብቅ ፍሬውን ያያል::

ይብልዑ ዕፀ ወቀምሕ:: የእንጨትን ፍሬ ይብሉ::

ይቀምሕ አንበሳ ሐሠረ ከመ ላሕም:: እንደ ላም አንበሳ አሠር ይበላል::

ወአዝነመ ሎሙ መና ይብልዑ:: ይበሉ ዘንድ መና አዘነመላቸው/አወረደላቸው::

ንሣእ መና ምስሌከ ወሑር ተቀበሎ:: ከአንተ ጋር እጅ መንሻ ውሰድና ሒደህ ተቀበለው::





# ምዕራፍ ፱.
# አዕማድ

አዕማድ የሚለው ቃል ዐመደ ደገፈ ከሚለው ግሥ የወጣ ሲሆን አዕማድ ማለት ደጋፊዎች ማለት ነው። አዕማድ የሚባሉት አምስቱ አርዕስቶች ማለትም አድራጊ፣ አስደራጊ፣ አደራራጊ፣ ተደራጊ፣ ተደራራጊ ዐምድ ሲሆኑ ለግሥ እርባታ መነሻና መቋቋሚያ ስለሆኑ አዕማድ ተብለዋል። ግሥ ሁሉ ገቢር እና ተገብሮ ተብሎ በሁለት ይከፈላል።

*ገቢር ግስ፦* ማለት ተሳቢና ተቀባይ ያለው ተሻናገሪ ግስ ሲሆን ሥራው ከአድራጊ ወደ ተደራጊ የሚያልፍ እና በተደራጊ ላይ የሚፈጸም ነው።

ምሳሌ ፩፦ አብ ጸውዐ መልደ። አባት ልጁን ጠራ።

ጸውዐ ገቢር ግሥ ወልደ ተሳቢ

፪፦ አየለ ቀተለ ከይሴ። አየለ እባብን ገደለ።

ቀተለ ገቢር ግሥ ከይሴ ተሳቢ

*ተገብሮ ግስ፦* ማለት ተሳቢ የሌለው የማይሻገር ግስ ሲሆን ሥራው ከአድራጊው የማይወጣ በአድራጊው ላይ ብቻ የሚፈጸም ነው።

ምሳሌ ፩፦ ተጸውዐ ወልድ። ልጅ ተጠራ

ተጸሑዐ ተገብሮ ግሥ ወልድ ስም

ከዚህም በተጨማሪ ገቢርም ተገብሮም ግስ ያልሆነ ዐጉል ግስ አለ። ዐጉል ግስ ተሳቢ የሌለው ሥራው ከአድራጊው የማይወጣ በአድራጊው ላይ ብቻ የሚፈጸም ነው። ይህም ተገብሮ ግስ ያስመስለዋል ነገር ግን ተገብሮ ግሥ አንድ ዐጉል ግስ ተሳቢ የሌለው ሲሆን ገባሪ ሊኖረው ይችላል። ዐጉል ግስግን ገባሪ የለውም።

ምሳሌ:- ተቀትለ ተገብሮ ግሥ ሲሆን ቀተለ ገባሪ ግሥ ነው።

ሞተ ዐጉል ግስ ሲሆን ገባሪ ግስ የለውም።

ምሳሌ:- ተጸሑዐ ተገብሮ ግስሲሆን ጸውዐ ገባሪ ግስነው

ወርዘወ ዐጉል ግሥ ሲሆን ገባሪ ግስ የለውም።

በአጠቃላይ ከላይ እንደገለጽነው ግሥ ሁሉ ገቢር እና ተገብሮ ተብሎ በሁለት ይከፈላል፡፡ ዐጉል ግሥ ምንም ተገብሮ ግሥ ባይሆን ቁጥሩ ከተገብሮ ግሥ ነው፡፡

**የገቢር ግሶች ምሳሌ፡-** ኀደገ፣ ጸሐፈ፣ኀጥአ፣ ፈነወ፣ ለበወ፣ ለመደ፣ ሐለመ፣ሐሰወ፣ መነነ፣ሐስረ፣ አዘዘ፣ ወሀበ የመሰለው ሁሉ ነው፡፡

የተገብሮ ግሦች ምሳሌ ተኅድገ፣ ተጽሕፈ ነድ ተወልደ ተሰቅላ ተሰምዐ ተከፍለ ተወድየ ተርእየ ተረግዘ ተፈነወ ተግሕ ተረፈ… የመሰለው ሁሉ ነው፡፡

☞ <u>በመነሻው “ተ“ ያለበት ብቻ ተገብሮ ግሥ ነው ማለት አይቻልም፡፡</u>

ምክንያቱም “ተ“ በመነሻ ሳይኖር ቅርጸ ንባቡ ገቢር ግሥ የመሰለ ስምን የማይስብ ተገብሮ ግሥ አለና፡፡

***ምሳሌ፡-*** ሐይወ አልዓዛር፡፡አልዓዛር ሕያው ሆነ/ዳነ/፡፡

መጽአ ብእሲ፡፡ ሰውየው መጣ፡፡

ነደ እሳት፡፡ እሳት ነደደ፡፡

ሐጸ ማይ፡፡ ውሃ ጎደለ፡፡

<u>**ገቢር ግሥ የመሰሉ ተገብሮ ግሦች፡-**</u> ከብረ፣ ሞተ፣ ዐርገ፣ ሀለወ፣ ሀርበደ፣ ሐመ፣ መረ፣ መትሐ፣ ምዕዘ፣ ሞቀ፣ ሐጽረ፣ ወዐለ፣ መስየ፣ ረስሐ፣ ረግዐ፣ ቀንዐ፣ ቀንአ፣ አከለ፣ ወረደ፣ ዐብደ፣ ዝሕነ፣ ደምጸ፣ በርሀ፣ ቁሐ፣ ጸንዐ፣ መልዐ፣ ረትዐ፣ ሮጸ፣ ብህመ፣ ብዕለ፣ ቦአ፣ ቶስሐ፣ ነቅሐ፣ ነቅዐ፣ ነጽሐ፣ ነፍጸ፣ ወርዘወ፣ ወጽአ፣ ጸብሐ፡ የመሰለው ሁሉ ነው፡፡





***<u>ምልማድ ፱.፩.</u>፡-*** የተሰጡትን ገቢርና ተገብሮ ግሦች አጥኑ ፡፡

| ገቢር ግሥን ወደ ተገብሮ ግሥ መለወጥ | | ተገብሮ ግሥን ወደ ገቢር ግሥ መለወጥ | |
|---|---|---|---|
| <u>ገቢር ግሥ</u> | <u>ተገብሮ ግሥ</u> | <u>ተገብሮ ግሥ</u> | <u>ገቢር ግሥ</u> |
| መርሐ | ተመርሐ | ተሐንጸ | ሐነጸ |
| ሠዐረ | ተሥዕረ | ተሐርየ | ሐረየ |
| ሰምዐ | ተሰምዐ | ተቀደሰ | ቀደሰ |
| ርእየ | ተርእየ | ተቀድሐ | ቀድሐ |
| ከሰተ | ተከስተ | ተተክለ | ተከለ |
| ወለደ | ተወልደ | ተኰርዐ | ኰርዐ |
| ፈለጠ | ተፈልጠ | ተገድፈ | ገደፈ |
| ፈነወ | ተፈነወ | ተፈትሐ | ፈትሐ |
| ሰብሐ | ተሰብሐ | ተለቅሐ | ለቅሐ |
| ላጸየ | ተላጸየ | ተለክዐ | ለክዐ |
| ሐጥአ | ተሐጥአ | ተሐሰወ | ሐሰወ |
| ሐመየ | ተሐምየ | ተሐዝለ | ሐዘለ |
| ሐቀለ | ተሐቀለ | ተሐብለ | ሐበለ |
| መስሐ | ተመስሐ | ተሞዐ | ሞዐ |
| ሞቅሐ | ተሞቅሐ | ተመንሰወ | መንሰወ |
| ሞርቅሐ | ተሞርቅሐ | ተመገበ | መገበ |
| ሞጥሐ | ተሞጥሐ | ተማህረከ | ማህረከ |
| ሞጽሐ | ተሞጽሐ | ተሠረወ | ሠረወ |
| ሦዐ | ተሦዐ | ተረግዘ | ረገዘ |
| ሠርዐ | ተሠርዐ | ተሴሰየ | ሴሰየ |
| ሤመ | ተሠይመ/ተሤመ | ተሰፈወ | ሰፈወ |
| ረሐነ | ተርሕነ | ተስሕበ | ሰሐበ |
| ረመለ | ተረምለ | ተሰንቀወ | ሰነቀወ |
| ረሰየ | ተረሰየ | ተሰክየ | ሰከየ |
| ረስዐ | ተረስዐ | ተነጽሐ | ነጽሐ |
| ረከበ | ተረክበ | ተክዕወ | ከዐወ |
| ሰዐበ | ተስዕበ | ተአውቀ | ኦቀ |
| ሰፍሐ | ተሰፍሐ | ተአለደ | አለደ |
| ሰጥሐ | ተሰጥሐ | ተውህበ | ወሀበ |
| ቀድሐ | ተቀድሐ | ተወሰከ | ወሰከ |
| ቀነወ | ተቀነወ | ተወርወ | ወረወ |
| ቀደመ | ተቀድመ | ተዘርወ | ዘረወ |
| ቀተለ | ተቀትለ | ተጠብሐ | ጠብሐ |
| በልዐ | ተበልዐ | ተጸፍዐ | ጸፍዐ |
| በተከ | ተበትከ | ተጸልአ | ጸልአ |
| በጥሐ | ተበጥሐ | ተጸውዐ | ጸውዐ |
| ተፈከረ | ፈከረ | ተፈትሐ | ፈትሐ |

# የአዕማድ ምልአትና ህፀፅ

አዕማድ የሚባሉ አምስት መሆናቸውን እንዲሁም አድራጊ አስደራጊ አደራራጊ ተደራራጊ አደራራጊ መሆናቸውን በመነሻሉ ገልጸናል፡፡ ይሁን እና ግሦች ሁሉ በአምስት አዕማድ ይታወቃሉ ማለት አይደለም፡፡ ለእርባታቸው ሕፀፅ እና ምልአት አለበት፡፡ የአዕማድ ሕፀፅ አንዱ ምክንያት ልማድ የተባሉ ቀለማትን ‹‹አ›› ‹‹አን›› እና ‹‹አስታ›› በመጨመር እና ሳይጨምር በንባብ አድራጊ በፍቺ ተደራጊ በንባብ አስደራጊ በፍቺ ተደራጊ እና ተደራራጊ የመሰለውን ሁሉ ሆኖ በመነገር ነው፡፡

ምሳሌ፡- አንገሠ - አነገሠ አስደራጊ ይመስላል ነገር ግን አነገሠ ብሎ አድራጊ ነው ነግሠ - ነገሠ ተገብሮ ግሥ ነው፡፡ ስለሆነም ነግሠ አራት አዕማድ አለው፡፡

ምሳሌ ፪፡- አስተርአየ- አደራራጊ ይመስላል ነገር ግን ታየ ብሎ ተደራጊ አሳየ ብሎ አስደራጊ ነው፡፡

የአዕማድ ሕፀፅ እና ምልአት ማሳያ

| <u>አድራጊ</u> | <u>አስደራጊ</u> | <u>አደራራጊ</u> | <u>ተደራጊ</u> | <u>ተደራራጊ</u> |
|---|---|---|---|---|
| ቀተለ | አቅተለ | አስተቃተለ | ተቀትለ | ተቃተለ |
| ከፈለ | አክፈለ | አስተካፈለ | ተከፈለ | ተካፈለ |
| ነጸረ | አንጸረ | አስተናጸረ | ተነጸረ | ተናጸረ |
| ጸልአ | አጽልአ | አስተጻልአ | ተጸልአ | ተጻልአ |
| ርእየ | አርአየ/አስተርአየ | አስተራአየ | ተርእየ /አስተርአየ | ተረአየ |
| ባረከ | አባረለ | አስተባረከ | ተባረከ | ተባረከ |
| ደንገፀ | አደንገፀ | አስተደናገፀ | ተደናገፀ | ---- |
| አብአ | …. | አስተባውአ | ቦአ/ተባውአ | ተባውአ |
| ማህረከ | አማህረከ | አስተማህረከ | ተማህረከ | ……. |





| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| ዋሐደ | አዋሐደ | አስተዋሐደ | ተዋሐደ | .......... |
| ሐነፀ | አሕነፀ | …. | ተሐንፀ | …. |
| ቀደሰ | አቅደሰ | …. | ተቀደሰ | … |
| አድሐነ | ..... | .... | ድሕነ/ተድሕነ | ..... |
| ዝነመ | … | .... | ዘንመ | …. |
| ….. | … | …. | ኮነ/ከወነ/ተከወነ | ….. |
| አሀለወ | አሀለወ | … | ሀለወ | ….. |
| አሕመመ/አሰተሐመመ | --- | አስተሐመ | ሐመ | ተሐመመ |
| አፍልሰ /አስተፋለሰ | አፈለሰ | አስተፋለሰ | ፈለሰ/ተፈለሰ | ተፋለሰ |

አዕማድ የሚባሉት አምስቱ አርዕስቶች ማለትም አድራጊ፣ አስደራጊ፣ አደራራጊ፣ ተደራጊ እና ተደራራጊ ዐምድ ሲሆኑ ለግሥ እርባታ መነሻና መቋቋሚያ ስለሆኑ አዕማድ ተብለዋል፡፡ ለእርባታቸው ሕፀፅና ምልአት አለው፡፡ አዕማድ በዐሥሩ መራሕያን ይዘረዘራሉ፡፡ በዐቢይ፣ በንዑስ፣ በደቂቅ አንቀጽ ይዘልቃሉ፡፡ በዝርዝር ጊዜም ፍጹም እንደመራሕያን ይሄዳሉ በዐቢይ አንቀጽ ይገኛሉ በንዑስና በደቂቅ አንቀጽ ይታጣሉ፡፡ አዕማደ ግሥ “ተ” “አ” “አስተ” የተባሉትን በመነሻ እየጨመሩ ይነገራሉ፡፡ እኒህም **ልማድ** በመባል ይታወቃሉ፡፡

ምሳሌ፡- አ (+) ነግሠ = አንገሠ አስደራጊ ይመስላል ግን አነገሠ ብሎ አድራጊ ነው፡፡

አንቀልቀለ = አስደራጊ ይመስላል ነገር ግን ተናወጸ ብሎ ተደራራጊ አናወጸ ብሎ አደራራጊ ነው፡፡

አንሶሰወ = አስደራጊ ይመስላል ነገር ግን ተመላለሰ ብሎ ተደራራጊ አመላለሰ ብሎ አደራራጊ ነው፡፡

አስቈረረ = አስደራጊ ይመስላል ነገር ግን ተጸየፈ ብሎ አድራጊ አጸየፈ ብሎ አስደራጊ ነው፡፡

አስተርአየ = አደራራጊ ይመስላል ነገር ግን ታየ ብሎ ተደራጊ አሳየ ብሎ አስደራጊ ነው፡፡

## ፬.፫. የአዕማድ ንዑስ እርባታ

አዕማድ በዐሥሩ መራሕያን ይዘረዘራሉ ፣ በዐቢይ ፣በንዑስ፣ በደቂቅ አንቀጽ ይዘልቃሉ ። በዝርዝር ጊዜም ፍጹም እንደመራሕያን ይሄዳሉ ፣ በዐቢይ አንቀጽ ይገኛሉ ፣በንዑስ እና በደቂቅ አንቀጽ ይታጣሉ ። እለሆነም የአዕማድ ንዑስ እርባታ ቀተለ በሚለው ግሥ እንደሚከተለው እናሳያለን ፡-

| | ግሥ/ አድራጊ | አስደራጊ | አደራራጊ | ተደራጊ | ተደራራጊ |
|---|---|---|---|---|---|
| ውእቱ ኀላፊ | ቀተለ | አቅተለ | አስተቃተለ | ተቀትለ | ተቃተለ |
| ትንቢት | ይቀትል | ያቀትል | ያስተቃትል | ይትቀተል | ይትቃተል |
| ዘንድ | ይቅትል | ያቅትል | ያስተቃትል | ይትቀተል | ይትቃተል |
| ትእዛዝ | ይቅትል | ያቅትል | ያስተቃትል | ይትቀተል | ይትቃተል |
| ውእቶሙ | ቀተሉ | አቅተሉ | አስተቃተሉ | ተቀትሉ | ተቃተሉ |
| ትንቢት | ይቀትሉ | ያቀትሉ | ያስተቃትሉ | ይትቀተሉ | ይትቃተሉ |
| ዘንድ | ይቀትሉ | ያቅትሉ | ያስተቃትሉ | ይትቀተሉ | ይትቃተሉ |
| ትእዛዝ | ይቀትሉ | ያቅትሉ | ያስተቃትሉ | ይትቀተሉ | ይትቃተሉ |
| ይእቲ | ቀተለት | አቅተለት | አስተቃተለት | ተቀትለት | ተቃተለት |
| ትንቢት | ትቀትል | ታቀትል | ታስተቃትል | ትትቀተል | ትትቃተል |
| ዘንድ | ትቅትል | ታቅትል | ታስተቃትል | ትትቀተል | ትትቃተል |
| ትእዛዝ | ትቅትል | ታቅትል | ታስተቃትል | ትትቀተል | ትትቃተል |
| ውእቶን | ቀተላ | አቅተላ | አስተቃተላ | ተቀትላ | ተቃተላ |
| ትንቢት | ይቀትላ | ያቀትላ | ያስተቃትላ | ይትቀተላ | ይትቃተላ |
| ዘንድ | ይቅትላ | ያቅትላ | ያስተቃትላ | ይትቀተላ | ይትቃተላ |
| ትእዛዝ | ይቅትላ | ያቅትላ | ያስተቃትላ | ይትቀተላ | ይትቃተላ |





| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| አንተ | ቀተልከ | አቅተልከ | አስተቃተልከ | ተቀተልከ | ተቃተልከ |
| ትንቢት | ትቀትል | ታቀትል | ታስተቃትል | ትትቀተል | ትትቃተል |
| ዘንድ | ትቅትል | ታቅትል | ታስተቃትል | ትትቀተል | ትትቃተል |
| ትእዛዝ | ቅትል | አቅትል | አስተቃትል | ተቀተል | ተቃተል |
| አንትሙ | ቀተልክሙ | አቅተልክሙ | አስተቃተልክሙ | ተቀተልክሙ | ተቃተልክሙ |
| ትንቢት | ትቀትሉ | ታቀትሉ | ታስተቃትሉ | ትትቀተሉ | ትትቃተሉ |
| ዘንድ | ትቅትሉ | ታቅትሉ | ታስተቃትሉ | ትትቀተሉ | ትትቃተሉ |
| ትእዛዝ | ቅትሉ | አቅትሉ | አስተቃትሉ | ተቀተሉ | ተቃተሉ |
| አንቲ | ቀተልኪ | አቅተልኪ | አስተቃተልኪ | ተቀተልኪ | ተቃተልኪ |
| ትንቢት | ትቀትሊ | ታቀትሊ | ታስተቃትሊ | ትትቀተሊ | ትትቃተሊ |
| ዘንድ | ተቅትሊ | ታቅትሊ | ታስተቃትሊ | ትትቀተሊ | ትትቃተሊ |
| ትእዛዝ | ቅትሊ | አቅትሊ | አስተቃትሊ | ተቀተሊ | ተቃተሊ |
| አንትን | ቀተልክን | አቅተልክን | አስተቃተልክን | ተቀተልክን | ተቃተልክን |
| ትንቢት | ትቀትላ | ታቀትላ | ታስተቃትላ | ትትቀተላ | ትትቃተላ |
| ዘንድ | ትቅትላ | ታቅትላ | ታስተቃትላ | ትትቀተላ | ትትቃተላ |
| ትእዛዝ | ቅትላ | አቅትላ | አስተቃትላ | ተቀተላ | ተቃተላ |
| ንሕነ | ቀተልነ | አቅተልነ | አስተቃተልነ | ተቀተልነ | ተቃተልነ |
| ትንቢት | ንቀትል | ናቀትል | ናስተቃትል | ንትቀተል | ንትቃተል |
| ዘንድ | ንቅትል | ናቅትል | ናስተቃትል | ንትቀተል | ንትቃተል |
| ትእዛዝ | ንቅትል | ናቅትል | ናስተቃትል | ንትቀተል | ንትቃተል |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| አነ | ቀተልኩ | አቅተልኩ | አስተቃተልኩ | ተቀተልኩ | ተቃተልኩ |
| ትንቢት | እቀትል | አቀትል | አስተቃትል | እትቀተል | እትቃተል |
| ዘንድ | እቅትል | አቅትል | አስተቃትል | እትቀተል | እትቃተል |
| ትእዛዝ | እቅትል | አቅትል | አስተቃትል | እትቀተል | እትቃተል |

## ፱.፩. የቦዝ አንቀጽ አዕማድ እርባ

| | ግሥ/አድራጊ | አስደራጊ | አደራራጊ | ተደራጊ | ተደራራጊ |
|---|---|---|---|---|---|
| ውእቱ | ቀቲሎ | አቅቲሎ | አስተቃቲሎ | ተቀቲሎ | ተቃቲሎ |
| ውእቶሙ | ቀቲሎሙ | አቅቲሎሙ | አስተቃቲሎሙ | ተቀቲሎሙ | ተቃቲሎሙ |
| ይእቲ | ቀቲላ | አቅቲላ | አስተቃቲላ | ተቀቲላ | ተቃቲላ |
| ውእቶን | ቀቲሎን | አቅቲሎን | አስተቃቲሎን | ተቀቲሎን | ተቃቲሎን |
| አንተ | ቀቲለከ | አቅቲለከ | አስተቃቲለከ | ተቀቲለከ | ተቃቲለከ |
| አንትሙ | ቀቲለክሙ | አቅቲለክሙ | አስተቃቲለክሙ | ተቀቲለክሙ | ተቃቲለክሙ |
| አንቲ | ቀቲለኪ | አቅቲለኪ | አስተቃቲለኪ | ተቀቲለኪ | ተቃቲለኪ |
| አንትን | ቀቲለክን | አቅቲለክን | አስተቃቲለክን | ተቀቲለክን | ተቃቲለክን |
| አነ | ቀቲልየ | አቅቲልየ | አስተቃቲልየ | ተቀቲልየ | ተቃቲልየ |
| ንሕነ | ቀቲለነ | አቅቲለነ | አስተቃቲለነ | ተቀቲለነ | ተቃቲለነ |





# ምዕራፍ ፲.
# ተቃርኖ ስዋሰው /አሉታ/

በግእዝ ሰዋሰው እርስ በርሱ አዎንታና አሉታ/አፍራሽ/ ሆኖ በሁለት ስልቶች እየተቃረነ ይነገራል።እነሱም፡-

፩ ፥ የባዕዳን ቀለማት የሰዋሰው መቃረንና

፪ ፥ የሰዋሰው እርስ በእርሱ መቃረን ናቸው።

## ፲.፩. የባዕዳን ቀለማት የሰዋሰው መቃረን

የግእዝ ሰዋሰው በባዕዳን ቀለማት የራሱ አሉታ /አፍራሽ/ ሆኖ ራሱን ይቃረናል። የታወቁት የግእዝ ቋንቋ አሉታ አራት ናቸው።

*እነርሱም፡-* ፩. አኮ ፫. ኢ

፪. አል ፬. ሐሰ

## ፩. አኮ

"አኮ" ውእቱ በነባር አንቀጽነቱ የሚኖረው ትርጓሜ አፍራሽ/አሉታ/ ነው። አሉታነቱም እንደሚከተለው ነው።

| ውእቱ | አኮ |
|---|---|
| ነው፣ ነበረ | አይደለም፣ አልነበረም |
| ናት፣ ነበረች | አይደለችም፣ አልነበረችም |
| ናቸው፣ ነበሩ | አይደሉም፣ አልነበሩም |
| ነህ፣ ነበርህ | አይደለህም፣ አልነበርህም |
| ናችሁ፣ ነበራችሁ | አይደላችሁም፣ አልነበራችሁም |
| ነሽ ፣ ነበርሽ | አይደለሽም ፣አልነበርሽም |
| ነኝ፣ ነበርኩኝ | አይደለሁም፣ አልነበርኩም |
| ነን፣ ነበርን | አይደለንም፣ አልነበርንም |

| | | |
|---|---|---|
| ምሳሌ፦ | አዎንታ፡- | አንተ ውእቱ ዘተሐንጽ ቤትየ፡፡ |
| | አሉታ፡- | አኮ አንተ ዘተሐንጽ ቤትየ፡፡ |
| | | አኮ ዘተሐንጽ አንተ ቤትየ፡፡ |
| | አዎንታ፡- | አንተውእቱ ዘቀተልኮ ለዝንቱ አርዌ፡፡ |
| | አሉታ፡- | አኮ አንተ ዘቀተልኮ ለዝንቱ አርዌ፡፡ |
| | | አኮ ዘቀተልኮ አንተ ለዝንቱ አርዌ፡፡ |
| | አዎንታ፡- | ውእቱ ሕዝብየ እሉ፡፡ |
| | አሉታ፡- | አኮ ሕዝብየ እሉ፡፡ |

**ምልማድ ፲፩.፡-**

**የሚከተሉትን ፩. ነገሮች ከአዎንታ ወደ አሉታ ለውጡ፡፡**

፩. ትጉሕ ውእቱ ዮሐንስ፡፡
፪. ዝንቱ ውእቱ ዘገብረ ዘንተግብረ፡፡
፫. ንሕነ ውእቱ እለ ገበርነ ዘንተ ግብረ፡፡
፬. አንትን ውእቱ ትጉሓን፡፡
፭. በኀብስት ክመ ዘየሐዩ ሰብእ፡፡

## ፪. አል

"አል" "ቦ" በነባር አንቀጽነቱ የሚኖረው ትርጓሜ አፍራሽ/አሉታ/ ነው፡፡

| ቦ | አልቦ |
|---|---|
| አለ፣ ነበረ | የለም፣ አልነበረም |
| አለች፣ ነበረች | የለችም፣ አልነበረችም |
| አሉ፣ ነበሩ | የሉም፣ አልነበሩም |
| አለህ፣ ነበርህ | የለህም፣ አልነበርህም |
| አላችሁ፣ ነበራችሁ | የላችሁም፣ አልነበራችሁም |
| አለሽ ፣ ነበርሽ | የለሽም፣ አልነበርሽም |
| አለሁኝ፣ ነበርኩኝ | የለሁም፣ አልነበርኩም |
| አለን፣ ነበርን | የለንም፣ አልነበርንም |





| አዎንታ | አሉታ |
|---|---|
| ፩. ቦ ያዕቆብ ውስተ ጉባዔ፡፡ | አልቦ ያዕቆብ ውስተ ጉባዔ፡፡ |
| ፪. ቦ ማርታ ውስተ ጉባዔ፡፡ | አልቦ ማርታ ውስተ ጉባዔ፡፡ |
| ፫. ቦ ሊቃውንቲነ ውስተ ጉባዔ፡፡ | አልቦ ሊቃውንቲነ ውስተ ጉባዔ፡፡ |
| ፬. ቦ አንተ ውስተ ጉባዔ፡፡ | አልቦ አንተ ውስተ ጉባዔ፡፡ |

## «ቦ » በዝርዝር አፈታት ሲነገር

ቦ/ቦቱ፡- አለው፣አለለት፣ አለበት፣ ኖረው፣ ኖረበት፣ ኑሮበታል፣ ነበረበት
ባ/ባቲ፡-አላት፣ አለላት፣ አለባት፣ ኖራት፣ ኖረባት፣ ኑሮባታል፣ ነበረባት
እያለ በዐሥሩም ይረባል፡፡

| አዎንታ | አሉታ |
|---|---|
| ቦ/ቦቱ | አልቦ/አልቦቱ |
| ቦሙ/ቦቶሙ | አልቦሙ |
| ባ/ባቲ | አልባቲ |
| ቦን/ቦቶን | አልቦን |
| ብከ | አልብከ |
| ብክሙ | አልብክሙ |
| ብኪ | አልብኪ |
| ብክን | አልብክሙ |
| ብየ | አልብየ |
| ብነ | አልብነ |

ምሳሌ፡-

| | |
|---|---|
| ፩.ቦቱ ዘመድ፡፡ | አልቦቱ ዘመድ፡፡ |
| ፪.ባቲ ዘመድ፡፡ | አልባቲ ዘመድ፡፡ |
| ፫.ብከ ዘመድ፡፡ | አልብከ ዘመድ፡፡ |
| ቦቱ፡- አለበት፣ ነበረበት | አልቦቱ፡- የለበትም፣ አልነበረበትም |

| አዎንታ | አሉታ |
|---|---|
| ፩.ቦቱ ዕዳ | አልቦቱ ዕዳ |
| ፪.ባቲ ዕዳ | አልባቲ ዕዳ |
| ፫.ቦሙ ዕዳ | አልቦሙ ዕዳ |

## ፫. ኢ

“ኢ” የዘር/የግሥ/ የአናቅጽ አፍራሽ/አሉታ/ ነው፡፡ትርጉሙም፡-

በቀዳማይ አንቀጽ ላይ ሲወድቅ “አል”

ካልዓይና ትእዛዝ ላይ ሲወድቅ “አ”

በዘንድ አንቀጽ ላይ ሲወድቅ “እንዳ” “ላ” “ሳ” ነው፡፡

### የቀዳማይ አንቀጽ አዎንታና አሉታ፡-

| | አዎንታ | | አሉታ | |
|---|---|---|---|---|
| ውእቱ | ቀተለ | ገደለ | ኢቀተለ | አልገደለም |
| ውእቶሙ | ቀተሉ | ገደሉ | ኢቀተሉ | አልገደሉም |
| ይእቲ | ቀተለት | ገደለች | ኢቀተለት | አልገደለችም |
| ውእቶን | ቀተላ | ገደሉ | ኢቀተላ | አልገደሉም |
| አንተ | ቀተልከ | ገደልኽ | ኢቀተልከ | አልገደልኽም |
| አንትሙ | ቀተልክሙ | ገደላችኹ | ኢቀተልክሙ | አልገደላችኹም |
| አንቲ | ቀተልኪ | ገደልሽ | ኢቀተልኪ | አልገደልሽም |
| አንትን | ቀተልክን | ገደላችኹ | ኢቀተልክን | አልገደላችኹም |
| አነ | ቀተልኩ | ገደልኹ | ኢቀተልኩ | አልገደልኹም |
| ንሕነ | ቀተልነ | ገደልን | ኢቀተልነ | አልገደልንም |





### የካልዓይ አንቀጽ አዎንታና አሉታ፡-

| | አዎንታ | | አሉታ | |
|---|---|---|---|---|
| ውእቱ | ይቀትል | ይገድላል | ኢይቀትል | አይገድልም |
| ውእቶሙ | ይቀትሉ | ይገድላሉ | ኢይቀትሉ | አይገድሉም |
| ይእቲ | ትቀትል | ትገድላለች | ኢትቀትል | አትገድልም |
| ውእቶን | ይቀትላ | ይገድላሉ | ኢይቀትላ | አይገድሉም |
| አንተ | ትቀትል | ትገድላለኽ | ኢትቀትል | አትገድልም |
| አንትሙ | ትቀትሉ | ትገድላላችኹ | ኢትቀትሉ | አትገድሉም |
| አንቲ | ትቀትሊ | ትገድያለሽ | ኢትቀትሊ | አትገድይም |
| አንትን | ትቀትላ | ትገድላላችኹ | ኢትቀትላ | አትገድሉም |
| አነ | እቀትል | እገድላለኹ | ኢይቀትል | አልገድልም |
| ንሕነ | ንቀትል | እንገድላለን | ኢንቀትል | አንገድልም |

### የዘንድ አንቀጽ አዎንታና አሉታ፡-

| | አዎንታ | | አሉታ | |
|---|---|---|---|---|
| ውእቱ | ይቅትል | ይገድል ዘንድ | ኢይቅትል | እንዳ/ላይ/ሳይገድል |
| ውእቶሙ | ይቅትሉ | ይገድሉ ዘንድ | ኢይቅትሉ | እንዳ/ሳይ/ላይገድሉ |
| ይእቲ | ትቅትል | ትገድል ዘንድ | ኢትቅትል | እንዳ/ሳትላትገድል |
| ውእቶን | ይቅትላ | ይገድሉ ዘንድ | ኢይቅትላ | እንዳ/ሳይ/ላይገድሉ |
| አንተ | ትቅትል | ትገድል ዘንድ | ኢትቅትል | እንዳ/ሳት/ላትገድል |
| አንትሙ | ትቅትሉ | ትገድሉ ዘንድ | ኢትቅትሉ | እንዳ/ሳት/ላትገድሉ |
| አንቲ | ትቅትሊ | ትገድዪ ዘንድ | ኢትቅትሊ | እንዳ/ሳት/ላትገድዪ |
| አንትን | ትቅትላ | ትገድሉ ዘንድ | ኢትቅትላ | እንዳ/ሳት/ላትገድሉ |
| አነ | እቅትል | እገድል ዘንድ | ኢይቅትል | እንዳ/ሳል/ላልገድል |
| ንሕነ | ንቅትል | እንገድል ዘንድ | ኢንቅትል | እንዳ/ሳን/ላንገድል |

## የትእዛዝ አንቀጽ አሉታና አዎንታ:-

| | አዎንታ | | አሉታ | |
|---|---|---|---|---|
| ውእቱ | ይቅትል | ይግደል | ኢይቅትል | አይግደል |
| ውእቶሙ | ይቅትሉ | ይግደሉ | ኢይቅትሉ | አይግደሉ |
| ይእቲ | ትቅትል | ትግደል | ኢትቅትል | አትግደል |
| ውእቶን | ይቅትላ | ይግደሉ | ኢይቅትላ | አይግደሉ |
| አንተ | ቅትል | ግደል | ኢትቅትል | አትግደል |
| አንትሙ | ቅትሉ | ግደሉ | ኢትቅትሉ | አትግደሉ |
| አንቲ | ቅትሊ | ግደዪ | ኢትቅትሊ | አትግደዪ |
| አንትን | ቅትላ | ግደሉ | ኢትቅትላ | አትግደሉ |
| አነ | እቅትል | ልግደል | ኢይቅትል | አልግደል |
| ንሕነ | ንቅትል | እንግደል | ኢንቅትል | አንግደል |

☞ ሁለተኛ መደቦች ላይ በትእዛዝ አንቀጽ ተሠውረው የነበሩት አሥራው ቀለማት በአሉታ ጊዜ ይከሠታሉ::

**ምልማድ ፲.፪ :-**

### ፩. የሚከተሉትን አዎንታዎች ወደ አሉታ ቀይሩ::

፩. መጻእኩ ፪. ንበውእ ፫. ይቄድስ ፬. ተጠወሩ ፭. ጸሐፍኩ

### ፪.ትክክለኛውን መልስ ምረጡ::

፩. «ኢትሑሩ» የሚለው አንቀጽ ---------------- ነው

ሀ. ትእዛዝ ለ. ዘንድ ሐ. ትንቢት መ. ሀናለ ሠ. መ.የለም

፪.ኢይንብብ ልሳንየ ሐሰተ:: የዐ. ነገሩ ባለቤት --------------------- ነው::

ሀ. አነ ለ. ውእቱ ሐ. አንተ መ. ሀ እና ለ ሠ. መ. የለም

፫. ኢይመጽእ -------------- ኀበ ቤተክርስቲያን::

ሀ. አበበ ለ. አነ ሐ. አንተ መ. ሀናለ ሠ. መ.የለም

፬. ይቁማ ብሎ ቆማ ካለ ኢትቁም ብሎ --------------- ይላል::

ሀ. ቆምከ ለ. ኢቆመት ሐ. ኢቆምከ መ. ለናሐ

፭. ኢትመጽእኑ ------------ ኀበ ቤተ ትምህርት ጌሠም::

ሀ. አልማዝ ለ. አበበ ሐ. አንተ መ. ሀናሐ ሠ. መ. የለም





**ማስታወሻ:-**

፩. «ኢ»በኅልስ ውስጠ ዘ/ኅልስ ቅጽል/ "ያል" "የማ" የሚል ትርጉም አለው::

*ምሳሌ:-*

| አዎንታ | አሉታ |
|---|---|
| ቀታሊ - የገደለ፣የሚገድል | ኢቀታሊ - ያልገደለ፣ የማይገድል |
| ቀታሊት - የገደለች፣የምትገድል | ኢቀታሊት - ያልገደለች፣የማትገድል |

፪. "ኢ" በቦዝ አንቀጽ ሲገባ "ሳ" የሚል ትርጉም ይኖረዋል::

*ምሳሌ:-*

| አዎንታ | አሉታ |
|---|---|
| ቀቲሎ - ገድሎ | ኢቀቲሎ - ሳይገድል |
| ቀቲላ - ገድላ | ኢቀቲላ - ሳትገድል |

፫. "ኢ" የለም ተብሎም ይተረጎማል::

*ምሳሌ:-*

ኢመምህር ወኢ ደቀመዝሙር:: አስተማሪም ተማሪም የለም::

ኢአማኒ ወኢተኣማኒ:: የሚያምንም የሚታመንም የለም::

ኢአግኣዚ ወኢገብር:: ጌታም ባርያም የለም::

፬. «ኢ ›› እንደ ‹‹አኮ›› አይደለም ተብሎ ይፈታል:: ኢ እና አኮ አንሄዳቸው እንደ ውእቱ ነው:: እሱ የሚስባቸውን ይስባሉ::

ምሳሌ ፩ :- አኮ ወይም ኢ መፍትው አድልዎ በፍትሕ::

በፍርድ ማድላት የሚገባ አይደለም ::

፪. አኮ ወይም ኢ ሕዝብየ እሉ:: እነዚህ ወገኖቼ አይደሉም

፫. ተነስሖቱ ለይሁዳ አኮ ወይም ኢ ከመ ተነስሖቱ ለጴጥሮስ የይሁዳ መጸጸት እንደ ጴጥሮስ መጸጸት አይደለም::

## ፬. ሐሰ

### *የዐረፍተ ነገር ጽድቅ አፍራሽ /አሉታ/ ነው::*

“ሐሰ”ውሸት፣አይደለም፣አይገባም፣አይሆንም ተብሎ በአሉታይተረጎማል::

“ሐሰ” በ“በ”ና“ለ” አሉታነት ይነገራል::

ሐሰ ቦቱ:- በእርሱ አይኾንበትም፣ አይኹንበት፣ አይድረስበት::

ሐሰ ቦሙ:- በእነርሱ አይኾንባቸውም፣ አይኹንባቸው፣ አይድረስባቸው

ሐሰ ባቲ:- በእርሷ አይኾንባትም፣ አይኹንባት፣ አይድረስባት::

ሐሰ ቦን:- በእነርሱ አይኾንባቸውም፣ አይኹንባቸው፣ አይድረስባቸው::

ሐሰ ብከ:- በአንተ አይኾንብህም፣ አይኹንብህ፣ አይድረስብህ::

ሐሰ ብክሙ:- በእናንተ አይኾንባቹም፣ አይኹንባቹ፣ አይድረስባቹ::

ሐሰ ብኪ:- በአንቺ አይኾንብሽም፣ አይኹንብሽ፣ አይድረስብሽ::

ሐሰ ብክን:- በእናንተ አይኾንባቹም፣ አይኹንባቹ፣ አይድረስባቹ::

ሐሰ ብየ:- በእኔ አይኾንብኝም፣ አይኹንብኝ፣ አይድረስብኝ::

ሐሰ ብነ:- በእኛ አይኾንብንም፣ አይኹንብን ፣ አይድረስብን::

ሐሰ ሎቱ:- ሐሰት ይኹንለት፣ ሕልም ይሁንለት:::

ሐሰ ሎቶሙ:- ሐሰት ይኹንላቸው፣ ሕልም ይኹንላቸው::

ሐሰ ላቲ:- ሐሰት ይኹንላት፣ ሕልም ይኹንላት::

ሐሰ ሎቶን:- ሐሰት ይኹንላቸው፣ ሕልም ይኹንላቸው::

ሐሰ ለከ:- ሐሰት ይኹንልህ፣ ሕልም ይኹንልህ::

ሐሰ ለክሙ:- ሐሰት ይኹንላቹ፣ ሕልም ይኹንላቹ::

ሐሰ ለኪ:- ሐሰት ይኹንልሽ፣ ሕልም ይኹንልሽ::

ሐሰ ለክን:- ሐሰት ይኹንላቹ፣ ሕልም ይኹንላቹ::





ሐሰ ልየ:- ሐሰት ይኹንልኝ፣ ሕልም ይኹንልኝ

ሐሰ ለነ:- ሐሰት ይኹንልን ፣ ሕልም ይኹንልን

**ምልማድ ፲.፫ :-አሉታውን ወደ አዎንታ ለውጡ::**

፩.ኢያንተገት
፪.ኢትብጻሕ
፫.ኢታፀርዕ
፬.ኢይሬእይዋ
፭.ኢተሐለየ
፮.ኢትፍርሂ
፯.ኢርእየ

### ፲.፪.የሰዋሰው እርስ በራስ መቃረን

አንዱ ሰዋሰው ሌላውን ሰዋሰው /አንዱ ቃል ሌላውን ቃል/ ሲቃረን የሰዋሰው ወይም የቃላት እርስ በእርስ መቃረን ይባላል::

*ምሳሌ:-*

| አዎንታ | | አሉታ | |
|---|---|---|---|
| ዐርገ | - ወጣ | ወረደ | - ወረደ |
| ጠቢብ | - ብልህ | ዐብድ | - ሰነፍ |
| ቀርበ | - ቀረበ | ርኅቀ | - ራቀ |
| ኀየለ | - በረታ | ደክመ | - ደከመ |

**ምልማድ ፲.፬ :-አዛምድ**

በ “ሀ” ረድፍ ላሉት አዎንታዊ ቃላት አሉታቸውን በ “ለ” ረድፍ ፈልግ::

| “ሀ” | “ለ” |
|---|---|
| ፩፥ ከሠተ---------- | ሀ. ጸድቀ |
| ፪፥ ሐነጸ----------- | ለ. ሠወረ |
| ፫፥ ቡሩክ---------- | ሐ. አብርሃ |
| ፬፥ ሕያው--------- | መ. ነሠተ |
| ፭፥ ተግሀ---------- | ሠ. ርጉም |
| | ረ. ኖለወ |
| | ሰ. ምውት |
| | ቀ. ሠርወ |
| | በ. ሀከየ |
| | ተ. ኀረየ |

## ተጨማሪ

- **እወ፣ አሜን፣ አማን** - አዎን ተብለው ይፈታሉ።

  ምሳሌ፡- አንተኑ ዘትመጽእ፡፡የምትመጣው አንተ ነህን?

  እወ/አሜን/አማን፡፡አዎን፡፡

- **እንጋ፣ እንዳኢ** - እንጃ ተብለው ይፈታሉ፡፡

  ምሳሌ፡-ነጸረኑ፡፡ተመለከተን/አየ እንዴ? እንጋ/እንዳኢ፡፡እንጃ፡፡

  አልቦ ዘየዐብየነ በዝንቱ ግብር፡፡በዚህ ሥራ የሚበልጠን የለም፡፡

  እንጋ/እንዳኢ፡፡እንጃ፡፡

- **ሀብ፣ ህንካ ፣ እንካ** - ውሰድ ተብለው ይፈታሉ፡፡

  ምሳሌ፡- ሀበኒ ዕሴትየ፡፡ዋጋዬን ስጠኝ፡፡ ሀብ/ህንካ፡፡ውሰድ፡፡

- **አህ፣ አይ፣ ኅድግ** - ተው ተብለው ይፈታሉ፡፡እሺ/በጀ/በጎ፡፡

  ምሳሌ፡-እቀትሎ ለጸርየ፡፡ጠላቴን እገድለዋለኹ፡፡

  አህ/አይ/ኅድግ፡፡ተው/ይቅርብህ፡፡

- **ኦሆ** - እሺ/በጀ/በጎ ተብሎ ይፈታል፡፡

  ምሳሌ፡- ኦሆ በሃሊ፡፡ እሺ/በጀ/በጎ የሚል፡፡

  ኦሆ በልዎ ለክርስቶስ፡፡ ክርስቶስን እሺ/በጀ/በጎ በሉት፡፡

  ሑር ውስተ ዐፀደ ወይንየ፡፡ ወደ ወይኔ ቦታ ሂድ፡፡

  ኦሆ አሐውር፡፡ እሺ እሄዳለሁ፡፡

- **እንቢ፣ እንቢየ፡-** እንቢ፣ እንቢኝ ተብለው ይፈታሉ፡፡

  ምሳሌ፡- ሑር በምክረ ረሲዓን፡፡

  በክፉዎች ምክር ሂድ፡፡እንቢየ፡፡እንቢ/እንቢኝ፡፡

- **እንቋዕ፣ አህ፣ አይ፣ጥቀ** - እንኳን ፣እሰይ ተብለው ይፈታሉ፡፡

  ምሳሌ፡- እንቋዕ ሞተ ሰሎሞን እንበለ ይርአይ ሙስናሃ ለሀገሩ፡፡

  የሀገሩን ጥፋት ሳያይ ሰሎሞን እንኳን ሞተ፡፡





ምንት ይብለኒ ጸርየ በእንተ ዘረከበኒ መከራ?

ስለደረሰብኝ መከራ ጠላቴ ምን ይለኛል?

ዕንቋ ዕንቋ ረከቦ መከራ፡፡እሰይ እሰይ መከራ አገኘው፡፡

ይሙትኑ እትከ?ወንድምህ ይሙትን?

ጥቀ ይሙት ሕማምሂ ኢይርከቦ፡፡

እንኳን ሊሞት ሕመም እንኳ አያግኘው፡፡

- **አ፣ አሌ፣ ወይ፣ ሰይ፣ አህ** - ወዮ ተብለው ይፈታሉ፡፡

  ምሳሌ፡-አሌ/ወይ/ ሊተ ሕገ ወትእዛዘ በእንተ ዘኢዐቀብኩ፡፡

  ወዮልኝ ሕግንናትዛዝን አልጠበቅኹምና፡፡

  ወድኀረኒ በእንተ ዘኢነሳሕኩ፡፡

  ተመልሼም ንስሐ ስላልገባኹ፡፡

  ሰይ ልየ ዘርኅቁ እማኅደርየ፡፡

  ከማደሪያዬ ስለራቅኹ ወዮልኝ፡፡

# ምዕራፍ ፲፩.

## ዝርዝር እርባታ

የእርባታ ስሞች እንደ አገባብ ስሞች በሦስት ይከፈላሉ እኒህም ዐቢይ ወይም ዝርዝር እርባ ንዑስ እርባ እና ደቂቅ እርባ ናቸው። ደቂቅ እርባ እንደ ዝርዝር እና ንዑስ እርባ ካልዓይ ዘንድ እና ትእዛዝ እናቅጽ የሌሉት በቀዳማይ ወይም ኃላፊ ብቻ የሚነገር የነባር አንቀጽ ዓይነትና ክፍል ነው።

ንዑስ እርባ በኃላፊ ብቻ በአሥር አካል የሚነገር ሲሆን አድራጊውን ብቻ የሚያሳይ የተደራጊውን ብዛት ፆታና መደብ የማይለይ እርባ ነው።

ዐቢይ እርባ /ዝርዝር እርባ በኃላፊ ብቻ በሰማኒያ አካል የሚዘምት የአድራጊውን አንድ እና ብዙ ወንድ እና ሴት ቅርብ እና ሩቅ የሚለይ የእርባታ ዓይነት ነው።

የእርባታ ዓይነቶችን ከላይ እንደተገለጸው ዝርዝር እርባታ የባለቤቱን ብቻ ሳይሆን የተሳቢውንም አንድና ብዙነት ወንድና ሴትነት፣ ሩቅና ቅርብነት ዘርዝሮ የሚያመለክት የእርባታ ዓይነት ነው።

በዝርዝር እርባታ ጊዜ በግሡ መድረሻ ላይ በምዕላድነት እየገቡ እርባታ መሪዎች የሚሆኑት ፊደላት <u>"ግሣውያን የተሳቢ አጸፋ ተውላጣተ ስም /የባለቤትና የተሳቢ ዝርዝር/"</u> ይባላሉ። እነርሱም ከዚህ በታች ቀርበዋል።





### ፲፩.፩ የእርባታ መሪዎች የባለቤትና ተሳቢ ዝርዝር

| እርባታ መደቦች | የባለቤት ዝርዝር | ውእቱ | ውእቶሙ | ይእቲ | ውእቶን | አንተ | አንትሙ | አንቲ | አንትን | አነ | ንሕነ |
|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|---|
| ውእቱ | ግእዝ | ሳብዕ | ሙ | ራብዕ | ን | ከ | ክሙ | ኪ | ክን | ኒ | ነ |
| ውእቶሙ | ካዕብ | ዎ | ዎሙ | ዋ | ዎን | ከ | ክሙ | ኪ | ክን | ኒ | ነ |
| ይእቲ | ተ | ቶ | ቶሙ | ታ | ቶን | ተከ | ተክሙ | ተኪ | ተክን | ተኒ | ተነ |
| ውእቶን | ራብዕ | ሁ | ሆሙ | ሃ | ሆን | ከ | ክሙ | ኪ | ክን | ኒ | ነ |
| አንተ | ከ | ሳብዕ | ከሙ | ራብዕ | ከን | - | - | - | - | ኒ | ነ |
| አንትሙ | ክሙ | ምዎ | ክምዎሙ | ምዋ | ክምዎን | - | - | - | - | ክሙኒ | ክሙነ |
| አንቲ | ኪ | ኪዮ | ኪዮሙ | ኪያ | ያን | - | - | - | - | ኒ | ነ |
| አንትን | ክን | ክናሁ | ናሆሙ | ናሃ | ሆን | - | - | - | - | ክናኒ | ክናነ |
| አነ | ኩ | ክዎ | ክዎሙ | ክዋ | ክዎን | ኩከ | ኩክሙ | ኩኪ | ኩክን | - | - |
| ንሕነ | ነ | ናሁ | ናሆሙ | ናሃ | ናሆን | ከ | ክሙ | ኪ | ክን | - | - |

## ፲፩.፪. የዝርዝር እርባታ ንባብ ሠንጠረዥ

| | | |
|---|---|---|
| ውእቱ | ውእቱን<br>ይእቲን<br>ውእቶንን | ሲዘረዝር ቀዳማይና ካልዓይ አንቀጽ ወዳቂ ወይም ተጣይ ንባብ ነው:: |
| አንተ | ውእቱን<br>ይእቲን<br>ውእቶንን | ሲዘረዝር ቀዳማይና ካልዓይ አንቀጽ ወዳቂ ወይም ተጣይ ንባብ ነው:: |
| ንሕነ | ውእቱን<br>ይእቲን<br>ውእቶንን | ሲዘረዝር ቀዳማይና ካልዓይ አንቀጽ ወዳቂ ወይም ተጣይ ንባብ ነው:: |
| ውእቶሙ | | ሲዘረዝሩ ከአንትን በስተቀር ሁሉም ተነሽ ንባብ ሲሆን አንትንን ሲዘረዝሩ ንባቡ ተ ጣይ ነው :: |
| ይእቲ | ውእቱን<br>ይእቲን<br>ውእቶንን | ስትዘረዝር ካልዓይ አንቀጽ ወዳቂ ወይንም ተጣይ ንባብ ነው:: |
| አነ | ውእቱን<br>ይእቲን<br>ውእቶንን | ሲዘረዝር ካልዓይ አንቀጽ ወዳቂ ወይም ተ ጣይ ንባብ ነው:: |
| ውእቶን | ውእቶንን | ሲዘረዝሩ ቀዳማይና ካልዓይ አንቀጽ ተጣይ ንባብ ነው:: |
| አንትን | ውእቶንን | ሲዘረዝሩ ቀዳማይና ካልዓይ አንቀጽ ተጣይ ንባብ ነው:: |
| አንቲ | | ስትዘረዝር ሁሉም ተነሽ ንባብ ነው:: |
| አንትሙ | | ሲዘረዝሩ ሁሉም ተነሽ ንባብ ነው:: |

**ማስታወሻ:-** “ክን” “ሣ” “ሁ” እነዚህ ቀለማት ከቀዳማይ እስከ ትእዛዝ አንቀጽ በመድረሻ ከመጡ ንባቡ ወድቆ ይነበባል::





## ፲፩.፫. የአእመረ ዝርዝር እርባታ
## ክፍል አንድ ሦስተኛ መደቦች ባለቤት ሆነው:-

**ውእቱ ዐሥሩን መራሕያን ሲዘረዝር:-** ውእቱ ሦስቱንም መደቦች ይዘረዝራል::

| ውእቱ | ውእቱ | ይእቲ | አንተ | አንቲ | አነ |
|---|---|---|---|---|---|
| አእመረ | አእመሮ | አእመራ | አእመረከ | አእመረኪ | አእመረኒ |
| የአምር | የአምሮ | የአምራ | የአምረከ | የአምረኪ | የአምረኒ |
| ያእምር | ያእምሮ | ያእምራ | ያምርከ | ያእምርኪ | ያእምረኒ |
| ያእምር | ያእምሮ | ያእምራ | ያምርከ | ያእምርኪ | ያእምረኒ |

| ውእቶሙ | ውእቶን | አንትሙ | አንትን | ንሕነ |
|---|---|---|---|---|
| አእመሮሙ | አእመሮን | አእመረክሙ | አእመረክን | አእመረነ |
| የአምሮሙ | የአምሮን | የአምረክሙ | የአምረክን | የአምረነ |
| ያእምሮሙ | ያእምሮን | ያእምርክሙ | ያእምርክን | ያእምረነ |
| ያእምሮሙ | ያእምሮን | ያእምርክሙ | ያእምርክን | ያእምረነ |

**ውእቶሙ ዐሥሩን መራሕያን ሲዘረዝሩ:-** ውእቶሙ ሦስቱንም መደቦች ይዘረዝራሉ::

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| አእመሩ | አእመርዎ | አእመርዋ | አእመሩከ | አእመሩኪ | አእመሩኒ |
| የአምሩ | የአምርዎ | የአምርዋ | የአምሩከ | የአምሩኪ | የአምሩኒ |
| ያእምሩ | ያእምርዎ | ያእምርዋ | ያእምሩከ | ያእምሩኪ | ያእምሩኒ |
| ያእምሩ | ያእምርዎ | ያእምርዋ | ያእምሩከ | ያእምሩኪ | ያእምሩኒ |

| ውእቶሙ | ውእቶን | አንትሙ | አንትን | ንሕነ |
|---|---|---|---|---|
| አእመርዎሙ | አእመርዎን | አእመሩክሙ | አእመሩክን | አእመሩነ |
| የአምርዎሙ | የአምርዎን | የአምሩክሙ | የአምሩክን | የአምሩነ |
| ያእምርዎሙ | ያእምርዎን | ያእምሩክሙ | ያእምሩክን | ያእምሩነ |
| ያእምርዎሙ | ያእምርዎን | ያእምሩክሙ | ያእምሩክን | ያእምሩነ |

**ይእቲ ዐሥሩን መራሕያን ስትዘረዝር:-** ይእቲ ሦስቱንም መደቦች ትዘረዝራለች::

| ይእቲ | ውእቱ | ይእቲ | አንተ | አንቲ | አነ |
|---|---|---|---|---|---|
| አእመረት | አእመረቶ | አእመረታ | አእመረተከ | አእመረተኪ | አእመረተኒ |
| ተአምር | ተአምሮ | ተአምራ | ተአምረከ | ተአምረኪ | ተአምረኒ |
| ታእምር | ታእምሮ | ታእምራ | ታእምርከ | ታእምርኪ | ታእምረኒ |
| ታእምር | ታእምሮ | ታእምራ | ታእምርከ | ታእምርኪ | ታእምረኒ |

| ውእቶሙ | ውእቶን | አንትሙ | አንትን | ንሕነ |
|---|---|---|---|---|
| አእመረቶሙ | አእመርቶን | አእመረተክሙ | አእመረተክን | አእመረተነ |
| ተአምሮሙ | ተአምሮን | ተአምረክሙ | ተአምረክን | ተአምረነ |
| ታእምሮሙ | ታእምሮን | ታእምርክሙ | ታእምርክን | ታእምረነ |
| ታእምሮሙ | ታእምሮን | ታእምርክሙ | ታእምርክን | ታእምረነ |

**ውእቶን ዐሥሩን መራሕያን ሲዘረዝሩ:-** ውእቶን ሦስቱንም መደቦች ይዘረዝራሉ::

| ውእቶን | ውእቱ | ይእቲ | አንተ | አንቲ | አነ |
|---|---|---|---|---|---|
| አእመራ | አእመራሁ | አእመራሃ | አእመራከ | አእመራኪ | አእመራኒ |
| የአምራ | የአምራሁ | የአምራሃ | የአምራከ | የአምራኪ | የአምራኒ |
| ያእምራ | ያእምራሁ | ያእምራሃ | ያእምራከ | ያእምራኪ | ያእምራኒ |
| ያእምራ | ያእምራሁ | ያእምራሃ | ያእምራከ | ያእምራኪ | ያእምራኒ |

| ውእቶሙ | ውእቶን | አንትሙ | አንትን | ንሕነ |
|---|---|---|---|---|
| አእመራሆሙ | አእመራሆን | አእመራክሙ | አእመራክን | አእመራነ |
| የአምራሆሙ | የአምራሆን | የአምራክሙ | የአምራክን | የአምራነ |
| ያእምራሆሙ | ያእምራሆን | ያእምራክሙ | ያእምራክን | ያእምራነ |
| ያእምራሆሙ | ያእምራሆን | ያእምራክሙ | ያእምራክን | ያእምራነ |





## ክፍል ሁለት ሁለተኛ መደቦች ባለቤት ሆነው

**አንተ ስድስቱን መራሕያን ሲዘረዝር:-** አንተ ፩ኛ እና ፫ኛ መደቦችን ይዘረዝራል::

| አንተ | ውእቱ | ይእቲ | አነ |
|---|---|---|---|
| አእመርከ | አእመርኮ | አእመርካ | አእመርከኒ |
| ተአምር | ተአምሮ | ተአምራ | ተአምረኒ |
| ታእምር | ታእምሮ | ታእምራ | ታእምረኒ |
| አእምር | አእምሮ | አእምራ | አእምረኒ |

| ውእቶሙ | ውእቶን | ንሕነ |
|---|---|---|
| አእመርኮሙ | አእመርኮን | አእመርከነ |
| ተአምሮሙ | ተአምሮን | ተአምረነ |
| ታአእምሮሙ | ታእምሮን | ታእምረነ |
| አእምሮሙ | አእምሮን | አእምረነ |

**አንትሙ ስድስቱን መራሕያን ሲዘረዝሩ:-** አንትሙ ፩ኛ እና ፫ኛ መደቦችን ይዘረዝራሉ::

| አንትሙ | ውእቱ | ይእቲ | አነ |
|---|---|---|---|
| አእመርክሙ | አእመርክምዎ | አእመርክምዋ | አእመርክሙኒ |
| ተአምሩ | ተአምርዎ | ተአምርዋ | ተአምሩኒ |
| ታእምሩ | ታእምርዎ | ታእምርዋ | ታእምሩኒ |
| አእምሩ | አእምርዎ | አእምርዋ | አእምሩኒ |

| ውእቶሙ | ውእቶን | ንሕነ |
|---|---|---|
| አእመርክምዎሙ | አእመርክምዎን | አእመርክሙነ |
| ተአምርዎሙ | ተአምርዎን | ተአምሩነ |
| ታእምርዎሙ | ታእምርዎን | ታእምሩነ |
| አእምርዎሙ | አእምርዎን | አእምሩነ |

<u>አንቲ ስድስቱን መራሕያን ስትዘረዝር፡-</u> አንቲ ፩ኛ እና ፫ኛ መደቦችን ትዘረዝራለች፡፡

| አንቲ | ውእቱ | ይእቲ | አነ |
|---|---|---|---|
| አእመርኪ | አእመርኪዮ | አእመርኪያ | አእመርክኒ |
| ተአምሪ | ተአምሪዮ | ተአምሪያ | ተአምርኒ |
| ታእምሪ | ታእምሪዮ | ታእምሪያ | ታእምርኒ |
| አእምሪ | አእምሪዮ | አእምሪያ | አእምርኒ |

| ውእቶሙ | ውእቶን | ንሕነ |
|---|---|---|
| አእመርኪዮሙ | አእመርኪዮን | አእመርክነ |
| ተአምሪዮሙ | ተአምሪዮን | ተአምርነ |
| ታእምሪዮሙ | ታእምሪዮን | ታእምርነ |
| አእምሪዮሙ | አእምሪዮን | አእምርነ |

<u>አንትን ስድስቱን መራሕያን ሲዘረዝሩ፡-</u> አንትን ፩ኛ እና፫ኛ መደቦችን ይዘረዝራሉ፡፡

| አንትን | ውእቱ | ይእቲ | አነ |
|---|---|---|---|
| አእመርክን | አእመርክናሁ | አእመርክናሃ | አእመርክናኒ |
| ተአምራ | ተአምራሁ | ተአምራሃ | ተአምራኒ |
| ታእምራ | ታእምራሁ | ታእምራሃ | ታእምራኒ |
| አእምራ | አእምራሁ | አእምራሃ | አእመራኒ |

| ውእቶሙ | ውእቶን | ንሕነ |
|---|---|---|
| አእመርክናሆሙ | አእመርክናሆን | አእመርክናነ |
| ተአምራሆሙ | ተአምራሆን | ተአምራነ |
| ታእምራሆሙ | ታእምራሆን | ታእምራነ |
| አእምራሆሙ | አእምራሆን | አእምራነ |





## <u>ክፍል ሦስት አንደኛ መደቦች ባለቤት ሆነው</u>

<u>አነ ሥምንቱን መራሕያን ሲዘረዝር፡-</u> አነ ፪ኛ እና ፫ኛ መደቦችን ይዘረዝራል፡፡

| አነ | ውእቱ | ይእቲ | አንተ | አንቲ |
|---|---|---|---|---|
| አእመርኩ | አእመርክዎ | አእመርክዋ | አእመርኩከ | አእመርኩኪ |
| አአምር | አአምሮ | አአምራ | አአምረከ | አአምረኪ |
| ኣእምር | ኣእምሮ | ኣእምራ | ኣእምርከ | ኣእምርኪ |
| ኣእምር | ኣእምሮ | ኣእምራ | ኣእምርከ | ኣእምርኪ |

| ውእቶሙ | ውእቶን | አንትሙ | አንትን |
|---|---|---|---|
| አእመርክዎሙ | አእመርክዎን | አእመርኩክሙ | አእመርኩክን |
| አአምሮሙ | አአምሮን | አአምረክሙ | አአምረክን |
| ኣእምሮሙ | ኣእምሮን | ኣእምርክመ | ኣእምርክን |
| ኣእምሮሙ | ኣእምሮን | ኣእምርክመ | ኣእምርክን |

<u>ንሕነ ሥምንቱን መራሕያን ሲዘረዝር፡-</u> ንሕነ ፪ኛ እና ፫ኛ መደቦችን ይዘረዝራል፡፡

| ንሕነ | ውእቱ | ይእቲ | አንተ | አንቲ |
|---|---|---|---|---|
| አእመርነ | አእመርኖ/ አእመርናሁ | አእመርና/ አእመርናሃ | አእመርነከ /አእመርናከ | አእመርነኪ /አእመርናኪ |
| ነአምር | ነአምሮ | ነአምራ | ነአምረከ | ነአምረኪ |
| ናእምር | ናእምሮ | ናእምራ | ናእምርከ | ናእምርኪ |
| ናእምር | ናእምሮ | ናእምራ | ናእምርከ | ናእምርኪ |

| ውእቶሙ | ውእቶን | አንትሙ | አንትን |
|---|---|---|---|
| አእመርኖሙ/ አእመርናሆሙ | አእመርኖን/ አእመርናሆን | አእመርነክሙ/ አእመርናክሙ | አአመርነክን /አእመርናክን |
| ነአምራሆሙ | ነአምሮን | ነአምረክሙ | ነአምረክን |
| ናእምራሆሙ | ናእምሮን | ናእምርክሙ | ናእምርክን |
| ናእምራሆሙ | ናእምሮን | ናእምርክሙ | ናእምርክን |

**ምልማድ ፲፩.፩. :-**

**የሚከተሉትን አንቀጾች ባለቤት ትርጉምና ንባብ አሳዩ።**

፩. አእመራሆን

፪. ያእምርዋ

፫. አእምርኒ

፬ አእመራሁ

፭. አእመርናሁ

## ፲፩.፬. የቀተለ ዝርዝር እርባታ

**ውእቱ**

| | | | |
|---|---|---|---|
| ቀተሎ | ቀተሎሙ | ቀተላ | ቀተሎን |
| ይቀትሎ | ይቀትሎሙ | ይቀትላ | ይቀትሎን |
| ይቅትሎ | ይቅትሎሙ | ይቅትላ | ይቅትሎን |
| » | » | » | » |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ቀተለከ | ቀተለክሙ | ቀተለኪ | ቀተለክን | ቀተለኒ | ቀተለነ |
| ይቀትለከ | ይቀትለክሙ | ይቀትለኪ | ይቀትለክን | ይቀትለኒ | ይቀትለነ |
| ይቅትልከ | ይቅትልክሙ | ይቅትልኪ | ይቅትልክን | ይቅትለኒ | ይቅትለነ |
| » | » | » | » | » | » |

**ውእቶሙ**

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ቀተልዎ | ቀተልዎሙ | ቀተልዋ | ቀተልዎን | ቀተሉከ | ቀተሉክሙ |
| ይቀትልዎ | ይቀትልዎሙ | ይቀትልዋ | ይቀትልዎን | ይቀትሉከ | ቀትሉክሙ |
| ይቅትልዎ | ይቅትልዎሙ | ይቅትልዋ | ይቅትልዎን | ይቅትሉከ | ይቅትሉክሙ |
| » | » | » | » | » | » |

| | | | |
|---|---|---|---|
| ቀተሉኪ | ቀተሉክን | ቀተሉኒ | ቀተሉነ |
| ይቀትሉኪ | ይቀትሉክን | ይቀትሉኒ | ይቀትሉነ |
| ይቅትሉኪ | ይቅትሉክን | ይቅትሉኒ | ይቅትሉነ |
| » | » | » | » |





**ይእቲ**

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ቀተለቶ | ቀተሎቶሙ | ቀተለታ | ቀተለቶን | ቀተለተከ | ቀተለተክሙ |
| ትቀትሎ | ትቀትሎሙ | ትቀትላ | ትቀትሎን | ትቀትለከ | ትቀትለክሙ |
| ትቅትሎ | ትቅትሎሙ | ትቅትላ | ትቅትሎን | ትቅትልከ | ትቅትልክሙ |
| » | » | » | » | » | » |

| | | | |
|---|---|---|---|
| ቀተለተኪ | ቀተለተክን | ቀተለተኒ | ቀተለተነ |
| ትቀትለኪ | ትቀትለክን | ትቀትለኒ | ትቀትለነ |
| ትቅትልኪ | ትቅትልክን | ትቅትለኒ | ትቅትለነ |
| » | » | » | » |

**ውእቶን**

| | | | |
|---|---|---|---|
| ቀተላሁ | ቀተላሆሙ | ቀተላሃ | ቀተላሆን |
| ይቀትላሁ | ይቀትላሆሙ | ይቀትላሃ | ይቀተላሆን |
| ይቅትላሁ | ይቅትላሆሙ | ይቅትላሃ | ይቅትላሆን |
| » | » | » | » |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ቀተላከ | ቀተላክሙ | ቀተላኪ | ቀተላክን | ቀተላኒ | ቀተላነ |
| ይቀትላከ | ይቀትላክሙ | ይቀትላኪ | ይቀትላክን | ይቀትላኒ | ይቀትላነ |
| ይቅትላከ | ይቅትላክሙ | ይቅትላኪ | ይቅትላክን | ይቅትላኒ | ይቅትላነ |
| » | » | » | » | » | » |

**አንተ**

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ቀተልኮ | ቀተልኮሙ | ቀተልካ | ቀተልኮን | ቀተልከኒ | ቀተልከነ |
| ትቀትሎ | ትቀትሎሙ | ትቀትላ | ትቀትሎን | ትቀትለኒ | ትቀትለነ |
| ትቅትሎ | ትቅትሎሙ | ትቅትላ | ትቅትሎን | ትቅትለኒ | ትቅትለነ |
| ቅትሎ | ቅትሎሙ | ቅትላ | ቅትሎን | ቅትለኒ | ቅትለነ |

## አንትሙ

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ቀተልክምዎ | ቀተልክምዎሙ | ቀተልክምዋ | ቀተልክምዎን | ቀተልክሙኒ | ቀተልክሙነ |
| ትቀትልዎ | ትቀትልዎሙ | ትቀትልዋ | ትቀትልዎን | ትቀትሉኒ | ትቀትሉነ |
| ትቅትልዎ | ትቅትልዎሙ | ትቅትልዋ | ትቅትልዎን | ትቅተሉኒ | ትቅትሉነ |
| ቅትልዎ | ቅትልዎሙ | ቅትልዋ | ቅትልዎን | ቅትሉኒ | ቅትሉነ |

## አንቲ

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ቀተልኪዮ | ቀተልኪዮሙ | ቀተልኪያ | ቀተልኪዮን | ቀተልክኒ | ቀተልክነ |
| ትቀትሊዮ | ትቀትሊዮሙ | ትቀትሊያ | ትቀትሊዮን | ትቀትልኒ | ትቀትሊነ |
| ትቅትሊዮ | ትቅትሊዮሙ | ትቅትሊያ | ትቅትሊዮን | ትቅትልኒ | ትቅትሊነ |
| ቅትሊዮ | ቅትሊዮሙ | ቅትሊያ | ቅትሊዮን | ቅትልኒ | ቅትሊነ |

## አንትን

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ቀተልክናሁ | ቀተልክናሆሙ | ቀተልክናሃ | ቀተልክናሆን | ቀተልክናኒ | ቀተልክናነ |
| ትቀትላሁ | ትቀትላሆሙ | ትቀትላሃ | ትቀትላሆን | ትቀትላኒ | ትቀትላነ |
| ትቅትላሁ | ትቅትላሆሙ | ትቅትላሃ | ትቅትላሆን | ትቅትላኒ | ትቅትላነ |
| ቅትላሁ | ቅትላሆሙ | ቅትላሃ | ቅትላሆን | ቅትላኒ | ቅትላነ |

## አነ

| | | | |
|---|---|---|---|
| ቀተልክዎ | ቀተልክዎሙ | ቀተልክዋ | ቀተልክዎን |
| እቀትሎ | እቀትሎሙ | እቀትላ | እቀትሎን |
| እቅትሎ | እቅትሎሙ | እቅትላ | እቅትሎን |
| » | » | » | » |
| ቀተልኩክ | ቀተልኩክሙ | ቀተልኩኪ | ቀተልኩክን |
| እቀትለክ | እቀትለክሙ | እቀትለኪ | እቀትለክን |
| እቅትልክ | እቅትልክሙ | እቅትልኪ | እቅትልክን |
| » | » | » | » |





## ንሕነ

| | | | |
|---|---|---|---|
| ቀተልናሁ | ቀተልናሆሙ | ቀተልናሃ | ቀተልናሆን |
| ንቀትሎ | ንቀትሎሙ | ንቀትላ | ንቀትሎን |
| ንቅትሎ | ንቅትሎሙ | ንቅትላ | ንቅትሎን |
| » | » | » | » |
| ቀተልናክ | ቀተልናክሙ | ቀተልናኪ | ቀተልናክን |
| ንቀትለክ | ንቀትለክሙ | ንቀትለኪ | ንቀትለክን |
| ንቅትልክ | ንቅትልክሙ | ንቅትልኪ | ንቅትልክን |
| » | » | » | » |

## ፲፩.፭. የይቤ ዝርዝር እርባታ

### ውእቱ

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ይቤሎ | ይቤሎሙ | ይቤላ | ይቤሎን | ይቤለክ | ይቤለክሙ |
| ይብሎ | ይብሎሙ | ይብላ | ይብሎን | ይብለክ | ይብለክሙ |
| ይበሎ | ይበሎሙ | ይበላ | ይበሎን | ይበልክ | ይበልክሙ |
| » | » | » | » | » | » |

| | | | |
|---|---|---|---|
| ይቤለኪ | ይቤለክን | ይቤለኒ | ይቤለነ |
| ይብለኪ | ይብለክን | ይብለኒ | ይብለነ |
| ይበልኪ | ይበልክን | ይበለኒ | ይበለነ |
| » | » | » | » |

### ውእቶሙ

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ይቤልዎ | ይቤልዎሙ | ይቤልዋ | ይቤልዎን | ይቤሉክ | ይቤሉክሙ |
| ይብልዎ | ይብልዎሙ | ይብልዋ | ይብልዎን | ይብሉክ | ይብሉክሙ |
| ይበልዎ | ይበልዎሙ | ይበልዋ | ይበልዎን | ይበሉክ | ይበሉክሙ |
| » | » | » | » | » | » |

| | | | |
|---|---|---|---|
| ይቤሉኪ | ይቤሉክን | ይቤሉኒ | ይቤሉነ |
| ይብሉኪ | ይብሉክን | ይብሉኒ | ይብሉነ |
| ይበሉኪ | ይበሉክን | ይበሉኒ | ይበሉነ |
| » | » | » | » |

**ይእቲ**

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ትቤሎ | ትቤሎሙ | ትቤላ | ትቤሎን | ትቤለከ | ትቤለክሙ |
| ትብሎ | ትብሎሙ | ትብላ | ትብሎን | ትብለከ | ትብለክሙ |
| ትበሎ | ትበሎሙ | ትበላ | ትበሎን | ትበልከ | ትበልክሙ |
| » | » | » | » | » | » |

| | | | |
|---|---|---|---|
| ትቤለኪ | ትቤለክን | ትቤለኒ | ትቤለነ |
| ትብለኪ | ትብለክን | ትብለኒ | ትብለነ |
| ትበልኪ | ትበልክን | ትበለኒ | ትበለነ |
| » | » | » | » |

**ውእቶን**

| | | | |
|---|---|---|---|
| ይቤላሁ | ይቤላሆሙ | ይቤላሃ | ይቤላሆን |
| ይብላሁ | ይብላሆሙ | ይብላሃ | ይብላሆን |
| ይበላሁ | ይበላሆሙ | ይበላሃ | ይበላሆን |
| » | » | » | » |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ይቤላከ | ይቤላክሙ | ይቤላኪ | ይቤላክን | ይቤላኒ | ይቤላነ |
| ይብላከ | ይብላክሙ | ይብላኪ | ይብላክን | ይብላኒ | ይብላነ |
| ይበላከ | ይበላክሙ | ይበላኪ | ይበላክን | ይበላኒ | ይበላነ |
| » | » | » | » | » | » |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| **አንተ** | ትቤሎ | ትቤሎሙ | ትቤላ | ትቤሎን | ትቤለኒ | ትቤለነ |
| | ትብሎ | ትብሎሙ | ትብላ | ትብሎን | ትብለኒ | ትብለነ |
| | ትበሎ | ትበሎሙ | ትበላ | ትበሎን | ትበለኒ | ትበለነ |
| | በሎ | በሎሙ | በላ | በሎን | በለኒ | በለነ |





**አንትሙ**

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ትቤልዎ | ትቤልዎሙ | ትቤልዋ | ትቤልዎን | ትቤሉኒ | ትቤሉነ |
| ትብልዎ | ትብልዎሙ | ትብልዋ | ትብልዎን | ትብሉኒ | ትብሉነ |
| ትበልዎ | ትበልዎሙ | ትበልዋ | ትበልዎን | ትበሉኒ | ትበሉነ |
| በልዎ | በልዎሙ | በልዋ | በልዎን | በሉኒ | በሉነ |

**አንቲ**

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ትቤሊዮ | ትቤሊዮሙ | ትቤሊያ | ትቤሊዮን | ትቤልኒ | ትቤልነ |
| ትብሊዮ | ትብሊዮሙ | ትብሊያ | ትብሊዮን | ትብልኒ | ትብልነ |
| ትበሊዮ | ትበሊዮሙ | ትበሊያ | ትበሊዮን | ትበልኒ | ትበልነ |
| በሊዮ | በሊዮሙ | በሊያ | በሊዮን | በልኒ | በልነ |

**አንትን**

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ትቤላሁ | ትቤላሆሙ | ትቤላሃ | ትቤላሆን | ትቤላኒ | ትቤላነ |
| ትብላሁ | ትብላሆሙ | ትብላሃ | ትብላሆን | ትብላኒ | ትብላነ |
| ትበላሁ | ትበላሆሙ | ትበላሃ | ትበላሆን | ትበላኒ | ትበላነ |
| በላሁ | በላሆሙ | በላሃ | በላሆን | በላኒ | በላነ |

**አነ**

| | | | |
|---|---|---|---|
| እቤሎ | እቤሎሙ | እቤላ | እቤሎን |
| እብሎ | እብሎሙ | እብላ | እብሎን |
| እበሎ | እበሎሙ | እበላ | እበሎን |
| » | » | » | » |
| እቤለከ | እቤለክሙ | እቤለኪ | እቤለክን |
| እብለከ | እብለክሙ | እብለኪ | እብለክን |
| እበልከ | እበልክሙ | እበልኪ | እበልክን |
| » | » | » | » |

**ንሕነ**

| | | | |
|---|---|---|---|
| ንቤሎ | ንቤሎሙ | ንቤላ | ንቤሎን |
| ንብሎ | ንብሎሙ | ንብላ | ንብሎን |
| ንበሎ | ንበሎሙ | ንበላ | ንበሎን |
| » | » | » | » |

| | | | |
|---|---|---|---|
| ንቤለከ | ንቤለክሙ | ንቤለኪ | ንቤለክን |
| ንብለከ | ንብለክሙ | ንብለኪ | ንብለክን |
| ንበልከ | ንበልክሙ | ንበልኪ | ንበልክን |
| » | » | » | » |

**ምልማድ :-**

**ትክክለኛውን መልስ ምረጡ**

፩÷አበበ -------------- አስቴር ይጼውዐኪ አቡኪ::

ሀ. ይቤላ ለ. ትቤላ ሐ. ይቤላሃ መ. ትቤላሃ

፪. ክርስቶስ -------------በ ወንጌል ተፋቀሩ በበይናቲክሙ::

ሀ. ይቤ ለ. ይቤለነ ሐ. ይቤሎ መ. ሀናለ

፫. ሂሩት ወሠናይት ------------ እንቋዕ መጻእነ::

ሀ. ይቤላ ለ. ትቤላ ሐ. ይቤላሃ መ. ትቤላሃ

፬. ማርያም --------------- ለመልአከ ገብርኤል ይኩነኒ በከመ ትቤለኒ::

ሀ. ትቤ ለ. ትቤሎ ሐ. ትቤሊ መ. ይቤላ ሠ. ሀናለ

፭. አንሰ --------------- አማልክት አንትሙ ወደቂቀ ልዑል ኵልክሙ::

ሀ.ይቤላ ለ.ትቤሉ ሐ. እቤ መ.ሁሉም

## ፲፩.፮. የጎደገ ዝርዝር እርባታ

**ውእቱ**

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ጎደጎ | ጎደጎሙ | ጎደጋ | ጎደጎን | ጎደገከ | ጎደገክሙ |
| የጎድጎ | የጎድጎሙ | የጎድጋ | የጎድጎን | የጎድገከ | የጎድገክሙ |
| ይጎድጎ | ይጎድጎሙ | ይጎድጋ | ይጎድጎን | ይጎድገ | ይጎድግሙ |
| » | » | » | » | » | » |

| | | | |
|---|---|---|---|
| ጎደገኪ | ጎደገክን | ጎደገኒ | ጎደገነ |
| የጎድገኪ | የጎድገክን | የጎድገኒ | የጎድገነ |
| ይጎድጊ | ይጎድግን | ይጎድገኒ | ይጎድገነ |
| » | » | » | » |

**ውእቶሙ**

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ጎደግዎ | ጎደግዎሙ | ጎደግዋ | ጎደግዎን | ጎደጉከ | ጎደጉክሙ |
| የጎድግዎ | የጎድግዎሙ | የጎድግዋ | የጎድግዎን | የጎድጉከ | የጎድጉክሙ |
| ይጎድግዎ | ይጎድግዎሙ | ይጎድግዋ | ይጎድግዎን | ይጎድጉከ | ይጎድጉክሙ |
| » | » | » | » | » | » |





| | | | |
|---|---|---|---|
| ጎደጉኪ | ጎደጉክን | ጎደጉኒ | ጎደጉነ |
| የጎድጉኪ | የጎድጉክን | የጎድጉኒ | የጎድጉነ |
| ይጎድጉኪ | ይጎድጉክን | ይጎድጉኒ | ይጎድጉነ |
| » | » | » | » |

**ይእቲ**

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ጎደገቶ | ጎደገቶሙ | ጎደገታ | ጎደገቶን | ጎደገተከ | ጎደገተክሙ |
| ተጎድጎ | ተጎድጎሙ | ተጎድጋ | ተጎድጎን | ተጎድገከ | ተጎድገክሙ |
| ትጎድጎ | ትጎድጎሙ | ትጎድጋ | ትጎድጎን | ትጎድገ | ትጎድግሙ |
| » | » | » | » | » | » |

| | | | |
|---|---|---|---|
| ጎደገተኪ | ጎደገተክን | ጎደገተኒ | ጎደገተነ |
| ተጎድገኪ | ተጎድገክን | ተጎድገኒ | ተጎድገነ |
| ትጎድጊ | ትጎድግን | ትጎድገኒ | ትጎድገነ |
| » | » | » | » |

**ውእቶን**

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ጎደጋሁ | ጎደጋሆሙ | ጎደጋሃ | ጎደጋሆን | ጎደጋከ | ጎደጋክሙ |
| የጎድጋሁ | የጎድጋሆሙ | የጎድጋሃ | የጎድጋሆን | የጎድጋከ | የጎድጋክሙ |
| ይጎድጋሁ | ይጎድጋሆሙ | ይጎድጋሃ | ይጎድጋሆን | ይጎድጋከ | ይጎድጋክሙ |
| » | » | » | » | » | » |

| | | | |
|---|---|---|---|
| ጎደጋኪ | ጎደጋክን | ጎደጋኒ | ጎደጋነ |
| የጎድጋኪ | የጎድጋክን | የጎድጋኒ | የጎድጋነ |
| ይጎድጋኪ | ይጎድጋክን | ይጎድጋኒ | ይጎድጋነ |
| » | » | » | » |

**አንተ**

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ጎደጎ | ጎደጎሙ | ጎደጋ | ጎደጎን | ጎደገኒ | ጎደገነ |
| ተጎድጎ | ተጎድጎሙ | ተጎድጋ | ተጎድጎን | ተጎድገኒ | ተጎድገነ |
| ትጎድጎ | ትጎድጎሙ | ትጎድጋ | ትጎድጎን | ትጎድገኒ | ትጎድገነ |
| ጎድጎ | ጎድጎሙ | ጎድጋ | ጎድጎን | ጎድገኒ | ጎድገነ |

<u>አንትሙ</u>

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ኀደግምዎ | ኀደግምዎሙ | ኀደግምዋ | ኀደግምዎን | ኀደግሙኒ | ኀደግሙነ |
| ተኀድግዎ | ተኀድግዎሙ | ተኀድግዋ | ተኀድግዎን | ተኀድጉኒ | ተኀድጉነ |
| ትኅድግዎ | ትኅድግዎሙ | ትኅድግዋ | ትኅድግዎን | ትኅድጉኒ | ትኅድጉነ |
| ኅድግዎ | ኅድግዎሙ | ኅድግዋ | ኅድግዎን | ኅድጉኒ | ኅድጉነ |

<u>አንቲ</u>

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ኀደጊዮ | ኀደጊዮሙ | ኀደጊያ | ኀደጊዮን | ኀደግኒ | ኀደጊነ |
| ተኀድጊዮ | ተኀድጊዮሙ | ተኀድጊያ | ተኀድጊዮን | ተኀድግኒ | ተኀድጊነ |
| ትኅድጊዮ | ትኅድጊዮሙ | ትኅድጊያ | ትኅድጊዮን | ትኅድግኒ | ትኅድጊነ |
| ኅድጊዮ | ኅድጊዮሙ | ኅድጊያ | ኅድጊዮን | ኅድግኒ | ኅድጊነ |

<u>አንትን</u>

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ኀደግናሁ | ኀደግናሆሙ | ኀደግናሃ | ኀደግናሆን | ኀደግናኒ | ኀደግናነ |
| ተኀድጋሁ | ተኀድጋሆሙ | ተኀድጋሃ | ተኀድጋሆን | ተኀድጋኒ | ተኀድጋነ |
| ትኅድጋሁ | ትኅድጋሆሙ | ትኅድጋሃ | ትኅድጋሆን | ትኅድጋኒ | ትኅድጋነ |
| ኅድጋሁ | ኅድጋሆሙ | ኅድጋሃ | ኅድጋሆን | ኅድጋኒ | ኅድጋነ |

<u>አነ</u>

| | | | |
|---|---|---|---|
| ኀደግዎ | ኀደግዎሙ | ኀደግዋ | ኀደግዎን |
| አኀድጎ | አኀድጎሙ | አኀድጋ | አኀድጎን |
| እኅድጎ | እኅድጎሙ | እኅድጋ | እኅድጎን |
| » | » | » | » |
| ኀደጉከ | ኀደጉክሙ | ኀደጉኪ | ኀደጉክን |
| አኀድገከ | አኀድገክሙ | አኀድገኪ | አኀድገክን |
| እኅድገ | እኅድግሙ | እኅድጊ | እኅድግን |
| » | » | » | » |

<u>ንሕነ</u>

| | | | |
|---|---|---|---|
| ኀደግናሁ | ኀደግናሆሙ | ኀደግናሃ | ኀደግናሆን |
| ነኀድጋሁ | ነኀድጋሆሙ | ነኀድጋሃ | ነኀድጋሆን |
| ንኅድጋሁ | ንኅድጋሆሙ | ንኅድጋሃ | ንኅድጋሆን |
| » | » | » | » |





| | | | |
|---|---|---|---|
| ኀደግናከ | ኀደግናክሙ | ኀደግናኪ | ኀደግናክን |
| ነኀድገከ | ነኀድገክሙ | ነኀድገኪ | ነኀድጋክን |
| ንኅድገ | ንኅድግሙ | ንኅድጊ | ንኅድግን |
| » | » | » | » |

## <u>፲፩.፯. የአዕማድ ዝርዝር</u>

**<u>የአእማድ ዝርዝር እርባታ፡-</u>**
**የተመረጠው አእማድ <u>አቅተለ</u>**
**<u>ውእቱ</u>**

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| አቅተለ | አቅተሎ | አቅተሎሙ | አቅተላ | አቅትሎን | አቅተለከ | አቅተለክሙ |
| ያቀትል | ያቀትሎ | ያቀትሎሙ | ያቀትላ | ያቀትሎን | ያቀትለከ | ያቀትለክሙ |
| ያቅትል | ያቅትሎ | ያቅትሎሙ | ያቅትላ | ያቅትሎን | ያቅትልከ | ያቅትልክሙ |
| » | » | » | » | » | » | » |

| | | | |
|---|---|---|---|
| አቅተለኪ | አቅተለክን | አቅተለኒ | አቅተለነ |
| ያቀትለኪ | ያቀትለክን | ያቀትለኒ | ያቀትለነ |
| ያቅትልኪ | ያቅትልክን | ያቅትለኒ | ያቅትለነ |
| » | » | » | » |

**<u>ውእቶሙ</u>**

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| አቅተሉ | አቅተልዎ | አቅተልዎሙ | አቅተልዋ | አቅተልዎን | አቅተሉከ | አቅተሉክሙ |
| ያቀትሉ | ያቀትልዎ | ያቀትልዎሙ | ያቀትልዋ | ያቀትልዎን | ያቀትሉከ | ያቀትሉክሙ |
| ያቅትሉ | ያቅትልዎ | ያቅትልዎሙ | ያቅትልዋ | ያቅትልዎን | ያቅትሉከ | ያቅትሉክሙ |
| » | » | » | » | » | » | » |

| | | | |
|---|---|---|---|
| አቅተሉኪ | አቅተሉክን | አቅተሉኒ | አቅትሉነ |
| ያቀትሉኪ | ያቀትሉክን | ያቀትሉኒ | ያቀትሉነ |
| ያቅትሉኪ | ያቅትሉክን | ያቅትሉኒ | ያቅትሉነ |
| » | » | » | » |

**<u>ይእቲ</u>**

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| አቅተለት | አቅተለቶ | አቀተለቶሙ | አቅተለታ | አቀትለቶን |
| ታቀትል | ታቀትሎ | ታቀትሎሙ | ታቀትላ | ታቀትሎን |
| ታቅትል | ታቅትሎ | ታቅትሎሙ | ታቅትላ | ታቅትሎን |
| » | » | » | » | » |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| አቅተለተከ | አቅተለተክሙ | አቅተለተኪ | አቅተለተክን | አቅተለተኒ | አቅተለተነ |
| ታቀትለከ | ታቀትለክሙ | ታቀትለኪ | ታቀትለክን | ታቀትለኒ | ታቀትለነ |
| ታቅትልከ | ታቅትልክሙ | ታቅትልኪ | ታቅትልክን | ታቅትለኒ | ታቅትለነ |
| » | » | » | » | » | » |

**ውእቶን**

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| አቅተላ | አቅተላሁ | አቅተላሆሙ | አቅተላሃ | አቅተላሆን | አቅተላከ |
| ያቀትላ | ያቀትላሁ | ያቀትላሆሙ | ያቀትላሃ | ያቀትላሆን | ያቀትላከ |
| ያቅትላ | ያቅትላሁ | ያቅትላሆሙ | ያቅትላሃ | ያቅትላሆን | ያቅትላከ |
| » » | » | » | » | » | » |

| | | | | |
|---|---|---|---|---|
| አቅተላክሙ | አቅተላኪ | አቅተላክን | አቅተላኒ | አቅተላነ |
| ያቀትላክሙ | ያቀትላኪ | ያቀትላክን | ያቀትላኒ | ያቀትላነ |
| ያቅትላክሙ | ያቅትላኪ | ያቅትላክን | ያቅትላኒ | ያቅትላነ |
| » | » | » | » | » |

**አንተ**

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| አቅተልኮ | አቅተልኮሙ | አቅተልካ | አቅተልኮን | አቅተልከኒ | አቅተልከነ |
| ታቀትሎ | ታቀትሎሙ | ታቀትላ | ታቀትሎን | ታቀትለኒ | ታቀትለነ |
| ታቅትሎ | ታቅትሎሙ | ታቅትላ | ታቅትሎን | ታቅትለኒ | ታቅትለነ |
| አቅትሎ | አቅትሎሙ | አቅትላ | አቅትሎን | አቅትለኒ | አቅትለነ |

**አንትሙ**

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| አቅተልክምዎ | አቅተልክምዎሙ | አቅተልክምዋ | አቅተልክምዎን | አቅተልክሙኒ | አቅተልክሙነ |
| ታቀትልዎ | ታቀትልዎሙ | ታቀትልዋ | ታቀትልዎን | ታቀትሉኒ | ታቀትሉነ |
| ታቅትልዎሙ | ታቅትልዋ | ታቅትልዎን | ታቅትሉኒ | ታቅትልዎ | ታቅትሉነ |
| አቅትልዎ | አቅትልዎሙ | አቅትልዋ | አቅትልዎን | አቅትሉኒ | አቅትሉነ |

**አንቲ**

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| አቅተልኪዮ | አቅተልኪዮሙ | አቅተልኪያ | አቅተልኪዮን | አቅተልክኒ | አቅተልክነ |
| ታቀትሊዮ | ታቀትሊዮሙ | ታቀትሊያ | ታቀትሊዮን | ታቀትልኒ | ታቀትሊነ |
| ታቅትሊዮ | ታቅትሊዮሙ | ታቅትሊያ | ታቅትሊዮን | ታቅትልኒ | ታቅትሊነ |
| አቅትሊዮ | አቅትሊዮሙ | አቅትሊያ | አቅትሊዮን | አቅትልኒ | አቅትሊነ |





**አንትን**

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| አቅተልክናሁ | አቅተልክናሆሙ | አቅተልክናሃ | አቅተልክናሆን | አቅተልክናኒ | አቅተልክናነ |
| ታቀትላሁ | ታቀትላሆሙ | ታቀትላሃ | ታቀትላሆን | ታቀትላኒ | ታቀትላነ |
| ታቅትላሁ | ታቅትላሆሙ | ታቅትላሃ | ታቅትላሆን | ታቅትላኒ | ታቅትላነ |
| አቅትላሁ | አቅትላሆሙ | አቅትላሃ | አቅትላሆን | አቅትላኒ | አቅትላነ |

**አነ**

| | | | |
|---|---|---|---|
| አቅተልክዎ | አቅተልክዎሙ | አቅተልክዋ | አቅተልክዎን |
| አቀትልዎ | አቀትልዎሙ | አቀትላ | አቀትልዎን |
| አቅትልዎ | አቅትልዎሙ | አቅትላ | አቅትልዎን |
| » | » | » | » |

| | | | |
|---|---|---|---|
| አቅተልኩከ | አቅተልኩክሙ | አቅተልኩኪ | አቅተልኩክን |
| አቀትለከ | አቀትለክሙ | አቀትለኪ | አቀትለክን |
| አቅትልከ | አቅትልክሙ | አቅትልኪ | አቅትልክን |
| » | » | » | » |

**ንሕነ**

| | | | |
|---|---|---|---|
| አቅተልናሁ/ኖ | አቅተልናሆሙ/ኖሙ | አቅተልናሃ/ና | አቅተልናሆን/ኖን |
| ናቀትሎ | ናቀትሎሙ | ናቀትላ | ናቀትሎን |
| ናቅትሎ | ናቅትሎሙ | ናቅትላ | ናቅትሎን |
| » | » | » | » |

| | | | |
|---|---|---|---|
| አቅተልናከ | አቅተልናክሙ | አቅተልናኪ | አቅተልናክን |
| ናቀትለከ | ናቀትለክሙ | ናቀትለኪ | ናቀትለክን |
| ናቅትልከ | ናቅትልክሙ | ናቅትልኪ | ናቅትልክን |
| » | » | » | » |

## ፲፩.፰.፯ “ቦዝ” አንቀጽ ዝርዝር እርባታ

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| ውእቱ | ቀቲሎሁ | ቀቲሎሆሙ | ውእቶሙ | ቀቲሎሙ | |
| | ቀቲሎሃ | ቀቲሎሆን | | ቀቲሎሙሁ | ቀቲሎሙሆሙ |
| | ቀቲሎከ | ቀቲሎክሙ | | ቀቲሎሙሃ | ቀቲሎሙሆን |
| | ቀቲሎኪ | ቀቲሎክን | | ቀቲሎሙከ | ቀቲሎሙክሙ |
| | ቀቲሎኒ | ቀቲሎነ | | ቀቲሎሙኪ | ቀቲሎሙክን |
| | | | | ቀቲሎሙኒ | ቀቲሎሙነ |

| ይእቲ | | ውእቶን | |
|---|---|---|---|
| ቀቲላሀ | ቀቲላሆሙ | ቀቲሎንሀ | ቀተሎንሆሙ |
| ቀቲላሃ | ቀቲላሆን | ቀቲሎንሃ | ቀቲሎንሆን |
| ቀቲላከ | ቀቲላክሙ | ቀቲሎንከ | ቀቲሎንክሙ |
| ቀቲላኪ | ቀቲላክን | ቀቲሎንኪ | ቀቲሎንክን |
| ቀቲላኒ | ቀቲላነ | ቀቲሎንኒ | ቀቲሎንነ |

| አንተ | | አንትሙ | |
|---|---|---|---|
| ቀቲለከሀ | ቀቲለከሆሙ | ቀቲለክሙሀ | ቀቲለክሙሆሙ |
| ቀቲለከሃ | ቀቲለከሆን | ቀቲለክሙሃ | ቀቲለክሙሆን |
| ቀቲለከኒ | ቀቲለከነ | ቀቲለክሙኒ | ቀቲለክሙሃ |

| አንቲ | | አንትን | |
|---|---|---|---|
| ቀቲለኪሀ | ቀቲለኪሆሙ | ቀቲለክንሀ | ቀቲለክንሆሙ |
| ቀቲለኪሃ | ቀቲለኪሆን | ቀቲለክንሃ | ቀቲለክንሆን |
| ቀቲለክኒ | ቀቲለክነ | ቀቲለክናኒ | ቀቲለክናነ |

| አነ | | ንሕነ | |
|---|---|---|---|
| ቀቲልየሀ | ቀቲልየሆሙ | ቀቲለነሀ | ቀቲለነሆሙ |
| ቀቲልየሃ | ቀቲልየሆን | ቀቲለነሃ | ቀቲለነሆን |
| ቀቲልየከ | ቀቲልየክሙ | ቀቲለነከ | ቀቲለነክሙ |
| ቀቲልየኪ | ቀቲልየክን | ቀቲለነኪ | ቀቲለነክን |





## ምዕራፍ ፲፪.

## ክፍላተ ንግግር/ የንግግር ክፍሎች

ሰው ሐሳቡን በንግግርም ሆነ በጽሑፍ የሚገለጽባቸው ቃላት ክፍላተ ንግግር ይባላሉ ማንኛውም ቋንቋ ስልቱ ተመርምሮ እንደ ቋንቋው ስልትና ብልጽግና የንግግሩ ክፍል ይወሰናል:: ክፍላተ ንግግር በልዩ ልዩ ቋንቋዎች ቁጥራቸው የተለያየ ነው:: በግእዝ ቋንቋ ፲፩ የንግግር ክፍሎች አሉ::እነርሱም:-

፩. ስም/ዘር ና ነባር/
፪. መስተአምር
፫. ቅጽል
፬. ተውላጠ ስም
፭. ግሥ
፮. አንቀጽ አጎላማሽ
፯. ደቂቅ አገባብ
፰. አዳማቂ
፱. ዐቢይ አገባብ
፲. ንዑስ አገባብ
፲፩. ቃለ አጋኖ ናቸው::

## ፲፪.፩. ስም/ዘር ና ነባር/

### ፲፪.፩. ፥ ፩. ስም

ስም ማንኛውም ህላዌ ሰውም ሆነ እንስሳ አምላክም ሆነ መላእክት ባህርይ ወይም አካል ያለውም ሆነ የሌለው የሚጠራበት ቃል ነው።

***ምሳሌ፡-*** ሰብእ ፣ አንበሳ፣ ሰማይ ፣ ባሕር፣ አምላክ

**ስም** በአራት ዋና ዋና ክፍሎች ይከፈላል፡-

- ፩፥ ስመ ኵሉ/የወል ስም
- ፪፥ ስመ ተጸውዖ /የመጠርያ ስም/
- ፫፥ ስመ እንግልጋ /የጥቅል ስም/
- ፬፥ ስመ ረቂቅ /የነገር ወይም የግብር ስም/

### ፲፪.፩.፩. ስመ ኵሉ/የወል ስም

የወል ስም ማለት አንድ ዓይነት የሆነ የጋራ ወይም የሁሉም ስም ማለት ነው። የሰዎችን፣ የነገሮችን ስብስብ በአንድነት የሚገልጽና ለቤት አገልግሎት የሚሆኑ ሰው የሰራቸው ቁሳቁስ የሚጠሩበት ስያሜ ነው።

***ምሳሌ፡-*** ሰብእ፣ ላሕም ፣ወልድ ፣ቤት ፣መንጦላዕት፣ ዐራት ፣ መንበር የመሰለውን ሁሉ ነው።

### ፲፪.፩.፪. ስመ ተጸውዖ /የመጠርያ ስም/

የተጸውዖ ስም ማለት ማንኛውም ፍጥረት ከፈጣሪው የተለየ ለግሉ ስም ወጥቶለት የሚጠራበት ስም ነው።

***ምሳሌ፡-*** ጴጥሮስ፣ ዳዊት ፣ኢትዮጵያ፣ ጎንደር፣ ግዮን ፣ኢየሩሳሌም የመሰለውን ሁሉ ነው።





☞ በተጸውዖ ስም ላይ ተደርበው የሚነገሩ የአክብሮት የማዕረግ የተዛምዶ የተቀብዖ/የሹመት/ስሞች አሉ።

ምሳሌ፡- ምዕተሐራ ፣ሊቀሊቃውንት፣ ርዕሰ ብሔር ፣ ረቢ፣ ጳጳስ፣ ዲያቆን የመሰለውን ሁሉ ነው።

### ፲፪.፩.፫. ስመ እንግልጋ /የጥቅል ስም/

የጥቅል ስም ውስጡ ብዛት ያለው አንድ ስብስብ የሚጠራበት ነው። በውስጡ ብዙ የወል ስም የያዘ ነው።

ምሳሌ፡- ሕዝብ ፣ መርዔት፣ ሐራ፣ ፍጥረት

### ፲፪.፩.፬. ስመ ረቂቅ /የነገር ወይም የግብር ስም/

ስመ ረቂቅ ማለት በዓይን የማይታይ፣ በእጅ የማይዳሰስ፣ በዓይን ታይተው፡ በእጅ ፣ የማይዳሰሱ፣ በጆሮ ፣ ተሰምተው፣ በዓይን የማይታዩ፣ ዓይነትን ግብርንና ሁኔታን የሚያመለክቱ ጉልህ ሆነው የማይጨበጡ በአእምሮ ብቻ የሚታሰቡ ረቂቅ ነገሮች የሚጠሩበት ስም ነው።

ምሳሌ፡- ሕይወት፣ ሞት፣ ድንቁርና፣ ቅዳሴ ፣ ህልም፣ ንዴት፣ እግዚአብሔር ፣ አእምሮ፣ ጽላሎት ፣ብርሃን የመሰለውን ሁሉ ነው።

***ምልማድ ፲፪.፩.፡-***

**የሚከተሉትን ስሞች ክፍላቸውን ግለጽ።**

ምሳሌ፡- ኤፍራጥስ = ስመ ተጸውዖ

| | | |
|---|---|---|
| ፩.ነዳይ | ፬.እስራኤል | ፯.ምግባር |
| ፪.ላሊበላ | ፭.ቅፕርት | ፰.አህዛብ |
| ፫.ሙቀት | ፮.ነፋስ | |

**፪. የስም ሙያ :-** ማንኛውም ቃል በዐረፍተ ነገር ውስጥ የሚገኝበት ሁኔታ ሙያ ይባላል:: ስም እንዳገባቡ አራት ሙያዎች አሉት::

ይኸውም:- ፩. ባለቤት ፪. የሰሚ ባለቤት

፫. ተሳቢ ፬. ዘርፍ መሆን ነው::

**፩. ባለቤት:-** ስም በዐ/ነገር ውስጥ ባለቤት ሲሆን አንቀጽ ከነንዙ የሚነገርለት ማለት ነው::

ምሳሌ:- ሞተ ሰብእ:: ሞተ አንቀጽ ሲሆን ሰብእ ባለቤት ነው::

- አበበ መጽአ ኀበ ቤተክርስትያን::
- ተሐንጸ ቤት ዲበ ኰኵሕ::
- ሐዋርያት ሐረዩ ማትያስሃ::
- እሙንቱ ኀሠሥዋ ለነፍስየ::

**፪ የሰሚ ባለቤት :-** መጣራት (ጽዋዔ) ካለ በሩቅም በቅርብም ይነገራል ለሩቅ ሲሆን ባለቤቱ ተጠሪ ሲባል በቅርብ ሲሆን ባለቤቱ ሰሚ ይባላል:: የሰሚ ባለቤት የሚባለው ሁል ጊዜ ዐረፍተ ነገር የሚነገረው ለሁለተኛ መደቦች (አንተ፣ አንቲ፣ አንትሙ ፣አንትን) ሲሆን ነው:: ሲነገርም ኦ ን ይዞም ሳይዝም ሊሆን ይችላል::

***ምሳሌ*** :- ኦ አዳም መሬት አንተ ::

- አቡነ ዘበሰማያት ::
- ኦ ወልድየ ስምዐኒ ዘእብለከ
- ኦ ማርያም ንጽሕት አንቲ::
- ወለነፍስየሰ አንተ አድሐንካ ::





**፫ ተሳቢ:-** ተሳቢ መሆን አንዱ የስም ሙያ ሲሆን ርቱዕ ተሳቢ ወይም ኢርቱዕ ተሳቢ በመባል በ ሁለት ይከፈላል ::

**ሀ. ርቱዕ ተሳቢ** የሚባለው ገቢር አናግሮ ለገቢር ግሥ ሲሳብ ነው::

ምሳሌ :- አምላክ ፈጠረ ዓለመ::

- አድኀነ ርእሰከ ወኪያነሂ::
- ኪያከ እሴብሕ እግዚኦ::
- ሐጸበ እዴሁ::
- ተሰብረ እዴሁ::

- የወንዝና የሀገር ወይም የተጸውዖ ስም ሃ ን አስከትሎ ይገባል:: ሃ ን ካልያዘ ግን ገቢር አናግሮ ይገባል ::

***ምሳሌ*** :- ተለው ሐዋርያት ክርስቶስሃ::

ወፈነዎሙ ቤቴልሔምሃ::

አርድእት ሐወጹ ኢየሩሳሌምሃ::

. ሃ አንዳንድ ጊዜ ከተውላጠ ስም ጋር ይገባል::

***ምሳሌ:-*** መነሃ::

እገሌሃ::

. የሚከተሉትን ቃላት ተሳቢዎች ሲሆኑ በሕገወጥነታቸው በተለይ ማጥናት ያስፈልጋል::

| ስም | የስም ዝርዝር በመራሕያን | ተሳቢ | የተሳቢ ዝርዝር |
|---|---|---|---|
| አብ | አቡየ፣አቡነ ... | አበ | አባየ ፣ አባነ ... |
| ሐም/ሐማት/ | ሐሙየ፣ሐሙነ... | ሐመ | ሐማየ ፣ሐማነ ... |
| አፍ | አፉየ፣አፉነ... | አፈ | አፉየ ፣ አፉነ ... |
| እኍ | እኁየ፣እኁነ... | እኆ | እኃየ ፣ እኃነ ... |
| እድ | እዴየ፣እዴነ... | እደ | አዴየ፣ እዴነ... |

**ለ. ኢ ርቱዕ ተሳቢ:-** ቃሉን ምንም ሳይለውጥ ደቂቅ አገባብ ይወድቅበታል::

ምሳሌ:- እሑር ኀበ ቤትየ::

- ረፊቀ ዲበ መንበር::
- ሞተ በእንተ ሀገሩ::

**፬. ዘርፍ:-** የሚባለው ባለገንዘብነትን ወይም የተፈጥሮ መገኛነትን ይዞ ከባለቤቱ ወይም ከተሳቢው ቀጥሎ የሚገኘው ስም ነው::

*ምሳሌ:-* ቤተ ክርስቲያን:: ለሚለው ዋናው ቃል ቤት ሲሆን ባለገንዘብነት ለመግለጽ ክርስቲያን ተቀጥሎአል::ስለዚህ ዘርፍ የሚገልጸው ባለቤትነትን ነው::

- ወንጌለ ማርቆስ::
- መስቀሉ ለክርስቶስ::
- ቤታ ለእምየ::
- ወርቀ ኢትዮጵያ:: /የተፈጥሮ መገኛነት/

**ዘርፍ በ፫ መንገድ ይጣመራል/ይያያዛል/**

*ይኸውም:-* ሀ. በማናበብ

ለ. በ "ለ"

ሐ. በ ዘ፣እንተ፣እለ፣ይዛረፋሉ

**ሀ. በማናበብ** ዘርፍ በተነባቢነት የሚያያይዘው ገቢር መሆን የሚችሉ ስሞችን ነው::

*ምሳሌ:-* ፍኖተ ሰላም

- ብእሴ እግዚአብሔር
- ደብተራ ኦሪት
- ከበሮ ማኅሌት





**ለ. በ "ለ" :-** ለ የሚያያይዘው ስምን ዘርዝሮ ሲሆን አንድና ብዙ ወንድና ሴትን ያያይዛል::

*ምሳሌ:-* ቤት የሚለው ስም ሲዘረዘር ለውእቱ ቤቱ ይሆናል:: በ ለ ዘርፍ አያያዥነት ሲነገር

*ለምሳሌ:-* ቤት እና ዮሐንስ:: ቤቱ ለዮሐንስ:: ይሆናል::

- ⇒ ቤቶን ለአንስት::
- ⇒ ወልዱ ለንጉሥ::
- ⇒ ምክሮሙ ለጠቢባን::
- ⇒ ቀስተ መሐሳሁ ለኖኅ::እንላለን::

**ማስታወሻ:-** ከላይ በ ለ ከተያያዙት ቀለማት ተሳቢ ወይም ባለቤት ተከታይ ሆኖ ለ ቀዳሚ ሲሆን **ዘርፍ ደፊ** ይባላል ይኸውም አብዛኛውን ጊዜ ለቅኔ ቤት /ለቅኔ/የሚያገለግል ነው::

*ምሳሌ:-* ለዮሐንስ ቤቱ::

- ⇒ ለአንስት ቤቶን::
- ⇒ ለንጉሥ ወልዱ::
- ⇒ ለጠቢባን ምክሮሙ::
- ⇒ ለኖኅ ቀስተ መሐሳሁ::

ዘርፍ ከሁለት ቃል በላይ ከተያያዘ የዘርፍ ዘርፍ ይባላል::

መሰንቆ መዝሙር የተያያዙት ሳይዘረዘሩ ነው በአጠቃቀማቸው ዙርያም ሁለት ዘርፍ ለምሳሌ መንበረ ክብር ብንል የዘርፍ ዘርፍ ለመድረግ ክብር የሚለውን መዘርዘርና አያያዥ መጠቀም ነው::

መንበረ ክብሩ ለሰሎሞን:: /የዘርፍ ዘርፍ ሆነ ::

መሰንቆ መዝሙሩ ለዳዊት:: /የዘርፍ ዘርፍ

ለዳዊት መሰንቆ መዝሙሩ:: /ዘርፍ ደፊ

ለሰለሞን መንበረ ክብሩ::/ዘርፍ ደፊ

ሐ. <u>ዘ፣እንተ፣እለ፡-</u> የሚያያይዙት ሳይዘረዝሩ ነው፡፡ በአጠቃቀማቸውም ዙሪያ ሁለት ዓይነት አመለካከት አለ፡፡

የመጀመርያው አመለካከት ዘ -ለአንድ ለብዙ

እንተ- ለአንድ ብቻ/ጾታ ሳይለይ

እለ ለብዙ

***ምሳሌ*** ፡- አማልክት ዘአህዛብ፡፡

⇒ ወለት ዘንግሥት

⇒ መላእክት እለሰማይ፡፡

⇒ ዕቁባት እለ ሰሎሞን፡፡

⇒ ቤት እንተ እኅትየ፡፡

⇒ ባሕታዊ እንተ ገዳም፡፡

⇒ ቤት ዘንጉሥ፡፡

⇒ ባሕታዊ እንተ ጎጃም፡፡

ሁለተኛው አመለካከት፡- ዘ -ለወንድ ብቻ

⇒ እንተ- ለሴት ብቻ

⇒ እላ - ለብዙ

***ምሳሌ፡-*** መዝሙር ዘዳዊት፡፡

⇒ ብእሲት እንተ ሎጥ፡፡

⇒ መዘምራን እለዳዊት

በ ዘ፣ እንተ፣ እለ፣ የተያያዙ ስሞች ዘርፍ ሊደፉ ይችላሉ፡፡

⇒ ዘአህዛብ አማልክት፡፡

⇒ እንተ ንግሥት ወለት፡፡

⇒ እለ ሰሎሞን ዕቁባት፡፡





## <u>፲፪.፪. መስተአምር</u>

መስተአምር ትርጉሙ ማወቅያ መታወቅያ ማለት ነው፡፡ በሁለት ተናጋሪዎች መካከል ሦስተኛ ሰው ወይም ነገር የተወቀ ሲሆን ያ ያልኩህ እያሉ ከመደጋገም ለመዳን ሳድሱን ካዕብ እያደረጉ በተቀረው ግን ሁን የመሰሉ ቀለማት እየጨመሩ የሚነጋገሩበት ስልት ነው፡፡

⇒ ተክል - ተክሉ

⇒ ብእሲ - ብእሲሁ

***ምሳሌ*** ፡- መጽአ ብእሲ፡፡ ብእሲ የሚለውን ብእሲሁ ብለን መጽአ ብእሲሁ ፡፡እንላለን

⇒ በጽሐ ዕፁ ለበሊዕ፡፡

## <u>፲፪.፫. ቅጽል</u>

### <u>፲፪.፫. ÷ ፩. ቅጽል</u>

ቅጽል የሚለው ቃል ተቀጸለ ተቀዳጀ ከሚለው ግሥ የወጣ ሲሆን ቅጽል ማለት ተጨማሪ ቃል መለያ፣ ምልክት ማለት ሲሆን ቅጽል የባለቤትን ስምና ግብር ጠባይና አኳኋን መልክ ዓይነት ወርድ ቁመት ስፍርና ቁጥር ሌላውንም ሁሉ የሚያሳይ የሚገልጥ የስምና የግብር ፍካሬ ማለት ነው፡፡

***<u>ቅጽል</u>*** ፡- ዘር ቅጽል እና ነባር ቅጽል ተብሎ በሁለት ይከፍላል፡፡

፩÷ ዘር ቅጽል፡- አንቀጽ ያለው ሲሆን የሚከተሉትን ያጠቃልላል፡፡

*ሀ/* <u>ውስጠ ዘ ቅጽል</u> ፡- በውስቱ የአማርኛ ፍቺ የ ያለበት ቅጽል ማለት ነው፡፡

ምሳሌዎች፡- ቅቱል ኮነ ሰማዕተ፡፡

ጻድቅ ኢዮብ ወረሰ መንግሥተ፡፡

ምውት አልአዛር ተንሥአ።

ንጉሥ ዳዊት ዘመረ መዝሙረ።

ሐጺር ዘኬዎስ ይትወከፍ ነግደ።

ለ. *<u>መስም ውስጠ ዘ ቅጽል</u>*

ምሳሌ፡- መፍክር ዳንኤል ፍከረ ሕልመ

መዝምር ዳዊት ዘመረ መዝሙረ

ሐ. *<u>ወገን ውስጠ ዘ ቅጽል</u>* ፡- ወገናዊነትን የሚያሳይ የቅጽል ዓይነት ሲሆን በመድረሻው ‹‹ዊ›› እና ‹‹ይ›› ን ይጨምራል

ምሳሌዎች ፡- ምድራዊ አዳም አምጽአ ሞተ።

አረጋዊ አብርሃም ጸድቀ በአሚን።

መ. *<u>አኀዝ ቅጽል</u>* ፡- ቁጥርን መጠንን የሚገልጽ ቅጽል ሲሆን ዝርዝር አኃዝ ቅጽል ወይም በውስንነት የሚነገር አኀዝ ቅጽል እና መድበል አኀዝ ቅጽል ወይም ያለውሳኔ የሚነገር አኀዝ ቅጽል ተብሎ በሁለት ይከፈላል።

ምሳሌዎች ፡- ክልኤቱ ሰብአዓይን ተፈነዉ እምኀበ ኢያሱ

አሐዱ ብእሴ ይወርድ ኀበ ግብፅ

ብዙኀን ኖሎት መጽኡ

ኵሉ ብርክ ይስግድ ለስሙ።

ሠ/ *<u>ዘር ውስጠ ዘ ቅጽል</u>*፦ ዘርፍ እየያዘ ለሳም የሚቀደል የቅጽል ዓይነት ሲሆን ዘርፍ ካልያዘ ወይም ካልተናበበ ቅጽል አይሆንም ባለቤት ወይም በቂ ውስጠ ዘ ይሆናል እንጂ

ምሳሌዎች፡- ክብረ ቅዱሳን ክርስቶስ ገብረ ሰላመ ።

አክሊለ ሰማዕት ወልድ ታስቅለ

ፍቅር ያስተማሕር

ምክር ሠናይት ።





ረ/ *<u>መድበል ውስጠ ዘ ቅጽል</u>* ፦ መድበል ጾታ ሳይለይ ሴቶችንም ወንዶችንም የሚይዝ አድራጊነትን የሚያሳይ ዘር ሲሆን በቅጽልነት ያገለግላል።

ምሳሌዎች ፡- ቅደምት ሰብእ ኮኑ ጸሐርተ

ዐበይት ነቢያት ሠርዐ ሕገ

፪÷ *<u>ነባር ቅጽል</u>* ፡- ግስ የሌለው የተጸውዖ ስም እና አንባብን የያዘ ቅጽል ሲሆን መጠይቅ ውስጠ ዘ እና ግልጸ ዘ ነገር ቅጽሎችም ይገኙበታል።

ሀ/ *<u>መተርጎም ቅጽል</u>*

ምሳሎዎች ፡- ያዕቆብ እስራኤል ወለደ ደቂቀ

ስምዖን ጴጥሮስ ተሰቅለ ቍልቍሊተ

ለ/ ነባር ውስጠ ዘ ቅጽል

ምሳሌዎች፡- አድያመ ዮርዳኖስ ገሊላ አስተጋብኦት ነቢያተ

ከነአን ሀገረ አብርሃም ታውሕዝ ሐሊበ

ሐ/ *<u>ንዑስ ቅጽል</u>*፦ መጠይቅ ተውላጠ ስም እየሆን የሚቀጸል የቅጽል አይነት ሲሆን ንዑስ መባሉ አንቀጽ ላይ ወድቆ ማሰሪያነትን ስለማያስቀር ነው።

ምሳሌ፡- ምንት ግብር ይሤኒ ለሰብእ እም አይቴ ሀገር መጽአ ዝንቱ ብእሲ

## *ሌሎች የቅጽል ዓይነቶች*

፩ ወገናዊ ቅጽል ፪ የግብር ቅጽል ፫ የዓይነት ቅጽል

፬ አመልካች/ደቂቅ/ ቅጽል ፭ መጠይቅ/ንዑስ/ ቅጽል

፮ አገናዛቢ ቅጽል ፯ አዛማጅ/ግልጸዘ/ ቅጽል ፰ አኀዝ ቅጽል

*<u>ወገናዊ ቅጽል</u>*፡- በተጸውዖ ስምም ሆነ በሀገር ስም ላይ ወድቆ ወገንነትን ፣ጎሳነትን ፣ወይም አባትነትን የሚያሳይ የቅጽል ክፍል ወገናዊ ቅጽል ይባላል።

**ለ**ወገናዊ ቅጽል መድረሻውን ራብዕ እያደረገ በተባዕታይ ነጠላ "**ዊ**" በአንስታይ ነጠላ **ዊት** በተባዕታይ ብዙ **ውያን** በአንስታይ ብዙ **ውያት** በመጨመር ይገኛል::

ምሳሌ:-

| ስም | ነጠላ ወገን ቅጽል | ብዙ ወገን ቅጽል |
|---|---|---|
| ኢትዮጵያ | ኢትዮጵያዊ/ዊት | ኢትዮጵያውያን/ውያት |
| እስራኤል | እስራኤላዊ/ዊት | እስራኤላውያን/ውያት |
| ሰማይ | ሰማያዊ/ዊት | ሰማያውያን/ውያት |
| ምድር | ምድራዊ/ዊት | ምድራውያን/ውያት |

***የግብር ቅጽል*** :- ማንኛውም ፍጥረት የሚሠራውን የሥራውን ሙያውንና ግብሩን የሚያሳይ የቅጽል ክፍል የግብር ቅጽል ይባላል::

. የግብር ቅጽል የሚባሉት ሣልስና ሳድስ ቅጽል ፣መስም ውስጠዘና መድበል ናቸው::

ምሳሌ:- ሣልስ ቅጽል:- መሐሪ፣ ቀታሊ፣ ሠዓሊ

ሳድስ ቅጽል:- ምሁር፣ ቅቱል፣ሥዑል፣ቡሩክ፣ስቡሕ

መስም ውስጠዘ ቅጽል:- መምህር፣ መኰንን፣ መስፍን

መድበል ቅጽል:- ቀተልት፣ጠበብት፣ ነገሥት

***የዓይነት ቅጽል:-*** የአንድን ነገር ፣የሰውን፣ የእንስሳን ወይንም የዕቃን አኳኃን ቁመትና ቀለም ዓይነት የሚገልጽ ቅጽል ነው::

ምሳሌ:-

ቀይሕ :- መልክዓ ደምየ ቀይሕ ውእቱ

ሐጺር :- ቆሙ ለዘኪዮስ ሐጺር ውእቱ

ጸሊም :- እምየ ጸሊም አልባሳት ገዝአት ልየ





***አመልካች /ደቂቅ/ቅጽል:-*** ከንደኞቹ ለይተን ይህ ወይም ያ እያልን ነገርን እንስሳን ወይም ሰውን የምናሳይበት የቅጽል ክፍል አመልካች /ደቂቅ/ቅጽል ይባላል::

| ምሳሌ:- ***ቅርብ*** | ***ሩቅ*** |
|---|---|
| ዝ/ዝንቱ/ - ይህ | ዝክቱ፣ዝኩ - ያ |
| ዛ/ዛቲ/ - ይህች | እንታክቲ -- ያች |
| እሉ/እሉንቱ/ እኒህ | እልክቱ እነኛ/እነዚያ |
| እላ/እላንቱ/ እኒህ | እልክቱ እነኛ/እነዚያ |

***ምሳሌ:-*** ዝንቱ መጽሐፍ ዚአየ ወእቱ::

ዝንቱ ብእሲ::

እሉ ዕደው ይሔውጹ ለእልክቱ አንስት::

***ማስታወሻ:*** ከዚህ በላይ ያየናቸው አመልካች ቅጽሎች የመራሕያን አመልካች ሲሆኑ የሚኖራቸው አገልግሎት ተመሳሳይ ነው::

⇒ አመልካች ቅጽሎች ከስም በፊት በመግባት ቅጽል ይሆናሉ ብቻ ቸውን ከሆኑ ግን ተውላጠ ስም /የስም ምትክ/ይሆናሉ::

ምሳሌ:- ውእቱ ብእሲ -ያ ሰው:: ዝንቱ ብእሲ- ይህ ሰው::

አነ ጳውሎስ - እኔ ጳውሎስ ነኝ:: ጳውሎስ አነ - ጳውሎስ ነኝ::

***መጠይቅ /ንዑስ/ቅጽል፡-*** የነገርም ሆነ የሰውን አኳኃን ጠይቀን የምንረዳበት የቅጽል ክፍል መጠይቅ /ንዑስ/ቅጽል ይባላል።

ምሳሌ፡-

| ***ነጠላ*** | ***ብዙ*** |
|---|---|
| መኑ፣አይ - የት/የትኛው/ሰውንና ነገርን ለመጠየቅ/ | እለመኑ - የትኞቹ እነማን |
| ስፍን - ሰንት | እስፍንት - ስንቶች |
| ምንት - ምን | ምንታት - ምኖች |

***ምሳሌ በዐ/ነገር፡-***

- ☞ መኑ መጽአ።
- ☞ እለመኑ ሖሩ።
- ☞ አይ ተሰቀለ ክርስቶስ።
- ☞ ምንት ይበቍዖ ለሰብእ።
- ☞ እስፍንቱ ሐዋርያት ሐረየ ክርስቶስ።
- ☞ አያት አዝማዲከ እምኩሉ ሰብእ።
- ☞ ኦ ሰብእ ምንተ ትትዌበይ እንዘ መሬት አንተ።
- ☞ ምንት ሰማዕከ።

***አገናዛቢ ቅጽል*** ፡- ለስም ዝርዝር የሚረዱ ባዕዳን ቀለማት አገናዛቢ ቅጽል ይባላሉ።

***ምሳሌ፡-***

| ***ነጠላ*** | | ***ብዙ*** | |
|---|---|---|---|
| አነ- | የ | ነሕነ- | ነ |
| አንተ - | ከ | አንትሙ - | ክሙ |
| አንቲ - | ኪ | አንትን - | ክን |
| ውእቱ - | ካዕብ/ሁ/ | ውእቶሙ - | ሙ/ሆሙ |
| ይእቲ - | ራብዕ/ሃ/ | ውእቶን - | ን/ሆን |

⇒ ከ፣ኪ፣ክሙ፣ክን.... ከግሥ ጋር ሲመጡ መዘርዝራነ ተውላጣተ ስም ይባላሉ።

⇒ የ፣ነ፣ክሙ..... ከስም ጋር ሲመጡ አገናዛቢ ቅጽል ይባላሉ።





***አዛማጅ /ግልጸ ዘ/ቅጽል*** ፡- የማሰርያ አንቀጽነትን አስቀርተው የሚቀጸሉ ቀለማት አዛማጅ/ ግልጸ ዘ/ ቅጽል ይባላሉ።

እነርሱም፡- ዘ፣እንተ፣እለ ናቸው። እነዚህ ቀለማት በቅጽልነታቸው አዛማጅ /ግልጸ ዘ/ ሲባሉ አንቀጽን ከማሰርያነት በማስቀረታቸው ዐቢይ አገባብ ይባላሉ።

***ምሳሌ፡-***

- ☞ ጳውሎስ ዘተጸውዐ ወተፈልጠ ለትምህርተ ወንጌል።
- ☞ ፊቨን እኅትነ እንተ ትትለአክ ለቤተክርስቲያን።
- ☞ ቦ ሰብእ እለ ተሐርዩ እምከርሠ እሞሙ።

***ማስታወሻ*** ፡- አዛማጅ ግልጸ ዘ ቅጽሎች ስም ከአጠገባቸው ከሌለ አዛማጅ ተውላጠ ስም ይባላሉ። የአንቀጽ ባለቤት ይሆናሉ።

***ምሳሌ፡-*** ዘየአምን በወልድ የሐዩ።

እለ ትነብሩ ተንሥኡ።

## ፲፪.፩. ተውላጠ ስም /የስም ምትክ/

ተውላጠ ስም/የስም ምትክ/

በስም ፈንታ/ ምትክ ሆኖ /ገብቶ/ስምን አህሎና መስሎ የሚሠራ ቃል ሁሉ ተውላጠ ስም ይባላል። ተውላጠ ስም በ ፯ ክፍሎች ይከፈላል።

- ሀ. ምድብ ተውላጠ ስም
- ለ. ድርብ ተውላጠ ስም
- ሐ. አገናዛቢ ተውላጠ ስም
- መ. አጸፋ ተውላጠ ስም
- ሠ. አዛማጅ ተውላጠ ስም
- ረ. አመልካች ተውላጠ ስም
- ሰ. መጠይቅ ተውላጠ ስም

***ምድብ ተዉላጠ ስም*** :- የስም ቦታን ተክተው የሚያገለግሉ መራሕያን ምድብ ተውላጠ ስሞች ይባላሉ::

***ምሳሌ:-*** አንተ፣ ወእቱ፣ ንሕነ........

***ድርብ ተውላጠ ስም*** :- በምሥጢር መራሕያንን ደርበው የሚነገሩ ተ ውላጠ ስሞች ድርብ ተውላጠ ስሞች ይባላሉ::

***ምሳሌ:-***

ለሊሁ - ራሱ　　ለሊሆሙ - ራሳቸው
ለሊሃ - ራሷ　　ለሊሆን - ራሳቸው
ለሊከ - ራስህ　　ለሊክሙ - ራሳችሁ
ለሊኪ - ራስሽ　　ለሊክን - ራሳችሁ
ለልየ - ራሴ　　ለሊነ - ራሳችን

***አገናዛቢ ተውላጠ ስም*** :- እነዚህ የ ዘ፣ እንተ ፣እለ ዝርዝሮች ናቸው::

ምሳሌ:-

- ☞ ዚአየ፣ ዚአነ ፣ዚአከ....
- ☞ እንቲአየ፣ እንቲአነ ፣ እንቲአከ....
- ☞ እሊአየ፣ እሊአነ፣ እሊአከ....

***.አጸፋ ተውላጠ ስም***:- በግሥ መነሻና መድረሻ እየገቡ በምድብ ተውላጠ ስም ስም የሚሰሩ ቀለማት አጸፋ ተውላጠ ስም ይባላሉ::

እነዚህም በሁለት ይከፈላሉ::

ሀ. መዘርዝራነ ተውላጠ ስም :- ኩ፣ ከ፣ክሙ፣ኪ፣ክን - - - -

ለ. አሥራው:- ተ፣አ፣የ፣ነ





***አዛማጅ ተውላጠ ስም:-*** ዘ፣እንተ፣እለ ከአጠገባቸው ስም ካለ ቅጽል ይባላሉ ከሌለ ደግሞ አዛማጅ ተውላጠ ስም ይባላሉ:: የአንቀጹም ባለቤቶች ይሆናሉ::

ምሳሌ:- እለ ትነብሩ ተንሥኡ::

***አመልካች ተውላጠ ስም***:- አመልካች /ደቂቅ/ ቅጽሎች ከስም ጋር ተቀጽለው ካልተነገሩ አመልካች ተውላጠ ስም ይባላሉ::

***ምሳሌ***:- ዝ፣ዝንቱ፣ዛቲ፣ እሎንቱ ፣ እሎንተ ፣ እላ ፣ እላንቱ

***መጠይቅ ተውላጠ ስም*** :- መጠይቅ /ንዑስ/ ቅጽሉች ከስም ጋር ካልተነገሩ መጠይቅ ተውላጠ ስም ይባላሉ::

ምሳሌ :- መኑ፣ ምንት፣አይ

*መኑ ተኀስስ ዝየ::*　　አይ አንገሠ ሳሙኤል::

***የተውላጠ ስም ሙያ***:- ተውላጠ ስም እንደ ስም አራት ዓይነት ሙያ አለው::ይኸውም:-

ሀ. ባለቤት:- አነ ፣ንሕነ፣ አንተ ፣አንቲ- - - - -

ለ. ተሳቢ:- ኪያየ ፣ኪያነ፣ ኪያከ - - - -

ሐ. ዘርፍ:- ዚአየ፣ ዚአነ፣ ዚአሁ - - - -

እንቲአየ፣ እንቲአነ፣ እንቲአሁ - - - -

መ. ተቀባይ:- ሊተ፣ ለከ፣ ለክሙ፣ ለኪ፣ለክን - - - -

ብየ፣ ብነ፣ ብከ፣ብክሙ፣ብኪ - - - - -

## ፲፪.፭. ግስ

ግሥ የ ዐ/ነገር ማሰሪያ አንቀጽ ነው።

ምሳሌ፡- ቀተለ፣ ቀደሰ፣ አእመረ

አበበ ቀተለ ከይሴ።

ስለ ግሥ የተጻፈውን ከላይ ተመልከት።

## ፲፪.፮. አንቀጽ አጎላማሽ /ተውሳከ ግስ/

### ፲፪.፮.፥ ፩.አንቀጽ አጎላማሽ

ከአንቀጽ ወይም ከግሥ አጠገብ እየዋሉ ግሥን የሚያጋንኑ ከፍ ከፍ የሚያደርጉ ቃላት አንቀጽ አጎላማሽ ወይም ተውሳከ ግሥ ይባላሉ።

. ተውሳከ ግሥ በ፱ ይከፈላል።

**፩. መስተአምራዊ ተውሳከ ግስ** ፡- መስተአምራዊ ማለት ማወቂያ መታወቂያ ማለት ነው። የ«ነ» ዝርዝሮች በዚህ ክፍል ይመደባሉ።

| | |
|---|---|
| ***ምሳሌ***፡- ነዋ /ነዮ እነሆ | ነዮሙ - እነኋቸው |
| ነያ - እነኋት | ነዮን - እነኋቸው |
| ነየከ - እነሆህ | ነየክሙ - እነኋችሁ |
| ነየኪ - እነሆሽ | ነየክን - እነኋችሁ |
| ነየ - እነሆኝ | ነየነ - እነሆን |

⇒ ነዋ በግዑ ለእግዚአብሔር ዘየአትት ኃጢአተ ዓለም።

⇒ ነያ እምከ።

⇒ ነዋ ወልድኪ።

⇒ ነዋ አመ ርእይዋ ለሀገርነ ሰዐሙ ምድረ





**፪. ኵነታዊ ተውሳከ ግስ**- የአንድን ነገር በምን ሁኔታና አኳኋን እንደተከናወነ የሚያመለክት ነው። የሚገኘውም ***ሳድስ ቅጽልና ስምን ገቢር*** አናግሮ ነው።

***ምሳሌ***፡- ፍጡነ ፣ ኅቡረ ፣ ሀኬተ ፣ ጽሚተ ፣ ግብተ

⇒ ፍጡነ ተንሥኡ ከመ ትርከብዎ ለሕፃን።

⇒ ጽሚተ ይመጽእ ሰራቂ።

⇒ ግብተ ይመጽእ ሞት።

**፫. መጠይቅ ተውሳከ ግስ**- ግሡን ጥያቄያዊ ለማድረግ እና ለአንክሮ የሚረዱ ናቸው።

ምሳሌ፡- ሁ ፣ ኑ ፣ ሚ ፣ ምንት ፣ አይቴ፣ እፎ ፣ ማእዜ

⇒ ተአምንሁ አንተ በወልደ እግዚአብሔር።

⇒ አይቴ አሐውር እመንፈስከ።

⇒ አይቴ ብሔራ ለጥበብ ወአይቴ ደወላ።

⇒ ሚ በዝኑ ጸላዕትየ።

⇒ መኑ የኀድገነ ፍቅሮ ለክርስቶስ ሕማምኑ ምንዳቤኑ፣ መጥባዕትኑ ኢኮነሁ።

**፬. መካናዊ ተውሳከ ግስ**- ቦታን ለማመልከት በግሥ ላይ ተጨምረው የሚነገሩ ናቸው።

***ምሳሌ፡-*** ዝየ፣ ህየ፣ ኵለሄ፣ ቅሩብ፣ ድኅረ፣ የማን፣ ጸጋም፣ ለፌ ፣ ወለፌ፣

⇒ ወሀለወት ህየ እሙ ለእግዚእ ኢየሱስ።

⇒ ያቀውም በየማኑ።

**፭. ጊዜያዊ ተውሳከ ግስ፡-** ጊዜን ለማመልከት ይረዳል።

***ምሳሌ፡-*** ዮም፣ ትማልም፣ ጌሠም፣ ይእዜ፣ ናሁ፣ ዓዲ፣ ጽባሕ፣ ሶቤሃ /አሜሃ/፣ዘልፈ

⇒ ዓዲ ኢበጸሐ ጊዜየ።

⇒ ዮም ንወድሳ ለማርያም።

⇒ ውእተ አሚረ ይሜስሉ ምሳሌ ሳዕሌክሙ::

***፮. አወንታ እና አሉታ ተውሳከ ግሥ***

ሀ. አወንታ ተውሳከ ግሥ

*ምሰሌ*:- እወ፣ አሆ፣ አሜን፣ አማን

☞ በአማን ተንሥአ እሙታን::

ለ. አሉታ ተውሳከ ግሥ:-

**ምሳሌ:-** ኢ፣ ኦል፣ አኮ፣ ሐሰ

***፯. አጋናኝ ተውሳከ ግሥ***:- የግሡን ድምጽ አጎላምሰው የሚናገሩ ናቸው::

ምሳሌ፦ ኬ ፣ ሶ፣ ኑ፣ እንቋዕ

☞ አድኅንሶ::

☞ አድኅንኬ ::

☞ ከለባትኒ ኑ ይበልዑ እምፍርፋራት::

***፰. አንዛዊ ተውሳከ ግሥ:-*** ከአንዛዊ ቅጽል የተገኘ ነው::

*ምሳሌ*፦ ምዕረ፣ ካዕበ /ዳግመ፣ ሥልስ፣ ርብዐ

☞ ሥልስ ጊዜ ትክህደኒ ዘእንበለ ይንቁ ዶርሆ::

***፱. መጠናዊ ተውሳከ ግሥ*** :- መጠንን የሚያመለክት ነው::

*ምሳሌ*፦ ኀዳጥ፣ ጥቀ፣ ፈድፋደ፣

☞ አቡየ ያፈቅረኒ ጥቀ::





# አገባብ

አገባብ መፍትው ርዕት ድሎት ከሚለው የግእዝ ቃል የወጣ ሲሆን መፍትው ርዕት ድሎት ማለት የተገባ ግቡ የሚገባ ሥርዓት ማለት ሲሆን አገባብ በሰዋስው ግእዝ የነገር አጣጣል የንባብ አስካክ ወይም መምህር የሚፈርደው ፍትሐ ሰዋስው ማለት ነው:: በሌላም በኩል አገባብ ማለት የብትን ቃል ሁሉ መሰብሰቢያና ማስማሚያ የቋንቋ ቅመም የንባብ ማጣፈጫ የምሥጢር መግለጫ ማለት ነው::

አገባብ በሰዋስው መነሻ መካከል መድረሻ ሊገባ ይችላል አገባብ የምንላቸው ሦስት ናቸው እነርሱም ዐቢይ አገባብ፣ ንዑስ አገባብ እና ደቂቅ አገባብ ተብለው ይታወቃሉ:: እሲህንም ከዚህ እንደሚከተለው እናያቸዋለን::

## ፲፪.፯. ደቂቅ አገባብ / መስተዋድድ/

በስም መነሻ ላይ እየተነገረ አንዱ ከሌላው በንግግር የሚዛመድበትን ሁኔታ የሚያመለክት ቃል ደቂቅ አገባብ /መስተዋድድ/ ይባላል::

ደቂቅ አገባብ የተባሉበት ምክንያት በአንቀጽ ላይ ስለማይወድቁ እና አንቀጹን ከማሰሪያነት ስለማያስቀሩ እና ተረፈ ንዑስ ስለሆነ ነው::

***ምሳሌ:-*** ቆመ እግዚእ ባሕር:: እነዚህ ተለያይተው የነበሩትን ስሜት እንዲሰጡ ለማድረግ ደቂቅ አገባብ እንጠቀማለን::

⇒ ቆመ እግዚእነ **ማዕከለ** ባሕር::

⇒ ፀንሰት ድንግል እንበለ ዘርዐ ብእሲ::

⇒ ኢይከብር ነቢይ በሀገሩ::

☛**ደቂቅ አገባብ:-** የሚዘረዘሩ እና የማይዘረዘሩ ተብለው በሁለት ይከፈላሉ::

**የማይዘረዘሩ:-** እስከ ፣ እም፣ እንበይነ....

**የሚዘረዘሩ:-** ላዕለ ፣ ከመ፣ እምነ.......

እነዚህ የሚዘረዘሩት አብዛኛውን መድረሻቸውን ኃምስ አድርገው በአገናዛቢ ቅጽል ይዘረዘራሉ።

ምሳሌ፡- ዲበ፡- ዲቤሁ ፣ ዲቤሆሙ፣ ዲቤሃ፣ ዲቤሆን . . . . . .

ከመ፡- ከማሁ፣ ከማሆሙ፣ ከማሃ፣ ከማሆን . . . . . .

<u>ማስታወሻ</u>፡- «በ» እና «እም» ከሌሎች መስተዋድዳን ጋር ተደርበው ሲገቡ አዳማቂ ይሆናሉ።

*<u>ምሳሌ</u>፡-* ቅድመ ዓለም። እም ቅድመ ዓለም።

ዲበ ምድር። በዲበ ምድር።

- ☞ ርኢኩከ ታሕተ ዕፀ በለስ።
- ☞ ርኢኩከ በታሕተ ዕፀ በለስ።

## <u>የደቂቅ አገባብ አተረጓጎም</u>

ደቂቅ አገባብ ቃልን ከቃል የሚያይዙ ወይም የሚያዛምዱ እንደመሆናቸው መጠን ሰፋ ያለ ትርጓሜ ይዘው ይገኛሉ።በመጠኑ ለማሳየት ያህል የሚከተሉት ቀርበዋል።

፩፥ <u>ዲበ፣ መልዕልተ፣ ላዕለ</u>፡- ላይ፣ በ . . . ላይ፣ ወደ. . . ላይ

*ምሳሌ፡-* ዲበ ሐዋርያት ኀደረ መንፈስ ቅዱስ።

- ☞ መንፈስ ቅዱስ ወረደ ላዕለ ሐዋርያት።
- ☞ ዐርጉ መልዕልተ ወግር።

፪. <u>ታሕተ፣ መትሕተ፡-</u> ታች፣ በታች፣ ወደታች

*<u>ምሳሌ</u>፡-* ተበውሀ ገብርኤል መትሕተ ሥላሴ ።/ ተበውሀ - ባለሟልነት ተሰጠው /።

- ☞ ተሠልጠ ሚካኤል ታሕተ እግዚአብሔር ።/ተሠልጠ -አለቃ ሆነ ሥልጣን አገኘ/





፫፥ <u>ውስተ፣ ውሳጤ ፣ ማዕከለ፡-</u> ውስጥ፣ በ . . . ውስጥ፣ በማዕከል

*ምሳሌ፡-* ነበሩ መነኰሳት ውሳጤ ገዳም።

- ☞ ማዕከለ ክልዔ ፈያት ተሰቅለ ክርስቶስ።
- ☞ ውስተ ማኅፀነ ድንግል ኀደረ።

፬፥ <u>በይነ፣ በእንተ፡-</u> ስለ

- ☞ ተዘከር እግዚኦ በይነ ቅዱሳን።
- ☞ በእንተ ሔዋን ተዐጽወ ኆኅተ ገነት።

፭ <u>እም ፣ እምነ ፡-</u> ከ

*ምሳሌ* ፡- ተወልደ ክርስቶስ እም ቅድስት ድንግል ማርያም።

- ☞ መኑ ይመስለከ እምነ አማልክት እግዚኦ።
- ☞ ነግሠ ሞት እም አዳም እስከ ሙሴ።

፮. <u>ቤዛ ፣ህየንተ፡-</u> ስለ ....ፈንታ

- ☞ ተሰቅለ ክርስቶስ ቤዛ አዳም።
- ☞ ህየንተ አበውኪ ተወልዱ ለኪ ደቂቅ።

፯. <u>ኀበ፣መንገለ ፡-</u> ወደ ፡ ዘንድ

- ☞ ሑር ኀበ ብሔር።
- ☞ ተፈሥሒ ኦ ማርያም እስመ ረከብኪ ሞገሠ በኀበ እግዚአብሔር።

፰. <u>ጊዜ ፡-</u> በ....ጊዜ

- ☞ ጊዜ ስድስቱ ሰዓት ሰቀልዎ አይሁድ ለኢየሱስ።

፱. <u>መጠነ</u> ፡- ያህል

- ☞ ነበረ አዳም ውስተ ገነት መጠነ ሰብዓቱ ዓመት።

፲. **እንበለ** :-ያለ....በቀር

- ☞ እንበለ መከራ ኢይትረከብ ፀጋ እግዚአብሔር::
- ☞ አልቦ አምላክ ዘእንበለ እግዚአብሔር::

## የ "ለ" እና የ "በ" አተረጓጎም

"ለ":- በቁም ቀሪ /ለ/ ፣ አዳማቂ /ትርጉም የለሽ/፣ ተጠቃሽ ተሳቢ/ን/፣ ዘርፍ አያያዥ /የ/ ሆኖ ያገለግላል::

- ⇒ ተሰቅለ ክርስቶስ ለደቂቀ አዳም:: ( በቁም ቀሪ /ለ/ )
- ⇒ ጻድቅ ለዘለዓለም ኢያንቀለቅል:: ( በቁም ቀሪ /ለ/ )
- ⇒ ኢትበሉ ለጌሠም ጌሠምሰ ትሔሊ ለርእሳ:: ( በቁም ቀሪ /ለ/ )
- ⇒ ዘጸምአ ለይምጻእ ኀቤየ:: (አዳማቂ /ትርጉም የለሽ/ )
- ⇒ ለትባእ ጸሎትየ ቅድሜከ::(አዳማቂ /ትርጉም የለሽ/ )
- ⇒ ሰቀልዎ አይሁድ ለክርስቶስ:: (ተጠቃሽ ተሳቢ/ን/)
- ⇒ አዳም አእመራ ለሔዋን:: (ተጠቃሽ ተሳቢ/ን/)
- ⇒ አይቴ ውእቱ ብሔራ ለጥበብ:: (ዘርፍ አያያዥ /የ/)
- ⇒ ሐዲስ ውእቱ ልብሱ ለሳሙኤል:: ( ዘርፍ አያያዥ /የ/ )

"ለ" ደጊመ ቀለም ሲሆን ማለትም "ለለ" ከሆነ "በየ" ተብሎ ይፈታል::

ምሳሌ:- ለለዕለቱ /በየዕለቱ/

ለለአሐዱ /በየአንዳንዱ/

"በ" በቁም ቀሪ /በ/፣ ለ ፣ጊዜ ተብሎ ይፈታል

ምሳሌ:- አድኀነነ በመስኮቱ ወቤዘወነ በትስብዕቱ::( በቁም ቀሪ /በ/ )

- ☞ ይኄይስ ተአምኖ በእግዚአብሔር:: ( በቁም ቀሪ /በ/ )
- ☞ ወመሐለ ሙሴ በይእቲ ዕለት:: ( በቁም ቀሪ /በ/ )
- ☞ ተናጸሩ ገጽ በገጽ::( ለ ተብሎ ይፈታል )
- ☞ በምዳቤየ ተዘከርኩከ እግዚኦ::( ጊዜ ተብሎ ይፈታል





**ምልማድ ፲፪.፪. :-**

**ዐ/ነገሮቹን ከተርጎምህ በኋላ የ "ለ" እና የ"በ"ን ሙያ ግለጽ::**

፩. ለይምጽኡ ኀቤየ እለ የኀሥሡ ሊተ::

፪. ኢይከብር ነቢይ በሀገሩ::

፫. እሉ እሙንቱ ሕፃናቲሃ ለማርታ::

፬. ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ይብሉ መላእክት እንዘ ይሰብሕዎ ለእግዚአብሔር::

### ፲፪.፫. አዳማቂ

- ☞ አንዱ የደቂቅ አገባብ ከሌላኛው ደቂቅ አገባብ ላይ ተደርቦ ያለሙያ ያለ አገልግሎት ሲነገር አዳማቂ ይባላል::
- ☞ አዳማቂ ለምሥጢር ተጨምሮ የሚያጎላው ቀርቶ የሚያጎድለው የለም አብዛኛው የተለመደው ለዜማና ጉንጭ ሞልቶ ለመናገር ሲፈለግ ብቻ ነው::
- ☞ አዳማቂ እነዚህ ናቸው ተብለው አይወሰኑም በማንኛውም ዐ.ነገር ላይ ያለ አገልግሎት ከተገኘ አዳማቂ ይባላል::

| ምሳሌ:- ያለ አዳማቂ | አዳማቂ ተጨምሮ |
|---|---|
| - ነበረ ዲበ መንበር:: | - ነበረ በዲበ መንበር:: |
| - መጻእኩ እም ደብረ ሊባኖስ:: | - መጻእኩ እምነ ደብረ ሊባኖስ:: |
| - ይኩን ሠላም :: | - ለይኩን ሠላም:: |
| - ከመ ትቤ:: | - በከመ ትቤ:: |
| - ይኩነኒ ከመ ትቤለኒ :: | - ይኩነኒ በከመ ትቤለኒ:: |

## ፲፪.፱. ዐቢይ አገባብ /መስተጻምር/

**ዐቢይ አገባብ** ፡- በሰዋስው ላይ የወደቀ ሰዋስውን የሚያሳካ ዐረፍተ ነገርን የሚያስማማ በተለይም በዐበይት አናቅጽ የገባ ማሰርያነትን የሚያስለቅቅ ሁሉ ዐቢይ አገባብ ይባላል፡፡

በስማቸውና በግብራቸው ከንዑስ ከደቂቅ ተለይተው ዐበይት አገባቦች ከሚባሉት መካከል የሚከተሉት ይገኙበታል፡፡

እስመ፣ አኮኑ፣ እንተ፣ በይነ፣ እንበይነ፣ ሀየንተ፣ ተውላጠ፣ ፍዳ/በቀለ፣ኀበ፣ መንገለ፣ ውእደ፣ እንዘ፣ መጠነ/ዐቅመ፣ አምጣነ፣ ከመ፣ አርአያ፣እስከ፣ አመ/ሶበ/ጊዜ፣ ባህቱ/እንበለ ዓዲ የመሰሉት ሁሉ ናቸው፡፡

<u>**ምሳሌ ፩፡-**</u>ማርያም ወለደት አምላከ፡፡ማርያም አምላክን ወለደች፡፡ “ወለደት” ማሰሪያ ሆኗል፡፡

- ☞ ማርያም ዘወለደት አምላከ /ማርያም አምላክን የወለደች…“ወለደት” የሚለው አንቀጽ ላይ ዐቢይ ዐገባብ ስለወደቀበት ዐ.ነገሩ አልታሠረም፡፡ ስለዚህ ዐቢይ አገባብ አንቀጽ ላይ ሲወድቁ ማሠሪያነትን እንደሚያስቀሩ በዚህ ይታወቃል፡፡ ስለሆነም ዐ.ነገሩን ለማሠር ሌላ ማሠሪያ እንጠቀማለን ማለት ነው፡፡
- ☞ ማርያም ዘወለደት አምላከ ወትረ ድንግል ይእቲ፡፡ ማርያም አምላክን የወለደች ዘለዓለም ድንግል ናት፡፡

<u>**ምሳሌ ፪፡-**</u> መጽአ ትማልም፡፡ትላንትና መጣ፡፡“ መጽአ” ማሰሪያ አንቀጽ ሆኗል፡፡

- ☞ ዘመጽአ ትማልም፡፡ትላንትና የመጣው..“መጽአ” ዐቢይ ዐገባብ ስለወደቀበት ዐ.ነገሩ አልታሠረም፡፡
- ☞ ዘመጽአ ትማልም እኁየ ውእቱ፡፡ ትላንትና የመጣው ወንድሜ ነው፡፡





## <u>የዐቢይ አገባብ አተረጓጎም</u>

ዐበይት አገባባት በአናቅጽ ላይ እየወደቁ እንደግሡ የእርባ ደረጃ ልዮ ልዮ ትርጓሜ ይዘው ይገኛሉ፡፡

፩፦ **<u>እስመ ፣አምጣነ ፣አኮኑ ፡-</u>** በዐቢይ አንቅጽ ላይ እየወደቁ «ና» ተ ብለው ይተረጎማሉ፡፡

- ☞ ሰማዕት ኢይፈርሁ ሞተ ሥጋ እስመ ይሬእይዋ ለመንግሥተ ሰማይ በዓይነ ተስፋ፡፡
- ☞ ኢትተክዙ እስመ ቀርበ ዘመነ ፍስሐ፡፡
- ☞ ተወክፈ አዳም ፍትሐ ሞት አምጣነ ኢዐቀበ ትእዛዘ ንጉሥ፡፡

፪፦ **<u>ከመ</u>፡-** በኃላፊና በትንቢት አንቀጽ ላይ እየወደቀ “እንደ፣ እንዲ፣ እንዳ፣ እንድ” ተብሎ ይፈታል፡፡

ምሳሌ፡- ተሰቅለ ጴጥሮስ ከመ ተሰቅለ ክርስቶስ፡፡

- ☞ ተነበዩ ነቢያት ከመ ይትወለድ ክርስቶስ፡፡
- ☞ የአትትዎ ለነዋእ ከመ ኢይርዐይ ስብሐተ እግዚአብሔር፡፡

፫. **<u>ዘ ፣እንተ፣ እለ፡-</u>** በቀዳማይ ና በትንቢት አንቀጽ እየገቡ “የ” ተብለው ይተረጓማሉ፡፡

- ☞ ተሰቅለ ክርስቶስ ዘፈጠረ መላእክተ፡፡
- ☞ ሐዋርያት መሀሩ እለ አእመሩ፡፡

፬. **<u>እንዘ</u>፡-** በካልዓይ አንቀጽ እየገባ “ሲ፣ ሳ፣ ስ፣ እየ” ተብሎ ይተረጓማል፡፡

***<u>ምሳሌ፡-</u>*** እፎ ይከውነኒ ዝንቱ እንዘ ኢየአምር ብእሴ፡፡

- ☞ ተርኅወ ሰማይ እንዘ ይጼሊ እግዚእ፡፡
- ☞ እግዚአብሔር እንዘ ትወርድ ሲያለ በአካለ ነፍስ ኢነጻሩከ አይሁድ፡፡

፩. <u>አመ፣ ሶበ ፣ጊዜ፡-</u>በቀዳማይና በካልዓይ አንቀጽ እየገቡ "በ . . ጊዜ" ተብለው ይተረጎማሉ፡፡

<u>*ምሳሌ፡-*</u> አመ ተሰቅለ ክርስቶስ ፀሐይ ጸልመ፡፡

- ☞ ሶበ ይመጽአኒ እኩይ ኢትርሐቅ እምኔየ፡፡
- ☞ ሶበ ትመጽእ በመንግሥትከ ተዘከረነ በምሕረትከ፡፡
- ☞ ጊዜ ምጽአቱ ለወልደ እጓለ እመሕያው ይትከወስ ኵሉ ኃይለ ሰማያት፡፡

፪. <u>እመ፡-</u>በቀዳማይ፣ በካልዓይ አንቀጽ እየገባ " ከ፣ካ፣ቢ፣ባ፣ብ " ተብሎ ይፈታል፡፡

*ምሳሌ፡-* እመ እግዚአብሔር ምስሌነ መኑ ይክህለነ፡፡

- ☞ እፎ እንከ ተአምኑኒ እምነገርኩክሙ ዘበሰማያት፡፡
- ☞ እመ አኮ እግዚአብሔር ምስሌነ ንጠፍዕ ፡፡
- ☞ እመ እግዚአብሔር ሐነፀ ቤቶ ከንቶ ኢይከውን ጻማሆሙ ለሐናፅያን፡፡
- ☞ እመ እግዚአብሔር ኢሐነፀ ቤተ ከንቶ ይጻምዉ እለ ሐንጹ፡፡

፫. <u>ቅድመ፣ እንበለ ፡-</u> በሣልሳይ አንቀጽ (በዘንድ አንቀጽ ) እየገቡ "ሳ" ተብለው ይተረጎማሉ ፡፡

- ☞ ቅድመን እም አንበለን ዘ ያዳምቁታል፡፡

*ምሳሌ፡-* እም ቅድመ ይፍጥሮ ለአዳም የአምር ግብሮ እግዚአብሔር፡፡

- ☞ ወለደት አምላክ ዘእንበለ ታእምር ብእሲ፡፡





፬. <u>እስከ ፣እስከነ ፡-</u> በቀዳማይና በካልዓይ አንቀጽ እየገቡ "እስከ፣ ድረስ" ተብለው ይፈታሉ፡፡

*ምሳሌ፡-* ንቁም በበህላዌነ እስከ ንረክቦ ለአምላክነ፡፡

- ☞ ኢወለደት ኤልሳቤጥ እስከነ ትልህቅ፡፡
- ☞ ኢወለደት ሜልኮል አስከ አመ ሞተት፡፡

፭. <u>በእንተ፣በይነ፣እንበይነ፣ህየንተ፡-</u>"ዘ"ን በር ከፋች አድርገው በመነገር ስለ ተብለው ይፈታሉ፡፡

*ምሳሌ፡-* ንዑ ንወድሳ ለማርያም በእንተ ዘወለደት አምላከ፡፡

- ☞ ይሜንን ሰብእ ዓለመ በእንተ ጽድቅ፡፡
- ☞ በይነ አብርሃም ወረደ እግዚአብሔር፡፡
- ☞ እንበይነ ዘተዋረደ አዳም ሞተ እግዚእ፡፡
- ☞ ሞተ እግዚእ ህየንተ አዳም፡፡
- ☞ በከየት ራሔል እንበይነ ዘቀተሉ ደቂቃ፡፡

፮. <u>ድኅረ፡-</u> በቀዳማይ አንቀጽ ብቻ እየገባ «በ . . . ኋላ» ተብሎ ይፈታል፡፡

"እም" እያደመቀውም ሳያዳምቀውም ይነገራል፡፡

*ምሳሌ፡-* እም ድኅረ ዐርገ እግዚእነ ፈነወ ለአርዳኢሁ ጽራቅሊጦስሀ፡፡

- ☞ ድኅረ ነግሠ ዳዊት ነግሠ ሰሎሞን
- ☞ እምድኅረ ተንሥአ እግዚእነ እሙታን አስተራዩን ቀዲሙ ለአንስት፡፡

## ፲፪.፲.ንዑስ አገባብ

ንዑስ አገባብ ከስም በፊት ወይም በኋላ ገብቶ ሁለት ቃላትን የሚያጫፍር ግሥ ላይ ወድቆ ማሠሪያነትን የማያስቀር የንግግር ክፍል ነው::

*ምሳሌ:-* መጻእኩ ውስተ ቤትከ ዳእሙ ኢነበርኩ::

☞ አበበ መጽአ ከበደሰ ሖረ::

☞ ሚካኤል ወገብርኤል መጽኡ::

## የንዑስ አገባብ አተረጓጎም

**፩.** <u>ወ :-</u> ና፣ ግን ፣ ም . . . ተብለው ይፈታሉ::

☞ አዳም ወሔዋን::

☞ ያዕቆብሀ አፍቀርኩ ወኤሳውሀ ጸላዕኩ::

☞ ተጸውአ ጴጥሮስ ወያዕቆብ ወዮሐንስ::

**፪.** <u>አው ፣ወሚመ:-</u> ወይም ተብለው ይፈታሉ::

☞ አንተ ብእሲ ሑር ወሚመ ንበር::

☞ አልብየ አኀት አው ወአኀው::

**፫.** <u>ሂ፣ኒ:-</u> ም፣ ደግሞ ተብለው ይፈታሉ::

☞ ኩኑ ቅዱሳነ እስመ አነሂ ቅዱስ::

☞ ሑር ወአነኒ እመጽእ::

**፬.** <u>ሰ :-</u> ግን ፣ ሰ፣ ማ . . . ተብሎ ይፈታል::

☞ ማርያምሰ ኀርየት መክፈልተ ሰናየ ዘኢየኀይድዋ::

☞ እንከሰ ንግበር ጽድቅ::

**፭.** <u>አላ</u>:- እንጂ ተብሎ ይፈታል::

☞ ኢታብአነ እግዚኦ ውስተ መንሱት አላ አድኅነነ::





## ፲፪.፲፩. ቃለ አጋኖ

ሐሳባችንን በአድናቆት፣ በአስተዋርዶ፣ ወይም በአክብሮት፣ በጥልቅ ስሜት ምንገልጽበት የንግግር ክፍል ቃለ አጋኖ ይባላል:: ለቃለ አጋኖ ከምንጠቀምባቸው ጥቂቶቹ:-

**እግዚኦ፣ ኦ፣ ወይ፣ አሌ፣ አህ.....የመሰሉት ሁሉ ናቸው::**

*ምሳሌ:-* - እግዚኦ አድኅነነ::

☞ እግዚኦ አምላክነ ስማዕ ጸሎተነ ወስእለተነ::

☞ ኦ ሰብእ ምንት ትትዔበይ እንዘ መሬት አንተ::

☞ ወይ ለነ እስመ በዝኀት ኃጢአት ላዕሌነ::

☞ አሌ ለክሙ ጸሐፍት ፈሪሳውያን::

☞ አህ እስመ ሞተ እኁየ::

☞ ምንተኑ ትኔጽሩ!?

## ምዕራፍ ፲፫.

## ዐረፍተ ነገር

ሰው ሀሳቡን በንግግርም ሆነ በጽሑፍ የሚገልጽበት የቃላት ስብስብ ዐረፍተ ነገር ይባላል::

በሰዋስው ትርጓሜው ዐረፍተ ነገር የሚለው አዕረፈ- ዐረፈ/ ፋታ አገኘ/ ከሚለው ግሥ የተገኘ ዘር በመሆኑ ዐረፍተ ነገር ማለት የነገር የሃሳብ መወሰኛ ማረፍያ ማለት ነው::

አንድ ቃል ብቻውንም ሆነ ከባልንጀሮቹ ጋር ተስማምቶ አንድ ሃሳብ ሲገልጽ ዐረፍተ ነገር ይባላል:: በግእዝ ቋንቋ አንቀጽ ሐሳብን ሊገልጽ ይችላል::

*ምሳሌ:-* እጽሕፍ፣ንግበር፣ንዐ፣ሑር፣ስተይ፣ኑማ፣ንብላዕ

## ፲፫.፩. የዐረፍተ ነገር ይዘት

ዐረፍተ ነገር በአጭሩ ሁለት ክፍሎችን ይይዛል እነርሱም ባለቤ ትና መፈክር ይበላሉ::

- ☞ ባለቤት ዘርፍ ሲኖረው ዘርፍ የያዘ ባለቤት ይባላል::መፈክር አንቀጽና ርቱዕ ተሳቢና ኢርቱዕ ተሳቢ የያዘ ሊሆን ይችላል::
- ☞ መፈክር የባለቤት አኳኃንና ሁኔታ ሥራንም የሚገልጽ ነው::

***ምሳሌ፡-*** *__መምህር__ መጽአ ውስተ __ቤተ ትምህርት__::*

*መምህር-ባለቤት ቤተ ትምህርት-መፈክር*

☞ *__መምህረ ታሪክ__ መጽአ ውስተ ቤተ ትምህርት::*

*__መምህረ ታሪክ__* - ዘርፍ የያዘ ባለቤት::

*__መጽአ ውስተ ቤተ ትምህርት__* -ኢ. ርቱዕ ተሳቢ የያዘ አንቀጽ::

☞ *መምህረ ታሪክ አምጽአ መጻሕፍተ::*

*__መምህረ ታሪክ__* - ዘርፍ የያዘ ባለቤት::

*__አምጽአ መጻሕፍተ__* - ርቱዕ ተሳቢ የያዘ አንቀጽ/መፈክር/::

☞ *እግዚእ አጋእዝት ዐርገ ሰማያተ::*

*__እግዚአ አጋእዝት__* - ዘርፍ የያዘ ባለቤት::

*__ዐርገ ሰማያተ__*- ርቱዕ ተሳቢ የያዘ አንቀጽ/መፈክር/::

## ፲፫.፪. የዐረፍተ ነገር ዓይነቶች

የዐረፍተ ነገር ዓይነቶች ሦስት ሲሆኑ በአዎንታና በአሉታ ይነገራሉ::

### ፩. መተርክ /ሐተታዊ/ ዐረፍተ ነገር፡-

መተርክ ማለት ማውግያ መተረቻ ወጋዊ ተረታዊ ማለት ሲሆን ሁኔታን ምግባርን የሚገልጽ የዐ/ነገር ክፍል ነው:: ብዙ ጊዜ ንግግር የሚደረገው በዚህ የዐረፍተ ነገር ክፍል ነው::





***__መተርክ አዎንታ፡-__*** *ትማልም ጊዜ ስድስቱ ሰዓት አሐዱ እምነ አዕርክትየ መጽአ በይእቲ ዕለት ወወዐልነ እንዘ ንትዋነይ እስከ ምሴት::*

- ☞ *መርሐሙ መዓልተ በደመና ወኵሎ ሌሊተ በብርሃነ እሳት::*
- ☞ *ወአዝነመ ሎሙ መና እምሰማይ::*
- ☞ *ቀደሳ እግዚአብሔር ለሰንበት እንተ ባቲ አዕረፈ::*

***__መተርክ አሉታ__*** *፡- ኦ እንትየ ሑር ኀበ ፈቀድከ እስመ ኢይመጽእ አነ::*

### ፪. መጠይቅ /ጥያቄያዊ/ዐረፍተ ነገር ፡-

መጠይቅ ማለት መጠየቂያ ፣መረጃ ማለት ሲሆን ጥያቄን የሚያነሳ የዐረፍተ ነገር ክፍል ነው::

***__መጠይቅ አዎንታ__*** *፡- መጽአኑ እኑከ ኀበ ቤትከ?*

- ☞ *መኑ የኀድር ውስተ ጽላሎቱ ለአምላከ ሰማይ?*
- ☞ *አይቴ አሐውር እመንፈስከ?*
- ☞ *መኑ መሀረከ ወመኑ ነገረከ ከመ ታእምር ዘንተ?*
- ☞ *ማእዜ ይከውን ማዕረር?*

***__መጠይቅ አሉታ፡-__*** *አልብከኑ ዘመድ ውስተ ዝንቱ ብሔር?*

**፫. *__መአዝዝ /ትእዛዛዊ/ ዐረፍተ ነገር፡-__*** መአዝዝ ማለት አዛዥ ማለት ሲሆን በትእዛዝ አንቀጽ ላይ የተመሠረተ ትእዛዝን፣ ልመናን ለማቅረብ ወይም ለማስተላለፍ የሚያገለግል:: ትእዛዛዊ ትርጉምን የያዘ በምሥጢር ግን ትእዛዝ ሊሆንም ላይሆንም የሚችል የዐረፍተ ነገር ክፍል ነው::

**መአዝዝ አምንታ:-** ወልድየ ብላዕ ወስተይ እንዘ ቦ አነ::

- ☞ ሑሩ ውስተ ኵሉ ዓለም ወስበኩ ወንጌለ::
- ☞ ንግበር ሰብአ በአርአያነ ወበአምሳሊነ::
- ☞ ስምዓ ጸሎተነ ወስእለተነ ወሥረይ ኵሎ ኃጢአተነ::
- ☞ አመ ከመ ዮም ያብጽሐነ::

**መአዝዝ አሉታ:-** ኢታምልክ ባዕድ አምላክ ዘ ንበሌየ::

## ፲፫.፫. የዐረፍተ ነገር ውስጣዊ ክፍሎች

ዐረፍተ ነገር እንደ ክፍሉና እንደ አገባቡ በሦስት ክፍል ይከፈላል::

፩. **ንዑስ ዐረፍተ ነገር** :-ንዑስ ዐረፍተ ነገር የሚባለው ዐቢይ ወይም ንዑስ አገባብ የሌለበት ዐረፍተ ነገር ነው::

ምሳሌ:- ቀተልኪ ከይሴ::

- ☞ አዕርክትየ መጽአ ውስተ ቤተ ትምህርት::

፪. **ምክዕቢት ዐረፍተ ነገር :-** ምክዕቢት ማለት እጥፍ ድርብ ማለት ሲሆን በንዑስ አገባብ የሚጫፈሩ /የሚያያዙ/ ዐረፍተ ነገሮች ምክዕቢት ይባላሉ::

**ምሳሌ:-** መምህር ተሰአለነ አሐደ ጥያቄ ወአሐዱ መርድእ አውስአ ሎቱ::

አበበ መጽአ ኀቤየ ዳእሙ አልማዝ ሖረት ኀበ ቤተ ትምህርት::

፫. **ዐቢይ ዐረፍተ ነገር :-** ማሠሪያነቱን ዐቢይ አገባብ ወድቆ ያስቀረው ዐቢይ ሐረግ በውስጡ የያዘ የዐረፍተ ነገር ክፍል ነው::

**ምሳሌ**:- አአምሮ ለዘመጽአ ትማልም ዐርክከ::

ሶበ ይመጽእ እትየ እነግሮ ኩሉ ዘሰማዕኩ::





## ፲፫.፬. የሐረግ ዓይነቶች

ሐረግ በሁለት ይከፈላል:: እነርሱም ዐቢይና ንዑስ ሐረግ ይባላሉ::

፩. **ዐቢይ ሐረግ :-** ዐቢይ አገባብ ወድቆ እንዳያሥር የሚያደርገውን አንቀጽ ከነተሳቢው ይይዛል::

**ምሳሌ:-** እንዘ ትመጽእ ኀቤየ ንግረኒ ቀዲሙ::

፪. **ንዑስ ሐረግ :-**ባለቤትና አንቀጽ የሌለው እነዚህን /ባለቤትና አንቀጽ/ ቢይዝ ግን ሐሳብ ሊገልጥ የሚችል የቃላት ስብስብ ነው::

**ምሳሌ** :- ሐዊረ ፍኖት::

- ☞ እበውእ ውስተ ቤተ እግዚአብሔር::

**ምልማድ ፲፫.፩.** :-

**የሚከተለውን ካነበብህ በኋላ ለተሰጡት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጥ::**

ንሕነ ዘራብዓይ ክፍል አርድእት እስመ ነአምር ከመ ብርሃን ውእቱ ትምህርት እንዘ ንሰምዕ ድምፀ መጥቅዕ ንበውእ በበክፍልነ ወእንዘ ቦእነ ንሕነ ይበውእ መምህርነ ወይብለነ "ሰላም ለክሙ አርድእት" ወንሕነኒ ንቤ "ሰላም ለከ መምህር" ወሶበ ይቤለነ ንበሩ ንነብር በበመካን ዘይሜህረነ ንሰምዕ ወዘይጽሕፍ ለነ ኵሉ ንጽሕፍ::

፩. እንዘ ንሰምዕ ድምፀ መጥቅዕ:: ሲል ምን ማለቱ ነው::

ሀ. መጥምቅ የተባለ ድምፅ እየሰማን

ለ. የደወል ድምጽ ስንሰማ

ሐ. ደወል ሲደወል ከሰማን በኋላ

መ. እየተደወለ ሳለ

፪. ከሚከተሉት ዐቢይ ሐረግ የቱ ነው፡፡

ሀ. እንዘ ንሰምዕ          ሐ. ሰላም ለክሙ

ለ. ኵሉ ንጽሕፍ          መ. ሁሉም

፫. በምንባቡ መሠረት “ወይብለነ” የተባለው?

ሀ. ለአርድእት በሙሉ          ለ. ለመምህር

ሐ. ለተማሪና ለመምህር          መ. ሁሉም

፬.ይህ ምንባብ በ-------------- ዐረፍተ ነገር ዓይነት ሊመደብ ይችላል፡፡

ሀ. መተርክ          ለ. መጠይቅ

ሐ. መአዝዝ          መ. ሁሉም

## ፲፫.፮. <u>የቃላት ጥናት</u>

በዚህ ክፍል የምናያቸው ቃላት በግሥና በስም ላይ እየወደቁ ትርጉም የሚቀይሩ የግእዝ ቃላትን ለመተርጎም የሚረዱ ቀለማትን ነው፡፡

**፩. ኒ፡-** ትርጉሙ ምᎇ ደግሞ፣ እንኳ፣ ግን..

*ምሳሌ፡-* ኦ አርድዕት ተንሥኡ ወሑሩ አነኒ እተልወክሙ፡፡

ተማሪዎች ሆይ ተነሱና ሂዱ እኔም እከተላአችኋለሁ፡፡

☞ ተፈነወ ማርቆስ ኀበ ግብፅ ወዮሐንስኒ ኀበ ኤፌሶን፡፡

ማርቆስ ወደ ግብፅ ተላከ ዮሐንስ ደግሞ ወደ ኤፌሶን፡፡

☞ ተዐኅዘ ሙሴ ወተዐሥረ ኤልያስኒ አምሰጠ በሠረገላ፡፡

ሙሴ ተያዘና ታሠረ ኤልያስ ግን በሠረገላ አመለጠ፡፡

☞ ኢየአምር አንሰ ዕለተ ሞትየ ወጠቢብኒ ኢየአምር፡፡

እኔስ የምሞትበትን ቀን አላውቅም አዋቂ እንኳ የሚሞትበትን አያውቅም፡፡





**፪. ሰ፡-** ትርጉም ግን፣ ስ ፣ሳ፣ ማ፣ ና..

*ምሳሌ፡-* አንትሙ ተሐውሩ ኀበ ዘመድ አነሰ አሐውር ኀበ ባዕድ፡፡

እናንተ ወደ ዘመድ ትሔዳላችሁ እኔ ግን ወደ ባዕድ እሔዳለሁ፡፡

☞ ይእቲሰ መጽአት አኃታሰ ተረፈትኑ?

እኅቷስ መጣች እህቷስ/ሳ ቀረችን?

☞ ውእቱሰ ተንሥአ ትማልም፡፡

እሱማ ትላንት ተነሣ፡፡

☞ ጎድግሰ ነገረ ቅንአት ግበር ዘይደልወከ፡፡

የቅናት ነገርን ተውና የሚገባህን አድርግ፡፡

**፫. ሂ፡-** ትርጉም ም፣ግን፣ነገር ግን፣ደግሞ..

ምሳሌ ፡- አቡየ ይገብር እስከ ይእዜ አነሂ እገብር ዘንተ፡፡

አባቴ እስካሁን ይሠራል እኔም ይህን እሠራለሁ፡፡

☞ እኁየ ይጽሕፍ ሊተ ጦማረ ወአነሂ እጽሕፍ ሎቱ፡፡

ወንድሜ ደብዳቤ ይጽፍልኛል እኔም/እኔም ደግሞ እጽፍለታለሁ፡፡

☞ ዮሐንስ ተቀትለ ውስተ ቀትል ምኒልክሂ ኢተቀትለ፡፡

ዮሐንስ በውጊያው ተገደለ ምኒልክ ግን / ነገር ግን ምኒልክ አልተገደለም፡፡

**፬. ወ፡-** ወ እስከ ፳፯ የሚደርሱ ትርጉሞች አሉት ከእነዚህም

*መካከል* ፡- ና፣ም፣በ-ጊዜ ፣ሰ፣ፈጽሞ፣እንኳ፣ነገር ግን፣እንጅ........

ተብሎ ይፈታል፡፡

*ምሳሌ* ፡- አብ ወእም ወውሉድ ወአዝማድ፡፡

አባትና እናት ልጅም ዘመድም፡፡

☞ ወጸቢሖ ተማከሩ ሊቃነ ካህናት::

በነጋም ጊዜ የካህናት አለቆች ተማከሩ::

☞ ዕድ ወአንስት::

ወንድና ሴት::

☞ ኢትበሉ ምንተ ንበል ወምንተ ንሰቲ ወምንተ ንለብስ::

ምን እንበላለን ምንስ እንጠጣለን ምንስ እንለብሳለን አትበሉ::

“ወ” ተመሳሳይ ትርጉም ያላቸውን ግሦች ፈጽሞ ተብሎ እንዲተረጎም ያደርጋል::

***ምሳሌ*** :- ተምአ ወተቆጥአ::

ፈጽሞ ተቆጣ::

☞ ፈድፋደ ወበዝኀ::

ፈጽሞ በዛ ተትረፈረፈ::

☞ ኢረከብኩ ኀብስተ ወኢመጠነ እድ::

እንጀራ አላገኘሁም እጅ የምታኽል እንኳ::

☞ አልቦ ዘይገብራ ለሠናይት ወኢአሐዱ::

መልካም የሚያደርግ የለም አንድስ እንኳ::

☞ በልዓ ወኢሰትየ::

በላ ነገር ግን አልጠጣም::

☞ ተንሥአ ወኢሖረ::

ተነሣ ነገር ግን አልሔደም::

“ወ” በአኃዝ ሲነገር ተጠቅልሎ ይተረጎማል::

☞ ዐሥርቱ ወ አሐዱ ::

ዐሥራ አንድ::

“ወ” ውጥን ጨራሽ ይሆናል::





***ምሳሌ*** :- ተአሥረ ዮሐንስ ሊቅ ወካልዓኒሁ ከማሁ::

☞ ሊቁ ዮሐንስ ታሠረ ሌሎችም እንዲሁ ታሠሩ::

“ወ” ማሠሪያ አንቀጾችን ይከፍላል ያያይዛል::

. ረከበ ወተፈሥሐ::

☞ አገኘ ተደሰተ::

. ይምጻ ወይርአይ::

ይምጣ ይይ::

“ወ” የወደቀበትን ግሥ ቦዝ ያደርጋል::

. ሖረ <u>ወኀደረ</u>::

☞ <u>ትቶ</u> ሔደ::

. ተንሥአ <u>ወሐይወ</u>::

<u>ድኖ</u> ሔደ::

“ወ” የወደቀበትን ግሥ ማሠሪያ ያልወደቀበትን ግሥ ቦዝ ያደርጋል::

ምሳሌ :- <u>ሐመ</u> ወሞተ::

☞ <u>ታሞ</u> ሞተ::

. <u>ይምጻእ</u> ወይስተይ::

☞ <u>መጥቶ</u> ይጠጣ::

### ፲፫.፯. <u>መጠይቃን ቃላት</u>

**<u>፲፫.፯. ÷ ፩. ሰውን ለመጠየቅ:-</u>**

**መኑ፣ አይ :-ትርጉም ማን**

**እለመኑ ፣እለአይ/አያት:- ትርጉም እነማን**

**አይ :- ነገርን፣ ጊዜን፣ ቦታን ለመጠየቅ ያገለግላል::**

**<u>ሀ. በበቂነት ሲነገሩ/ተውላጠ ስም ሲሆኑ :-</u>**

☞ መኑ ውእቱ ዝንቱ ብእሲ?

ይህ ሰው ማን ነው?

☞ መኑ ይእቲ እምከ?
እናትህ ማን ናት?

☞ መነ ተኀሥሥ ዝየ?
እዚህ ማንን ትፈልጋለህ?

☞ እለ መኑ እሙንቱ አእርክቲከ?
ወዳጆችህ እነማን ናቸው?

☞ አያት እሙንቱ አብያጺከ?
ጓደኞችህ እነማን ናቸው?

☞ ወልደ መኑ አንተ?
የማን ልጅ ነህ?

☞ ኀበ መኑ ተፈነወ መልአክ?
መልአክ ወደ ማን ተላከ?

☞ አየ አንገሠ ሳሙኤል?
ሳሙኤል ማንን አነገሠ?

ለ. <u>በቅጽልነት ሲነገሩ፡-</u>

☞ አይ ሰብእ ተሰቅለ በቀራንዮ?
በቀራንዮ የተሰቀለው ሰው ማን ነው?

☞ መኑ ሰበእ ዘየሐዩ ወኢይሬእያ ለሞት?
ሞትን የማያያት የሚኖር ሰው ማን ነው?

፪. <u>ነገርን ለመጠየቅ፡-</u>

ምንት ፣ አይ፡-ትርጉም ምን
ምንታት ፣ አያት፡- ትርጉም ምኖች

ሀ. <u>በበቂነት ሲነገሩ፡-</u>

☞ ምንት ተአምረሁ ለምጽአትከ?
የመምጣትህ ምልክቱ ምንድን ነው?

☞ አይ ወረደ እምሰማይ?
ከሰማይ የወረደው ምንድን ነው?





☞ አያት ይትረዐዩ ላዕለ ጠፈር?
በሰማይ ላይ የሚታዩ ምንድን/ ምኖች ናቸው?

ለ. <u>በቅጽልነት ሲነገሩ፡-</u>

☞ በይነ ምንት ነገር ታፈቅር አዝማዲከ?
ዘመዶችህን ስለምን ትወዳለህ?

☞ ምንቱ ለዳዊት ሰሎሞን እኁሁኑ ወሚመ ወልዱሁ?
ሰሎሞን ለዳዊት ምኑ ነው ወንድሙ ነውን ወይስ ዘመዱ?

☞ ዳዊት ምንትከ ሰሎሞን?
ሰሉሞን ዳዊት ምንህ ነው?

፫. <u>ጊዜን ለመጠየቅ ፡-</u>

ማእዜ ፣አይ ፡- ትርጉም መቼ

☞ ማእዜ ተወልደ ክርስቶስ?
ክርስቶስ መቼ ተወለደ?

☞ አየ ዘመነ /በአይ ዘመን/ ይመጽእ ክርስቶስ?
ክርስቶስ በየትኛው ዘመን ይመጣል?

፬. <u>ቦታን ለመጠየቅ፡-</u>

አይ፣ አይቴ፡- ትርጉም የት ፣ወዴት

☞ አይቴ ወእቱ ቤትከ?
ቤትህ የት ነው?

☞ አይቴ ብሔራ ለጥበብ ወአይቴ ደወላ?
የጥበብ ሀገሯ ወዴት ነው አውራጃዋስ ወዴት ነው?

☞ እም አይ ሀገር ሖረ አብርሃም ኀበ ግብፅ?
አብርሃም ከግብፅ ሀገር ወዴት አገር ሔደ?

፫.ቁጥር ለመጠየቅ :-

ስፍን፡- ትርጉም ስንት ለነጠላ

እስፍንት፡- ትርጉም ስንቶች /ምንያህል/ ስንት ለብዙ

ምሳሌ፡- እስፍንቱ መዋዕሊከ?

☞ ዘመኖችህ ስንት ናቸው /እድሜህ ስንት ነው/?

☞ ስፍን ሕፃና ለሳራ?

የሳራ ልጁ ስንት ነው?

☞ እስፍንተ ሐዋርያተ ሐረየ ክርስቶስ?

ክርስቶስ ስንት ሐዋርያትን መረጠ?

<u>ከፋዮች</u>

አይ ፣ አያት፡- ትርጉም ማንኛው ፣ የትኛው

አያት፡- ትርጉም ማንኛቸው ፣የትኞቹ

ምሳሌ ፡- አይ ዕጽ ይኄይስ እምዕጸው?

☞ ከእንጨቶች የሚበልጠው የትኛው ነው?

☞ አይ ይእቲ ዛቲ እንተ ታስተርኢ እምርሑቅ ከመ ማኅቶት ደብረ ገነት ይእቲ::

ይህች ከሩቅ እንደ መብራት የምትታይ/የምታበራ/ ማንኛዋ ናት ደብረ ገነት ናት::

☞ አያት እምሐዋርያት ወእም አርድእት ጸሐፉ ወንጌለ?

ከሐዋርያትና ከአርድእት ማንኞቹ ወንጌልን ጻፉ?

እፎ፡-ትርጉሙ እንዴት፣እረግ፣ምንኛ ሲሆን በአንክሮ ፣በጥያቄ ፣በድንጋፄ ይነገራል::





☞ እፎ ሰቀሉከ ካህናተ ይሁዳ ወሌዊ!::

የይሁዳና የሌዊ ከህናት እንዴት ሰቀሉህ!::

☞ እፎ ወድቀ ኮከበ ጽባሕ እም ሰማይ!::

የአጥቢያ ኮከብ ከሰማይ እንዴት ወደቀ!::

☞ እፎ ሠናይት ሀገረ ገነት!::

ገነት ምንኛ ያማረች ናት!::

" ሁ " " ና " " ኑ " የቃላት ትራስ እየሆኑ ጥያቄን ለመጠየቅ ይረዳሉ::

ምሳሌ ፡- ይትከሀልኑ ይጻእ ኄር እምናዝሬት?

ከናዝሬት ቸር ሰው ይወጣልን /ሊወጣ ይችላልን ?

☞ መኑ የኀድገነ ፍቅሮ ለክርስቶስ ሕማምኑ ምንዳቤኑ መጥባዕትኑ ኢኮነሁ ከመዝ::

የክርስቶስን ፍቅር ማን ያስተወናል ሕማም ነውን ችግር ነውን ሰይፍ ነውን እንዲህስ አይሆንም::

☞ ንጉሥኑ መጽአ?

ንጉሡ መጣን?

☞ እምኄየሁ ይሴወር?

ከኔ ይሰወራልን ?

☞ የቦ ትራስ ሲሆኑ በውኑ ተብለው ይፈታሉ::

ምሳሌ ፡- ቦኑ ለዓለም ይገድፍ እግዚአብሔር?

☞ በውኑ እግዚአብሔር ዓለምን ይተዋል?

. ቦሁ ዘይሴወር እምኔየ?

☞ በውኑ ከእኔ ይሰወራል?

# ምዕራፍ ፲፩.

## ቅኔ

ቅኔ የምስጋና ግጥም ሲሆን ዘጠኝ ክፍሎች አሉት:: እነርሱም:-

፩. <u>ጉባዔ ቃና:-</u> ሁለት ቤት እና አራት ሐረጎች አሉት::ይህም

የትስብዕትና የመለኮት ወይም የተዋህዶ ምሳሌ ነው:: ጉባዔ ቃና ለምን

ተባለ ቢሉ አንዳንድ አባቶች የቃና ሠርግን አስመለክቶ ስለተጀመረ ነው ይላሉ:: ሌሎች ደግሞ ተማሪ በዚህ ተነስቶ ቅኔን ስለሚጀምር / ስለሚማር ጉባዔው ተቃና በሚል ጉባዔ ቃና ተብሏል ይላሉ::

ጉባዔ ቃና በግእዝም በዕዝልም ይቀኛል::

፩. <u>ጉባዔ ቃና</u>

ለጸብህ ሞት ጸዋሚ መልአከ ሰማይ ኀደጋ

ጸብህ ሞት እስመ ተሠርአት በሥጋ::

*ትርጉም*:- ወጥ ሞትን ጸዋሚ የሆነ የሰማይ መልአክ ተዋት

ሞት ወጥ በሥጋ ተሠርታለችና::

ሰምና ወርቅ:- ጾመኛው የሥጋ ወጥን ተወ::መልአክ አይሞትም

መሞት የሥጋ ባህሪ ነውና::

*ሙያ*:- ለጸብህ ለ ደቂቅ አገባብ ሲሆን ፍቺው ን ሙያው ተጠቃሽ

ተሳቢ:: የን ባለቤቶች ጸብህ ሞት/ሰምናወርቅ/ተጠቃሽ ን የወደቀበት

ተሳቢ:: ጸዋሚና መልአክ /ሰምና ወርቅ/ምሳሌ :- ሙያው የቅኔ ባለቤ ት:: ሰማይ የመልአክ ዘርፍ ኀደጋ ማሰሪያ አንቀጽ ይስባል እንጂ አይሳብም::





ጸብህ ሞት: ምሳሌ /ሰም ወርቅ/ ሙያው የአስረጂ ባለቤት እስመ ዐቢይ አገባብ /ና/ እና አስረጅ ተሠርአት እንዳያስር እስመ ወድቆ አሳሪነቱን አስቀርቷል:: በሥጋ: በ ደቂቅ አገባብ/በቁም ቀሪ/ ሙያው ማድረጊያ::

፪. <u>ዘአምላክየ:-</u> ሦስት ቤት አምስት ሐረጋት ያሉት ሲሆን

የምሥጢረ ሥላሴ ምሳሌ ነው:: ዘአምላክየ ሁል ጊዜ ዜማው ዕዝል ነው የሚደረሰውም በዐቢይ ጾም መወድስ ሲደርስና ስብሐተ ነግህ ሲደርስ አብዛኛውን ጊዜ ሰኞ ማክሰኞ ሐሙስ ነው:: ዘአምላክየ መባሉ አምላክየ እገይስ ኀቤከ ከተባለ በኋላ ስለሚደርስ ነው::

<u>ዘአምላክየ</u>

ዐይነ ሐራዊ ዘኖመ እምንዋመ ዑረት ነቅሀ

እስመ ማይ መቁረሬ አበሳ ላዕሌሁ ተነዝሀ

ወበቅድሜሁ መስቀል ማኅቶተ ዓለም አብርሀ::

፫. <u>ሚበዝኁ :-</u> ሦስት ቤት እና ስምንት ሐረጋት አሉት የሥላሴ ምሳሌ ነው:: ዜማው ግእዝ ሲሆን ሚበዝኁ መባሉ ሚበዝኁ ከሚለው የዳዊት መዝሙር በኋላ ስለሚደርስ ነው:: ዘወትር እሑድና በሌ ላው መወድስ በሚደርስበት ጊዜና በዐቢይ ጾም ጊዜ ይደርሳል::

### <u>ሚበዝኁ</u>

ትቤ መጽሐፍ ቢጸከ አፍቅር ወለርእስከ ኢ.ታደሉ

እምትእዛዘ መጽሐፍሂ ገቢረ ትሩፋት እስመ ይደሉ

በዕለተ ስቅለት አይሁድ ነፍሰ ቢጸሙ አሕየው ወርእሶሙ ቀተሉ::

፬. <u>ዋዜማ:-</u> ሁለት ዓይነት ሲሆን ረጅም ዋዜማ አምስት ቤትና ዘጠኝ

ሐረጋት ሲኖሩት አጭሩ ዋዜማ ሁለት ቤት ነው:: ዜማው አራራይ ሲሆን ዋዜማ መባሉ በዐበይት በዓላት ዋዜማ ስለሚደርስ ነው::

**ዋዜማ**

ጌጋይ ሐፀ ጌጋይ ኢቀተለቶ ለስምዖን እንዘ ትረግዞ ገቦሁ
ሥጋ በሥጋ እስመ ሖረት ናሁ
ወዘኢያስቈርር ደመ ኪዳነ ድንግል እኅትሁ
በማይ ኀፀበ አልባሲሁ
ዘበሞቱ ለምውት ተነዝኀ።

፭. **ሥላሴ** ፡- ስድስት ቤትና አሥራ አንድ ሐረጋት አሉት የስድስቱ ቃላተ ወንጌል ምሳሌ ነው። ዜማው ዕዝል ሲሆን ሥላሴ መባሉ በሠለስቱ ደቂቅ ስለሚጀምር ነው። በታላላቅ በዓላት ዋዜማ ሁልጊዜ ይደርሳል።

**ሥላሴ**

መልዕልተ መስቀል ዕፅ ትንሣኤ
ኃጢአተ ኵሉ ዓለም ድኅረ ምስሌሁ ሰቀለ
ጊዜ ፍና ቀትር ይፈጽም አምሳለ
ሥነ መለኮት ክርስቶስ እንዘ ይትዐጸፍ ዐባለ
አመ ውስተ ሰማይ ተለዐለ
አዳም አጥረየ ብዕለ
ወሰይጣን እምክብሩ ተኀጒለ።

፮. **ዘይእዜ** ፡- አምስት ቤትና አሥራ አንድ ሐረጋት አሉት። የአምስቱ አዕማድ ምሳሌ ሲሆን ዘይእዜ መባሉ "ይእዜ ትስዕሮ ለገብርከ" ከሚለው ጸሎት በኋላ ስለሚደርስ ነው። ረጅምና አጭር አለው ከላይ ያየነው ረጅሙን ሲሆን ዜማው ዕዝል ነው። አጭር ዘይእዜ ሁለት ቤት አለው በተጨማሪ ሣህልከ ወይም የሦስት ቤት ዘይእዜ አለ ምድቡ በአጭር ቤት ሆኖ ሦስት ቤትና ሰባት ሐረጋት ያሉት ነው።ሣህልከ መባሉ "እግዚኦ መሐረኒ በከመ ዕበየ ሣህልከ"የሚለው ከተዘመረ በኋላ ስለሚደርስ ነው ዜማው አራራይ ነው። አጭር ዘይእዜ ለንጉሥ ክብር ለአለቃ የሚቀኙት ነው። ረጅም ዘይእዜ በበዓላት ዋዜማ የሚደርስ ነው። ሣህልከ ግን መወድስ ሲደርስ የሚቀኙት ነው።





**ዘይእዜ**

ሙሴ ወቃል ሐረስተ ጊዜ
ዘአርዑተ ግብጽ አክበደ ወአርዑተ ግብጽ አቅለለ
ኦሪት ለፌ ወለፌ ወንጌለ
እስከ ለነብያት ዘርዐ ወለሐዋርያት እስከ አብቈለ
ተበቀለ ሰብአ ወኢተበቀለ
አመ ብሔረ ግብጽ ወረደ ወአመ ዐርገ መስቀለ
ተበቀለ ሰብአ ወኢተበቀለ።

፯. **መወድስ**፡- ሁለት ዓይነት ሲሆን

**፩.ፍታሕ ሊተ**፡- ስምንት ቤትና አሥራ ስምንት ሐረጋት አሉት ዜማው አራራይ ነው።

**መወድስ**

እምዘመደ ሰብእ ይኄይስ ዘመደ እንስሳ
ወፍቅረ እንስሳ የዐቢ እምተፋቅሮ ሰብእ ለለጊዜሁ
እንዘ ገፋዒሁ ለይስሐቅ እደ አብርሃም አቡሁ
በግዕ አኮኑ ለይስሐቅ ቤዛሁ
ወከመ ኢይትረፍ አምሳሊሁ ኢየሱስሀ ሰቀሉ አይሁድ አዝማዲሁ
ንሕነሂ ሶበ ሰማዕነ በመጽሐፈ ዕዳ ዜናሁ
ምንት እም እንስሳ ለሰብእ ፍድፋዴሁ
እንዘ አድግ የአምር ፍኖተ ምቅማሑ
አምጣነ እሥራኤል ኢጠየቁ ወኢያእመሩ ሥላሴሁ።

፪. <u>ኵልክሙ</u> ፡- ዘጠኝ ቤትና ሃያ ሐረጋት አሉት ኵልክሙ አሕዛብ ጥፍሑ እደዊክሙ እየተባለ ይደርሳል።

☞ መወድስ ቅኔ በእድሜ ለገፉ ለታወቁ አባቶች የሚሰጥ/እንዲቀኙ የሚደረግ ነው።

## <u>አጭር ኵልክሙ</u>

አስቈቀወ ወልድ ዕፀ መቃብር በቃሉ

እስመ ይመስሎ ዘይትበላዕ ኵሉ።

፫. <u>ክብር ይእቲ፡-</u> አራት ቤትና ስምንት ሐረግ ያሉት ሲሆን ክብር ይእቲ መባሉ“ ክብር ይእቲ ዛቲ ለኵሉ ጻድቃኑ ”የሚለው መዝሙር ከተዘመረ በኋላ ስለሚደርስ ነው።በዚህም ነገረ መስቀሉ ይነገርበታል ተቀኚውም ተቀባዩም በለሆሳስ ይቀኙዋል።ክብር ይእቲ በግእዝ እና በዕዝል ይባላል።በአራራይ የሚባል ክብር ይእቲ አለ ይህም ሌላ ስም አለው“ሐዋርያቲሁ ከበበ እግረ አርዳኢሁ ሐፀበ” ይባላል ሁለት ቤትና አራት ሐረጋት አሉት።

## <u>ክብር ይእቲ</u>

እፎ አይሁድ እምተለዐሉ ወእም አፈድፈዱ ሣህለ

እመ እደ አምላክ ዐሠሩ እምቅድመ ይፍጥር ሲኦለ

ባሕቱ ኢንመሀር እንተ ከመዝ አምሳለ

አምጣነ ሠናይ ሎሙ ተፈጥሮታ ከመ ትኩኖሙ ክፍለ።





፬. <u>ዕጣነ ሞገር፡-</u> በግእዝና ዕዝል የሚባል ሲሆን ግእዙ ሰባት ቤትና አሥራ ስምንት ሐረጋት ዕዝሉ አሥራ አንድ ቤትና አሥራ ስምንት ሐረጋት አሉት። ዕጣነ ሞገር መባሉ የጸሎት የማዕጠንት የምስጋና መደምደሚያ ስለሆነ ነው።ከዚህ በኋላ ምንም ጸሎት ምስጋና አይቀርብም።

## <u>ዕጣነ ሞገር</u>

አመ ወረደ ክርስቶስ ቈላተ ሲኦለ በነፍሱ

ነፍሳተ ብዙኃን ዔወወ እለ አበሱ

ወአወፈዮሙ በትፍሥሕት ለአብ ወለመንፈሱ አመሰ ተዋረሱ

ነፍሳተ ብዙኃን ዔወውከ ከማሁ ከመ ይትቀደሱ

በቅኔ ጣዖት ፍጹም ዘረኵሱ

ሠርፀ ድንግል ዘትጌይስ ተናግሮ እም አበዊከ ዘነግሡ

ኀበ ኀበ ይትሌዓል ፍና እስመ ለለጌሠም ታናሶሱ

ጊዮርጊስ ሰማዕት ዘኢይሔሱ

ተዝካረ ትጋህከ ይጽሐፍ በጽንፈ ልብሱ

ወይልክያ በጌራ ዘርእሱ።

<u>ሕንጼሃ</u> ፡- ሁለት ቤትና ሦስት ሐረጋት አሉት።

## <u>ሕንጼሃ</u>

እንከ ቀራንዮ ኢይበጽሕ እግዚእነ

እስመ ቀራንዮ ምድረ ደም ኮነ።

<u>የ ሀ ቤት ግሥ</u>

ሀለወ= ኖረ ተገኘ ሆነ
ሀርበደ= ተርበደበደ ደነገጠ
ሀበበ= ሰደበ  ነቀፈ አቃለለ
ሀሰወ= ወነጨፈ ዘነበ
ሀከየ= ሰነፈ ታከተ
ሀወከ/ሆከ= አወከ በጠበጠ
ሀየከ/ሄከ= አሳመጠ አኘከ
ሀየየ/ሀየ= ቸል አለ አቃለለ
ሀይመነ = አመነ ታመነ
ሀየደ= ቀማ ነጠቀ
ሀደመ= ተረተ አንቀላፋ ጨለመ
ሀድአ= ጸጥ ዝም አለ
ሀጕለ= ጠፋ ተቸገረ
ሄጸ= ነቀነቀ ሰበቀ ወጋ ገመሰ
ሀፈወ= ወዛ ደከመ
ሀፐለ= አጠበ መታ ደበደበ

<u>የ ለ ቤት ግሥ</u>

ልሕቀ= አደገ ሸመገለ
ልህበ= ሞቀ ተኰሰ
ለሐሰ= ላሰ ቀመሰ
ለሐኰ = ሸክላ ሠራ ፈጠረ
ለሐወ= አለቀሰ ጮኸ
ልሕመ= ላመ
ልሕየ= ወዛ አማረ
ለመደ= ለመደ
ለምለመ= ለመለመ
ለሰነ= ተናገረ
ለስሐ= አልጫ ሆነ
ለቅሐ= አበደረ
ለበወ=አስተዋለ ልብአደረገ
ለብሐ= ሠራ
ለብሰ= ለበሰ ተጐናፀፈ
ለትሐ= ተጐነጨ
ለአከ= ላከ ሰደደ
ለዐለ= ከፍከፍ አለ
ለወወ= ጠመጠመ
ለጸቀ= ተጣበቀ ደረሰ
ለፈፈ= ጠቀለለ ጻፈ ሸፈነ

## <u>የ ሐ ግሥ</u>

ሐለመ= ዐለመ ሕልም አየ
ሐለለ=ወተት አለበ
ሐለየ= አመሰገነ ሠፈነ
ሐመለ= ለቀመ ቀጠፈ
ሐመመ/ሐመ= ታመመ
ሐመየ = አማ
ሐሰመ= ከፋ
ሐረሰ= አረሰ ገመሰ
ሐሰወ= ዋሸ
ሐረመ= ተወ ጾመ
ሐርተመ= ጕሰቆለ
ሐቀለ= ቀማ ሸፈተ
ሐቀረ= ቆፈረ መረመረ
ሐበየ= ወከለ ጠበቀ
ሐተተ= መረመረ
ሐነጸ= ሠራ አነጸ ገነባ
ሐከመ= ብልህ ሆነ
ሐወረ /ሖረ= ሄደ
ሐወሰ/ሖሰ= ፈጠነ ቸኰለ
ሐወዘ= አማረ ጣፈጠ





ሐየሰ /ሔሰ= ነቀፈ ተቸ
ሐየበ /ሔበ= ቀዳ ጠለቀ
ሐይወ= ዳነ
ሐደሰ=አዲስ አደረገ
ሐገገ = ደነገገ
ሐጽረ= አጠረ
ሐጸጸ/ሐጸ= ጎደለ
ሐፀነ= አሳደገ ተንከባከበ

<u>የመ ቤት ግሥ</u>

መሀረ=አስተማረ
ማህረከ=ማረከ ሰለበ
መሀከ=ራራ ይቅር አለ
ምህወ=ቀለጠ ማማ
መለለ=መለል አለ
መለሰ=መለሰ ለወጠ
መለከ=ገዛ አቸነፈ
መልሐ=አጣፈጠ
መልጎ=መዘዘ ነለቀ
መልአ=ሞላ፣ጢምአለ
መሐለ=ማለ
መሐረ=ይቅር አለ፣ተወ
መሐወ=ነቀለ አፈለሰ
መሐዘ=ጎለመሰ አደገ
መሐጸ=ፈለጠ ቆረጠ ለየ
መመተ=ጎደለ አነሰ
መምዐ=ፈራ አፈገፈገ
መሠጠ=ነጠቀ ቀማ
መረረ/መረ=ጎመዘዘ
መረደ=ሞረደሸፈተአመለጠ
መረየ=ቀየረ፣ ለወጠ
መርሐ=መራ
መርሰሰ=ዳሰሰ፣ ዳበሰ
መርዐ=ተዳራ
መሰለ=ተረተ አወራ አወጋ
መሰለ= በመልክ መሰለ
መስሐ=ምሳ ጋበዘ
መሰከ=ያዘ ጎተተ
መስወ=ቀለጠ ፈሰሰ
መስየ= መሸ
ማሰነ=ጠፋ
ማረየ=ማረተ ጠነቆለ
ሞቀ=ሞቀ ተኮሰ
ሞቅጠ=ያዘ አሰረ
መተረ=ቆረጠ መተረ
መነነ=ናቀ ጠላ ችላ አለ
መንተወ=መንታ ሆነ
መንኰሰ=ሞተ
መንደበ=አስጨነቀ
ምዕዘ=ጥሩጥሩ ሸተተ
መከረ=መከረ አሰበ
መገበ= ቀለበ መፋበ
መጠነ=ለከ ሰፈረ

## የሠ ቤት ግሥ

ሣሀለ/ተሠሀለ=ይቅር አለ

ሣህበበ=ሻገተ

ሠለሰ=ሦስት አደረገ

ሠሐቀ=ሳቀ

ሠለጠ=ሠለጠነ

ሠምረ=ወደደ ፈቀደ

ሠረቀ=ወጣ

ሤመ=ሾመ ሸለመ

ሠዘረ=ሠነዘረ

ሠረየ=መድኃኒት አደረገ

ሣረረ=መሠረተ

ሠርዐ=ሠራ አዘጋጀ

ሠረጸ=ወጣ በቀለ አደገ

ሠርሐ= አሰናበተ በተነ

ሣቀየ=አሰቃየ

ሠብሐ=ወፈረ ሰባ

ሠነቀ=ሥንቅ ያዘ

ሠነየ=አማረ

ሦዐ= ሰዋ

ሠዐለ= ስዕል ሳለ

ሠየበ/ሤበ= ሸበተ

ሤጠ= ሸጠ

ሠገረ= ተራመደ

ሠገወ/ተሠገወ=ሰው ሆነ

ሠጠቀ= ሰነጠቀ

ሠጠጠ= ቀደደ ከፈለ

## የ ረ ቤት ግሥ

ረሐነ=ጫነ ተሸከመ

ርሕሰ= ራሰ ረጠበ

ርሕቀ= ራቀ

ርሕበ= ሰፋ ተዘረጋ

ረመመ/ረመ= ራመመ

ረሰወ= መልሕቅ ጣለ

ረሰየ= አደረገ ፈጠረ

ረስዐ=ሸመገለ አረጀ ረሳ

ረቀቀ ረቀ= ረቀቀ

ረበበ/ረበ= ዘረጋ

ረብሐ= ረባ ጠቀመ

ረብዐ=አራት አደረገ

ረትዐ= ቀና ረታ አሸነፈ

ርኅበ= ተራበ

ርኅወ= ከፈተ

ርእሰ= አለቃ ሆነ

ርእየ= አየ

ረከበ= አገኘ

ረኰሰ= ረከሰ ጎደፈ

ረዐየ= ጠበቀ ተንከባከበ

ርዕደ= ራደ ተንቀጠቀጠ

ረድአ= ረዳ አገዘ

ረገዘ= ወጋ





ረገፀ= ረገጠ

ረገመ= ረገመ

ረግዐ= ረጋ ቆመ

ረጥበ= ረጠበ

ረፈቀ= ተቀመጠ

ሮጸ= ሮጠ

## የ ሰ ቤት ግሥ

ሰሐበ= ሳበ ጎተተ

ሰለመ= ሰላምን አደረገ

ሰለበ= ሰለበ ቆረጠ

ሰለጠ= ጨረሰ ፈጸመ

ስሕተ= ሳተ ዘነጋ

ስሕወ= ተሳበ ተጎተተ

ሰመነ= ስምንት አደረገ

ሰመከ= ተጠጋ ተደገፈ

ሰመየ= ስም አወጣ

ሰምዐ= ሰማ አደመጠ

ሰረረ= በረረ መጠቀ

ሰረቀ= ሰረቀ

ሰረየ= ፈታ ለቀቀ

ሰርሐ= ጣረ ጋረ ሠራ

ሰሰለ= ወገደ ገለል አለ

ሰረበ= ማገ ፈሰሰ

ሰቀለ= ሰቀለ

ሰቈረ= በሳ ነደለ

ሰበረ= ሰበረ ቀጠቀጠ

ሰበቀ= ለቀቀ

ሰበከ= አስተማረ

ሰብለ= ዘረዘረ

ሰብሐ= አመሰገነ

ሰብዐ= ሰባት አደረገ

ሰትየ= ጠጣ

ሰነነ= ጥርስ አወጣ

ሰነየ= ሁለት አደረገ

ሰንሰለ=አያያዘ

ሰንቀወ= መታ ደረደረ

ሰንበተ= አከበረ ቆየ

ሰአለ= ለመነ

ስእነ= ደከመ ተሳነ

ሰከለ= አፈራ አበበ

ሰከበ= ተኛ

ሰከመ=ተሸከመ

ሰከበ= ተኛ

ሰከመ=ተሸከመ ቆብጫነ

ሰክረ= ሰከረ

ሰክነ= አረፈ ቦታ ያዘ

ሰወቀ/ሶቀ= ደገፈ ያዘ

ሰወጠ/ሶጠ= ጨመረ

ሰዐመ= ሳመ

ሰዐረ= ሻረ

ሰዘረ= ለከ

ሰየፈ= ቆረጠ ከፈለ

ሰይሐ/ሴሐ=ወገጠ/

ሴሰየ= መገበ/ቀለበ

ሰይጠነ= ከሰሰ አሳጣ

ሰደሰ= ስድስት አደረገ

ሰደደ= አባረረ አስወጣ

ሰገለ= ጠነቆለ ተጠበበ

ሰገደ= ሰገደ አጎነበሰ

ሰጠረ= መሰጠረ

ሰጠወ= ሰጠ

ሰጠጠ= ቀደደ

ሰጥሐ= አሰጣ ዘረጋ

ሰጥመ= ሰጠመ

ሰፈረ= ለከ መጠነ

ሰፈነ= ገዛ

ሰፈፈ= ተንሳፈፈ

ሰፍሐ= ሰፋ ተስፋፋ

## የ ቀ ቤት ግሥ

ቀለለ/ቀለ= ቀለለ አነሰ

ቀልቀለ= ነቀነቀ ቀላቀለ

ቀለየ= ጥልቅ ሆነ

ቄልቄለ= አዘቅዝቆ ሄደ

ቀልዐ= ገፈፈ ገለጠ

ቀሐመ= ቃመ ገመተ

ቀመረ= ቆጠረ

ቀምሐ= አፈራ

ቀሠመ=ቀሰመለቀመ

ቀሠፈ= ባጭር አስቀረ

ቈረረ/ቈረ= ቀዘቀዘ በረደ

ቀረጸ= ቀረጠ

ቀርበ= ቀረበ

ቀረጠ=ቀረጠ ምስል ሠራ

ቀሰመ= አጣፈጠ

ቈሰለ= ቆሰለ

ቀበረ= ቀበረ

ቀብዐ= ቀባ ለቀለቀ

ቀብጸ= ተስፋ አጣ

ቀተለ= ገደለ

ቀነተ= ታጠቀ

ቀነወ= ቸነከረ

ቀነየ= ገዛ

ቀንአ= ቀና ተመቀኘ

ቀወመ/ቆመ= ቆመ

ቀይሐ/ቄሐ= ቀላ

ቀደሰ= አመሰገነ

ቀድሐ= ቀዳ ጠለቀ

ቀጠፈ= ቀጠፈ

ቀጥቀጠ= ቀጠቀጠ

ቀጥነ= ቀጠነ

ቀጸበ= ጠቀሰ

ቀፈለ= ቆፈረ ፈለፈለ





## የ በ ቤት ግሥ

ብህለ = አለ ተናገረ

በልኀ = ተሳለ

በሐ = እንዴት ዋልክ አለ

በልዐ = አዳነ ታደገ

ባሕተወ =ተለየ ብቸኛ ሆነ

በረረ/በረ = በረረ

በረቀ=ብልጭአለ/አንጸባረቀ

ባረከ = አመሰገነ

በከከ/በከ = ብላሽ ሆነ

በረደ = በረደ ቀዘቀዘ

በርሀ = በራ ታየ ተገለጠ

በሰለ = በሰለ

በቀለ = ተበቀለ

በተከ = ቆረጠ በጠሰ

በኍበኍ = ሸተተ በሰበሰ

በከየ = አለቀሰ

በወዘ/ ቦዘ = ፈዘዘ

በውአ /ቦአ =ገባ

በዝኀ = በዛ በረከተ

በየተ/ቤተ = አደረ

ቤዘወ = አዳነ ታደገ

በጠለ = ጠፋ ፈረሰ

በጽሐ = ደረሰ

በፅዐ = ተሳለ ወሰነ ከበረ

## የ ተ ቤት ግሥ

ተለመ = ጀመረ ሰለጠቀ

ተለወ = ተከተለ

ተሐሰየ = ተደሰተ

ተለዐለ = ከፍከፍ አለ

ተላጸቀ = ተጠጋ

ተመርኰዘ = ተመረኮዘ

ተመንደበ = ተቸገረ

ተምዐ = ተቆጣ

ተመይጠ = ተመለሰ

ተሠገወ = ሥጋ ለበሰ

ተሣሃለ = ይቅር አለ

ተሣለቀ = ተዘባበተ

ቶስሐ = ጨመረ

ተሰነአወ = ተስማማ

ተሳተፈ = አንድ ሆነ

ተርጐመ = ተረጎመ

ተርፈ = ተረፈ ቀረ

ተቃወመ = ተከራከረ

ተትሕተ = ተዋረደ

ተነበየ= ትንቢት ተናገረ

ተንሥአ = ተነሣ

ተንበለ = ለመነ

ተዐገሠ = ታገሠ

ተከለ = ተከለ

ተከዘ = ተከዘ

ተክህነ = አገለገለ

ተደመመ/ተደመ=ተደነቀ

ተድኅረ = ወደኋላ አለ

ተግሕሠ = ፈቀቅ አለ

ተግሀ = ተጋ

ተጸወነ = ተጠበቀተጠጋ

ተፀነሰ = ተፀነሰ ተረገዘ

ተፈሥሐ = ተደሰተ

## የ ኀ ቤት ግሥ

ኀለፈ = አለፈ ተሻገረ

ኈለቈ = ቆጠረ ጀመረ

ኀለየ = ዘመረ

ኀልቀ = አለቀ አረጀ

ኀሠሠ = ፈለገ

ኀረየ = መረጠ

ኀስረ = ኀሰቀለ

ኀበለ = ዋሸ

ኀብረ = ተባበረ

ኀብአ = ሸሸገ

ኀበዘ = ጋገረ

ኀተመ=አተመቆለፈ ዘጋ

ኀተወ = በራ

ኀየለ = በረታ

ኀየረ/ ኄረ = ቸረ ለገሰ

ኀየሰ = ተሻለ በለጠ

ኀደረ = አደረ

ኀደገ = ተወ ጠሳ

ኀጥአ = አጣ

ኀጽረ = አጠረ

ኀጸወ = ሰለበ ቆረጠ

ኀፍረ = አፈረ ፈራ

## የ ነ ቤት ግሥ

ነሀበ = ሠራ አቀለጠ

ነሐሰ = ግንብ ሠራ ገነባ

ናሕንሐ =በዛ ተትረፈረፈ

ነሠተ = አፈረሰ ናደ

ነሠገ = ቆለፈ

ነሥአ = ወሰደ ተቀበለ

ነሰቀ = ደረደረ

ነስነሰ = ረጨ ፈነጠቀ

ነስሐ = ተጠጠተ

ነቅለ =ነቀለመዘዘ መነገለ

ነቀወ = ጮኸ

ነቅሐ = ነቃ ከእንቅልፍ

ነቅዐ = መነጨ

ነበረ = ተቀመጠ ኖረ

ነበበ /ነበ = ተናገረ

ነትገ = ኀደለ አነሰ

ንኅለ = አኮረፈ

ንእሰ = አነሰ

ኖኀ = ረዘመ በዛ

ነከረ = ለየ ነጠለ





ነወመ/ኖመ = ተኛ

ነውለወ / ኖለወ = ጠበቀ

ናዘዘ = አጽናና አረጋጋ

ነደለ = በሳ ሸነቆረ

ነደደ / ነደ = ነደደ

ነድአ = ነዳ ተከተለ

ነድየ = ተቸገረ ደኸየ

ነገረ = ነገረ አወራ

ነገደ = ሄደ ነጎደ

ነግሀ = ነጋ ጠባ

ነግሠ = ነገሠ

ነጠጠ = ዘለለ ፈነጨ

ነጥበ = ነጠበ

ነጸረ =ተመለከተአስተዋለ

ነፀፈ = ደረቀ ነጠፈ

ነፈቀ = ከፈለ ለየ

ነፍሰ = ነፈሰ

ነፍኀ=ሆድ ነፋ ቀበተተ

ነፍጸ = ሸሸ ራቀ ጠፋ

## የ አ ቤት ግሥ

አለለ = አመነዘረ ፈለገ

አለደ = ሰበሰበ

አሐደ = አንድ አደረገ

አልጸቀ = ደረሰ

አመረ = አመለከተ

አምለከ = አመለከ

አምሰጠ=አመለጠ

አምኀ = እጅ ነሳ ሰገደ

አምነ = አመነ

አረገ = ሸመገለ አረጀ

አሥገረ=አሰገረአጠመደ

አሰረ = አሰረ አቆራኘ

አስቈረረ = አስጠየፈ

አስቈቀወ = አለቀሰ

አስተርአየ= አሳየ ገለጠ

አስተብቍዐ = ለመነ

አስተዋደደ = አስማማ

አስተጋብአ = ሰበሰበ

አርመመ = ዝም አለ

አበየ = እምቢ አለ

አበሰ = በደለ

አብአ = አገባ

አኀዘ = ያዘ ጨበጠ

አነመ=ሠራሸመነ

አንቀልቀለ=አነዋወጠ

አንበበ = አነበበ

አንከረ = አደነቀ

አንጐድጐደ= አንጎደጎደ

አእኰተ=አመሰገነ

አእተተ=አራቀ አስራቀ

አዕረፈ = አሳረፈ

አከየ = ከፋ

አከለ = በቃ፤ መገበ

አውሰበ=ሚስትአገባ

አውገዘ= አስገዘተ

አዘዘ = አዘዘ ናዘዘ

አይድዐ = አለ ተናገረ

አደመ = አማረ

አጥረየ= ጥሪት አስገዛ

አድምዐ=ሰማ አደመጠ

አፍቀረ= ወደደ ተቀበለ

አእመረ=አወቀ አሳወቀ

## የ ከ ቤት ግሥ

ክህለ = ቻለ

ክሕደ = ካደ ከዳ

ከለለ=ጋረደ ከለለ አከበረ

ከልሐ = ጮኸ

ከልአ = ከለከለ አገደ

ከለዐ=ሁለትአደረገ

ከሠተ = ገለጠ

ከረየ = ቆፈረ ማሰ

ከርመ = ከረመ

ኰስተረ = ጠረገ

ከበበ = ከበበ

ከበተ = ሸሸገ

ከብረ = ከበረ ተከበረ

ከተበ = ጻፈ ከተበ

ኰነነ = ገዛ ፈረደ

ከንፈ = በረረ ከነፈ

ከወነ /ኮነ = ኾነ

ከወወ= ቀለጠፈ ፈጠነ

ኰዐተ = ቆፈረ

ከደነ = ከደነ ገጠመ

ከፈለ = ከፈለ ለየ

## የ ወ ቤት ግሥ

ወሀበ = ሰጠ

ወለደ = ወለደ

ውሕዘ= ፈለቀ ፈሰሰ

ወለደ = ወለደ

ውሕዘ= ፈለቀ ፈሰሰ

ወለጠ = ለወጠ

ወሠረ = ገዘገዘ ቆረጠ

ወሰነ = ደነገገ

ወረሰ = ወረሰ

ወረቀ= ተፋ ትፍ አለ

ወረደ = ወረደ

ወርዘወ=ጎለመሰ አደገ

ወሰከ = ጨመረ

ወሰደ = ወሰደ

ወቀሰ = ወቀሰ ከሰሰ

ወቅዐ=ወቃ መታ

ወክሐ = ደነፋ አቅራራ

ወውዐ = ደነፋ ጮኸ

ውዕየ = ተቃጠለ ነደደ

ወዘፈ = አጌጠ ለወጠ





ወደሰ = አወደሰአመሰገነ

ወደየ = ጨመረ ዶለ

ወድቀ = ወደቀ

ወደደ = ወደደ አፈቀረ

ወድአ = ጨረሰ ፈጸመ

ወገረ = ወረወረ መታ

ወገዘ = ገዘተ ለየ

ወጠነ = ጀመረ

ወጽአ = ወጣ

ወፈረ =ተሰማራ

ወከለ=ወከለ፣ውልአደረገ

## የ ዐ ቤት ግሥ

ዐለወ = ከዳ በደለ

ዐመቀ = ታመቀ

ዐመደ = ደገፈ

ዐመፀ = ሸፈተ አመለጠ

ዐሠረ = ዐሥር አደረገ

ዐረቀ=አስታረቀ አስማማ

ዐረዘ = አለበሰ

ዐረየ =ተከከለ አስተከከለ

ዐርበ = ገባ መሸ

ዐርገ = ወጣ አረገ

ዐሰበ = ደሞዝ ከፈለ

ዐቀለ = ጥልቅ አደረገ

ዐቀበ = ጠበቀ

ዐብየ = ከፍከፍ አለ

ዐተበ= አማተበ አመሳቀለ

ዐወቀ/ዖቀ=አወቀአስተዋለ

ዐወረ/ዖረ=ታወረዕውርሆነ

ዐወደ/ዖደ= ዞረ ተመላለሰ

ዐየለ/ዔለ = ዞረ

ዐየነ=አየገመገመመለከተ

ዐገተ = ከበበ ያዘ

ዐጠነ= አጠነዕጣን አጤሰ

ዐጠፈ = አጠፈ ጠቀለለ

ዐጸወ =ዘጋ ገጠመ ቆለፈ

ዐጸበ = ተጨነቀ ተደነቀ

## የ ዘ ቤት ግሥ

ዝሕለ = ዛገ

ዛህለለ=ዘልዘልአለባካናሆነ

ዘልገሰ = ታመመ ቆሰለ

ዘለፈ = ሰደበ ተዝለፈለፈ

ዘመረ = ዘመረ አመሰገነ

ዘመነ = ዘመንኛ ሆነ

ዘመወ=ሴሰነ

ዘረወ = በተነ

ዘርዐ = ዘራ ነሰነሰ

ዘበጠ = መታ

ዘብሐ = አረደ

ዘንመ = ዘነበ

ዘንግዐ = ረሳ ዘነጋ

ዘከረ = አሰበ አወሳ

ዜነወ = አወራ ተናገረ

ዘገበ = ሰበሰበ አከማቸ

ዘግሐ = ዘጋ ገጠመ

## የ የ ቤት ግሥ

የበበ = እልል አለ

የብሰ = ደረቀ ከረረ

ይቤ = አለ

የውሀ =አባበለ ገራ አለዘበ

የሀደ = አሳመነ ገዘረ

የመነ = ቀና

## የ ደ ቤት ግሥ

ዳህመመ = አፈረሰ ቆፈረ

ደለለ=ጠጕሩን አበጠረ

ደለወ = ተገባ አስተካከለ

ደሐረ = ፈታ

ደመረ = ጨመረ

ደመወ = ደማ

ደምሰሰ = አጠፋ ደመሰሰ

ደምፀ = ተሰማ ጮኸ

ደረሰ = ደረሰ ተረጎመ

ደረገ = አንድ ሆነ አደራጀ

ደርግሐ = ሰፋ ጠቀመ

ደቀሰ = ተኛ አንቀላፋ

ደቀቀ /ደቀ = ደቀቀ አነሰ

ደበረ = ገደመ ደብር ሠራ

ደብተረ =ሰፋ ተከለ ዘረጋ

ድኅነ =ዳነ ተረፈ አመለጠ

ደነሰ = አደፈ ረከሰ

ደንገለ = ጠበቀ

ደንገፀ = ደነገጠ ፈራ

ደክመ=ደከመ ታከተ ሰነፈ

ደወየ = ታመመ

ደየነ = ዳኘ ፈረደ ቀጣ

ዴደየ = ፈረጠጠ ፈነጨ

ዴገነ = ተለተለ

ደገመ = ደገመ ደጋገመ

ደገፈ = ደገፈ አጠና

ደፈነ = ቀበረ ደፈነ ሸሸገ

ደፍዐ = ደፋ ከነበለ ጣለ

## የ ገ ቤት ግሥ

ገሀደ = ገለጠ አሳየ

ገሀሀ =በራ ፍጹም ደመቀ

ገለበ=አጠመደ መረብ ጣለ

ገለየ = ቆረጠ ለየ ገለጠ

ገሐሠ=ገባ ዐረፈ ፊለሰ

ጓሕለወ = ሸነገለ አታለለ

ጕሕቈ = ጎበጠ

ገመሰ = ከፈለ ቆረሰ

ገምዐ = ላጨ ሸለተ

ገሠጸ = ቀጣ ተቆጣ መከረ

ገሠሠ=ግሥ ገሠሠ አወረደ

ጕሥዐ=አወጣተናገረ አገሣ





ገረመ = ተፈራ ተገረመ

ገሰሰ = ዳሰሰ ዳበሰ

ገብረ = ሠራ አደረገ ፈጠረ

ገብአ = ገባ ዘለቀ

ገነዘ = ገነዘ ከፈነ ጠቀለለ

ገነየ = ገዛ ታዘዘ

ጕንደየ = ዘገየ ቆየ

ገንጸለ = ገለበጠ አሽቀነጠረ

ገአዘ = አዘነ ነቀፈ

ገዐረ = ጮኸ ተጨነቀ

ገዘመ = ቀረጠ

ገዘረ = ገዘረ ቆረጠ

ገዝአ = ገዛ ገዢ ሆነ

ገዝፈ = ገዘፈ ደነደነ

ገየሠ/ጌሠ=ገሠገሠ

ጕየየ /ጕየ = ሸሸ ኮበለለ

ጌገየ = በደለ ሳተ

ገደለ = አቆሰለ አረደ

ጕድዐ = ጎዳ

ጕድጕደ=ደጅ መታ

ገደፈ = ጣለ ተወ

ጕጕዐ = ጓጓ ቸኮለ ተመኘ

ጕጽፈረ = አከከ ጫረ

ገፍትዐ = ገፈተረ ገለበጠ

ገፍዐ = ገፋ በደለ

## የ ጠ ቤት ግሥ

ጠለሰ = ጠፋ እልም አለ

ጠለቀ = ነከረ ዘፈቀ

ጥሕረ = ጮኸ አገሣ

ጠምዐ=ነከረ ዘፈቀ አሳደፈ

ጠቀለ = በነገር ነከ

ጠቅዐ = መታ ደወለ

ጠበበ/ጠበ=ተራቀቀ፡ተጠበበ

ጠበወ = ጠባ ጎረሰ

ጠብለለ=ጠቀለለ ሸበለለ

ጠብሐ = አረደ ሰዋ

ጠብጠበ=ገረፈ መታ

ጠብዐ = ጨከነ ቆረጠ

ጠንቀቀ=ጠነቀቀ አስተዋለ

ጠወበ/ጦበ=ጠቀለለ ሸበለለ

ጠየሰ/ጤሰ = ጨሰ ተነነ

ጥዕመ = ቀመሰ

ጥዕየ = ዳነ ጤና አገኘ

ጠየቀ = ተረዳ መረመረ

ጠፈረ = ታታ

ጠፍሐ = አጨበጨበ

## የ ጸ ቤት ግሥ

ጸለለ = ጠለለ ተንሳፈፈ

ጸለየ = ለመነ ተሳለ

ጸልሐወ = ሸነገለ አታለለ

ጸልመ = ጨለመ ጠቆረ

ጸልዐ = ጠላ አቄመ

ጸሐፈ = ጻፈ

ጸመመ /ጸመ = ደነቆረ

ጸምአ = ጠማ ተጠማ

ጸመወ = ደከመ ታከተ

ጸረቀ = ጋገረ አነጎተ

ጸርሐ = ጠራ ጮኸ

ጸበለ = ትቢያ ሆነ

ጸበበ = ጠበበ አነሰ

ጸበተ = ዋኘ

ጸንሐ = ጸና ቆየ

ጸንዐ = ጠና ጠነከረ

ጸወመ/ጸመ = ተወ ጦመ

ጸወረ/ጸረ = ተሸከመ

ጸወነ = አስጠጋ አዳነ

ጸውዐ = ጠራ ተጣራ

ጸዐለ=ሰደበአዋረደ አጣጣለ

ጸዐቀ = ተጨነቀ ተጠበበ

ጸዐነ = ጫነ አሸከመ

ጸይሐ/ጼሐ = ጠረገ

ጸዕደወ = ነጣ ጠራ

ጸደለ = በራ

ጸድቀ=ታመነእውነተኛ ሆነ

ጸግበ = ጠገበ

ጸገወ = ሰጠ ለገሰ

ጸገየ = አበበ አፈራ

ጸፍዐ = በጥፊ መታ

## የፀ ቤት ግሥ

ፀሐሰ = አሸበሸበ አሸረገደ

ፀመረ=ጨመረ ደረበ ለጠቀ

ፀመደ = ጠመደ

ፀረሰ = በለዘ ፈዘዘ ደነዘዘ

ፀበጠ = አጥብቆ ያዘ

ፀብሰ = ልምሾ ሆነ

ፀንሰ = ፀነሰ አረገዘ

ፀወሰ = ሰለለ ልበሾ ሆነ

ፀወገ = ፊቱን አጠቆረ

ፄወወ = ማረከ

ፀግዐ = ተጠጋ አስጠጋ

## የ ፈ ቤት ግሥ

ፈለመ = ጀመረ

ፈለሰ = ተሰደደ ፈለሰ

ፈለከ= ፈጠረ ከፈለ ደረደረ

ፈለጠ = ለየ

ፈልሐ = ፈላ ተፍለቀለቀ

ፈልሰፈ = ተራቀቀ አወቀ

ፍሕመ = ፋመ ጋመ

ፈረየ = አፈራ ረባ





ፈቀደ = ወደደ

ፈቅዐ = ገመሰ

ፈተለ = ፈተለ ገመደ

ፈተተ = ቆረሰ ገመሰ

ፈተነ = ፈተነ

ፈትሐ = ፈታ ፈረደ

ፈተወ = ተመኘ ከጀለ

ፈነወ = ላከ ሰደደ

ፈከረ = ተረጎመ ፈታ

ፈየተ = ቀማ መነተፈ

ፈደለ = ጻፈ

ፈደየ = ከፈለ መለሰ

ፈድፈደ = በዛ ተረፈ

ፈጠረ = ፈጠረ አስገኘ

ፈጸመ =ለጎመ ዘጋ አፈነ

ፈፀመ = ጨረሰ

ፈወሰ = አዳነ ፈወሰ

ፈወዘ/ፎዘ = ወለወለ

<u>ምልማድ ፫.፩.</u>

፩.ሁላችን የእግዚአብሔር ልጆች ነን:: ነባር አንቀጽ::
፪.ከንጹሐን ንጹሕ አንቺ ነሽ::የስም ምትክ እና ነባር አንቀጽ::
፫.የአሥራ ሁለቱ ሐዋርያት ስማቸው ይህ ነው::ነባር አንቀጽ::
፬.አንተ ምሕረትን ትሠጣለህ::የስም ምትክ::
፭.እናንተ እዚህ ለምን ቆማችሁ::የስም ምትክ::
፮.እኛ የጽድቅ መንገድን ተከተልን:: የስም ምትክ/አመልካች ቅጽል::
፯.እነዚህ አጋንንት ወጥተው አሣማዎቹ ላይ ገቡ::አመልካች ቅጽል::
፰.ሕይወትን አግኝታለችና ያች ሴት ደስ አላት::አመልካች ቅጽል::
፱.በዚያ ሀገር ያሉ እረኞች ደነገጡ::አመልካች ቅጽል::
፲.እናንተ የእግዚአብሔር ቤተ መቅደሱ ናችሁ::የስም ምትክ እና ነባር አንቀጽ::
፲፩.ያች ሴት ያችን ዘማ ራቀቻት::አመልካች ቅጽል::
፲፪.እነዚያን ደንቆሮዎች አንተ አዳንክ::አመልካች ቅጽል እና ተሳቢ::
፲፫.አቤቱ አንተን እናመሰግናለን::
፲፬ በእስራኤል ጭፍራ ላይ የነገሠ ዳዊት አውታር ባለው በገና አንቺን አመሰገነ::ተሳቢ::
፲፭ እኔን የተቀበለ አባቴን ተቀበለ::ተሳቢ::
፲፮ እሱ ግን በመካከላቸው አልፎ ሔደ::የስም ምትክ::
፲፯ በዚያች ሌሊት ምንም ያጠመዱት የለም::አመልካች ቅጽል::
፲፰ የአባትህ ስም ማን ነው::ነባር አንቀጽ::
፲፱ የአባቴ ስም ዮሐንስ ነው:: ነባር አንቀጽ::
፳ የዮሐንስ ምስክርነቱ ይህ ነው:: ነባር አንቀጽ::
፳፩ በዚያች ዕለት በመሸ ጊዜ መጣ::አመልካች ቅጽል::

**ምልማድ ፫.፪**

ሀ. ርስት ለ. ብሔር

| | | | |
|---|---|---|---|
| ርስትየ | ርስትነ | ብሔርየ | ብሔርነ |
| ርስትከ | ርስትክሙ | ብሔርከ | ብሔርክሙ |
| ርስትኪ | ርስትክን | ብሔርኪ | ብሔርክን |
| ርስቱ | ርስቶሙ | ብሔሩ | ብሔሮሙ |
| ርስታ | ርስቶን | ብሔራ | ብሔሮን |

ሐ.ግብር

| | |
|---|---|
| ግብርየ | ግብርነ |
| ግብርከ | ግብርክሙ |
| ግብርኪ | ግብርክን |
| ግብሩ | ግብሮሙ |
| ግብራ | ግብሮን |

**ምልማድ ፫.፭. :-**

ሀ. የሚከተሉትን ተርጉሙ::

፩.ወልድ እንደሚመጣ ነገረ::

፪.እስራኤል እንዳዘዛቸው አደረጉ::

፫.አንተ በዘይት ቀባኸኝ::

፬.የሚሰማኝን አገኘሁ::

፭.ዓይኔ ጠላቶቼን አየች ::

ለ. የሚከተሉትን ወደ ተሳቢ ለውጡ::

፩.ዜናዌ ፪.ትካዜ ፫.ሀገሮ ፬.ማርቆስሀ ወንጌላዌ ፭.ተዋሕዶ ፮.ተሰዓተ ቅዱሳን ፯.ናትናኤልሀ ፰.ዝማሬ ሐዲሰ ፱.ድንግልና ፲.ቀይሐ ላሕመ ፲፩.ሰማየ ወ ምድረ ፲፪.ሕፃነ ወ እሞ ፲፫.ዐቢየ ብርሃነ ፲፬.ዮሐንስሃ መጥምቀ ፲፭.ዐሠርተትዕዛዛተ ፲፮.ወልደ ፲፯.ሐና ፲፰.ሥላሴ ፲፱.አበ





**ምልማድ ፫·፫·:-**

| | ሀ.ቅዳሴ | ለ.ጌራ | ሐ.ኅሊና | መ.ውቅሮ | ሠ.ፀልቦ | ረ.ፍካሬ |
|---|---|---|---|---|---|---|
| አነ | ቅዳሴየ | ጌራየ | ኅሊናየ | ውቅሮየ | ፀልቦየ | ፍካሬየ |
| ንሕነ | ቅዳሴነ | ጌራነ | ኅሊናነ | ውቅሮነ | ፀልቦነ | ፍካሬነ |
| አንተ | ቅዳሴከ | ጌራከ | ኅሊናከ | ውቅሮከ | ፀልቦከ | ፍካሬከ |
| አንትሙ | ቅዳሴክሙ | ጌራክሙ | ኅሊናክሙ | ውቅሮክሙ | ፀልቦክሙ | ፍካሬክሙ |
| አንቲ | ቅዳሴኪ | ጌራኪ | ኅሊናኪ | ውቅሮኪ | ፀልቦኪ | ፍካሬኪ |
| አንትን | ቅዳሴክን | ጌራክን | ኅሊናክን | ውቅሮክን | ፀልቦክን | ፍካሬክን |
| ውእቱ | ቅዳሴሁ | ጌራሁ | ኅሊናሁ | ውቅሮሁ | ፀልቦሁ | ፍካሬሁ |
| ውእቶሙ | ቅዳሴሆሙ | ጌራሆሙ | ኅሊናሆሙ | ውቅሮሆሙ | ፀልቦሆሙ | ፍካሬሆሙ |
| ይእቲ | ቅዳሴሃ | ጌራሃ | ኅሊናሃ | ውቅሮሃ | ፀልቦሃ | ፍካሬሃ |
| ውእቶን | ቅዳሴሆን | ጌራሆን | ኅሊናሆን | ውቅሮሆን | ፀልቦሆን | ፍካሬሆን |

| | ሰ.ጽጌ | ቀ.ሥጋ | በ.ቤዛ | ተ.ኵለንታ | ነ.ጊዜ |
|---|---|---|---|---|---|
| አነ | ጽጌየ | ሥጋየ | ቤዛየ | ኵለንታየ | ጊዜየ |
| ንሕነ | ጽጌነ | ሥጋነ | ቤዛነ | ኵለንታየ | ጊዜነ |
| አንተ | ጽጌከ | ሥጋከ | ቤዛከ | ኵለንታከ | ጊዜከ |
| አንትሙ | ጽጌክሙ | ሥጋክሙ | ቤዛክሙ | ኵለንታክሙ | ጊዜክሙ |
| አንቲ | ጽጌኪ | ሥጋኪ | ቤዛኪ | ኵለንታኪ | ጊዜኪ |
| አንትን | ጽጌክን | ሥጋክን | ቤዛክን | ኵለንታክን | ጊዜክን |
| ውእቱ | ጽጌሁ | ሥጋሁ | ቤዛሁ | ኵለንታሁ | ጊዜሁ |
| ውእቶሙ | ጽጌሆሙ | ሥጋሆሙ | ቤዛሆሙ | ኵለንታሆሙ | ጊዜሆሙ |
| ይእቲ | ጽጌሃ | ሥጋሃ | ቤዛሃ | ኵለንታሃ | ጊዜሃ |
| ውእቶን | ጽጌሆን | ሥጋሆን | ቤዛሆን | ኵለንታሆን | ጊዜሆን |

**ምልማድ ፫.፬.:-**

ሀእምነ ለእስከ

| | | | |
|---|---|---|---|
| እምኔየ | እምኔነ | እስከኔየ | እስከኔነ |
| እምኔከ | እምኔክሙ | እስከኔከ | እስከኔክሙ |
| እምኔኪ | እምኔነክን | እስከኔኪ | እስከኔክን |
| እምኔሁ | እምኔሆሙ | እስከኔሁ | እስከኔሆሙ |
| እምኔሃ | እምኔሆን | እስከኔሃ | እስከኔነሆን |

ሐ. የሚከተሉትን ዐረፍተ ነገሮች ተሳቢ በመለየት ተርጉሙ::

፩.እደው:: ዳዊት ወንዶችን ላከ::

፪.ደዌነ:: እሱ ደዌአችንን ወሰደ::

፫.ምጽዋተ:: ከመስዋዕት ይልቅ ምጽዋትን እወዳለሁ::

፬.ከንቶ :: ሕዝቡም ከንቱን ተናገሩ::

፭.መድምመ:: እግዚአብሔር ድንቅን ያደርጋል::

**ምልማድ ፫.፮. :-**

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | ፩ሖረ | ፪ሐለመ | ፫ኀሠሠ | ፬ሐወጸ | ፭ነበረ | ፮ቆመ |
| አነ | ሖርኩ | ሐለምኩ | ኀሠሥኩ | ሐወጽኩ | ነበርኩ | ቆምኩ |
| ንሕነ | ሖርነ | ሐለምነ | ኀሠሥነ | ሐወጽነ | ነበርነ | ቆምነ |
| አንተ | ሖርከ | ሐለምከ | ኀሠሥከ | ሐወጽከ | ነበርከ | ቆምከ |
| አንትሙ | ሖርክሙ | ሐለምክሙ | ኀሠሥክሙ | ሐወጽክሙ | ነበርክሙ | ቆምክሙ |
| አንቲ | ሖርኪ | ሐለምኪ | ኀሠሥኪ | ሐወጽኪ | ነበርኪ | ቆምኪ |
| አንትን | ሖርክን | ሐለምክን | ኀሠሥክን | ሐወጽክን | ነበርክን | ቆምክን |
| ውእቱ | ሖረ | ሐለመ | ኀሠሠ | ሐወጸ | ነበረ | ቆመ |
| ውእቶሙ | ሖሩ | ሐለሙ | ኀሠሡ | ሐወጹ | ነበሩ | ቆሙ |
| ይእቲ | ሖረት | ሐለመት | ኀሠሠት | ሐወጸት | ነበረት | ቆመት |
| ውእቶን | ሖራ | ሐለማ | ኀሠሣ | ሐወጻ | ነበራ | ቆማ |

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | ፯በከየ ፧ | ፰ርኅበ ፧ | ፱ጸለየ ፧ | ፲ተለወ ፧ | ፲፩አኀዘ ፧ | ፲፪ ተሣየጠ |
| አነ | በከይኩ | ርኅብኩ | ጸለይኩ | ተለውኩ | አኀዝኩ | ተሣየጥኩ |
| ንሕነ | በከይነ | ርኅብነ | ጸለይነ | ተለውነ | አኀዝነ | ተሣየጥነ |
| አንተ | በከይከ | ርኅብከ | ጸለይከ | ተለውከ | አኀዝከ | ተሣየጥከ |
| አንትሙ | በከይክሙ | ርኅብክሙ | ጸለይክሙ | ተለውክሙ | አኀዝክሙ | ተሣየጥክሙ |
| አንቲ | በከይኪ | ርኅብኪ | ጸለይኪ | ተለውኪ | አኀዝኪ | ተሣየጥኪ |
| አንትን | በከይክን | ርኅብክን | ጸለይክን | ተለውክን | አኀዝክን | ተሣየጥክን |
| ውእቱ | በከየ | ርኅበ | ጸለየ | ተለወ | አኀዘ | ተሣየጠ |
| ውእቶሙ | በከዩ | ርኅቡ | ጸለዩ | ተለዉ | አኀዙ | ተሣየጡ |
| ይእቲ | በከየት | ርኅበት | ጸለየት | ተለወት | አኀዘት | ተሣየጠት |
| ውእቶን | በከያ | ርኅባ | ጸለያ | ተለዋ | አኀዛ | ተሣየጣ |





ምልማድ ፫.፯.:-

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ፩ወጽአ | ፪በጽሐ | ፫መርሐ | ፬ተፈሥሐ | ፭ገብረ |
| አነ | ወጻእኩ | በጻሕኩ | መራሕኩ | ተፈሣሕኩ | ገበርኩ |
| ንሕነ | ወጻእነ | በጻሕነ | መራሕነ | ተፈሣሕነ | ገበርነ |
| አንተ | ወጻእከ | በጻሕከ | መራሕከ | ተፈሣሕከ | ገበርከ |
| አንትሙ | ወጻእክሙ | በጻሕክሙ | መራሕክሙ | ተፈሣሕክሙ | ገበርክሙ |
| አንቲ | ወጻእኪ | በጻሕኪ | መራሕኪ | ተፈሣሕኪ | ገበርኪ |
| አንትን | ወጻእክን | በጻሕክን | መራሕክን | ተፈሣሕክን | ገበርክን |
| ውእቱ | ወጽአ | በጽሐ | መርሐ | ተፈሥሐ | ገብረ |
| ውእቶሙ | ወጽኡ | በጽሑ | መርሑ | ተፈሥሑ | ገብሩ |
| ይእቲ | ወጽአት | በጽሐት | መርሐት | ተፈሥሐት | ገብረት |
| ውእቶን | ወጽኣ | በጽሓ | መርሓ | ተፈሥሓ | ገብራ |

| | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | ፮ነሥአ ፧ | ፯ጸውዐ ፧ | ፰ሰብሐ፧ | ፱ርእየ ፧ | ፲ብህለ |
| አነ | ነሣእኩ | ጸዋዕኩ | ሰባሕኩ | ርኢኩ | ብህልኩ |
| ንሕነ | ነሣእነ | ጸዋዕነ | ሰባሕነ | ርኢነ | ብህልነ |
| አንተ | ነሣእከ | ጸዋዕከ | ሰባሕከ | ርኢከ | ብህልከ |
| አንትሙ | ነሣእክሙ | ጸዋዕክሙ | ሰባሕክሙ | ርኢክሙ | ብህልክሙ |
| አንቲ | ነሣእኪ | ጸዋዕኪ | ሰባሕኪ | ርኢኪ | ብህልኪ |
| አንትን | ነሣእክን | ጸዋዕክን | ሰባሕክን | ርኢክን | ብህልክን |
| ውእቱ | ነሥአ | ጸውዐ | ሰብሐ | ርእየ | ብህለ |
| ውእቶሙ | ነሥኡ | ጸውዑ | ሰብሑ | ርእዩ | ብህሉ |
| ይእቲ | ነሥአት | ጸውዐት | ሰብሐት | ርእየት | ብህለት |
| ውእቶን | ነሥኣ | ጸውዓ | ሰብሓ | ርእያ | ብህላ |

ምልማድ ፫.፰:-

| | | | | | | |
|---|---|---|---|---|---|---|
| | ፩.ኀደገ | ፪.አጥመቀ | ፫.ባረከ | ፬.ልህቀ | ፭.ሠሐቀ | ፮.መለከ |
| አነ | ኀደጉ | አጥመቁ | ባረኩ | ልህቁ | ሠሐቁ | መለኩ |
| ንሕነ | ኀደግነ | አጥመቅነ | ባረክነ | ልህቅነ | ሠሐቅነ | መለክነ |
| አንተ | ኀደገ | አጥመቀ | ባረከ | ልህቀ | ሠሐቀ | መለከ |
| አንትሙ | ኀደግሙ | አጥመቅሙ | ባረክሙ | ልህቅሙ | ሠሐቅሙ | መለክሙ |
| አንቲ | ኀደጊ | አጥመቂ | ባረኪ | ልህቂ | ሠሐቂ | መለከ |

አንትን ኀደግን አጥመቅን ባረክን ልህቅን ሠሐቅን መለክን

ውእቱ ኀደገ አጥመቀ ባረከ ልህቀ ሠሐቀ መለከ

ውእቶሙ ኀደጉ አጥመቁ ባረኩ ልህቁ ሠሐቁ መለኩ
ይእቲ ኀደገት አጥመቀት ባረከት ልህቀት ሠሐቀት መለከት

ውእቶን ኀደጋ አጥመቃ ባረካ ልህቃ ሠሐቃ መለካ

<u>ምልማድ ፫.፱፡-</u> ሀ. የሚከተሉትን ግሶች በአሥሩ መራሕያን ዘርዝር።

ማሰነ ፪.ኰነነ ፫.አጽነነ ፬.ከፈነ ፭.አፍጠነ ፮.ከደነ

አነ ማሰንኩ ኰነንኩ አጽነንኩ ከፈንኩ አፍጠንኩ ከደንኩ

ንሕነ ማሰነ ኰነነ አጽነነ ከፈነ አፍጠነ ከደነ

አንተ ማሰንከ ኰነንከ አጽነንከ ከፈንከ አፍጠንከ ከደንከ

አንትሙ ማሰንክሙ ኰነንክሙ አጽነንክሙ ከፈንክሙ አፍጠንክሙ ከደንክሙ

አንቲ ማሰንኪ ኰነንኪ አጽነንኪ ከፈንኪ አፍጠንኪ ከደንኪ
አንትን ማሰንክን ኰነንክን አጽነንክን ከፈንክን አፍጠንክን ከደንክን

ውእቱ ማሰነ ኰነነ አጽነነ ከፈነ አፍጠነ ከደነ
ውእቶሙ ማሰኑ ኰነኑ አጽነኑ ከፈኑ አፍጠኑ ከደኑ
ይእቲ ማሰነት ኰነነት አጽነነት ከፈነት አፍጠነት ከደነት

ውእቶን ማሰና ኰነና አጽነና ከፈና አፍጠና ከደና

ለ. <u>በምሳሌው መሠረት የሚከተለውን ክፍት ቦታ ሙሉ።</u>

፩.<u>መጻእክሙ</u> ፪.<u>ሖርኪ</u> ፫.<u>በልዐት</u> ፬.<u>ሰሐቁ</u> ፭.<u>ኮነ</u> ፮.<u>ረፈቁ</u> ፯.<u>ዐርጉ</u>

፰.<u>በጻሕከ</u> ፱.<u>ባልሐነ</u> ፲.<u>ደንገፅኩ</u> ፲፩.<u>ርኢኩ</u>

<u>ምልማድ፬.፩.፡-</u> የሚከተሉትን ግሦች በሥምንቱ አለቆች ሥር መድብ።

፩.ቀተለ፡-ሐረየ ወረደ ወሀበ መሐለ ፪.ቀደሰ፡- ሐወጸ ወደሰ
፫.ገብረ፡-በዝኀ ነሥአ ሰትየ መልሐ መጽአ ፬.አእመረ፡-ወርዘወ አርመመ
፭.ባረከ፡- ማሰነ ናዘዘ ፮.ሤመ፡- ሜጠ ቤዘወ
፯.ብህለ፡- ውዕየ ምዕዘ ፰.ቆመ፡- ኖለወ ሖረ ሮተ ሞዐ ፎሐ





<u>ምልማድ ፭.፩.፡- መ ስም ውስጠ ዘ ዘር አውጣላቸው።</u>
፩. መቀድስ ፪. መድኀን ፫. መፈውስ ፬. መተርጕም ፭. መተንብል
፮. መስተገብር ፯. መስእል ፰. መሰቅል ፱. መድበል

<u>ምልማድ ፭.፪.፡-ለሚከተሉት ግሦች ሳቢ ዘር አውጣላቸው ።</u>
፩. ቅብዐት ፪. ምትረት ፫.ስእለት ፬.ኅብረት ፭. ሕይወት
ሥርዐት ምሕረት ውእየት ዑረት ሢጠት ድቀት ፁረት ቂሐት
በአት ጸአት ጊሩት ኢኀት ዕሬት/ዕርየት/ ቲሐት ግብአት
ኅድረት ብልዐት ሥዕረት ብጽሐት

<u>ምልማድ ፭.፫፡-ለሚከተሉት ግሦች ዘመድ ዘር አውጣላቸው።</u>

፩.ዕጣን ፪.ልማድ ፫.ሕማም ፬.ስካር ፭.ሰንበት
ኄር ስምዕ ዋዕይ ንዋም ንዳድ ሥቃይ ቤት ንፋስ
ጦማር ሕፀፅ ንቃው ቃል ምክር መርሕ መድበል

<u>ምልማድ ፭.፬.፡-ለሚከተሉት ግሦች ባዕድ ዘር አውጣላቸው።</u>

፩. ማእሠር ፪. ምሥራቅ ፫. መንበር ፬. ሙራድ
አስካል፣ምራቅ፣መክርይ፣ታኄብ/ማኅየብ፣መልአክ፣መስፍን፣ምክዋው፣
ምስአል

<u>ምልማድ ፭.፭. ፡-ለሚከተሉት ግሦች ምዕላድ ዘር አውጣላቸው።</u>
፩. ብሥራት ፪. ቁርባን ፫. ንጽሕና ፬. ሰማዕት ፭. ትምክሕት
ሀብት ዕሬት ትዕግሥት ኪዳን ምዕዳን
ልቡና ጽሙና ጥዒና ተደንግሎት ምክንያት
ትውክልት ሕሊና

<u>ምልማድ ፭.፮.፡-ለሚከተሉት ግሦች ባዕድ ከምዕላድ ዘር አውጣላቸው።</u>
፩. መንግሥት ፪. መሥዋዕት ፫. ማዕጠንት ፬. መሠረት ፭. መልእክት
መክፈልት ትእምርት ትሥልስት መሥገርት መንጦላዕት
ትድምርት መሥፈርት

**ምልማድ ፩.፯.:-ለሚከተሉት ግሦች ጥሬ ዘር አውጣላቸው::**

፩. ሕዳሴ ፪. ውላጤ ፫. ምሕላ ፬. ድንጋፄ ፭. ወሬዛ

ሥጋ ወካሌ ተስፋ እንግልጋ ጉባኤ

ማዕፆ መርኆ

**ምልማድ ፩.፰.:-**

፩.ሐተት ፪.ስአልት ፫.ሰቀልት ፬.ሰረቅት

ወሀብት ወረድ ዐጸድ መሠጥ

**ምልማድ ፮.፩. :-**

**ለ.የሚከተሉትን ዐረፍተ ነገሮች ከተረጎምክ በኋላ አንቀጾችን ለይ::**

፩.እናንተ ምስክሮቼ ትሆናላችሁ::

ኮንክሙ *ትክውኑ* ትኩኑ ኩኑ::ካልዓይ አንቀጽ::

፪.ማርታ ብዙን ትደክሚያለሽ::

ሠራሕኪ *ትሠርሒ* ትሥርሒ ሥርሒ::ካልዓይ አንቀጽ::

፫.ሰማዮች የእግዚአብሔርን ክብር ይናገራሉ::

ነገሩ *ይነግሩ* ይንግሩ ይንግሩ::ካልዓይ አንቀጽ

ወሀበ ይሁብ *የሀብ* የሀብ::ትእዛዝ አንቀጽ::

፭.እነርሱ ከእርሱ ጋር ይዋሉ::

ወዐሉ ይውዕሉ *የዐሉ* የዐሉ::ትእዛዝ አንቀጽ::

.ባልንጀራህን እንደራስህ ውደድ::

አፍቀርከ ታፈቅር ታፍቅር *አፍቅር*::ትእዛዝ አንቀጽ::

፯.ሰላማችሁ ይመለስ /ላችሁ/::

ገብአ ይገብእ ይግባእ *ይግባእ::*ትእዛዝ አንቀጽ::

፰.ምንን ታስባላችሁ::

ሐለይክሙ *ትሔልዩ* ተሐልዩ ሐልዩ::ካልዓይ አንቀጽ::

፱.ሒድና ራስህን ለካህን አስመርምር /አሳይ/::

ሖርከ ተሐውር ትሑር *ሑር*::አፍተንከ ታፈትን ታፍትን *አፍትን* ::ትእዛዝ አንቀጽ::

.ጥበብ ከሁሉ ትበልጣለች /ትሻላለች/ ::

ሐየሰት *ትኄይስ* ተኀይስ ተኀይስ::ካልዓይ አንቀጽ::

፲፩. ተነስ አልጋህን ተሸክመህ ሂድ::ተንሣእከ ትትነሣእ ትትነሣእ *ተንሥእ*::ነሣእከ ትነሥእ ትንሣእ *ንሣእ*:: ትእዛዝ አንቀጽ::





.እርሱ ዘርን ይስጥ::

**ሐ.አዛምድ**

፩.አንተ መ፣ሀ ፪.አንትሙ ሐ ፫.ይእቲ ሀ ፬.ውእቶን ቀ

፭.ውእቱ ተ .አንቲ ወ ፯.አንትን ረ ፰.ውእቶሙ ገ

፱.አነ ለ፣ሠ .ንሕነ በ፣ተ

**ምልማድ ፱.፪. :- ልማዳቸውን ግለጽ**

ሀ.አስተብቍአ:-አደራራጊ ይመስላል ነገር ግን ማለደ ብሎ አድራጊ ነው::

ለ.አስተዐፀበ:- አደራራጊ ይመስላል ነገር ግን አስደነቀ ብሎ አስደራጊ አደነቀ ብሎ አድራጊ ነው::

ሐ.አይድዐ:-አስደራጊ ይመስላል ነገር ግን ተናገረ ብሎ አድራጊ ነው::

**ምልማድ፲.፩.:-**

**የሚከተሉትን ዐ. ነገሮች ከአዎንታ ወደ አሉታ ለውጡ::**

፩. አኮ ትጉሕ ዮሐንስ ::

፪. አኮ ዝንቱ ዘገብረ ዘንተግብረ::

፫. አኮ ንሕነ እለ ገበርነ ዘንተግብረ::

፬. አኮ አንትን ትጉሓን::

፭. አኮ በኀብስት ክመ ዘየሐዩ ሰብእ::

**ምልማድ ፲.፪ :-**

**1. የሚከተሉትን አዎንታዎች ወደ አሉታ ቀይሩ::**

፩. ኢመጻእኩ ፪. ኢንበውእ፫. ኢይቄድስ ፬. ኢተጠወሩ፭. ኢጸሐፍኩ

**፪.ትክክለኛውን መልስ ምረጡ::**

፩. መ. ሀናለ ፪. ሀ. አነ፫. መ. ሀናለ ፬. መ. ለናሐ ፭. መ. ሀናሐ

፮. መ. ሀናሐ

**ምልማድ ፲.፫:-አሉታውን ወደ አዎንታ ለውጡ::**

፩.አንተገት ፪.ትብጻሕ ፫.ታፀርዕ ፬.ይሬእይዋ ፭.ተሐለየ

፮.ትፍርሂ/ፍርሂ ፯.ርእየ

**ምልማድ ፲.፬.:-አዛምድ**

፩÷ ለ ፪÷ መ ፫÷ ሠ ፬÷ ሰ ፭÷ በ

**ምልማድ ፲፩.፩. :-**
**የሚከተሉትን አንቀጾች ባለቤት ትርጉምና ንባብ አሳዩ::**

፩. አእመራሆን:- ውእቶን:: አወቋቸው:: ተጣይ::

፪. ያእምርዋ:-ውእቶሙ:: ያውቋት ዘንድ/ይወቋት::ተነሽ::

፫. አእምርኒ:-አንቲ::እወቂኝ::ተነሽ::

፬ አእመራሁ:-ውእቶን::አወቁት::ወዳቂ::

፭. አእመርናሁ:-ንሕነ::አወቅነው::ወዳቂ::

**ምልማድ ፲፩.፪.:-**
**ትክክለኛውን መልስ ምረጡ**
፩.ሀ. ይቤላ ፪.መ. ሀናለ ፫.ሀ. ይቤላ ፬.ሠ. ሀናለ ፭.ሐ. እቤ
**ምልማድ ፲፪.፩.:-**
**የሚከተሉትን ስሞች ክፍላቸውን ግለጽ::**

፩.ነዳይ:-የወል ስም ፪.ላሊበላ:-የመጠሪያ ስም ፫.ሙቀት:-ስመ ረቂቅ

፬.እስራኤል:-የመጠሪያ ስም ፭.ቅዝቃዜ:-ስመ ረቂቅ ፮.ነፋስ:- ስመ ረቂቅ

፯.ምግባር:-ስመ ረቂቅ ፰.አህዛብ:-የጥቅል ስም

**ምልማድ ፲፪.፪. :-**

**ዐ/ነገሮቹን ከተረጎምህ በኋላ የ "ለ" እና የ"በ"ን ሙያ ግለጽ::**

፩.የሚፈልጉኝ ወደኔ ይምጡ::ለ=አዳማቂ /ትርጉም የለሽ/

፪.ነቢይ በሀገሩ አይከበርም::በ= በቁም ቀሪ

፫.የማርታ ሕፃናቶቿ እኒህ ናቸው::ለ= (ዘርፍ አያያዥ /የ/)

፬.መላእክት እግዚአብሔርን ሲያመሰግኑት ቅዱስ ቅዱስ ቅዱስ ይላሉ::ለ=(ተጠቃሽ ተሳቢ/ን/)

**ምልማድ ፲፫.፩. :-የሚከተለውን ካነበብህ በኋላ ለተሰጡት ጥያቄዎች ትክክለኛውን መልስ ምረጥ::**

፩. ለ. የደወል ድምጽ ስንሰማ ፪. ሀ. እንዘ ንሰምዕ
፫. ለ. ለመምህር ፬. ሀ. መተርክ





## ዋቢ መጻሕፍት

፩÷ መጽሐፈ ሰዋስው ወግስ ወመዝገበ ቃላት ሐዲስ::
ከአለቃ ኪዳነ ወልድ ክፍሌ ፲፱፻፵፰ ዓ.ም.

፪÷ ሰዋሰወ ግእዝ
አለቃ ታዬ (ትንሣኤ ዘጉባዔ) ፲፱፻፹፰ ዓ.ም.

፫÷ ርባሐ ስም ወአንቀጽ
በደስታ ተክለ ወልድ ፩፱፻፵፯ ዓ.ም.

፬÷ ጥንታዊ ግእዝ በዘመናዊ አቀራረብ
መምህር ዜና ማርቆስ እንዳለው ፳፻፬ ዓ.ም. ፫ኛ እትም

፭÷ ፍኖተ ግእዝ
መምህር ያሬድ ፈንታ ፲፱፹፯ ዓ.ም.

፭÷ ፍኖተ ግእዝ
መምህር ያሬድ ፈንታ ፲፱፹፯ ዓ.ም.

፮÷ የግእዝ ቅኔያት (ቅጽ አንድ)
የኢትዮጵያ ቋንቋዎች አካዳሚ

፯÷ መርኆ ሰዋስው ዘልሳነ ግእዝ
ከ ዘርዐ ዳዊት አድኀና